


ከመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል

www.ethiopianorthodox.org

# የመጽሐፍ ቅዱስ መማሪያ

## ፮ኛ መጽሐፍ

የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የድርሰት ክፍል ።

አዲስ አበባ ።

ያለ አሳታሚው ፈቃድ በሙሉም በከፊልም ማሳተም ክልክል ነው ።
የመንበረ ፀባዖት ቅ. ሥላሴ ካቴድራል የድርሰት ክፍል ።
የፖ. ሳ. ቍ. ፴፯፴፯
አዲስ አበባ ፲፱፻፸፪ ዓ. ም.

በብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ቅ. መጻሕፍትን አክብራ የተቀበለችበት ጊዜ በጣም ረዘም ያለ ነው ፤ ይኸውም ከክርስትና በፊትና ከክርስትና በኋላ እንደሆነ ሊቃውንቱ ይተርካሉ ። የመጻሕፍትም ኃይል ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ክርስቲያናዊ እምነቷን ጠብቃ ለመኖር ረድቷታል ። የክርስቲያንም ደሴት ሊያሰኛት የቻለው ቅሉ ፤ ሕዝባችን በቅ. መጻሕፍት መሪነት ትልቁም ፣ ትንሹም በአንድ ክርስቲያናዊ መንፈስ ተሳሥሮ ከመኖሩ ጋር ቅ. መጻሕፍትን አተኩሮ በመመልከቱና ክርስቲያናዊ ተግባሩን በመፈጸሙ ነው ። አባቶቻችን ነገሥታት ስለቅዱሳት መጻሕፍት አጠባበቅ ለሕዝቡም እንዴት እንደሚዳረስ በጠቅላላም ስለ ክርስቲያን ሃይማኖት አጠባበቅ በብዛት ሠርተዋል ፤ ለትውልድም እንዲተላለፍ ለማድረጋቸው ሕያው ታሪካቸው ይመሰክራል ።

እንደዛሬው ሁሉ የማተሚያ መኪና ባይኖርም እንኳ ቅ. መጻሕፍትና የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት በእጅ ጽሑፍ ተባዝተው ለሁሉም እንዲደርሱ ስላደረጉ ገዳማትና አድባራት በጠቅላላም አብያተ ክርስቲያናታችን በቅዱሳት መጻሕፍት በልጽገው ይገኛሉ ። እንዲሁም ከልዩ ልዩ ቋንቋ ወደግእዝ እንዲተረጐሙ ወዲያውም በቋሚ መጻሕፍትነት እንዲጻፉ ያደረጓቸው መጻሕፍት ፤ ለዘመናቸው አገልግሎት በቂ ጥቅምን ከመስጠታቸው ጋር ለአሁኑም ዘመን እንዲሁ ከፍ ያለ ጥቅምን በመስጠት ላይ ይገኛሉ ። የሰው ሕይወት በቅዱስ መጽሐፍ ደጋፊነት ተወስኖ እንዲኖር በግድ ያስፈልጋል ። አንድ ሰው በቅዱስ መጽሐፍ መሪነት ካልተመራና ጊዜውን ሳያባክን ካልሠራ በነፋስ ኃይል እንደሚወዛወዝ ሸንበቆ ምንም የያዘው ቁም ነገር ሳይኖር እንዲሁ ያልፋል ። ቅ. መጻሕፍትን በየጊዜው መመልከት ግን የሰው ልጅ ራሱን ገዝቶ ፈቃደ ብርቱነቱን አፅንቶ እንዲኖር ይረዳዋል ። ቅዱስ መጽሐፍን ቤተ ክርስቲያናችን በምትቀበለው መልክ ጠቅላላውን በአንድ ጥራዝ እንዲገኝ ከማድረጋችን ጋር እርሱንም ወደ አማርኛ አስተርጕመን አሳትመነዋል ። ዋናው ዓላማችንም በጠቅላላ ወገናችን ስለ ቅ. መጽሐፍ ያለውን ፍላጎት ለማርካት ነው ።

አሁንም ክርስቲያኑ ሕዝባችን በተለይም አዲሱ ትውልድ በሚስማማውና በሚገባው ዕቅድ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲማር አስበን በቀላሉ መንገድ እንዲዘጋጅ ያዘዝነው ተምሮ ተመራምሮ በእውነቱ ፀንቶ ለመኖር ይረዳዋል በማለት ነው ። ለሕዝባችን እንደፍላጎቱ ለማርካት በአቀድነው መሠረት የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ጊዜያችንን መስሎ የቤተ ክርስቲያናችንን ትምህርት ተከትሎ የተዘጋጀ እንደሆነ ዳር እስከዳር ያለው ተቀባይነት ሊሟላ እንደሚችል የታወቀ ነው ፤ በተምሮ ማስተማርም ሁሉ እንዲጠቀምበት ያለን እምነት ፍጹም ነው ።

ቀ. ኃ. ሥ.



www.ethiopianorthodox.org

# መ ቅ ድ ም

ቅ. መጽሐፍ የሰው ልጅ መመሪያ የሕይወቱም መምሪያ በመሆኑ ፤ የሰው ልጅ መራባት እንደጀመረ ወዲያውኑ አምላክ በቅዱሳን ነቢያት አድሮ ብሉያት መጻሕፍት እንዲጻፉ አድርጓል ። በኋላም ራሱ ሥጋን ለብሶ በምድር ተመላልሶ እንደ አምላክነቱ ቅ. ወንጌልን አስተምሯል ። ቀጥሎም ሐዋርያቱ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው የረቀቀውን አጉልተው ትንቢቱን አማናዊ አድርገው አስተምረዋል ፤ ቅ. መጽሐፍንም ጽፈው ሰጥተዋል ። ቅ. መጽሐፍ የሰው ልጅ የልቡናው ፋና ነው ፤ ያለርሱ ሕይወቱ በጨለማ ይዋጣል ፤ ያለርሱ ቢራመድ ይሰነካከላል ።

በእግዚአብሔር ቅ. ፈቃድና በርሱም ገላጭነት የተጻፈ ቅ. መጽሐፍ ለሰው ልጅ ለትምህርት ፣ ለተግሣጽ ይጠቅማል ፤ የዚህንም እውነተኛ አስረጂነት ቅ. ጳውሎስ በመረዳት ደቀ መዝሙሩን ጢሞቴዎስን ሲመክር ይገኛል (፪ ጢሞ. ፫፥ ፲፮፥፲፯) ።

ቤተ ክርስቲያን የጸጋ መዝገብ ስትሆን ምእመናን ደግሞ ጸጋውን እንዴት ሊካፈሉት የሚችሉ በቅ. መጽሐፍ መመሪያነት መሆኑ የታመነ ነው ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ዘመኑን ተከትላ ረጅሙን በማሳጠርና በመጠቅለል በየጊዜውም ቋንቋውን ከከባድ ወደቀላል በማሻሻል ተስማሚ የሆነ ዝግጅት በማድረግ ስታስተምር ቆይታለች ፤ አሁንም ታስተምራለች ።

ከዚህ ቀደም በሀገራችን በዚህ መልክ እየተዘጋጁ የቀረቡ ብዙ የመጽሐፍ ቅ. ታሪኮች እንደነበሩ ይታወቃል ። በተጨማሪም አሁን በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት የተዘጋጀ ሆኖ ቀርቧል ። ይሁን እንጂ ማንኛውም አማኒ ዳር እስከዳር እንዲጠቀምበት በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ሆኖ ተዘጋጅቷል ። ይኸንም የተቀደሰ ተግባር ለመጀመር የቻልነው የቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ ፤ የክርስቲያን ሃይማኖት ደጋፊ በሆኑ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መልካም ፈቃድና ትእዛዝ ነው ። የዚህንም ዝግጅት ኃላፊነት የመንበረ ፀባዖት ቅ. ሥላሴ ካቴድራል የወሰደና ያሳተመው ሲሆን ፤ በመላ ክርስቲያኑ ሕዝባችን እንዲጠቀምበት እምነታችን ከፍ ያለ ነው ።

በሥጋዊ ጥበብ የተራቀቀው ትውልድ መንፈሳዊው ጥበብ እንዳይነሣው ቅ. መጽሐፍን በማንበብ እንዲጠቀም ትንሽ ፣ ትልቅም ሳይል ሁሉም እንደፍላጎቱ እንዲደርሰው ከፍ ያለ ጥንቃቄ በማድረግ ቀላል መስሎ በታየን መንገድ አዘጋጅተን አቅርበናል ።

መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ ለማጥናት የሚያስችለውን « የመጽሐፍ ቅ. መማሪያ» ብለን የሰየምነውን ፩ኛውን ክፍል በዚህ መልክ ስናቀርብ ሁላችሁም በመማር ልዩም ምርምር በማድረግ እንድትጠቀሙበት በእግዚአብሔር መንፈስ እንታመናለን ።

የመንበረ ፀባዖት ቅ. ሥላሴ ካቴድራል የድርሰት ክፍል ።

# መ ግ ቢ ያ

የመጽሐፍ ቅዱስ መማሪያ ብለን የሰየምነው ይኸ መጽሐፍ ፩ኛ በትምህርት ቤት፤ ፪ኛ በአሑድ ትምህርት ቤት ፤ ፫ኛ በግልም በየቤቱ ሁሉም እንዲማርበትና እንዲያስተምርበት ታስቦ አግካይ መንገድን በመከተል የተዘጋጀ ነው ፤ መጽሐፉ ፫ት ክፍል ይኖረዋል ። ይኸውም በ፩ኛ ደረጃና በ፪ኛ ደረጃ ፤እንዲሁም ከፍተኛ ዕውቀት ላላቸው ሰዎች እንዲመች ሆኖ ተመጥኖ የተሠራ ሲሆን ፤ ፩ኛውም ሆነ ፪ኛው ክፍል ከብሉይና ከሐዲስ ኪዳን ተወጣጥቶ ክፍለ ዘመናትን በመከተል ለትምህርት ተስማሚ በሆነ መንገድ የተዘጋጀ ነው ፤ለምሳሌ ከመስከረም እስከ ታኅሣሥ መግቢያ የመዘጋጃ ጊዜ እንደመሆኑ ፤ ብሉያትንና መጻሕፍት ነቢያትን በመማር እንዲጠቀሙበት ተዘጋጅቷል ። ከታኅሣሥ እስከ ጰራቅሊጦስ ድረስ የመድኃኒት ዘመን እንደመሆኑ መጻሕፍት ሐዲሳትን በመከተል ተዘጋጅቷል ። ከሰኔ እስከ ነሐሴ መጨረሻ ባለው ጊዜ እንደገና ብሉይ ኪዳንን በመከተል ተዘጋጅቷል ።

ተማሪዎችም በዚህ መሠረት ሲማሩ እንደሚገባ ስናስገነዝብ ፤ አስተማሪዎችም በዚሁ መልክ እንዲያስተምሩ ፤ የግል ሰዎችም ቢሆኑ በዚህ መሠረት እንዲማሩ እምነታችን ፍጹም ነው ።

ከ፫ቱ ክፍል መጻሕፍት ውስጥ ፩ኛው ይኸ ሲሆን ፣ ፪ኛው ክፍል በመዘጋጀት ላይ ነው ። እያንዳንዱ ምዕራፍ ተመሳሳይ ከሆነበት ቦታ ላይ ምዕራፍና ቍጥሩን በማያያዝ እየጠቀስን አሳይተናል ። ከጥናቱ ቀጥሎ ለትምህርት ተስማሚ የሆኑ ጥቅሶች እንደማጠቃለያ ትምህርት ሆነው ገብተዋል ፤እንዲሁም በያንዳንዱ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ የትምህርቱን ጠቅላላ ስሜት የሚገልጡ ጥያቄዎች ስለሚገኙ፤አስተማሪው እርሱንና በርሱ መልክ ጥያቄ እንዲያቀርብ የሚገልጥ ሆኖ ተዘጋጅቷል ። አስተማሪውና ተማሪው በረጋ መንፈስ እንዲገነዘቡት ያስፈልጋል ። የተማሩትንም ሁሉ የሚገልጥ ቅ. መንፈስን መጥራት ስለሚያስፈልግ ፤ በየምዕራፉ መጨረሻ ላይ በጸሎት መልክ ተዘጋጅቶ ይገኛል ። የእግዚአብሔርን ስም የጠራ ሁሉ ይድናል ፤ ቀና ኅዳናን ያገኛልና ። ቤተ ክርስቲያናችን ይኸን ዝግጅት ለማድረግ የወሰነችበት እያንዳንዱ ወጣት ስለመንፈሳዊ ሕይወቱ ኃላፊነት ስላለበት ለመንፈሳዊ ሕይወቱ መመሪያ እንዲሆነው ሰፋ ያለ ጥናት ካደረገች በኋላ ነው ።

የመንበረ ፀባዖት ቅ. ሥላሴ ካቴድራል
የድርሰት ክፍል ።



# ማ ው ጫ ።

## ከ ብ ሉ ይ ኪ ዳ ን ።

ምዕራፍ ። ገጽ


፩ ፤ የሰማይና የምድር ፍጥረት ........ ፲፯
፪ ፤ የገነት ፍሥሐ ........ ፳
፫ ፤ የሰው ውድቀት ........ ፳፫
፬ ፤ ቃየልና አቤል ........ ፳፮
፭ ፤ የጥፋት ውኃ ........ ፳፱
፮ ፤ ቀስተ ደመና ........ ፴፪
፯ ፤ የባቢሎን ግንብ ........ ፴፭
፰ ፤ የአማኞች አባት አብርሃም ........ ፴፰
፱ ፤ የተስፋ ቃል ልጅ ........ ፵፩
፲ ፤ አብርሃም ይስሐቅን አቀረበ ........ ፵፬
፲፩ ፤ የይስሐቅና የርብቃ ጋብቻ ........ ፵፯
፲፪ ፤ ያዕቆብና ዔሳው ........ ፶
፲፫ ፤ ያዕቆብና ልጆቹ ........ ፶፫
፲፬ ፤ ለዳዊት የተሰጠ ተስፋ ........ ፶፮


## ከ ሐ ዲ ስ ኪ ዳ ን ።


፲፭ ፤ የአዋጅ ነጋሪ ልደት ........ ፶፱
፲፮ ፤ የመልአክ ብሥራት ........ ፷፪
፲፯ ፤ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ........ ፷፭
፲፰ ፤ የሰብአ ሰገል ስግደት ........ ፷፰
፲፱ ፤ ኢየሱስ በልጅነቱ ........ ፸፩
፳ ፤ የዮሐንስ ተግባር ........ ፸፬
፳፩ ፤ ጌታችን ተጠመቀ ........ ፸፯
፳፪ ፤ ጌታችን ተፈተነ ........ ፹
፳፫ ፤ የሥራው አጀማመር ........ ፹፫
፳፬ ፤ የአንድ ሰንበት ቀን ሥራ ........ ፹፮
፳፭ ፤ ኢየሱስ ኃጢአትን ያስተሠርያል ........ ፹፱
፳፮ ፤ የሐዋርያት መመረጥ ........ ፺፪
፳፯ ፤ የጌታችን ተአምራት ........ ፺፭




www.ethiopianorthodox.org


ምዕራፍ ። ገጽ



፳፰ ፤ ጌታችን የጸሎትን አቅድ አስተማረ .................... ፺፭
፳፱ ፤ ጌታችን ወደ ኢየሩሳሌም ሲወጣ .................... ፺፰
፴ ፤ ሆሣዕና .................... ፻፩
፴፩ ፤ የጌታችን መያዝ .................... ፻፬
፴፪ ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰቀለ .................... ፻፯
፴፫ ፤ ጌታችን ከሙታን ተነሣ .................... ፻፲፩
፴፬ ፤ ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ ታየ .................... ፻፲፬
፴፭ ፤ ጌታችን ዓረገ .................... ፻፲፯
፴፮ ፤ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ .................... ፻፲፱
፴፯ ፤ ተአምራት በሐዋርያት .................... ፻፳፪
፴፰ ፤ የኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ጥምቀት .................... ፻፳፯
፴፱ ፤ የጳውሎስ መጠራት .................... ፻፳፱



## ከብሉይ ኪዳን ።


፵ ፤ ዮሴፍ ተሸጠ .................... ፻፴፫
፵፩ ፤ ዮሴፍ ታሰረ .................... ፻፴፮
፵፪ ፤ ዮሴፍ ተሾመ .................... ፻፴፱
፵፫ ፤ ዮሴፍና ወንድሞቹ .................... ፻፵፪
፵፬ ፤ ያዕቆብ ወደ ግብፅ ወረደ .................... ፻፵፭
፵፭ ፤ የሙሴ ልደትና እድገት .................... ፻፵፰
፵፮ ፤ የሙሴ መጠራት .................... ፻፶፩
፵፯ ፤ የፈርዖን ደንዳናነት .................... ፻፶፬
፵፰ ፤ የግብፅ መቅሠፍቶች .................... ፻፶፯
፵፱ ፤ እስራኤል ከግብፅ ወጣ .................... ፻፷፩
፶ ፤ እስራኤል የኤርትራ ባሕርን ተሻገረ .................... ፻፷፬
፶፩ ፤ እግዚአብሔር ሕዝቡን እየመገበ መራቸው .................... ፻፷፯
፶፪ ፤ በሲና ተራራ እግዚአብሔር ሕግን ሰጠ .................... ፻፸




ከግብፅ ወደ ሲና
ሥርጽ ጐዳና
ረጅም ጉዞ
፶ ኪሎሜትር
ወደ ደማስቆ
ሴኬም
ቤቴል
ኬብሮን
ኤዶም
ሱኮት
ግብፅ
ማራ
ኤሊም
የሲን ምድረ በዳ
ራፊዲም
ሲና ተራራ
ምድያም


ቅድስት አገር በክርስቶስ ዘመን
፲ ኪሎሜትር
ወደ ጠርሴስ
ደማስቆ
ሶርያ
ቅፍርናሆም
ቤተሳይዳ
ገሊላ
ቃና
ናዝሬት
ጌርጌሴኖን
ታላቁ ባሕር
ሰማርያ
የዮርዳኖስ ወንዝ
ሴኬም
የያቦቅ ወንዝ
ቤቴል
ኢያሪኮ
ቤተ ራባ
ኢየሩሳሌም
ቢታንያ
ቤተልሔም
ይሁዳ
ኬብሮን
ጋዛ
የጨው ባሕር
የአርኖን ወንዝ
ቤርሳቤህ
ወደ ግብፅ
መንገዶች
ደብረ ዘይት

## ማ ሳ ሰ ቢ ያ ።

የዚህ መጽሐፍ አገላለጥና የጥቅሶች አገባብ ትንሽ ለየት ያለ ስለሚመስል ለአንባቢዎች እንዲመች ከዚህ በሚቀጥለው መንገድ እንገልጣለን ።

ዘፍጥ. ፩ ፥ ፩—፪ ፥ ፫ ። ይህ ማለት ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፩ ቊጥር ፩ እስከ ምዕራፍ ፪ ቊጥር ፫ ማለት ነው ።


ይህ ንዑስ ሠረዝ «፥» የሚገኘው ከምዕራፍና ከቊጥር መካከል ብቻ ሲገኝ ነው። «—»ሂድ የሚለው ምልክት ደግሞ «እስከ» ማለት ነው ።

በአንድ ቦታ ሁለት ወይም ከሁለት የሚበልጥ ክፍሎች ቢኖሩ ከእያንዳንዱ ክፍል መካከል ድርብ ሠረዝ «፤» ይቃተማል ። ለምሳሌ ዘፍጥ. ፩ ፥ ፳፯—፴፩ ፤ ፭ ፥ ፪ ፤ አሞጽ ፬ ፥ ፲፫ ። ይህም ማለት ኦሪት ዘፍጥረት ም. ፩ ቊ. ፳፯—፴፩ ፤ ም. ፭ ቊ. ፪ ፤ አሞጽ ም. ፬ ቊ. ፲፫ ማለት ነው ።

፪ ጴጥ. ፪ ፥ ፭ ፥ ፱ ፥ ፲ ማለት ፪ኛ ጴጥሮስ ም. ፪ ቊ. ፭ ቊ. ፱ ቊ. ፲ ማለት ነው ። ሌላውም በዚህ መልክ ስለሚሄድ አንባቢዎች ሁሉ በጥንቃቄ እንድ ትረዱልን እናሳስባለን ።

በአንድ ቃል አጠገብ * ሲገኝ ፥ በምዕራፉ ሥር መግለጫ መስጠቱን ያመለክታል ።





ምዕራፍ ፩ ።

## የሰማይና የምድር ፍጥረት ።

ዘፍጥ. ፩ ፥ ፩—፪ ፥ ፫ ።

፩ ፤ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ። ዘፍጥ. ፩ ፥ ፩ ።

የምንኖርባት ምድር ለዓይን በሚያምሩ፥ ለሕይወትም በሚጠቅሙ ነገሮች እንዴት ተሞላች ! በላያችን ያለው ሰማይ በስፋቱ ያስገርማል ፤ በየዕለቱም በፀሐይ ጮራ ፥ ደመናዎች በሚያወርዱልንም ዝናም እየ ተጠቀምን መልካም የሆነውን አየርን እየተነፈስን እንኖራለን ። ምድሪቱም ለሰውነታችን የሚስማማውን እህል በየ ዓመቱ ታበቅልልናለች ። እኛም ባልፈጠ ርናቸው በስንትና በስንት ዓይነት ነገር ለልብስም ሆነ ለቤት ፥ ለሥራ መሣሪያዎ ችም በሆኑ ነገሮች እየተጠቀምን እንኖ ራለን ። በምንደክምበት ጊዜ ለእንቅልፍ የሚመቸው ጨለማ ማታ ማታ ይመጣ ልናል ። ይህንም ሁሉ ስናስብ መኖሪያ የሆነችልን ምድር በእውነት መልካም መኖሪያ እንደ ሆነች እናስተውላለን ።

በመጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ የሚ ገኘው ቃል ፥ ይህን ድንቅ መኖሪያ ያዘጋ ጀልን እግዚአብሔር እንደ ሆነ ይነግረ ናል ። እግዚአብሔርም ሁሉን ቻይ ነውና ሰማይንና ምድርን የፈጠረ በቃሉ ነው። የሰው ቃል እንዲህ ያለ ኃይል የለውም ፤ እግዚአብሔር ግን በቃሉ ሲናገር ፥ ያል ሆኑትንም እንደ ሆኑት ሲጠራቸው ይፈ ጠራሉ ይሆናሉም ። እንደ እግዚአብሔር አምላካችን ያለ አንድም የለም ፤ ከእር ሱም በቀር ሌላ አምላክ የለም ። ሰማይና



www.ethiopianorthodox.org

ምድር ሳይፈጠሩ ፥ ዓመታትና ዘመናትም ሳይጀመሩ እግዚአብሔር ነበረ ። እርሱም መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም የሚኖር አምላክ ነው።

## ፪ ፤ እግዚአብሔር ምድርን ለሰው አዘጋጀ ።

ዘፍጥ. ፩ ፥ ፩—፳፭ ።

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ። ምድርም ባዶ ነበረች፥ አንዳችም አልነበረባትም ፤ ጨለማም በጥልቁ ውኃ ላይ ነበረ ። ነገር ግን በውኆች ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ ሰፍፎ ነበርና እግዚአብሔር ባዶ የሆነችው ፥ ጨለማ የነበረችውም ምድር የሰው መኖሪያ እንድትሆን በብዙ መልካም ነገሮች እንዲሞላት አሰበ ። እግዚአብሔርም በብርሃን ሆነ በጨለማ ለመሥራት ይችላል፤ ለእርሱ የሚሳነው ነገር የለምና ።

እግዚአብሔርም መኖሪያ እንድትሆን ምድርን ባዘጋጀ ጊዜ ከሁሉ አስቀድሞ ፥ «ብርሃን ይሁን » አለ ፤ ብርሃንም ሆነ ። እግዚአብሔርም ብርሃኑ መልካም እንደ ሆነ አየ ፤ ብርሃኑንም ቀን፥ጨለማውንም ሌሊት ብሎ ጠራቸው ። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ ፥ አንደኛ ቀን ።

እግዚአብሔርም ፥ «ጠፈር ይሁን» አለ ፤ ጠፈርም ሆነ ። ጠፈርም ከበላዩና ከበታቹ ያሉትን ውኆች ለየ ። እግዚአብሔርም ጠፈርን ሰማይ ብሎ ጠራው። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ ፥ ሁለተኛ ቀን።

እግዚአብሔርም ፥ «የብሱ ይገለጥ» ባለ ጊዜ ውኃ በአንድ ስፍራ ተሰበሰበ ። እግዚአብሔርም የብሱን ምድር የውኃ መከማቻውንም ባሕር አላቸው ። እግዚአብሔርም ፥ «ምድር ቡቃያን ታብቅል» በማለት ሣርንና ዘርን የሚሰጥ ቡቃያ ሁሉ ፍሬንም የሚያፈራ ዛፍ ሁሉ እንደየዓይነቱ ፈጠረ ። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ ፥ ሦስተኛ ቀን ።

እግዚአብሔርም ፥ «ብርሃናት በጠፈር ይሁኑ» ባለ ጊዜ በቀንና በሌሊት የሚሠለጥኑ ፀሐይና ጨረቃ ሆኑ ። ከዋክብትንም ደግሞ አደረገ ። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ ፥ አራተኛ ቀን ።

እግዚአብሔርም ፥ «ውኃ ፥ ሕያዋን ተንቀሳቃሾችን ታስገኝ ፥ ወፎችም ከምድር በላይ ይብረሩ » አለ ፤ እንዲሁም ሆነ ። እግዚአብሔርም በውኃ ለሚኖሩትና በአየር ለሚበርሩት ፍጥረታት ሁሉ ፥ « ብዙ ተባዙም » ብሎ ባረካቸው ። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ ፥ አምስተኛ ቀን ።

እግዚአብሔርም ፥ «ምድር እንስሳትንና ተንቀሳቃሾችን አራዊትንም ታውጣ» አለ ፤ እንዲሁም ሆነ ። እግዚአብሔርም አራዊትን እንስሳትንም የምድር ተንቀሳቃሾችንም ሁሉ እንደየወገኑ አደረገ ። እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ ።

## ፫ ፤ እግዚአብሔር ሰውን ፈጠረ ።

ዘፍጥ. ፩ ፥ ፳፮—፴፩ ፤ ፳ ፥ ፪ ፤ ዓሞጽ ፩ ፥ ፲፫ ።

ይህንም ሁሉ በመፍጠርና በማድረግ ምድርን ለሕይወትና ለደስታ በሚያስፈልገው ሁሉ ሞልቶ ካዘጋጃት በኋላ እግዚአብሔር የልቡን አሳብ የሚያካፍለውን በምድራዊ ፍጥረታት ሁሉ ላይ የሚሾመውን ገዥ ለመፍጠር ወዶ ፥ «ሰውን በመልካችን እንፍጠር » ብሎ ወንድና ሴት አድርጎ ሰውን እንደ ራሱ ምሳሌ ፈጠረ ። እግዚአብሔርም ባረካቸው ፥ « ብዙ ፥ ተባዙ ፥ ምድርንም ምሉዋት ግዙዋትም ፤ የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙዋቸው» አላቸው ። እግዚአብሔርም በፈጠራቸው ቀን አዳም ብሎ ስም አወጣላቸው ። እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ ፥ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ ። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ ፥ ስድስተኛ ቀን ።

## ፬ ፤ የሰንበት ቀን ።

ዘፍጥ. ፪ ፥ ፩—፫ ።

ሰማይንና ምድርን ሠራዊታቸውንም ሁሉ ከፈጸመ በኋላ በሰባተኛው ቀን እግዚአብሔር ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ፤ እግዚአብሔርም ሰባተኛውን ቀን ባረከው ቀደሰውም ።

* * *


በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ። ዘፍጥ. ፩ ፥ ፩ ።

በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ ፥
ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ ፤
የባሕርን ውኃ እንደ ረዋት የሚሰበስበው ፥
ቀላዮችንም በመዝገቦች የሚያኖራቸው ።
ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን ትፍራው ፥
በዓለም የሚኖሩ ሁሉም ከእርሱ የተነሣ ይደንግጡ ።
እርሱ ተናግሮአልና ፥ ሆኑም ፤
እርሱ አዘዘ ፥ ጸኑም ። መዝ. ፴፪ (፴፫) ፥ ፮—፱ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ የሁሉ ፈጣሪ ማን ነው ?
፪ ፤ ሰው በማን ምሳሌ ተፈጠረ ?
፫ ፤ እግዚአብሔር ለፈጠረው ሰው ምን አለው ?

ጸሎት ፤ እጆችህ ሠሩኝ አበጃጁኝም ፤
እንዳስተውል አድርገኝ ፤ ትእዛዛትህንም
እማራለሁ ። መዝ. ፻፲፰ (፻፲፱) ፥ ፸፫ ።



ምዕራፍ ፪ ።

## የገነት ፍሥሐ ።

ዘፍጥ. ፪ ፣ ፩—፳፭ ።

፩ ፤ የሰው ተፈጥሮ ።

ዘፍጥ. ፩ ፣ ፳፮—፳፰ ፤ ፪ ፣ ፯ ።

እግዚአብሔር ምድርን መልካም አድርጎ ካዘጋጃት በኋላ የምድራዊ ፍጥረታት ራስ የሚሆነውን ሰው በፈጠረ ጊዜ ከምድር አፈር አበጀው ፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ ።

እግዚአብሔር አምላክም ለሰው የሰጠው አካል በሚያስደንቅ ጥበብ የተሠራ ነው ። በዓይን ለማየት ፣ በጆሮ ለመስማት ፣ በአፍንጫ ለመተንፈስ ፣ በጥርስ ለመብላት ፣ በጉሮሮና በምላስ ለመናገር፣ በእጅ ለመሥራት ፣ በእግር ለመሄድ የሚችል አካል ድንቅ ሥራ አይደለምን? ነገር ግን ከዚህ በላይ እግዚአብሔር የሚያስብበትንና የሚያስተውልበትን አእምሮ ለሰው ሰጠው ። በዚህም አእምሮ ሰው ያስባል ፣ አሳቡንም በቋንቋ ይገልጣል ፣ ተምሮና መርምሮ ተመካክሮም ይሠራል፣ በአሳቡም አመዛዝኖ ይህን ወይም ያን አደርጋለሁ ብሎ ይመርጣል ይፈቅዳልም። ከዚህም ይልቅ ሰው ከፈጣሪ አምላኩ ጋር ለመተዋወቅ ፣ የእርሱንም ፈቃድ አስተውሎ በፍቅር ለእርሱ ለመታዘዝ ፣ በእርሱም ለመደሰት እንዲችል መንፈሳዊ ፍጥረት ሆኖ እንደ አምላኩ ምሳሌ ተፈጠረ ። ለዚህም ክብርና ደስታ እግዚአብሔር ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው ።



፪ ፤ ለሰው መኖሪያ የተተከለ ገነት ።

ዘፍጥ. ፪ ፣ ፰—፲፬ ።

እግዚአብሔር አምላክም ዔድን በሚባለው ሥፍራ ገነትን ተከለ ፤ የፈጠረውንም ሰው በዚያ አኖረው ። በገነትም ውስጥ ለመታየት የሚያምሩትን ለመብላትም የሚጣፍጡትን ዛፎች ሁሉ በየዓይነቱ ተከለ ። በገነትም መካከል የሕይወትን ዛፍና መልካምንና ክፉን የሚያስታውቀውን ዛፍ ተከለ ። ገነትንም የሚያጠጣ ወንዝ አደረገለት ። ዔድን ማለት ተድላ ማለት ነውና ይህ የተድላ ገነት መልካም የሆነ ለሰውም የሚስማማ መኖሪያ ቦታ ነበረ ።

፫ ፤ ለሰው የተሰጠ አደራና ትእዛዝ ።

ዘፍጥ. ፪ ፣ ፲፭—፲፯ ።

እግዚአብሔር አምላክም እንዲያበጃጀውና እንዲጠብቀው በዔድን ገነት ሰውን ወስዶ አኖረው ። እንደዚሁም በእጁ ሥራ ላይ ለሾመው ሰው መልካም የሆነ ሥራና አደራ በሰጠው ጊዜ ከክፉና ከሞት የሚጠብቀውን ትእዛዝ ጨምሮ፣ « ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ፤ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞት ትሞታለህና » አለው ።

፬ ፤ ለሰው የተሰጠ የጋብቻ ኑሮ ።

ዘፍጥ. ፪ ፣ ፲፰—፳፭ ።

እግዚአብሔር አምላክም የምድር አራዊትንና የሰማይ ወፎችን ወደ አዳም አመጣቸው ። አዳምም በተሰጠው ጥበብና ሥልጣን ሕያው ነፍስ ላለው ሁሉ ስም አወጣለት ። እግዚአብሔር ራሱ ቀንና ሌሊት ሰማይና ባሕር የሚባሉትን ሰየማቸው ፣ ነገር ግን ለአራዊትና ለወፎች ለተንቀሳቃሾችም ሁሉ ስም ያወጣላቸው በላያቸው የተሾመው ሰው ነበረ።

ከእነዚህ ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ ግን ለአዳም እንደ ራሱ ያለ ጓደኛ አልተገኘለትም።እግዚአብሔርም ፣ «ሰው ብቻውን እንዲሆን መልካም አይደለም ፤ የምትመቸውን ረዳት እንፍጠርለት » አለ።

በዚያን ጊዜም እግዚአብሔር አምላክ በአዳም ላይ ከባድ እንቅልፍን ጣለበት ፤ ከጐኑም አጥንትን ወስዶ ሴት አድርጎ ሠራት ። አዳምም በነቃ ጊዜ እግዚአብሔር ሴቲቱን ወደ እርሱ አመጣት ። አዳምም ባያት ጊዜ ደስ ብሎት፣ «ይህች አጥንት ከአጥንቴ ፣ ሥጋም ከሥጋዬ ናት» ብሎ ወደዳት ። እግዚአብሔርም ፣ «ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፣ ከሚስቱም ይጣመራል ፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ » ብሎ ለሰው የጋብቻን ኑሮ መሠረተለት ።

አዳምና ሚስቱም ፣ ለደስታቸው እስቦ ገነትን ባዘጋጀላቸው በእግዚአብሔር አምላክ ፍቅርና መልካምነት ታምነው ዕራቁታቸውን ሆነው ሳይተፋፈሩ በአንድነት ኖሩ ።



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር በመንገዱ ሁሉ ጻድቅ ነው ።
በሥራውም ሁሉ ቸር ነው ።
መዝ. ፻፵፬ (፻፵፭) ፥ ፲፯ ።

ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ ፤
ሥራህ ድንቅ ነው ፤ ነፍሴም እጅግ ታውቀዋለች ።
መዝ. ፻፴፰ (፻፴፱) ፥ ፲፬ ።

*　*　*

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ እግዚአብሔር ሰውን በምን ሥፍራ አኖረው ?
፪ ፤ ምንስ ትእዛዝ ሰጠው ?
፫ ፤ እግዚአብሔር ስለ ባልና ሚስት ኑሮ ምን አለ ? (ቈ. ፳፬ ።)

ጸሎት ፤ አቤቱ ፥ አሳቦችህ በእኔ ዘንድ እንደ ምን እጅግ
የተከበሩ ናቸው !
ቍጥራቸውም እንደምን በዛ !
ብቈጥራቸው ከአሸዋ ይልቅ ይበዛሉ ፤
ተነሣሁም ፥ እኔም ገና ከአንተ ጋር ነኝ ።
መዝ. ፻፴፰ (፻፴፱) ፥ ፲፯ ፥ ፲፰ ።





ምዕራፍ ፫ ።

## የሰው ውድቀት ።

ዘፍጥ. ፫ ።

፩ ፤ ሰው ተፈትኖ ወደቀ ።

ዘፍጥ. ፫ ፥ ፩—፳ ፤ ራእይ. ፲፪ ፥ ፱ ።

እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ፥ ተንኰለኛ ነበረ ። እባቡም ሴቲቱን ፥ « በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን ? » አላት ። ሴቲቱም ፥ እንዲህ ብሎ ስለ ተከለከለው ፍሬ በእባብ በኩል የሚያነጋግራት ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው የእግዚአብሔር ጠላት መሆኑን እንዳወቀች አይመስልም። ሰይጣን ሐሰተኛ የሐሰትም ሁሉ አባት ነውና ሰውን ለማጥፋት ስለ ፈለገ በተንኰል ራሱንም በመደበቅ እንዲያስታት አሰበ ።

ሴቲቱም ፥ «በገነት ካለው ዛፍ ፍሬ ሁሉ እንበላለን ፤ ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፍ ፍሬ እግዚአብሔር ፥ እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አለን» ብላ



www.ethiopianorthodox.org

መለሰችለት ። እባቡም እጅግ ደፍሮ ፥ « ሞትስ አትሞቱም ፤ አትብሉ ያለበት ምክንያት ከፍሬው በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንደሚከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንደ ምትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ» ብሎ የእግዚአብሔርን መልካምንትና እውነት ሊያጠራጥራት አሰበ ።

ሴቲቱም ወዲያውኑ የእግዚአብሔርን በጎ ስጦታና ፍቅር ረስታ ትእዛዙን በመተላለፍ ጥቅምዋን ያየች መሰላት ። የእባቡንም ቃል እያሰላሰለች ወደ ዛፉ ተመለከተች ። ፍሬው እንዴት ያማረ የሚያስጐመጅም ነበረ ! ከዚህም ይልቅ ጥበብን እንደሚሰጥ እባቡ አልነገራትምን ? እንዲሁ ተመኝታ እጅዋን ዘረጋች ለቀመችው በላችውም ፤ ለባልዋም ሰጠች ፤ እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ ።

ወዲያውም ደስታቸው በኀፍረት ፥ መታመናቸውም በድንጋጤ ተለወጠ ። የሁለታቸውም ዓይኖች ተከፈቱ ፥ ዕራቁታቸውን እንደ ሆኑ ዐወቁ ፤ እርስ በርሳቸውም ተፋፍረው የበለስ ቅጠሎችን ሰፍተው ለራሳቸው ግልድም አገለደሙ ። ቀኑም ሲመሽ የእግዚአብሔር አምላክን ድምፅ በገነት በሰሙ ጊዜ አዳምና ሚስቱ ከፊቱ ሸሽተው በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ ።

## ፪ ፤ ፈታኙ ተፈረደበት ።

ዘፍጥ. ፫፡፱—፲፭ ።

እግዚአብሔር አምላክም ፥ ከእርሱ የሚሠወረው ነገር ስለሌለ ሁሉን ዐውቆ ወዴት እንደ ተሸሸጉ አስተዋለ ። ነገር ግን የፈጠረውን ሰው ስለ ወደደ ፥ «ወዴት ነህ ? » ብሎ ጠራው ። አዳምም ፥ «ድምፅህን በሰማሁ ጊዜ ፈራሁ ተሸሸግሁም» አለው ። እግዚአብሔርም ፥ «ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍ በውኑ በላህን ? » አለው ። አዳምም ፥ «ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት ከዛፉ ፍሬ ሰጠችኝና በላሁ» አለ ። እግዚአብሔር አምላክም ለሴቲቱ ፥ «ይህን ያደረግሽው ምንድር ነው ? » አላት ። እርስዋም ፥ «እባቡ አሳተኝና በላሁ » አለች ።

እግዚአብሔር አምላክም እባቡን ፥ «ይህን ስላደረግህ የተረገምህ ትሆናለህ ፤ የሴት ዘርም ራስህን ይቀጠቅጣል ፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ» ብሎ የጥፋት ፍርድ ፈረደበት ። እባቡም ከሴት ዘር በሚወለደው በኩል እርሱ ራሱ እንደሚጠፋ በሰማ ጊዜ እንዴት ይቈጣ ይመስላችኋል ? ነገር ግን እግዚአብሔር አምላክ ከተናገረበት ፍርድ እንደማያመልጥ ዐወቀ ።

## ፫ ፤ የገነት ፍሥሐ በመከራ ተለወጠ ።

ዘፍጥ. ፫፡፲፮—፳፬ ።

እግዚአብሔር አምላክም የእባቡን ፍርድ ከተናገረ በኋላ ለሴቲቱ ፥ «በጭንቅ ትወልጃለሽ ፤ ባልሽ ገዥሽ ይሆናል » አላት ። ለአዳምም ፥ « ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን ፤ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ ፤ ወደ ወጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራ ትበላለህ ፤ አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ » አለው ።

ጭንቅ ፥ ድካም ፥ ሞት ፥ መቃብር ! የገነት ፍሥሐ ጠፍቶ በእውነት በመከራ ተለወጠ ። በእግዚአብሔር አምላክ ታምነው ለትእዛዙ በመታዘዝ ፈንታ ወደ ሞት የሚመራውን የሰይጣንን ሐሰተኛ ቃል በመስማት ምን ያህል ጉዳት አገኛቸው ! ከዚህም አሳዛኝ ውድቀት በኋላ በገነት



ለመኖር አልተፈቀደላቸውም ፤ እግዚአብሔር አምላክም ከዔድን ገነት አስወጣቸው ፤ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልን የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን አስይዞ በዔድን ምሥራቅ አስቀመጠ ።

* * *

እግዚአብሔር ሰውን እንዲህ አለው ፤
እነሆ ፥ እግዚአብሔርን መፍራት ጥበብ ነው ፤
ከኀጢአትም መራቅ ማስተዋል ነው ።

ኢዮብ ፳፰፡፳፰ ።

ኀጢአት የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች ።

ሕዝ. ፲፰፡፬ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ሴቲቱን የፈተናት ማን ነው ?
፪ ፤ አዳምና ሚስቱ የተከለከለውን ፍሬ ከበሉ በኋላ ምን አደረጉ ?
፫ ፤ መልካም ሆኖ ወደ ተፈጠረ ምድር መከራና ሞት የገባ በምን ምክንያት ነው ?

ጸሎት ፤ ጌታ ሆይ ፥ በአንተ ላይ ኀጢአት ስለ ሠራን ለእኛ . . የፊት ኀፍረት ነው ። በእርሱ ላይ ምንም እንኳ ያመፅን ብንሆን ፤ . . . ለጌታ ለአምላካችን ምሕረትና ይቅርታ ገንዘቡ ነው ። አቤቱ መልሰን ፥ ፊትህንም አብራ ፥ እኛም እንድናለን ።

ዳን. ፱፡፯፡፱ ፤ መዝ. ፸፱ (፹)፡፫ ።



ምዕራፍ ፬ ።

## ቃየልና አቤል ።

ዘፍጥ. ፬ ፡ ፳ ።

### ፩ ፤ አዳምና ሚስቱ ልጆችን ወለዱ ።

ዘፍጥ. ፫ ፡ ፳ ፡ ፳፩ ፡ ፬ ፡ ፩ ፡ ፪ ።

አዳምና ሚስቱ የፈጣሪያቸውን መልካም ትእዛዝ በመተላለፍ በወደቁ ጊዜ በነዘን ከገነት ወጡ ። ሆኖም እግዚአብሔር አምላክ ፤ በቶሎ ከሚረግፉት ለራሳቸው ከሠሩት ከቅጠል ልብስ የሚሻለውን የቁርበት ልብስ አዘጋጅቶ አልብሶአቸው ነበርና በፍቅር እንደሚያስብላቸው ተረዱ ። ከዚህም በላይ የሴት ዘር የእባቡን ራስ ይቀጠቅጣል በማለት ተስፋ አሰምቶአቸው ነበርና አዳም ፤ የሕያዋን ሁሉ እናት ናት ብሎ ሚስቱን ሔዋን አላት ።

ስለዚህም ተስፋ ከገነት ውጭ በችግርና በድካም ሲኖሩ ሔዋን ልጅ በወለደች ጊዜ እጅግ ደስ ብሎአት ፤ «ወንድ ልጅ ከእግዚአብሔር አገኘሁ» ስትል ቃየል ብላ ሰየመችው ። ደግሞም ወንድሙን አቤልን ወለደች ። እነዚህም ሁለት ወንድማማቾች ካደጉ በኋላ ቃየል ገበሬ ሆነ አቤልም የበግ ጠባቂ ሆነ ።

### ፪ ፤ የቃየልና የአቤል መሥዋዕት ።

ዘፍጥ. ፬ ፡ ፫—፭ ።

ከዕለታትም አንድ ቀን ቃየልና አቤል ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ለማቅረብ አሰቡ ። ቃየልም ከምድር ፍሬ ወስዶ መሥዋዕት ሲያቀርብ አቤል ከበጎቹ በኵራት መርጦ ከነስቡ መሥዋዕት አቀረበ ። ለሰው ዓይን በቃየልና በአቤል መካከል ብዙ ልዩነት ቢታይም ባይታይም በቅዱስ አምላክ ፊት ትልቅ ልዩነት ነበረ ። እግዚአብሔርም አቤል ስለ ኃጢአቱ አዝኖ በተዋረደ ልብ ፤ በእምነትም በተሞላ ልብ እንደ ቀረበ አየ ፤ እግዚአብሔርም አቤልንና መሥዋዕቱን ተቀበለ። ነገር ግን ልብን የሚመረምር አምላክ ወደ ቃየልና ወደ መሥዋዕቱ አልተመለከተም አልተቀበለውም ።

### ፫ ፤ የአቤል ሞት ።

ዘፍጥ. ፬ ፡ ፰—፲፭ ፤ ፩ ዮሐ. ፫ ፡ ፲፩—፲፪ ።

ቃየልም እግዚአብሔር አቤልን እንጂ እርሱን እንዳልተቀበለው ባየ ጊዜ ተቈጣ ፤ ፊቱንም አጠቈረ ። ኵርቶ ስለ ነበር እግዚአብሔርን ወንድሙንም ተቈጣ እንጂ በቅን ልብ ፤ አምላኬ ሆይ፤ ምን ማድረግ ይገባኛል ? አላለም ። እግዚአብሔርም ፤ «ለምን ተናደድህ ? » ብሎ በምሕረቱ ከኵራቱ እንዲመለስ ጊዜ ሰጠው ፤ ቃየል ግን ልቡን አጽንቶ አልመለስ አለ ። ቍጣውም እየበረታበት ሄደ ፤ የገዛ ራሱ ሥራ ክፉ ፤ የወንድሙም ሥራ ጽድቅ ስለ ነበረ ጠላው ። ከዕለታትም አንድ ቀን አቤልን ፤ «ና ወደ ሜዳ እንሂድ » አለው ፤ በሜዳም ሳሉ ቃየል በወንድሙ ላይ ተነሣ ገደለውም ።

እግዚአብሔርም ቃየልን ፤ «ወንድምህ አቤል ወዴት ነው ? » አለው ። እርሱም ፤ «አላውቅም ፤ የወንድሜ ጠባቂው ነኝን ? » አለ ። እግዚአብሔርም፤ «ምን አደረግህ ? የወንድምህ የደሙ ድምፅ ከምድር ወደ እኔ ይጮኻል » ብሎ ከእንግዲህ ወዲህ ቃየል የተረገመ ኰብላይ እንደሚሆን ነገረው ። ቃየልም በደረሰበት ቅጣት እንጐራጐረ ፤ « የሚያገኘኝ ሁሉ ይገድለኛል » አለ ። እግዚአብሔርም ፤ «እንግዲህ ቃየልን የገደለ ሁሉ ሰባት እጥፍ ይበቀልበታል » ብሎ ማንም ሰው እንዳይገድለው ምልክት አደረገለት ።

### ፬ ፤ የአቤል ምትክ ።

ዘፍጥ. ፬ ፡ ፳፭ ።

ከዚህም በኋላ ሔዋን ሌላ ልጅ ወለደችና ፤ «ቃየል በገደለው በአቤል ፈንታ እግዚአብሔር ሌላ ልጅ ተክቶልኛል » ስትል ሴት አለችው ። ሴት በትርጉም ሲገለጥ ምትክ ማለት ነው ። ለአዳምና ለሔዋንም ሌሎች ልጆች ፤ ወንዶችም ሴቶችም ተወለዱ ።

### ፭ ፤ የቃየልና የሴት ዘሮች ።

ዘፍጥ. ፬ ፡ ፲፯—፭ ፡ ፴፩ ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ከቃየልና ከሴት ዘሮች ከሆኑት ስለ አንዳንዶቹ እናነባለን ። ቃየልም ከተማን ሠራ ፤ ከተማዪቱን በልጁ ስም ሰየማት ። ከዘሮቹም የተወለዱ ሰዎች ብዙ ጠቃሚ ዕውቀትና ብልሃትን እየተማሩ ሄዱ ፤ ነገር ግን ወደ እግዚአብሔር አልተመለሱም ። ከአዳም ሰባተኛው በነበረ ላሜሕ በተባለ ሰው ታሪክ ኃጢአት እየበዛ እንደ ሄደ ይታያል። ላሜሕም በክፋቱ ይፎክር ነበር ። ነገር ግን





www.ethiopianorthodox.org

ሴት የሚባል የአቤል ምትክ፥ ሄኖስ የተባ ለውን ልጅ በወለደ ጊዜ ሰዎች በእግዚአ ብሔር ስም ይጠሩ ጀመሩ ። በሴት ዘርም ከአዳም ሰባተኛ የሆነ ሄኖክ የሚባል ሰው ከእግዚአብሔር ጋር አካሄዱን አደረገ ። በመጨረሻም ገና በሕይወቱ ሳለ እግዚ አብሔር ሄኖክን ወደ ራሱ ወሰደ ።

እስከ ዛሬም ድረስ እንደ ቃየልና እንደ ላሜሕ ክፉውን የሚከተሉ ሰዎች አሉ ። ነገር ግን ዓለም ምንም በክፋት ቢሞላ እንደ አቤል በእምነት ወደ እግዚ አብሔር በመመለስ ምሕረትን የሚቀ በሉ ሰዎች አሉ ፤ እንደ ሄኖክም ዕለት ዕለት ከእግዚአብሔር ጋር አካሄዳቸውን የሚያደርጉ ሰዎች አሉ ። እነርሱም የእ ግዚአብሔርን ዘላለማዊ መንግሥት ይወ ርሳሉ ።

* * *

የኀጥአን መሥዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ አስ
ጸያፊ ነው ፤
የቅኖች ጸሎት ግን በእርሱ ዘንድ የተወደደ ነው ።
ምሳ. ፲፭ ፡ ፰ ።

ኃጢአቱን የሚሠውር አይለማም ፤
የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል ።
ምሳ. ፳፰ ፡ ፲፫ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ የአዳም መጀመሪያዎች ልጆች እነማን ነበሩ ?
፪ ፤ ለመሥዋዕት ምንና ምን አቀረቡ ?
፫ ፤ ታላቁ ልጅ ወንድሙን የገደለ በምን ምክንያት ነበረ ?
፬ ፤ የአቤል ምትክ ማን ተባለ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፥ እነሆ እውነትን ወደድህ ፤ . . .
በደሌን ሁሉ ደምስስልኝ ።
አቤቱ ፥ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ ፥
የቅናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ ።
መዝ. ፶ (፶፩) ፡ ፯ ፡ ፱ ፡ ፲ ።





ምዕራፍ ፭ ።

## የጥፋት ውኃ ።

ዘፍጥ. ፯ ፡ ፯ ።

### ፩ ፤ የኃጢአት መስፋፋት ።

ዘፍጥ. ፮ ፡ ፩—፯ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ።

ሰዎች በምድር ላይ እየበዙ በሄዱ ጊዜ የሰው ክፋት ደግሞ እየበዛ እየተስፋ ፋም ሄደ ። ኃጢአት የሚደርስበትን ሁሉ ያበላሻልና ምድር ከሰው ግፍና ኃጢአት የተነሣ እየተበላሸች ትሄድ ነበር ።

በመጀመሪያ እግዚአብሔር የፈጠረ ውን ሁሉ ባየ ጊዜ እጅግ መልካም ነበረ እንጂ አንድም የተበላሸ ነገር አልነበረም። አሁን ግን እግዚአብሔር ምድርን ባየ ጊዜ በጣም አዘነ ፤ የሰው የልቡ አሳብ ፥ ምኞቱም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደ ሆነ ፥ ከሰውም ክፋት የተነሣ ያች እጅግ መል ካም የነበረች ምድር ፈጽሞ የተበላሸች፥ በግፍም የተሞላች መሆንዋን አየ ። ሰው ሁሉ በምድር ላይ መንገዱን አበላሽቶ ነበርና ።



www.ethiopianorthodox.org

፪ ፤ ጻድቁ ኖኅ ። ዘፍጥ. ፮ ፡ ፰—፲ ።

ነገር ግን ኖኅ የተባለው ሰው እንደ ቅድም አያቱ እንደ ሄኖክ ከእግዚአብሔር ጋር አካሄዱን ያደርግ ነበር ። እርሱም እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ፈልጎ በዙሪያው ያየውን ክፋት ሁሉ ጠላ ፤ ዕለት ዕለትም እግዚአብሔርን እያሰበና እየታ ዘዘ ይኖር ነበር ። ኖኅም በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን አገኘ ። ለኖኅም ሴም ፥ ካም ፥ ያፌትም የተባሉ ሦስት ልጆች ነበሩት።

፫ ፤ እግዚአብሔር ለኖኅ አሳቡን ነገረው። ዘፍጥ. ፮ ፡ ፲፫—፳፪ ።

እግዚአብሔርም በፈጠረው ሰው ክፋት አዝኖ ሳለ ከሚያስተውለው ሰው ከኖኅ ጋር በመነጋገር የልቡን አሳብ ሊያ ካፍለው ወደደ ። እግዚአብሔርም ኖኅን፥ « ምድር በሰው ግፍ ተሞልታ ተበላሽታለችና እኔም እነሆ በምድር ላይ የጥፋት ውኃን አመጣለሁ ፤ በምድር ያለው ሁሉ ይጠፋል ። ነገር ግን ከአንተ ጋር ቃል ኪዳኔን አቆማለሁና አንተና ቤተ ሰቦችህ ከጥፋት ውኃ እንድትድኑ መርከብ ሥራ» አለው ።

እግዚአብሔርም ፥ «ከአንተ ጋር በሕይወት እንዲኖሩ ከሕያው ፍጥረት ሁሉ ሁለት ሁለት እያደረግህ ወደ መርከብ ታገባለህ ፤ ተባትና እንስት ይሁኑ ። ከወፍ እንደ ወገኑ ፥ ከእንስሳም እንደ ወገኑ ፥ ከምድር ተንቀሳቃሽም ሁሉ እንደ ወገኑ ወደ አንተ ይግቡ ። ከሚበላውም መብል ሁሉ ለአንተ ውሰድ » ብሎ በመርከቢቱ ክፍሎችን እንዲያደርግ ፥ ታችኛውንም ሁለተኛውንም ሦስተኛውንም ደርብ እንዲያደርግላት ኖኅን አዘዘው ። ኖኅም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሁሉ እንዲሁ አደረገ ።

፬ ፤ የእግዚአብሔር ትዕግሥት ።

፩ ጴጥ. ፫ ፡ ፳ ፤ ፪ ጴጥ. ፪ ፡ ፭ ፡ ፱ ፡ ፲ ፤ ሉቃስ. ፲፯ ፡ ፳፯ ።

እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን እንጂ ለማጥፋት ስለማይወድ ፥ መርከቢቱ በምትሠራበት ረጅም ዘመን ሁሉ ታማኝ ሰዎች ንስሐ እንዲገቡ የጥፋትን ውኃ ያዘገይ ነበር ። ኖኅ ስለ ጽድቅና ስለሚመጣባቸው ፍርድ ምንም ቢነግራቸው አንድም ሰው ስንኳ ልብ አላደረገም ፤ ሁሉም በክፉ አሳባቸውና በክፉ መንገዳቸው እየሄዱ ልባቸውን አጸኑ ። በየዕለቱ ይበሉና ይጠጡ ያገቡና ይጋቡም ነበር እንጂ እግዚአብሔር የተናገረውን ልብ አላደረጉትም ። የጥፋትም ውኃ መጥቶ እንደሚያጠፋቸው በጭራሽ አላመኑም።

፭ ፤ የጥፋት ውኃ ። ዘፍጥ. ፯ ፡ ፩—፳፬ ።

መርከቢቱ ከተዘጋጀች በኋላ እግዚአብሔር ኖኅን ፥ «አንተና ቤተሰቦችህ ወደ መርከብ ግቡ ፤ ከአንተም ጋር ከአራዊትና ከወፎች ሁሉ ከየዓይነቱ ሁለት ሁለት ይዘህ ግባ ፤ ከሰባትም ቀን በኋላ የጥፋትን ውኃ በምድር ላይ እልካለሁ » አለው ። ኖኅም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አድርጎ ገባ ፤ እግዚአብሔርም የመርከቢቱን በር በስተኋላው ዘጋ ።

ከዚያም በኋላ የጥፋት ውኃ መጣ ። በምድር የነበሩ የታላቁ ቀላይ ምንጮች ተነደሉ ፥ ከሰማይም ከባድ የሆነ ዝናብ እስከ አርባ ቀንና እስከ አርባ ሌሊት ዘነበ ። ውኃውም እየበዛ በሄደ ጊዜ መርከቢቱን ከምድር ወደ ላይ ከፍ ከፍ አድርጎ አነሣ ። መርከቢቱም በውኃው ላይ ተንሳፈፈች ። ውኃውም ታላላቆች ተራራዎች ሁሉ እስኪሸፈኑ ድረስ በምድር ላይ እጅግ በጣም አሸነፈ ፤ በመርከቢቱ ያልገቡት ሁሉ በውኃ ጠፉ ሞቱም ። ኖኅም አብረውት በመርከብ ከነበሩት ጋር ብቻውን በሕይወት ቀረ ።



* * *


የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ። ሮሜ. ፮ ፡ ፳፫ ።

ንስሐ ግቡ ኃጢአትም ዕንቅፋት እንዳይሆንባችሁ ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ ። . . . የሚቹን ሞት አልፈቅድምና ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር ፤ ስለዚህ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ ። ሕዝ. ፲፰ ፡ ፴ ፡ ፴፪ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ የጥፋት ውኃ በምን ምክንያት መጣ ?
፪ ፤ ኖኅ በእግዚአብሔር ማመኑን በምን አሳየ ?
፫ ፤ ስንት ሰዎች ዳኑ ? እነማንስ ነበሩ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፥ አካሄዴን እንደ ቃልህ አቅና ፤
ኃጢአትም ሁሉ አይግዛኝ ።
መዝ. ፻፲፱ (፻፲፰) ፡ ፻፴፫ ።



ምዕራፍ ፮ ።

## ቀስተ ደመና ።

ዘፍጥ. ፰ ፥ ፩—፱ ፥ ፲፯ ።

፩ ፤ ውኃው እየጐደለ ሄደ ።

ዘፍጥ. ፰ ፥ ፩—፭ ።

እግዚአብሔርም ኖኅን በመርከብም ከእ ርሱ ጋር የነበሩትን ሁሉ አሰበ ፤ በም ድርም ላይ ነፋስን አነፈሰ ፤ ውኃውም እየጐደለ ሄደ እያደር እያደርም ቀለለ ። ኖኅም ወደ መርከብ በገባ በሰባተኛው ወር ከወሩም በአሥራ ሰባተኛው ቀን መርከቢቱ በአራራት ተራሮች ላይ ተቀመጠች ፤ መርከቢቱ ከተቀመጠች ከሁለት ወር ከአሥራ አምስት ቀን በኋላም የተራሮች ራሶች ተገልጠው ታዩ ።

፪ ፤ ኖኅ ቁራንና ርግብን ላከ ።

ዘፍጥ. ፰ ፥ ፮—፲፱ ።

የተራሮችም ራሶች ከተገለጡ ከአርባ ቀን በኋላ ኖኅ የመርከቢቱን መስኮት ከፍቶ ቁራን ሰደደ ። ቁራም ምድር እስ ክትደርቅ ድረስ ወዲያና ወዲህ ይበርር ነበር ። ኖኅም ውኃው ከምድር ፊት ጐድሎ እንደ ሆነ ለማወቅ ወድዶ ርግብን ሰደደ። ርግቢቱም የምታርፍበት ቦታ አጥታ ወደ ኖኅ ተመለሰች ፤ ኖኅም እጁን ከመስኮት ዘርግቶ ተቀበላት ። ከሰባትም ቀን በኋላ ኖኅ እንደገና ርግቢቱን ሰደደ ፤ በማታም ጊዜ የለመለመ የወይራ ቅጠል ይዛ ተመ ልሳ መጣች ። የለመለመ ቅጠልንም ባዩ ጊዜ ኖኅና ቤተ ሰቦቹ እንዴት እንደ ተደ ሰቱ እናስብ ። ምድር እንደገና መልካም መኖሪያ እንድትሆን ልማዳዊ የሆነ ልም ላሜና ውበት ልትለብስ ጀምራ እንደ ነበር በዚህ ዐወቁ ። ኖኅም እንደገና ሰባት ቀን ቈይቶ ርግቢቱን ሰደደ ፤ በዚህም ጊዜ አልተመለሰችም ፥ በደኅና የምታርፍበት ቦታ አግኝታ ነበረችና ። ኖኅም ጥቂት ሳምንት ከቈየ በኋላ የመርከቢቱን ክዳን አነሣ ፥ ውኃውም ከምድር ፊት እንደ ደረቀ አየ ።

፫ ፤ ኖኅ መሥዋዕትን አቀረበ ።

ዘፍጥ. ፰ ፥ ፲፫—፳፪ ።

ኖኅ ግን በችኰላ ከመርከብ አልወ ጣም ። ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ እንደ ገባ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ሊወጣ ወደደ ። የመርከቢቱን ክዳን ካነሣ ለሁ ለት ወር ጥቂት ቀን ሲቀር እግዚአብሔር፥ « አንተ ሚስትህንና ልጆችህን የልጆች ህንም ሚስቶች ይዘህ ከመርከብ ውጣ ፤ ከአንተ ጋር ያሉትን አራዊትና አዕዋፍ እንስሳትንም አውጣቸው ፤ በምድር ላይ ይርመስመሱ ይብዙም » አለው ። ኖኅም ወደ መርከብ ከገባ ከአንድ ዓመት ከአሥር ቀን በኋላ ከመርከብ ወጣ ። ከሁሉ በፊ ትም በምሕረቱ ያዳናቸውን አምላክ ለማ መስገንና ለማክበር ስለ ወደደ ለእግዚአ ብሔር መሠዊያን ሠርቶ መሥዋዕትን አቀረበ ።

እግዚአብሔርም በኖኅ መሥዋዕት ደስ አለው ፤ በልቡም ፥ «ምድርን ዳግ መኛ ስለ ሰው አልረግምም ፥ የሰው ልብ አሳብ ከታናሽነቱ ጀምሮ ክፉ ነውና » ሲል በምድር ዘመን ሁሉ መዝራትና ማጨድ ፥ ብርድና ሙቀት ፥ በጋና ክረ ምት ፥ ቀንና ሌሊት እንደማያቋርጡ ተናገረ ።

፬ ፤ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ።

ዘፍጥ. ፱ ፥ ፩—፲፯ ።

አዳምና ሔዋን በተፈጠሩ ጊዜ እግ ዚአብሔር እንደ ባረካቸው አሁን እንደ ገና ለኖኅና ለልጆቹ ፥ «ብዙ ተባዙ ምድ ርንም ምሉአት » ብሎ ባረካቸው ፤ ከእ ነርሱና ከሕያው ነፍስም ሁሉ ጋር ቃል ኪዳንን አድርጎ ፥ «እኔም ቃል ኪዳኔን ከእናንተና በኋላ ከሚመጣው ከዘራችሁ ሁሉ ጋር አቆማለሁ ፤ ሥጋ ያለውም ሁሉ ዳግመኛ በጥፋት ውኃ አይጠፋም» አለ።

እግዚአብሔርም ሰዎች ሁሉ ይህን የምሕረቱን ቃል ኪዳን እንዳይረሱ ምል ክትን ሰጥቶ ፥ «በምድር ላይ ደመናን በጋ ረድሁ ጊዜ ቀስቴ በደመናው ትታያለች፥ በእኔና በእናንተ መካከል ያለውን ቃል ኪዳኔን አስባለሁ » አለ ።

እግዚአብሔር ይህን ቃል ኪዳን ከሰው ጋር ያደረገው ከብዙ ዘመናት በፊት ነው ፤ ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ የጸና ሆኖ ይኖራል ። በየጊዜውም ቀስተ ደመናን በምናይበት ቍጥር ፥ ይህ የእግዚ አብሔር የምሕረቱና የትዕግሥቱ ምል ክት ነው ብለን እናመስግነው ። እርሱ በፍቅሩ እየታገሠ ሰዎች ከክፉ መንገዳ





www.ethiopianorthodox.org

ቸው ወደ እርሱ ተመልሰው እንዲድኑ ጊዜ ሰጥቶአል ፤ በየዕለቱና በየዓመቱም ይመግበናል እንጂ እንደ ኃጢአታችን አላደረገብንም ። ነገር ግን በኖኅ ዘመን እንደ ሆነ ንስሐ የማይገቡ ሰዎች የሚጠፉበት የፍርድ ቀን ይመጣል ።

* * *

ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ነው ፤
ርኅራኄው አያልቅምና ።
ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው ፣ ታማኝነትህ ብዙ ነው ።
ሰቆቃ. ፫ ፣ ፳፪ ፣ ፳፫ ።

እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት ፥ ቀርቦም ሳለ ጥሩት ፤ ክፉ ሰው መንገዱን በደለኛም አሳቡን ይተው ፤ ወደ እግዚአብሔርም ይመለስ እርሱም ይምረዋል ፥ ይቅርታውም ብዙ ነውና ወደ አምላካችን ይመለስ ። ኢሳ. ፶፭ ፣ ፮ ፣ ፯ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ከመርከቢቱ በወጣ ጊዜ ኖኅ ምን አደረገ ?
፪ ፤ እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር ኪዳን አድርጎ ምን ተስፋ ሰጠው ?
፫ ፤ እግዚአብሔር ለኪዳኑ ምልክት ምን ሰጠ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፥ ምሕረትህን እንዴት አበዛህ !
የሰው ልጆች በክንፎችህ ጥላ ይታመናሉ ።
ምሕረትህ ከሕይወት ይሻላልና
ከንፈሮቼ ያመሰግኑኻል ።
መዝ. ፴፭ (፴፮) ፣ ፯ ፤ መዝ. ፷፪ (፷፫) ፣ ፫ ።





ምዕራፍ ፮ ።

## የባቢሎን ግንብ ።

ዘፍጥ. ፱ ፣ ፲፰—፲፩ ፣ ፱ ።

፩ ፤ የኖኅ ዘሮች እየበዙ ሄዱ ።

ዘፍጥ. ፱ ፣ ፲፰ ፣ ፲፱ ።

ሴምና ካም ያፌትም የተባሉት ከመርከብ የወጡት የኖኅ ልጆች ልጆችን ወለዱ ፤ በምድር ላይም ሰዎች እንደገና እየበዙ ሄዱ ። እነዚህም ሰዎች እግዚአብሔር ፈጣሪያቸው ታላቅ መሐሪ አምላክ መሆኑን ዐወቁ ፤ ከመጀመሪያ ጀምሮ ያለው አድራጎቱ አልተሰወረባቸውም ። ምድራቱንም ከነመዝገብዋ ሰጥቶአቸው እንደ ነበር ዐወቁ ። እንደ ኖኅ በእግዚአብሔር ያመኑት ሁሉ እንደተባረኩ ፤ ያላመኑበት ግን እንደ ጠፉ ሰምተው ነበር ። እንግዲህ እነርሱ የየትኞቹን መንገድ ይመርጡ ይሆን ?

፪ ፤ በሰናዖር ሜዳ ከተማን ቈረቈሩ ።

ዘፍጥ. ፲፩ ፣ ፩—፬ ።

ከጥፋት ውኃ በኋላ የተወለዱ ሰዎች ሁሉ አንድ ወገን ነበሩ ፥ አንድ ቋንቋና



www.ethiopianorthodox.org

አንድ ንግግርም ይነጋገሩ ነበር ። እነርሱም ከነበሩበት አገር ተነሥተው ሲጓዙ በሰናዖር አገር ሰፊ ሜዳ አገኙ ፤ ይህም ሜዳ በጣም ስለ ተስማማቸው በዚያ ለመቀመጥ ወደዱ ። ድንጋይም ስላጡ ፥ « ኑ ጡብን እንሥራ » ብለው በእሳት ጡቦችን ይተኩሱ ጀመሩ።በጡብና በዝፍትም ቤቶችን ለመሥራት ጀምረው ፥ « ኑ፥ በምድር ላይ እንዳንበተን ለእኛ ከተማ እንሥራ » አሉ ። ነገር ግን ይህንን ሁሉ ሲያደርጉ የእግዚአብሔርን ፈቃድና አሳብ ለማወቅ በጭራሽ አልጠየቁም ።

እነርሱም ፥ «ስማችንን እንድናስጠራው ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ » አሉ ። አሁንም ጥዋት እስከማታ ብዙ ሥራ ነበራቸው ፤ ነገር ግን ያሰቡትና ያደረጉት ሁሉ ለራሳቸው ምኞትና ለራሳቸው ክብር ነበረ እንጂ በልግሥና በረከቱን ሁሉ ለሰጣቸው ለፈጣሪ አምላካቸው ክብር አላሰቡም ። እግዚአብሔርን እያወቁ አላመሰገኑትም አላከበሩትምም ፤ በራሳቸው ጥበብና ኃይል እየተመኩ ለመኖር ወደዱ ።

## ፫ ፤ እግዚአብሔር በተናቸው ።

ዘፍጥ. ፲፩ ፥ ፭—፱ ።

እግዚአብሔርም የአዳም ልጆች የሚያደርጉትን ሁሉ ዐወቀ ፤ በምድር ላይም የሰው ክፋትና ግፍ እንደገና እየባሰና እየተስፋፋም ለመሄድ እንደ ጀመረ አየ ። ሰዎችም ሁሉ አንድ ወገን ሆነው አንድ ቋንቋ ሲነጋገሩ የሚያስቡትን ለማድረግ የሚከለክል ነገር የለም ነበርና መጨረሻቸው ምን ይሆን ? ስለዚህ እግዚአብሔር፥ « ኑ እንውረድ ፤ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው » ብሎ ቋንቋቸውን ደባለቀ ።

ከዚህም በኋላ ከተማንና ግንብን በሚሠሩት ሰዎች መካከል አለመግባባት ሆነ ፤ ስምምነትም ስላልኖራቸው ከተማይቱንና ግንቡን መሥራት ትተው ወደየመንገዳቸው ሄዱ ፤ በምድርም ላይ ተበታተኑ ። የዚያችም የጀመሯት የከተማ ስም ባቢሎን ተባለ ።

## ፬ ፤ የሰው ነገድ ።

የሐዋ. ፲፯ ፥ ፳፬—፳፯ ፤
ሮሜ. ፩ ፥ ፲፰—፳፫ ፤ ራእይ ፯ ፥ ፱ ።

ከዚያም ዘመን ጀምሮ ልዩ ልዩ ቋንቋ የሚነጋገሩ ነገዶች በምድር ላይ ይስፋፉ ጀመር ። የሁሉም ፈጣሪ የሆነ እግዚአብሔር አምላክ ሕይወትንና እስትንፋስን፥ የሚኖሩበትንም ሥፍራና የሚመገቡትን ምግብ ለሁሉ እየሰጠ የምሕረቱን ኪዳን እያሰበ ይታገሣቸው ነበር ፤ እስከ ዛሬም ይታገሣል ። ነገር ግን የምድር ሕዝቦች ሁሉ ፥ አንድ እንኳ ሳይቀር እግዚአብሔርን አልፈለጉትም አላከበሩትም ። እያንዳንዱ ሕዝብ እንደየአሳባቸው ፀሐይንና ጨረቃንም ሆነ ፥ በገዛ ራሳቸው እጅ የሠሩትን ጣዖታት ሆነ ፥ በፈጣሪ አምላካቸው ፈንታ ፍጥረትን እያመለኩ ኖሩ ። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ታላቅ ንጉሥ ሆኖ በሁሉ ላይ ይገዛል ፤ ከየወገኑና ከየቋንቋውም ሁሉ ወደ እርሱ የሚመለሱትን ጠርቶ የራሱ ሕዝብ ያደርጋቸዋል ።

* * *

እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ
ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ ፤



እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ
ጠባቂ በከንቱ ይተጋል ።
መዝ. ፻፳፯ (፻፳፮) ፥ ፩ ።

እግዚአብሔር የአሕዛብን ምክር ያጠፋል ፥
የአሕዛብንም አሳብ ይመልሳል ።
የእግዚአብሔር ምክር ግን ለዘላለም ይኖራል ፥
የልቡም አሳብ ለልጅ ልጅ ነው ።
መዝ. ፴፫ (፴፪) ፥ ፲ ፥ ፲፩ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ከጥፋት ውኃ በኋላ የተወለዱ ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያከብሩ ነበሩን ? ወይስ ራሳቸውን ?
፪ ፤ ምን ለመሥራት ጀመሩ ?
፫ ፤ እግዚአብሔር የበተናቸው ምን በማድረግ ነበረ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፥ ከአማልክት የሚመስልህ የለም ፥
እንደ ሥራህም ያለ የለም ።
የፈጠርኻቸው አሕዛብ ሁሉ ይመጣሉ ፥
አቤቱ ፥ በፊትህም ይሰግዳሉ
ስምህንም ያከብራሉ ፤ . . .
አንተ ብቻህን ታላቅ አምላክ ነህና ።
መዝ. ፹፮ (፹፭) ፥ ፰—፲ ።



ምዕራፍ ፫ ።

## የአማኞች አባት አብርሃም ።

ዘፍጥ. ፲፩ ፥ ፲—፲፪ ፥ ፱ ፤ ፲፭ ፥ ፩—፳፩ ።

### ፩ ፤ እግዚአብሔር አብርሃምን መረጠ ።

ዘፍጥ. ፲፩ ፥ ፲—፳፯ ፤ ዘፍጥ. ፱ ፥ ፳፯ ።

ከባቢሎን ተበታትነው በምድር ላይ የተስፋፉ ሕዝቦች ሁሉ ልዑል እግዚአብሔርን ሳያከብሩ ለራሳቸው ጣዖታትን አድርገው ሊያመልኩአቸው ወደዱ ። እግዚአብሔር ግን ሰውን ከክፉ መንገዱ ወደ ራሱ እንዲመልሰው ያለውን መልካም አሳብ አልተወምና ይህን መልካም የማዳንን አሳብ የሚፈጽምበትን ሰው መረጠ ። ይህም ሰው አብርሃም ነበረ ፤ በመጀመሪያ ግን ስሙ አብራም ተባለ ።



አብራም የተወለደው ዑር በተባለው ከተማ ነበረ ፤ ዑርም ከባቢሎን በጣም ሩቅ አልነበረም ፤ በዚያም የሚኖሩት ሕዝብ ከለዳውያን ተብለው ሴም ከተባለው የኖኅ ልጅ ትውልድ የተገኙ ነበሩ ። ኖኅ በሽምግልናው ወራት ትንቢት ሲናገር ፥ «የሴም አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ » ብሎ ነበርና ከብዙ ዘመናት በኋላ ከሴም ዘር አብርሃም ተወለደ ። እግዚአብሔርም በዔድን ገነት የሰጠውን የተስፋ ቃል ለመፈጸም ሲያስብ ፥ ሰይጣንን የሚያሸንፍ «የሴት ዘር » የተባለው ከሴምና ከአብርሃም ትውልድ እንዲወለድ ያዘጋጅ ነበር ።

### ፪ ፤ እግዚአብሔር ለአብራም ተገለጠ ።

ኢያሱ ፳፬ ፥ ፪ ፤ የሐዋ. ፯ ፥ ፬ ።

የአብራም አባት ታራ ከነቤተሰቡ እንደ ከለዳውያን ሕዝብ ሁሉ በፈጣሪ አምላክ በእግዚአብሔር ፈንታ ሌሎችን አማልክት መርጦ ያመልክ ነበር ። ቢሆንም እግዚአብሔር እንዳይሠራ የሚከለክለው የለምና እርሱ ፥ የክብር አምላክ ለአብራም ተገለጠ ። አብራምም በእግዚአብሔር አመነ ፤ ከዚያም ወዲህ እርሱን ብቻ ያመልክ ጀመር ።

### ፫ ፤ እግዚአብሔር አብራምን ጠራ ።

ዘፍጥ. ፲፩ ፥ ፳፯—፲፪ ፥ ፱ ።

እግዚአብሔር አብራምን ፥ «ከአገርህና ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ አገር ና » አለው ። እግዚአብሔርም የተስፋ ቃል ጨምሮ ፥ «ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ ፥ እባርክሃለሁ ፥ ስምህንም አከብረዋለሁ ፤ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ» አለው።

ዑር በአንድ ወንዝ አጠገብ የተሠራ በጣም የሠለጠነ ከተማ ስለ ነበረ ለሰው ኑሮ የሚመች ነበረ ። አብራም ግን ከምድራዊ ምቾትና በዘመድ መካከል ከመኖር ይልቅ ከልዑል እግዚአብሔር ጋር ወደማያውቀው አገር ለመሄድ መርጦ ታዘዘ ።

በዚያን ጊዜም ታራ ከቤተሰቦቹ አንዳንዶችን ይዞ ከዑር ወጣና ካራን ወደ ሚባል ከተማ ተጓዘ ። ታራም በካራን ተቀመጠ በዚያም ሞተ ። አብራም ግን አባቱ ከሞተ በኋላ ሚስቱን ሦራንና የወንድሙን ልጅ ሎጥን * ይዞ ከብቱንና አገልጋዮቹን አስከትሎ እግዚአብሔር ወደ ሚያሳየው አገር መንገዱን ቀጠለ ። ወደ ከነዓን አገር ገብቶ ሴኬም እስከ ተባለው ሥፍራ ተጓዘ። በሴኬምም እግዚአብሔር ለአብራም ተገለጠለትና ፥ «ይህችን ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ » አለው ። አብራምም መሠዊያን ሠርቶ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን ሠዋ ። በአገሩ የነበሩ የከነዓን ሰዎች ሌሎችን አማልክት ያመልኩ ነበርና በሴኬም የአድባር ዛፍ ነበራቸው። አብራም ግን በእነርሱ መካከል እንግዳ ሆኖ በመጣ ጊዜ ሳይፈራ በግልጥ ለእግዚአብሔር ሠዋ ። ከዚያም በቤቴል ምሥራቅ ወዳለው ተራራ ወጣ ፤ በዚያም ድንኳኑን ተክሎ መሠዊያን ሠራ ። አብራም ወደ ከነዓን በገባ ጊዜ የሰባ አምስት ዓመት ሰው ነበረ ።

### ፬ ፤ ለአብራም የተሰጠ የዘር ተስፋ ።

ዘፍጥ. ፲፭ ፥ ፩—፳፩ ።

እግዚአብሔር ፥ «ይህችን የከነዓን ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ » ብሎ ነበር ፤ አብራም ግን ምንም ያረጀ ሰው ቢሆን ልጅ አልነበረውም ። ሦራ መካን ስለሆነች ልጅ አልወለደችለትም ነበር ። ዓመታ



www.ethiopianorthodox.org

ችም እያለፉ ሲሄዱ ገና ልጅ ሳትወል ድለች ስለ ቀረች አብራም አዘነ ።

ከዕለታትም አንድ ቀን በመሸ ጊዜ እግዚአብሔር ፥ «አብራም ሆይ አትፍራ ፤ እኔ ለአንተ ጋሻህ ነኝ ፤ ዋጋህም እጅግ ታላቅ ነው» አለው። አብራምም፥ «አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ ፥ ምን ትሰጠኛለህ ? እኔም ያለ ልጅ እሄዳለሁ» አለ። እግዚአ ብሔርም ወደ ሜዳ አብራምን አውጥቶ ፥ «ወደ ሰማይ ተመልከት ፤ ከዋክብትንም ልትቈጥራቸው ትችል እንደ ሆነ ቊጠር፤ ዘርህም እንደዚሁ ይሆናል » አለው ።

አብራምም ወደ ሰማይ እየተመለ ከተ የከዋክብትን ብዛት አየ ፤ በእግዚአ ብሔርም አመነ ። እግዚአብሔርም ፥ አብ ራም በእምነት በፊቴ ጸድቀሃል አለ ። አብራምም ፥ ልጅ እወልዳለሁ ዘሮቼም እጅግ ብዙ ይሆናሉ ብሎ ፥ በተሰጠው ተስፋ ደስ አለው ።

በዚያ ቀን እግዚአብሔር ለአብራም እንዲህ ብሎ ቃል ኪዳን አደረገ ፤ «ከግ ብፅ ወንዝ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ይህችን ምድር ለዘርህ ሰጥቼአለሁ ። » እግዚአብሔርም ፥ « ዘርህ ለእርሱ ባልሆ ነች ምድር ስደተኞች እንዲሆኑ በእር ግጥ ዕወቅ ፤ ባሪያዎች አድርገውም አራት መቶ ዓመት ያስጨንቋቸዋል ። ደግሞም በባርነት በሚገዙአቸው ሕዝብ ላይ እኔ እፈርዳለሁ ፤ ከዚያም በኋላ በብዙ ሀብት ይወጣሉ » ብሎ ሲያስረዳው ፥ በከነዓን የሚኖሩት የአሞራውያን ኃጢአት ገና ሞልቶ ስላልተፈጸመ ገና እስከ አያሌ መቶ ዓመት ምድሪቱን ለአብራም ዘሮች እንደማይሰጥ ነገረው ።

* * *

አብርሃም የተባለው ርስት አድርጎ ሊቀበለው ወዳ ለው ሥፍራ ለመውጣት በእምነት ታዘዘ ፤ ወዴትም እንደሚሄድ ሳያውቅ ወጣ ። ዕብራ. ፲፩ ፥ ፰ ።

አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ ፤ ጽድቅም ሆና ተቈጠረለት ። ዘፍጥ. ፲፭ ፥ ፮ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ እግዚአብሔር አብርሃምን በጠራ ጊዜ ምን አዘዘው?
፪ ፤ ምንስ ተስፋ ሰጠው ?
፫ ፤ አብርሃም ልጅ ባለመኖሩ ባዘነ ጊዜ እግዚአብሔር ምን ተስፋ ሰጠው ?

ጸሎት ፤ አንተ አምላኬ ነህና ፈቃድህን ለማድረግ አስ ተምረኝ ። መዝ. ፻፵፪ (፻፵፫) ፥ ፲ ።

* ስለ ሎጥ የምናነበው በዘፍጥ. ፲፫ና ፲፬ ፥ በም. ፲፰ ፥ ፲፮—፲፱ ፥ ፴፰ ነው ።





ምዕራፍ ፬ ።

## የተስፋ ቃል ልጅ ።

ዘፍጥ. ፲፮ ፥ ፩—፲፭ ፥ ፲፯ ፤ ፳፩ ፥ ፩—፯ ።

፩ ፤ አብራም እስማኤልን ወለደ ።

ዘፍጥ. ፲፮ ።

አብራም ፥ ዘሮችህ ከብዛታቸው የተ ነሣ ሰው ሊቈጥራቸው አይችልም የሚ ለውን ተስፋ አመነ ፤ ሚስቱ ግን መካን ሆና ስለቀረች ወደ ከነዓን በገቡ በአሥረ ኛው ዓመት የመውለድን ተስፋ ቈርጣ ባልዋን ፥ «እግዚአብሔር ልጅ አልሰጠኝ ምና ምናልባት ከእርስዋ ልጅ እንድናገኝ አጋር ወደምትባል ወደዚህች ግብፃዊት ባሪያ ግባ » ብላ መከረችው ። አብራምም ይህን የሦራን ምክር ሰምቶ ከአጋር እስ ማኤል* የሚባል ልጅ ወለደ ። እስማኤ ልም በተወለደ ጊዜ አብራም የሰማንያ ስድስት ዓመት ሰው ነበረ ፤ በልጁም መወለድ በጣም ደስ አለው ።



www.ethiopianorthodox.org

፪ ፤ የአብራምና የሦራ ስም ተለወጠ ።
ዘፍጥ. ፲፯ ።

አብራም የዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሰው ሲሆንና እስማኤል አሥራ ሦስተኛውን ዓመት ሲይዝ እግዚአብሔር እንደገና ለአብራም ተገለጠለትና ፡ «እኔ ሁሉን የሚችል አምላክ ነኝ ፤ በፊቴ ተመላለስ፣ ፍጹምም ሁን ፤ ቃል ኪዳኔንም በእኔና በአንተ መካከል አደርጋለሁ ፡ እጅግም አበዛሃለሁ » አለው ።

አብራምም በግምባሩ ወደቀ ፤ እግዚአብሔርም ፡ «ቃል ኪዳኔ ከአንተ ጋር ነው፤ ለብዙ ሕዝቦችም አባት ትሆናለህና ከዛሬ ጀምሮ ስምህ አብራም ሳይሆን አብርሃም* ይሆናል ፤ ለብዙ ሕዝቦች አባት አድርጌሃለሁና ነገሥታት ከአንተ ዘር ይገኛሉ » አለው ። እግዚአብሔርም ፡ «በእኔና በአንተም መካከል ለማቆመው ቃል ኪዳን ምልክት እንዲሆን በቤትህ የሚወለደው ወንድ ልጅ ሁሉ ስምንት ቀን ሲሆነው ይገረዝ » አለው ።

እግዚአብሔርም ፡ «የሚስትህ ስም ሦራ ሳይሆን ሣራ* ይሆናል ። እባርካታለሁ ፡ ልጅን ትወልድልሃለች ፡ የአሕዛብና የንጉሥታትም እናት ትሆናለች» አለው። አብርሃምም ይህን በሰማ ጊዜ በግምባሩ ወድቆ ሳቀ ፡ በልቡም ፡ « የመቶ ዓመት ሰው በውኑ ልጅ ይወልዳልን ? ዘጠና ዓመት የሆናትም ሣራ ትወልዳለችን ? » አለ ። አብርሃምም እግዚአብሔርን ፡ « እስማኤል በፊትህ ቢኖር በወደድሁ ነበር ! » አለው ።

እግዚአብሔር ግን ፡ «በእውነት ሣራ ወንድ ልጅን ትወልድልሃለች፥ ስሙንም ይስሐቅ* ብለህ ትጠራዋለህ ። ስለ እስማኤልም ሰምቼሃለሁ ፡ ባርኬዋለሁ፥ እጅግም አበዛዋለሁ ፤ ነገር ግን ቃል ኪዳኔን ሣራ ከምትወልድልህ ከይስሐቅ ጋር አቆማለሁ » አለው ።

፫ ፤ እግዚአብሔር ለሣራ የልጅን ተስፋ አሰማች ። ዘፍ. ፲፰ ፥ ፩—፲፭ ፤ ዕብ. ፲፩ ፥ ፲፩ ።
ከዕለታትም አንድ ቀን በቀትር ጊዜ አብርሃም በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው አየ ፤ ተነሥቶም ሊቀበላቸው ሮጠ ፡ ሰግዶም ፡ «አቤቱ ባሪያህን አትለፈኝ ብዬ እለምናለሁ ፤ ጥቂት ውኃ ይምጣላችሁ እግራችሁን ታጠቡ ፡ ከዚህችም ዛፍ በታች ዕረፉ ፤ ቍራሽ እንጀራም ላምጣላችሁ» ብሎ ከዛፍ በታች አስቀመጣቸው ።

አብርሃምም ወደ ሣራ ፈጥኖ ገባና፣ « ዱቄት አዘጋጅተሽ እንጎቻ አንጊ » ካላት በኋላ ወደ ላሞች ሮጦ እጅግ የሰባ ታናሽ ጥጃ አመጣ ፡ አርዶም አዘጋጀ ፤ ቆሞም ለመጡት እንግዶች ምግብ አቀረበላቸው ፤ እነርሱም በሉ ።

እንግዶቹም ፡ «ሚስትህ ሣራ ወዴት ናት ? » አሉት ። አብርሃምም ፡ «በድንኳኑ ውስጥ ናት » አለ ። እርሱም ፡ «የዛሬ ዓመት ወደ አንተ እመለሳለሁ ፤ ሚስትህ ሣራም ልጅን ትወልዳለች » አለ ።

ሣራም በድንኳኑ ደጃፍ በስተኋላው ሳለች ይህንን ቃል ሰማች ፤ ሣራም ፡ « ካረጀሁ በኋላ ጌታዬም ፈጽሞ ከሸመገለ በኋላ ልጅን እወልዳለሁን ?» ብላ በልብዋ ሳቀች ። እግዚአብሔርም አብርሃምን ፡ «ካረጀሁ በኋላ በውኑ እወልዳለሁን ? ስትል ሣራ ለምን ሳቀች ? በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን ? ሣራ ልጅን ትወልዳለች » አለው። ሣራም ፈርታ ፡ «አልሳቅሁም» ስትል ካደች ፤ እርሱም ፡ « አይደለም ፡ ሳቅሽ እንጂ » አላት ።

እግዚአብሔርም የተስፋውን ቃል እንድትሰማ በዚህ አኳኋን ካነጋገራት በኋላ ሣራ ራስዋ ስንኳ ምንም ዕድሜዋ ያለፈ ቢሆን ልጅን ለመውለድ ኃይልን በእምነት አገኘች ። ዕብራ. ፲፩ ፥ ፲፩ ።

፬ ፤ ይስሐቅ ተወለደ ። ዘፍጥ. ፳፩ ፥ ፩—፯ ።
እግዚአብሔርም እንደ ተናገረው ለሣራ አደረገላት ። በተናገረውም ወራት ለአብርሃም በእርጅናው ልጅ ወለደችለት ። አብርሃምም የልጁን ስም ይስሐቅ ብሎ ጠራው ፤ እግዚአብሔር እንዳዘዘውም በስምንተኛው ቀን ገረዘው ። ሣራም ከልክ ባለፈ ደስታዋ ፡ «እግዚአብሔር ሳቅ አደርጎልኛል ፤ ይህንን የሚሰማ ሁሉ በእኔ ምክንያት ይስቃል ። ሣራ ልጅን እንድታጠባ ለአብርሃም ማን በተናገረ ነበር ? » አለች ።

* * *

ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም ።
ሉቃ. ፩ ፥ ፴፯ ።

አብርሃም... ለእግዚአብሔር ክብር እየሰጠ ፡ የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንዲችል አጥብቆ እየተረዳ ፡ በእምነት በረታ እንጂ ... አልተጠራጠረም ።
ሮሜ. ፬ ፥ ፳ ፥ ፳፩ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ እግዚአብሔር የአብራምንና የሦራን ስሞች በለወጠ ጊዜ ምን ተስፋ ሰጠ ?
፪ ፤ በሁለት ልዩ ጊዜያት ሣራ ሳቀች ። ለምን ሳቀች ?
፫ ፤ ይስሐቅ በአማርኛ ሲተረጐም ምን ማለት ነው ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ በሥራህ ደስ አሰኘተኸኛልና ፤ . . .
አሳብህም እጅግ ጥልቅ ነው ።
መዝ. ፻፴፱ (፻፴፰) ፥ ፲፬ ።

* ስለ እስማኤል የምናነበው በዘፍጥ. ፲፮ ፤ በም. ፳፩ ፥ ፰—፳፩ ፤ በም. ፳፭ ፥ ፲፪—፲፰ ነው ።
* አብርሃም ማለት የብዙ ሕዝቦች አባት ማለት ነው ።
ሣራ ማለት ልዕልት ማለት ነው ።
ይስሐቅ ማለት ሳቅ ማለት ነው ።



ምዕራፍ ፲ ።

# አብርሃም ይስሐቅን አቀረበ ።

ዘፍጥ. ፳፪ ።

## ፩ ፤ የእምነት መፈተን ።

ዘፍጥ. ፳፪ ፡ ፩ ፡ ፪ ።

እንጠረኛ ወርቅን ሲያነጥር ፈጽሞ ጥሩ እንዲሆን በእሳት እያቀለጠ ያጣራዋል ። ለምን ብንል ፡ ወርቅ ውድ የከበረም ስለ ሆነ ነው ።

አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ ፤ ሣራ ይስሐቅን እስከምትወልድለት ድረስ ባበቅ በነበረበት ጊዜ እምነቱ እየበረታ ሄደ ። ከዚያም በኋላ እምነቱ እንዲፈጸም እሳትን በሚመስል ፈተና ተፈተነ። ለምን ብንል ፡ በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ሆኖ



የሚቈጠር እምነት፣በእሳት እንደሚነጠር ወርቅ መፈተን አለበት ።

ይስሐቅ እያደገ ሄደ ፤ ወላጆቹም ተደሰቱበት ። ከዕለታትም አንድ ቀን እግዚአብሔር የይስሐቅን አባት ፡ «አብ ርሃም ሆይ » አለው ። እርሱም ፡ «እነ ሆኘ » አለ ። እግዚአብሔርም ፡ የምት ወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያ አገር ሂድ ፤ እኔም በምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ ሠዋው» አለው ።

## ፪ ፤ የአብርሃም ታዛዥነት ።

ዘፍጥ. ፳፪ ፡ ፫—፮ ።

አብርሃምም በማለዳ ተነሥቶ አህያውን ጫነ ፡ ሁለቱን ሎሌዎቹንና ልጁን ይስሐ ቅን ከእርሱ ጋር ወሰደ ፤ ለመሥዋዕ ትም እንጨትን ፈለጠ ፤ ተነሥቶም እግ ዚአብሔር ወዳለው ቦታ ሄደ። በተነሣም በሦስተኛው ቀን አብርሃም ዓይኑን አነ ሣና ቦታውን ከሩቅ አየ ። ሎሌዎቹንም፣ « አህያውን ይዛችሁ እዚህ ቈዩ ፤ እኔና ልጄ ወደዚያ ሄደን እንሰግዳለን ፤ ወደ እናንተም እንመለሳለን » በማለት እን ጨቱን አንሥቶ ለልጁ ለይስሐቅ አሸከ መው ፤ እርሱም እሳትንና ቢላዋን በእጁ ያዘ ። ሁለቱም አብረው ሄዱ ።

## ፫ ፤ የይስሐቅ ጥያቄና መልሱ ።

ዘፍጥ. ፳፪ ፡ ፯—፲፬ ።

ይስሐቅ ለመሥዋዕት የሚያስፈልገውን ሁሉ ያውቅ ነበርና ከአባቱ ጋር ሲሄድ ፡ « አባቴ ሆይ » አለው ፤ አብርሃምም ፡ «እነሆኘ ልጄ» አለው ። ይስሐቅም ፡ «እሳቱና እንጨቱ ይኸው ፤ የመሥዋ ዕቱ በግ ግን ወዴት ነው ? » አለ ። አባቱ ፡ «ልጄ ሆይ ፡ የመሥዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል » አለው ። ሁለ ቱም አብረው ሄዱ ፤ እግዚአብሔር ወደ መረጠውም ቦታ ደረሱ ።

ከሦስት ቀን ጀምሮ አብርሃም በአሳብ የሚያምሰለስለው ጊዜ አሁን ደረሰ ። አብርሃምም ድንጋይን ወስዶ መሠዊያን ሠራ ፤ እንጨቱንም በላዩ ላይ ረበረበ ፤ ልጁን ይስሐቅንም አስሮ በመሠዊያው እንጨት ላይ አጋደመው ። አብርሃምም እጁን ዘረጋ ፤ ልጁንም ያርድ ዘንድ ቢላዋ አነሣ ።

በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር መል አክ በድምፅ ከሰማይ ጠርቶ ፡ «አብርሃም አብርሃም » አለው ፤ አብርሃምም ፡ «እነ ሆኘ » አለ ። እርሱም ፡ «በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ ፡ አንዳችም አታድርግ በት » አለው ። አብርሃምም ይህን ቃል ሲሰማ እጁን አወረደ ፤ የእግዚአብሔርም መልአክ ፡ «አንድ ልጅህን ለእኔ አልከለ ከልህምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደ ሆንህ አሁን ዐውቄአለሁ» አለ ።

አብርሃምም ዓይኑን አነሣ ፡ በስተ ኋላውም ተመለከተ ፤ እነሆም በአንድ ቊጥቋጦ ውስጥ በቀንዶቹ የተያዘ በግን አየ ። እነሆም እግዚአብሔር ያዘጋጀው በይስሐቅ ፈንታ የሚሠዋ በግ ተገኘ ። አብርሃምም ሄዶ በጉን አመጣ ፤ በልጁም ፈንታ መሥዋዕት አድርጎ ሠዋው ። አብ ርሃምም ያንን ቦታ «ያህዌ ይርኤ» ብሎ ጠራው ፤ ይህም ስም በአማርኛ «እግዚ አብሔር ያያል ያዘጋጃልም » ማለት ነው ።

## ፬ ፤ የእግዚአብሔር መሐላ ።

ዘፍጥ. ፳፪ ፡ ፲፭—፲፱ ፤ ዕብራ. ፲፩ ፡ ፲፯—፲፱ ፤ ያዕ. ፪ ፡ ፳፫ ።

የእግዚአብሔርም መልአክ ከሰማይ ሁለ ተኛ ጊዜ ጠርቶ ፡ «ይህን ነገር አድር



www.ethiopianorthodox.org

ገሃልና አንድ ልጅህንም አልከለከልህ ምና በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ ፥ ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብት በባሕር ዳርም እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ ። ዘርህም የጠላቶቹን ደጅ ይወርሳል ፤ የምድር ሕዝቦች ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ ፥ ቃሌን ሰምተሃልና ፤ ይህን ቃሌን ለመፈጸም በራሴ ማልሁ ይላል እግዚአብሔር » አለው ።

አብርሃም ልጁን ይዞ ወደ ሎሌዎቹ በተመለሰ ጊዜ በእንዴት ያለ ደስታና ምስጋና የሄደ ይመስለናል ! ልጁን እንዲሠዋ በሄደ ጊዜ እግዚአብሔር ፥ በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል ያለውን የተስፋ ቃል እያሰበ በልቡ ፥ እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ የሚፈጽም ታማኝ አምላክ ነውና ልጁ ይስሐቅ ቢሞት ስንኳ ከሙታን ሊያስነሣው ይችላል ብሎ ሄደ ። አሁንም ከተወደደው ልጁ ጋር ድንኳኑ ወደ ተተከለበት ሣራም ወዳለችበት መኖሪያ ስፍራ ሲመለስ ፥ እግዚአብሔር ትልቅ ነገር አድርጎልኛል ፤ ለወደፊትም በዘሬ የምድር ሕዝቦች ሁሉ እንደሚባረኩ እንደገና ነግሮኛል ብሎ በማሰብ እጅግ ደስ አለው ። ከእርሱ ከራሱና ከልጁ ከይስሐቅም በጣም የሚበልጠው ፥ የዓለም መድኃኒት የሚሆነው እንደሚመጣ ከሩቅ እያየ አስተዋለ ።

አብርሃም በተፈተነ ጊዜ እምነቱ ፍጹም እንደ ሆነ በመታዘዙ አሳየ ፤ እርሱም የእግዚአብሔር ወዳጅ ተባለ ።

* * *

እግዚአብሔር ለሚፈሩት ኃይላቸው ነው ፥
ቃል ኪዳኑንም ያስታውቃቸዋል ።
መዝ. ፳፱(፳፭) ፥ ፲፬ ።

ስምህን የሚያውቁ ሁሉ በአንተ ይታመናሉ ፥
አቤቱ ፥ የሚሹህን አትተዋቸውምና ።
መዝ. ፱ ፥ ፲ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ እግዚአብሔር ይስሐቅን እንዲያቀርብ አብርሃምን ወደ ምን ሥፍራ ላከው ?
፪ ፤ ይስሐቅ ፥ የመሥዋዕቱ በግ የት አለ ? ባለው ጊዜ አባቱ ምን መልስ ሰጠ ?
፫ ፤ በይስሐቅ ፈንታ የተሠዋ በግ እንዴት ተገኘ ?

ጸሎት ፤ የሠራዊት አምላክ ሆይ ፥
በአንተ የታመነ ሰው ምስጉን ነው ።
መዝ. ፹፫ (፹፬) ፥ ፲፪ ።





ምዕራፍ ፲፩ ።

## የይስሐቅና የርብቃ ጋብቻ ።

ዘፍጥ. ፳፬ ።

### ፩ ፤ አብርሃም ሎሌውን ላከ ።

ዘፍጥ. ፳፬ ፥ ፩—፱ ።

የይስሐቅ እናት ሣራ ከሞተች በኋላ አብርሃም ሎሌውን የቤቱን ሽማግሌ የከብቱን ሁሉ አዛዥ ፥ «ወደ ካራን ወደ ዘመዶቼ ቤት ሄደህ ለልጄ ለይስሐቅ ሚስትን ፈልገህ አምጣ ፤ ከዚህ አገር ከከነዓን ሴቶች ግን ሚስት እንደማትወስድለት አምልሃለሁ» አለው ።

ሎሌውም ፥ « ሴቲቱ ምናልባት ወደዚህ አገር ከእኔ ጋር ለመምጣት እንቢ ያለች እንደ ሆነ ልጅህን ወደ ወጣህበት አገር ልመልሰውን ? » አለው ። አብርሃምም ፥ «ልጄን ወደዚያ እንዳትመልስ ተጠንቀቅ ፤ ከአባቴ ቤትና ከአገሬ ያወጣኝ የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር ፥ እርሱ መልአኩን በፊትህ ይሰድዳል ፥ ከዚያም ለልጄ ሚስትን ትወስዳለህ ። ሴቲቱም ከአንተ ጋር ለመምጣት እንቢ ያለች እንደ ሆነ ከዚህ ካቀረብሁልህ መሐላ ንጹሕ ነህ ፤ ልጄን ግን ወደዚያ አትመልሰው» አለው። ሎሌውም ስለዚህ ነገር ማለለት ።

### ፪ ፤ እግዚአብሔር መንገድን አቀና ።

ዘፍጥ. ፳፬ ፥ ፲—፳፯ ።

ሎሌውም ከጌታው ግመሎች አሥር ወስዶ ከጌታውም ዕቃ መልካም መልካሙን ይዞ ተነሣ ፤ ወደ መስጴጦምያ ወደ አብርሃም ወንድም ወደ ናኮር ከተማ



www.ethiopianorthodox.org

ትጓዝ ። ሲመሽም ሴቶች ውኃ ሊቀዱ በሚወጡበት ጊዜ ከካራን ከተማ ውጪ በውኃው ጉድጓድ አጠገብ ግመሎቹን አስበረከከ ። እንዲህም ብሎ ጸለየ ፤ «የጌታዬ የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ሆይ ፡ መንገዴን ዛሬ በፊቴ አቅናልኝ እለምንሃለሁ ፤ ለጌታዬ ለአብርሃም ምሕረትን አድርግ ። እነሆ በዚህ የውኃ ምንጭ አጠገብ እኔ ቆሜአለሁ ፡ የዚህችም ከተማ ሴቶች ልጆች ውኃውን ሊቀዱ ይመጣሉ። እኔም ፡ ውኃ እንድጠጣ እንስራሽን አዘንብዪ የምላት እርስዋም ፡ አንተ ጠጣ ግመሎችህን ደግሞ አጠጣለሁ የምትለኝ ቆንጆ ፡ እርስዋ ለባሪያህ ለይስሐቅ ያዘጋጀሃት ትሁን ። »

ይህን ንግግሩን ሳይፈጽም እነሆ የናኮር የልጁ ልጅ ርብቃ እንስራዋን በጫንቃዋ ተሸክማ መጣች ። ብላቴናዪቱም መልክዋ እጅግ ያማረ፡ድንግልም ነበረች፡ ወደ ምንጭም ወርዳ እንስራዋን ሞላች ፤ ተመልሳም ወጣች ። ሎሌውም ሊገናኛት ሮጠና ፡ «ከእንስራሽ ጥቂት ውኃ እንድታጠጭኝ እለምንሻለሁ» አላት ።

እርስዋም ፡ «ጌታዬ ሆይ ፡ ጠጣ » ብላ እንስራዋን በእጅዋ አውርዳ አጠጣችው ። እርሱንም ካጠጣች በኋላ ፡ «ለግመሎችህ ደግሞ ሁሉም እስኪረኩ ድረስ ውኃ እቀዳለሁ» አለች ። ፈጥናም ውኃውን ከእንስራዋ በማጠጫው ውስጥ ገለበጠችው፤ለግመሎቹም ሁሉ ውኃ ቀዳች።

ሰውዬውም ትክ ብሎ ይመለከታት ነበር ፤ እግዚአብሔር መንገዱን አቅንቶለት እንደ ሆነም ለማወቅ ዝም አለ ። ግመሎቹም ከጠጡ በኋላ ሰውዬው የወርቅ ቀለበትና አምባር አውጥቶ ፡ «አንቺ የማን ልጅ ነሽ ? » አላት ። እርስዋም ፡ «እኔ ሚልካ ለናኮር የወለደችለት የባቱኤል ልጅ ነኝ» አለች ። ሰውዬውም አጐነበሰ ፡ ለእግዚአብሔርም ሰገደ ፤ እንዲህም ብሎ አመሰገነ ፤ «ቸርነቱንና እውነቱን ከጌታዬ ያላራቀ የጌታዬ የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን ፤ እኔ በመንገድ ሳለሁ እግዚአብሔር ወደ ጌታዬ ወንድሞች ቤት መራኝ ። »

፫ ፤ የርብቃ ወደ ከነዓን መሄድ ።

ዘፍጥ. ፳፬ ፡ ፳፰—፷፩ ።

ብላቴናዪቱም ሮጠች ፡ ለእናትዋም ቤት ነገሩን ሁሉ ተናገረች ። ለርብቃም ላባ የተባለ ወንድም ነበራት ፤ ላባም የወርቅ ቀለበቱንና አምባሩን አይቶ የርብቃን ቃል በሰማ ጊዜ ወደ ውኃው ምንጭ እየሮጠ የአብርሃምን ሎሌ ፡ «አንተ የእግዚአብሔር ቡሩክ ፡ ግባ ፡ ስለምን በውጭ ቆመሃል ?» ብሎ ወደ ቤት አገባው ፡ መብልንም በፊቱ አቀረበለት ፤ ሎሌው ግን ፡ «ነገሬን እስክናገር ድረስ አልበላም» ብሎ እርሱ የአብርሃም ሎሌ መሆኑንና በምን ምክንያት እንደ መጣ እግዚአብሔርም በመንገዱ እንደ መራው በሙሉ ነገራቸው ።

ላባና ባቱኤልም ሁሉን ከሰሙ በኋላ ፡ «ነገሩ ከእግዚአብሔር ዘንድ መጥቶአል ፡ ክፉም በጎም ልንመልስልህ አንችልም ። ርብቃ እነኋት በፊትህ ናት ፤ ይዘሃት ሂድ» አሉት ። የአብርሃምም ሎሌ ነገራቸውን በሰማ ጊዜ ወደ ምድር ወድቆ ለእግዚአብሔር ሰገደ ። ሎሌውም የብርና የወርቅ ጌጥና ልብስ አውጥቶ ለርብቃ ሰጣት ፤ የከበረ ስጦታንም ለወንድምዋና ለእናትዋ አቀረበ ። እርሱም ከእርሱ ጋር ያሉትም በሉ ጠጡም ፡ ከዚያም አደሩ ። ማልዶም ተነሣና ፡ « ወደ ጌታዬ እንድሄድ አሰናብቱኝ» አላቸው ። ወንድምዋና እናትዋም ፡ «ብላቴናዪቱ አንድ አሥር ቀን ያህል እንኳ ከእኛ ጋር ትቈይ ፤ ከዚያም በኋላ ትሄዳለች» አሉ ። ሎሌውም ፡ «እግዚአብሔር መንገዴን አቅንቶልኛልና አታዘግዩኝ» አላቸው ።

እነርሱም፡ «ብላቴናዪቱን እንጥራና ከአፍዋ እንጠይቅ » አሉ ። ርብቃንም ጠርተው ፡ «ከዚህ ሰው ጋር ትሄጃለሽን ? » አሉአት ። እርስዋም ፡ «እሄዳለሁ» አለች ።

በዚያን ጊዜ እኅታቸውን ርብቃን ሞግዚትዋንም የአብርሃምን ሎሌና ሰዎቹንም አሰናበቱአቸው ። ርብቃንም መረቁአትና ፡ «አንቺ እኅታችን እልፍ አእላፋት ሁኚ ፤ ዘርሽም የጠላቶችን ደጅ ይውረስ» አሉአት ። ርብቃም ተነሣች ደንገጥሮችዋም ፡ በግመሎች ላይ ተቀምጠው ያንን ሰው ተከተሉት ፤ ሎሌውም ርብቃን ተቀብሎ ሄደ ።

፬ ፤ የይስሐቅ ርብቃን ማግባት ።

ዘፍጥ. ፳፬ ፡ ፷፪-፷፯ ።

ይስሐቅም በመሸ ጊዜ በልቡ እያሰላሰለ ወደ ሜዳ ወጥቶ ነበር ፤ ዓይኖቹንም አቀና ፡ እነሆም ግመሎች ሲመጡ አየ ። ርብቃም ዓይኖችዋን አቀናች ፡ ይስሐቅንም አየች ፡ ከግመልም ወረደች ። ሎሌውንም ፡ «ሊገናኘን የሚመጣ ይህ ሰው ማን ነው ? » አለችው ። እርሱም ፡ «እርሱ ጌታዬ ነው» አላት ። እርስዋም መሸፈኛ ወስዳ ተከናነበች ። ሎሌውም የሆነውን ሁሉ ለይስሐቅ ነገረው ። ይስሐቅም ወደ እናቱ ወደ ሣራ ድንኳን አገባት ፡ ርብቃንም ወሰደ ሚስትም ሆነችው ። ይስሐቅም ወደዳት ፤ ከእናቱም ሞት ተጽናና ።

* * *

በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን ፤
በራስህም ማስተዋል አትደገፍ ፤
በመንገድህ ሁሉ እርሱን ዕወቅ ፤
እርሱም ጐዳናህን ያቀናልኻል ።

ምሳሌ ፫ ፡ ፭ ፡ ፮ ።

ቤትና ባለጠግነት ከአባቶች ዘንድ ይወረሳሉ ፤
አስተዋይ ሚስት ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ናት ።

ምሳሌ ፲፱ ፡ ፲፬ ።

* * *

**ጥያቄ ፤ ፩ ፤ አብርሃም ስለ ይስሐቅ ሎሌውን እንዴት አማለው ፤**
**፪ ፤ ሎሌው ርብቃን እንዲያገኝ ሲጸልይ ምን ለመነ ፤**
**፫ ፤ ርብቃ ይስሐቅን ያገባች በፈቃድዋ ነበረን ፤**

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ ነፍሴን ወደ አንተ አንሥቻለሁና
የምሄድበትን መንገድ አስታውቀኝ ።

መዝ. ፻፵፫ (፻፵፪) ፡ ፰ ።



ምዕራፍ ፲፪ ።

## ያዕቆብና ዔሳው ።

ዘፍጥ. ፳፭ ፥ ፲፱ - ፳፰ ፥ ፭ ።

### ፩ ፤ ርብቃ መንታ ወለደች ።

ዘፍጥ. ፳፭ ፥ ፲፱—፳፮ ።

ይስሐቅ ርብቃን ካገባ በኋላ ልጅ እን ድትወልድለት ይጠባበቅ ነበር ፤ ነገር ግን እስከ ብዙ ዓመት ድረስ አንድም ልጅ ሳትወልድ ቀረች ። ይስሐቅ ወደ እግዚአ ብሔር በጸለየ ጊዜ ግን ርብቃ መንታ ወለ ደች ።

ርብቃም ከፀነሰች በኋላ በአሳብዋ ተጨንቃ ጸለየች ። እግዚአብሔርም ፥ «የሁለት ሕዝቦች አባቶች የሚሆኑ ሕፃ ናት ትወልጃለሽ ፤ ታላቁም ለታናሹ ይገ ዛል» አላት ። የምትወልድበትም ጊዜ ሲደርስ ፥ በፊት የተወለደው ሕፃን ቀይና ጠጕራም ነበረ ፤ ስሙም ዔሳው ተባለ ። ዔሳው ማለትም ጠጕራም ማለት ነው ። ሁለተኛውም ሕፃን ሳይዘገይ የዔሳውን ተረከዝ በእጁ ይዞ ተወለደ ፤ ስሙም ያዕ ቆብ ተባለ ። ያዕቆብ ማለትም አሰናካይ ማለት ነው ።

### ፪ ፤ ዔሳው ብኵርናውን ንቆ ሸጠ ።

ዘፍጥ. ፳፭ ፥ ፳፯—፴፬ ፤ ዕብራ. ፲፪ ፥ ፲፭—፲፯ ።

ዔሳው ካደገ በኋላ አደን የሚያውቅ የበ ረሃ ሰው ሆነ ፤ ይስሐቅም ዔሳው ካደ ነው ይበላ ነበርና በተለይ ዔሳውን ወደደ። ያዕቆብ ግን በድንኳን የሚቀመጥ ጭምት ሰው ነበረና ርብቃ ያዕቆብን ትወድ ነበር።



ዔሳውና ያዕቆብ ለአባቶቻቸው ለአ ብርሃምና ለይስሐቅ የተሰጠውን የእግዚ አብሔርን የተስፋ ቃል ዐወቁ ፤ « እባር ክሃለሁ ፤ ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ ፥ በአንተም የምድር ነገዶች ሁሉ ይባረ ካሉ » የሚለውን አምላካዊ በረከት ሰም ተው ነበርና ። ያዕቆብ የእግዚአብሔርን በረከትና ተስፋ ወራሽ ለመሆን ተመኘ ፤ ዔሳው ግን የዚህን ዓለም ነገር የሚያስብ ሰው ስለ ነበረ የእግዚአብሔርን ነገር አላሰበም ፥ የተስፋ ቃሉንም እንደ ከንቱ ቈጠረው ።

አንድ ቀንም ዔሳው ደክሞ ከበረሃ በገባ ጊዜ ያዕቆብን፥ «ከዚህ ከሠራሽው ቀይ ወጥ አብላኝ» አለው ። ያዕቆብም፥ «በመጀመሪያ ብኵርናህን ሽጥልኝና » አለው ። ዔሳውም ፥ «እኔ ልሞት ነኝና ይህች ብኵርና ለምኔ ናት ? » አለ ። ያዕ ቆብም ፥ «ማልልኝ» አለው ፤ ማለለትም፤ በአንድ ሣህን ቀይ ወጥም ብኵርናውን ሸጠ ። ከዚህም በኋላ ዔሳው ኤዶም* ተባለ ፤ ኤዶም ማለትም ቀይ ማለት ነው።

### ፫ ፤ ያዕቆብ በተንኰል በረከትን ወሰደ ።

ዘፍጥ. ፳፯ ፥ ፩—፵፩ ።

ይስሐቅም ሸምግሎ ዕውር በሆነ ጊዜ ታላ ቁን ልጁን ዔሳውን ጠርቶ እንዲህ አለው፥ « ልጄ ሆይ ፥ እኔ አረጀሁ ፤ አሁንም ቀስትህን ውሰድ ፥ አደንም አድንልኝ ፤ ሳልሞትም ነፍሴ እንድትባርክህ የጣ ፈጠ መብል እኔ እንደምወደው አዘጋጅ ተህ አምጣልኝ» ። እንደዚሁ ይስሐቅ ፥ ታላቁ ለታናሹ ይገዛል የሚለውን የእግ ዚአብሔርን ቃል ሳያከብር የወደደውን ዔሳውን ለማላቅ አሰበ ።

ርብቃ ግን የባልዋን የይስሐቅን ቃል ሰምታ ያዕቆብን ፥ «ልጄ ሆይ ፥ ከመንጋው ሁለት ጠቦቶች አምጣልኝ ፤ እነርሱንም ጣፋጭ መብል ለአባትህ እን ደሚወደው አደርጋለሁ ፤ ለአባትህም ሳይሞት እንዲባርክህ ታቀርብለታለህ» አለችው ። ርብቃም ፥ እንደ ወንድሙ ጠጕራም ሰው እንዲመስል የጠቦቶቹን ለምድ በያዕቆብ እጆችና በአንገቱ አደረ ገች ። ያዕቆብም ወደ አባቱ ገብቶ ፥ «እኔ የበኵር ልጅህ ዔሳው ነኝ» ባለው ጊዜ ይስሐቅ የጠቦቶቹን ለምድ ዳስሶ ተታ ለለ ፤ ዔሳውም እንዳልሆነ ሳያስተውል ያዕቆብን ባረከው ። ነገር ግን በብልሃትና በሽንገላ መልካም ነገርን እንኳ መፈለግ የማይገባ ነው ፤ ይህም የርብቃና የያዕቆብ ሽንገላ ብዙ ጸብንና ኀዘንን አስከተለ ።

ያዕቆብም ከአባቱ ፊት ከወጣ በኋላ ወዲያው ዔሳው መጣ፥ አባቱንም ፥ «አባቴ ይነሣ ፤ ይብላም» አለው ። ይስሐ ቅም ፥ «አንተ ማን ነህ ? » አለው ። እር ሱም ፥ «እኔ የበኵር ልጅህ ዔሳው ነኝ» አለው ። ይስሐቅም እጅግ ደንግጦ ፥ «ያደ ነውን አደን ወደ እኔ ያመጣ ማን ነው ? ሳትመጣም በላሁ ባረክሁትም» አለ ። ዔሳውም እጅግ መራራ ጩኸት ጮኸ አለቀሰም ፤ ዔሳውም ፥ «በእውነት ስሙ ያዕቆብ ተባለ ፥ ሁለት ጊዜ አሰናክሎ ኛል» ብሎ አባቱን ፥ «ለእኔ በረከትን አላ ስቀረህልኝም ? » አለው ። ይስሐቅም ፥ «ጌታህ አደረግሁት ፤ ልጄ ሆይ ለአንተ ምን ላድርግ ? » አለው ። ዔሳውም ፥ «አባቴ ሆይ በረከትህ አንዲት ብቻ ናትን? እኔንም ደግሞ ባርከኝ » ብሎ አለቀሰ ። አባቱም ፥ «ለወንድምህ ትገዛለህ ፤ ነገር ግን በተቃወምኸው ጊዜ ቀንበሩን ከአን ገትህ ትጥላለህ» አለው ። ዔሳውም በያ



www.ethiopianorthodox.org

ዕቆብ ቂም ያዘበት ፤ በልቡም ፡ «የአባቴ የልቅሶ ቀን ቀርቦአል ፤ ከዚያም በኋላ ወንድሜን እገድላለሁ» አለ ።

፪ ፤ ያዕቆብ ወደ ካራን ተላከ ።

ዘፍጥ. ፳፯ ፡ ፵፩—፳፰ ፡ ፭ ፤ ፳፯ ፡ ፴፬ ፡ ፴፭ ።

ዔሳው ፡ ወንድሜን እገድለዋለሁ ማለቱን ርብቃ በሰማች ጊዜ ያዕቆብን ፡ « ልጄ ሆይ ተነሣና ወደ ወንድሜ ሂድ ፤ የዔሳው ቁጣ ከበረደም በኋላ ልኬ አስመጣሃለሁ » አለችው ። ርብቃም ለባልዋ፡ « ያዕቆብ ከዚህ አገር ሴቶች ልጆች ሚስት የሚያገባ ከሆነ በሕይወቴ መኖር ለምኔ ነው ?» አለች ። ይህም ንግግርዋ ቁም ነገር የያዘ ነበረ ፤ ዔሳው ከከነዓናውያን ሴቶችን ወስዶ በማግባቱ ወላጆቹን አሳዝኖ ነበርና ። ይስሐቅም ያዕቆብን ጠርቶ ፡ « ተነሣና ወደ ካራን ሂድ ፤ ከዚያም ከእናትህ ወንድም ሴቶች ልጆች ሚስት አግባ » አለው ። በዚያን ጊዜም ይስሐቅ ስለ ልጆቹ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳይቃወም የአብርሃምን በረከት ለያዕቆብ አጽንቶ ፡ «ሁሉን የሚችል አምላክ ለብዙ ሕዝብ ጉባኤ እንድትሆን ይባርክህ ፡ ያብዛህ ፡ ስደተኛ ሆነህ የተቀመጥህባትን እግዚአብሔርም ለአብርሃም የሰጣትን ምድር እንድትወርስ የአብርሃምን በረከት ለአንተም ለዘርህም ይስጥህ » ብሎ ያዕቆብን ወደ ካራን ሰደደው ።

* * *

በሰው ልብ ብዙ አሳብ አለ ፤
የእግዚአብሔር ምክር ግን እርሱ ይጸናል ።
ምሳሌ ፲፱ ፡ ፳፩ ።

አንደበትህን ከክፉ ከልክል ፡
ከንፈሮችህም ሽንገላን እንዳይናገሩ ።
መዝ. ፴፫ (፴፬) ፡ ፲፫ ።


* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ዔሳው ብኵርናውን እንደ ናቀ በምን አሳየ ?
፪ ፤ ርብቃና ያዕቆብ የእግዚአብሔርን በረከት በሽንገላ መፈለጋቸው መልካም ነውን ?
፫ ፤ ያዕቆብ ወደ ካራን የተላከ በምን ምክንያቶች ነበረ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ መርምረኝ ልቤንም ዕወቅ ፤
ፈትነኝ መንገዴንም ዕወቅ ፤
በደልንም በኔ ውስጥ ብታገኝ እይ ፤
የዘላለምንም መንገድ ምራኝ ።
መዝ. ፻፴፰ (፻፴፱) ፡ ፳፫—፳፬ ።

* ዔሳው የኤዶማውያን አባት እንደሆነ በዘፍጥ. ፴፮ ተጽፎ ይገኛል ።





ምዕራፍ ፲፫ ።

## ያዕቆብና ልጆቹ ።

ዘፍጥ. ፳፰ ፡ ፲—፴፭ ፡ ፳፱ ።

፩ ፤ የያዕቆብ ሕልም ።

ዘፍጥ. ፳፰ ፡ ፲—፲፯ ።

ያዕቆብም መንገዱን ሄደ ፤ ፀሐይም በጠለቀች ጊዜ በደረሰበት ሥፍራ ድንጋይን ተንተርሶ ተኛ ። በዚያን ጊዜ ብቸኝነት ይሰማው የለምን ? ያዕቆብ ስለ እግዚአብሔር ሰምቶ ነበር ፤ ነገር ግን ገና እግዚአብሔርን አላወቀም ነበር ፡ ከእርሱም ጋር መሆኑን አላስተዋለም ነበር ።

በዚያን ሌሊት ያዕቆብ ሕልም አለመ ። እነሆም ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስ በምድር ላይ የተተከለ መሰላል አየ ። እነሆም የእግዚአብሔር መላእክት ሲወጡበትና ሲወርዱበት ተመለከተ ። እነሆም እግዚአብሔር በላዩ ቆሞበት ነበር።

ይህንም ሁሉ በሕልሙ ሲያይ ሳለ እግዚአብሔር አምላክ ፡ « የአባትህ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ፤ ይህችን አንተ የተኛህባትን ምድር ለአንተም ለዘርህም እሰጣለሁ ፤ ዘርህም እንደ ምድር አሸዋ ይሆናል ፤ የምድርም ሕዝቦች ሁሉ በአንተ በዘርህም ይባረካሉ » አለው ። እግዚአብሔርም ፡ « እነሆም እኔ ከአንተ ጋር ነኝ ፡ በምትሄድበትም መንገድ ሁሉ



www.ethiopianorthodox.org

እጠብቅሃለሁ ፤ ወደዚችም ምድር እመልስሃለሁ ፤ የነገርሁህን ሁሉ እስካደርግልህ ድረስ አልተውህምና » አለው ።

ያዕቆብም ከእንቅልፉ ተነሥቶ ፤ « በእውነት እግዚአብሔር በዚህ ሥፍራ ነው ፤ እኔ አላወቅሁም ነበር » አለ ። ያዕቆብም ፈራ ፤ « ይህ ሥፍራ እንዴት ያስፈራል ፤ ይህ ሥፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ ሌላ አይደለም ፤ ይህም የሰማይ ደጅ ነው » አለ ።

## ፪ ፤ የያዕቆብ ብጽዓት ።

ዘፍጥ. ፳፰ ፥ ፲፰—፳፪ ።

ያዕቆብም ማለዳ ብሎ ተነሣ ፤ ተንተርሶት የነበረውንም ድንጋይ ወስዶ ሐውልት አድርጎ አቆመው ፤ በላዩም ዘይት አፈሰሰበት ፤ እንዲህም ብሎ ስእለት ተሳለ ፤ «እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቢሆን ፤ በምሄድባትም በዚች መንገድ ቢጠብቀኝ ፤ የምበላውንም እንጀራ የምለብሰውንም ልብስ ቢሰጠኝ ፤ ወደ አባቴ ቤትም በጤና ብመለስ ፤ እግዚአብሔር አምላኬ ይሆንልኛል ፤ ለሐውልት የተከልሁት ይህም ድንጋይ የእግዚአብሔር ቤት ይሆናል ፤ ከሰጠኸኝም ሁሉ ለአንተ ከአሥር አንድ አንዱን እሰጥሃለሁ » አለ ። የዚያንም ቦታ ስም ቤቴል አለው ። ቤቴል ማለትም የእግዚአብሔር ቤት ማለት ነው ።

## ፫ ፤ የያዕቆብ ልጆች ።

ዘፍጥ. ፳፱ ፥ ፩—፴ ፥ ፳፬ ፤ ፴፭ ፥ ፲፮—፳ ።

ያዕቆብም ወደ ካራን ከደረሰ በኋላ ከአጎቱ ከላባ ጋር ኑሮ እስከ ሰባት ዓመት ድረስ ስለ ታናሺቱ ልጁ ስለ ራሔል መንጋን በመጠበቅ አገለገለ ፤ ራሔልንም ይወድዳት ስለ ነበር እንደ ጥቂት ቀን መሰለው ። የሠርጉ ጊዜ ሲደርስ ግን ላባ ያዕቆብን አታልሎ በራሔል ፈንታ ታላቂቱን ልጁን ልያን ተክቶ ሰጠው ። ያዕቆብም ፤ « ለምን አታለልኸኝ ? » ባለው ጊዜ ላባ ፤ « የሠርጉ ቀኖች ከተፈጸሙ በኋላ ራሔልን ደግሞ እሰጥሃለሁና አንተ ሌላ ሰባት ዓመት ስለ እርስዋ ታገለግለኛለህ» ብሎ ከሠርጉ ቀኖች በኋላ ራሔልን ጨምሮ ለያዕቆብ ሰጠው ።

ያዕቆብም ብዙ ልጆችን ወለደ ፤ ከልያ የተወለዱት ፤ ሮቤል ስምዖን ሌዊ ይሁዳ ይሳኮርና ዛብሎን ነበሩ ፤ ከራሔልና ከልያ ባሪያዎች የተወለዱት ፤ ዳንና ንፍታሌም ፤ ጋድና አሴር ነበሩ ። ከዚያም በኋላ ራሔል ዮሴፍን ወለደች ፤ ከብዙ ዓመትም በኋላ ለያዕቆብ አሥራ ሁለተኛ ወንድ ልጅ ብንያምን በወለደች ጊዜ ራሔል ሞተች ፤ በቤተልሔምም ተቀበረች ።

## ፬ ፤ ያዕቆብ እስራኤል ተባለ ።

ዘፍጥ. ፴፪—፴፭ ።

ያዕቆብ በውጭ አገር ሃያ ዓመት ከኖረ በኋላ እግዚአብሔር ፤ « ወደ አባትህ ምድር ተመለስ ፤ ከአንተ ጋር እሆናለሁ » አለው ። ያዕቆብም ሄደ ፤ የእግዚአብሔር መላእክትም ተገናኙት ።

ያዕቆብ ግን ጭንቀት በዛበት ። ላባ በቍጣ ሲከተለው ፤ ዔሳውም ሊገናኘው ሲመጣ መንገዱ አስቸጋሪ እንደ መሰለው መጽሐፍ ቅዱስ በሰፊው ይነግረናል ። በዚህም ጊዜ ያዕቆብ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ ፤ እግዚአብሔርም በሌሊት ሰውን መስሎ ከያዕቆብ ጋር ተገናኘ ፤ እስከ ንጋትም ድረስ ታገለው ፤ ሲታገለውም የያዕቆብን የጭኑን ሹልዳ ነክቶ አደነዘዘው ። በዚያን ጊዜ ያዕቆብ በመታገል ፈንታ በእጁ ጨብጦ ፤ « ካልባረክኸኝ አልለቅህም» አለው ። እግዚአብሔርም ፤ «ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል ፤ ከእግዚአብሔር ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና» ብሎ ባረከው ። ያዕቆብም ፤ «እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ ፤ ሰውነቴም ድና ቀረች» ሲል የዚያን ሥፍራ ስም ጵኒኤል ብሎ ጠራው ። ጵኒኤል ማለትም የእግዚአብሔር ፊት ማለት ነው ።

ጵኒኤልንም ሲያልፍ ፀሐይ ወጣችለት ። በዚያን ቀንም በጭኑ ምክንያት እያነከሰ ወደ ከነዓን አገር ገብቶ በሰላም ከዔሳው ጋር ተገናኘ ። እስከዚህ ድረስ ያዕቆብ በገዛ ራሱ ብልሃት በረከትን ለማግኘት የሚፈልግና የሚታገል ሰው ነበረ ። አሁን ግን በራሱ ብልሃት ሳይሆን በእግዚአብሔር በአምላኩ በመታመን ፤ መንገዱን የሚያቅናለት እግዚአብሔር እንደሆነ ማስተዋል ጀመረ ። ተረከዝን የሚይዝ አሰናካይ የነበረ ያዕቆብ ፤ እስራኤል ተባለ ። እስራኤል ማለትም « ከእግዚአብሔር ጋር የሚገዛ » ማለት ነው ።

ያዕቆብም አባቱ ገና በሕይወቱ ሳለ አብርሃምና ይስሐቅ እንግዶች ሆነው ወደ ተቀመጡበት ወደ ኬብሮን መጣ ፤ በኬብሮን ሸለቆም ኖረ ። ከያዕቆብ ዘመን ጀምሮ እግዚአብሔር « የአብርሃም የይስሐቅም የያዕቆብም አምላክ » ተብሎ ሲጠራ ሁሉን ቻይ ታማኝም አምላክ መሆኑ ይታሰባል ።

* * *

መንገድህን ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ ፤
በእርሱም ታመን ፤ እርሱም ያደርግልኻል ።
መዝ. ፴፯ (፴፮) ፥ ፭ ።

ጌታ እግዚአብሔር የዘላለም አምባ ነውና
ለዘላለም በእግዚአብሔር ታመኑ ።
ኢሳ. ፳፮ ፥ ፬ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ያዕቆብ በሕልሙ ምን አየ ? ምንስ ተስፋ ተሰጠው?
፪ ፤ የሥፍራውን ስም ቤቴል ብሎ የሰየመው በምን ምክንያት ነበረ ?
፫ ፤ ወደ ከነዓን በተመለሰ ጊዜ ምን አዲስ ስም ተሰጠው ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፤ የልጅነቴን ኃጢአትና መተላለፍ አታስብብኝ ፤
አቤቱ ፤ ስለ ቸርነትህ ብዛት እንደ ምሕረትህ አስበኝ ።
መዝ. ፳፭ (፳፬) ፥ ፯ ።



ምዕራፍ ፲፩ ።

## ለዳዊት የተሰጠ ተስፋ ።

፩ ሳሙ. ፲፮ ፤ ፩—፲፫ ፤ ፪ ሳሙ. ፯ ፤ ፲፮ ።

### ፩ ፤ ዳዊት ለንጉሥነት ተቀባ ።

፩ ሳሙ. ፲፮ ፤ ፩—፲፫ ።

ከአብርሃም ዘመን ከአንድ ሺህ ዓመት ያህል በኋላ በእስራኤል አገር ፤ ቤተልሔም በተባለች ከተማ ከይሁዳ ነገድ ለሆነ እሴይ ለሚባል ሰው ስምንት ወንዶች ልጆች ነበሩት ፤ የስምንተኛው ልጅ ስም ዳዊት ነበረ ። ዳዊትም ገና ብላቴና ሳለ የአባቱን በጎች ይጠብቅ ነበር ።

በዚያን ዘመን ሳኦል የተባለው የእስራኤል ንጉሥ ለእግዚአብሔር የሚታዘዝ አልነበረምና እግዚአብሔር ለነቢዩ ሳሙኤል ፤ « በቀንድህ ዘይት ሞልተህ ወደ ቤተ ልሔም ሂድ ፤ ከናቅሁት ከሳኦል በኋላ በእስራኤል ላይ ንጉሥ የሚሆነውን ከቤተልሔማዊው ከእሴይ ልጆች መካከል አዘጋጅቻለሁ » አለው ።

ሳሙኤልም እግዚአብሔር የተናገረውን አደረገ ፤ ወደ ቤተልሔምም መጣ ። የእሴይንም ታላቅ ልጅ ባየው ጊዜ ቁመቱንና መልኩን ተመልክቶ ፤ በእውነት እግዚአብሔር የሚቀባው እርሱ ነው ብሎ አሰበ ። እግዚአብሔር ግን ፤ «ፊቱን የቁመቱንም ዘለግታ አትይ ፤ ሰው እንደሚያይ እግዚአብሔር አያይምና ናቅሁት፤ ሰው ፊትን ያያል ፤ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል » አለው ። እሴይም ሰባቱን ልጆቹን በነቢዩ ፊት አሳለፋቸው ፤ ሳሙኤልም ፤ « እግዚአብሔር እነዚህን አል መረጠም ፤ የቀረ ልጅ አለህን ? » አለው። እርሱም ፤ « ታናሹ ገና ቀርቶአል ፤ እነሆም በጎችን ይጠብቃል » አለ ። ሳሙኤልም ፤ « እርሱ እስኪመጣ ድረስ ለመብል አንቀመጥምና ልከህ አስመጣው » አለው ።

እሴይም ልኮ ዳዊትን አስመጣው ፤ እርሱም ቀይ ፤ ዓይኑም የተዋበ ፤ መልኩም ያማረ ነበረ ። እግዚአብሔርም ሳሙኤልን ፤ « ይህ ነውና ተነሥተህ ቅባው » አለው ። ሳሙኤልም የዘይቱን ቀንድ ወስዶ ቀባው ። ከዚያም ቀን ጀምሮ የእግዚአብሔር መንፈስ በዳዊት ላይ በኃይል አደረ ።

እንዲሁ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ እንዲነግሥ እንደ ልቡ የሆነውን ሰው ዳዊትን መረጠ። ይሁን እንጂ እስከ አያሌ ዓመት ድረስ ዳዊት ከንጉሥ ሳኦል ምቀኝነት የተነሣ እየተሳደደ መከራ ተቀበለ ። ጊዜው ሲደርስ ግን ትልቅ ንጉሥ ሆኖ ነገሠ ።

### ፪ ፤ ለንጉሥ ዳዊት የተሰጠ የዘሩ ተስፋ ።

፪ ሳሙ. ፯ ፤ ፲፪ ፤ ፲፫ ፤ ፲፮ ፤ ፲፰ ፤ ፲፱ ፤ ፳፱ ።

ዳዊት በኢየሩሳሌም ባለው በጽዮን አምባ ላይ መናገሻ ከተማውን ሠርቶ ከነገሠ በኋላ እግዚአብሔር ፤ « ከአንተ በኋላ ዘርህን አስነሣለሁ ፤ የመንግሥቱንም ዙፋን ለዘላለም አጸናለሁ » ብሎ የነገሥታት ሁሉ ንጉሥ እርሱ ክርስቶስ* ከዳዊት ቤት እንደሚወለድ ተስፋ ሰጠው ። ዳዊትም በዚህ ተስፋ ደስ አለው ፤ እግዚአብሔርንም ሲያመሰግን እንዲህ አለ ፤ « ጌታዬ እግዚአብሔር ሆይ ፤ እስከ ዚህ ያደረስሽኝ እኔ ማን ነኝ? ቤቴስ ምንድር ነው ? ጌታዬ እግዚአብሔር ሆይ ፤ ይህ በፊትህ ጥቂት ነበረ ፤ ስለ ባሪያህም ቤት ደግሞ ለሩቅ ዘመን ተናገረኻልና አሁን እንግዲህ ለዘላለም በፊትህ እንዲሆን የባሪያህ ቤት ይባረክ ። »

የእስራኤል ሕዝብ ይህን የተስፋ ቃል ይዘው ፤ ክርስቶስ ሲመጣ ከዳዊት ቤት ይወለዳል እያሉ ከትውልድ ወደ ትውልድ መምጣቱን ይጠባበቁ ነበሩ ። መንግሥታቸውና የዳዊት ቤት ነገሥታትም ከወደቁ በኋላ ስንኳ የተስፋውን ቃል በይበልጥ ይይዙ ነበር ።

### ፫ ፤ የተስፋው መፈጸም ።

ከዳዊት ዘመን ከአንድ ሺህ ዓመት ያህል በኋላ ተስፋው ተፈጸመ ። እግዚአብሔር አብ ፤ የዓለም መድኃኒት እንዲሆን አንድ ልጁን ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ላከ ። እርሱም እግዚአብሔር ወልድ ሲሆን ሰው ሆኖ ከዳዊት ቤት ሰብ ተወልዶ መጣ ፤ የተወለደም የዳዊት ከተማ በተባለው በቤተልሔም ነበረ ። በሚቀጥሉት ገጾች ስለ መምጣቱ ፤ ስለ ፈጸመው ሥራው ፤ ስለ ክብሩም እናነባለን ።

ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ከሕዝቡ ከእስራኤል ብዙዎች አልተቀበሉትም ። ምክንያቱም እነርሱ የፈለጉ በላያቸው ይገዛ የነበረውን የሮማውያንን ሥልጣን በመሻር የገዛ ራሳቸውን መንግሥት አድሶ በኢየሩሳሌም የሚነግሥ ምድራዊ ንጉሥ ነበረ ። እርሱ የመጣው ግን ከምድራዊ ጠላት ሁሉ የበለጠውን የሰይጣንን ሥልጣንና ሥራ በመሻር ሰውን ከኃጢአት አድኖ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊያገባው ነበረ ። ይህንም ለማድረግ ስለ ሰው ኃጢአት ምክንያት መሞት ነበረበት ።





www.ethiopianorthodox.org

አራቱ ወንጌላውያን ስለ ተቀበሉትና ስላልተቀበሉት ሰዎች በግልጽ ይነግሩናል ። ከእርሱ በቀር መድኀኒት ስለሌለ በእርሱ የሚያምን ሁሉ ከኃጢአት ነጽቶ ይድናል ፤ የማያምንበት ግን በኃጢአቱ ይጠፋል ።

* * *

በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና ።
ዮሐ. ፫ ፡ ፲፮ ።

ከዚህ ሰው (ከዳዊት) ዘር እግዚአብሔር እንደ ተስፋው ቃል . . .መድኀኒትን እርሱም ኢየሱስን አመጣ።
የሐዋ. ፲፫ ፡ ፳፫ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ዳዊት የማን ልጅ ነበረ ?
፪ ፤ የትስ ተወለደ ?
፫ ፤ ክርስቶስ የዳዊት ልጅ ተብሎ የሚጠራው በምን ምክንያት ነው ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ ምሕረትህን ለዘላለም እዘምራለሁ ፡
እውነትህንም በአፌ ለልጅ ልጅ እናገራለሁ ።
እንዲህ ብለሃልና ፡ ምሕረት ለዘላለም ይመሠረታል ፡
እውነትህም በሰማይ ይጸናል ።
መዝ. ፹፱ (፹፰) ፡ ፩ ፡ ፪ ።

* « ክርስቶስ» ማለት «የተቀባ » ማለት ነው ፤ በዕብራይስጥም « መሢሕ » ማለት ነው ።





ምዕራፍ ፲፩ ።

## የአዋጅ ነጋሪ ልደት ።

ሉቃ. ፩ ፡ ፭—፳፭ ፡ ፶፯—፹ ።

### ፩ ፤ መልአኩና ዘካርያስ ።

ሉቃ. ፩ ፡ ፭—፳፫ ።

ከጥንት ጀምሮ የተነገረው የተስፋ ቃል መፈጸሚያ ወራት ሲቀርብ እግዚአብሔር የክርስቶስ አዋጅ ነጋሪ የሚሆነውን ነቢይ ላከ ፤ የልደቱም ታሪክ እንደሚቀጥለው ነበረ ።

በእስራኤል ዋና ከተማ በኢየሩሳሌም ትልቅ ቤተ መቅደስ ነበረ ። በዚያም ቤተ መቅደስ ጥዋትና ማታ የእስራኤል ካህናት የበግ መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር እያቀረቡ እንደተሰጣቸው ሕግ አገልግሎታቸውን ይፈጽሙ ነበር ።

ከእነዚህም ካህናት አንዱ ዘካርያስ ይባል ነበር ። እርሱም ኤልሳቤጥ ከምትባል ከሚስቱ ጋር ከኢየሩሳሌም ውጭ በተራራማው አገር ይኖር ነበር ። ሁለቱም በእግዚአብሔር ፊት ያለ ነቀፋ የሚሄዱ ጻድቃን ነበሩ ፤ ሆኖም ልጅ አልነበራቸውም ። ከማርጀታቸውም በፊት ልጅ ለማግኘት ይጸልዩ ነበር ፤ ካረጁ በኋላ ግን የልጅን ተስፋ ቈርጠው እግዚአብሔር ልጅ የማይሰጣቸው መሰላቸው ።

ከዕለታትም አንድ ቀን ዘካርያስ በአገልግሎቱ ተራ ወደ ቤተ መቅ



www.ethiopianorthodox.org

ደስ ውስጥ ገብቶ ከወርቅ በተሠራው የዕጣን መሠዊያ ላይ ዕጣንን አጤሰ ፤ ሕዝቡም ሁሉ በውጭ ቆመው ይጸልዩ ነበር ። እነሆም የጌታ መልአክ በዕጣኑ መሠዊያ ቀኝ ቆሞ ለዘካርያስ ታየው ። ዘካርያስም መልአኩን ባየ ጊዜ ደነገጠ ፈራም ። መልአኩም ፣ « ዘካርያስ ሆይ ፣ አትፍራ ፤ ጸሎትህ ተሰምቶአልና ሚስትህ ኤልሳቤጥ ልጅ ትወልዳለች ፤ ስሙም ዮሐንስ ይባላል ፤ በመወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል » አለው ።

ዘካርያስም ተገርሞ ሲሰማ አነጋጋሪው መልአክ ፣ « ልጅህ ዮሐንስ ታላቅ ነቢይ ይሆናል ፤ በጌታ ፊት ሄዶ ለጌታ የተዘጋጁትን ሕዝብ ያሰናዳል » አለው።

ዘካርያስም መልአኩን ፣ « እኔ ሽማግሌ ሰው ነኝ ፣ ሚስቴም በዕድሜዋ አርጅታለችና ይህ እንደሚሆን በምን ዐውቃለሁ ? » ብሎ ጠየቀው ። መልአኩም መልሶ ፣ « እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ ፤ ይህችንም የምሥራች እንድነግርህ ተልኬ ነበር ፤ እነሆም ቃሌን ስላላመንህ ልጅህ እስኪሚወለድ ድረስ ዲዳ ትሆናለህ ፣ መናገርም አትችልም » አለው ።

በዚህም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በውጭ ቆመው ሲጠባበቁ በዘካርያስ መዘግየት ይደነቁ ነበር ። በወጣም ጊዜ በእጁ መጥቀስ እንጂ ሊያነጋግራቸው እንዳልቻለ አስተዋሉ ፤ በዚያን ጊዜም በቤተ መቅደስ ራእይ እንዳየ ተረዱ ።

፪ ፤ የዮሐንስ ልደት ።

ሉቃ. ፩ ፣ ፳፬ ፣ ፳፭ ፣ ፶፯—፷፮ ።

ዘካርያስም ወደ ቤቱ ተመለሰ ፤ የሆነውንም ሁሉ በጽሑፍ እንጂ በአንደበቱ ተናግሮ ለማስታወቅ አይችልም ነበር ። ኤልሳቤጥ ልጅን እንደምትወልድ ባወቀች ጊዜ እጅግ ደስ አላት ፣ እግዚአብሔርንም አመሰገነች ። በወራትዋም ልጅ ወለደች ፤ ጐረቤቶችዋና ዘመዶችዋም ከእርስዋ ጋር ተደሰቱ ።

ከአብርሃም ጊዜ ጀምሮ ለእስራኤል እንደ ተሰጠው ትእዛዝ በስምንተኛው ቀን ሕፃኑን ሊገርዙት መጡ ። ስሙንም ለመሰየም ሲወያዩ ፣ በአባቱ ስም ዘካርያስ ተብሎ ይሰየም አሉ ። እናቱ ግን ፣ « አይሆንም ፣ ዮሐንስ ይባል እንጂ » አለች ። እነርሱም ፣ « ከወገንሽ ማንም በዚህ ስም የተጠራ የለም » ብለው አባቱን በጥቅሻ ጠየቁ ። ዘካርያስም ብራና ለምኖ ፣ « ስሙ ዮሐንስ ነው » ሲል ጻፈ ። ሁሉም ሲያደንቁ ሳሉ የዘካርያስ ምላስ በዚያን ጊዜ ተፈታ ፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገነ ተናገረ ። ይህንም የሰሙ ሰዎች ሁሉ ፣ « እንኪያስ ይህ ሕፃን ምን ይሆን ? » እያሉ ፈሩ ፤ ነገሩንም በልባቸው አኑረው አሰቡበት ።

፫ ፤ የዘካርያስ ምስጋና ።

ሉቃ. ፩ ፣ ፷፯—፸፱ ።

ዘካርያስ እጅግ ተደሰተ ፤ በመንፈስ ቅዱስም ተሞልቶ ትንቢት ሲናገር ፣ «የእስራኤል ጌታ አምላክ ይባረክ ፣ በዳዊት ቤት የመዳን ቀንድን አስነሥቶልናል ፤ ለአባታችን ለአብርሃምም የማለውን መሐላውን አስቦ አዳነን » ሲል የክርስቶስን መምጣት በምስጋና አወራ ። ከዚያም በኋላ ወደ ሕፃኑ ወደ ዮሐንስ ዞወር ብሎ ፣ « አንተ ሕፃን ሆይ ፣ የልዑል ነቢይ ትባላለህ ፣ መንገዱን ልትጠርግ በጌታ ፊት ትሄዳለህ ፤ እግዚአብሔርም በምሕረቱ ያዘጋጀውን መዳን ለሕዝቡ ታስታውቃቸዋለህ » አለው ።



፬ ፤ የዮሐንስ እድገት ። ሉቃ. ፩ ፣ ፹ ።

ዮሐንስም አደገ ፤ በእግዚአብሔር ዕውቀት እየበረታ በመንፈስም እየጠነከረ ሄደ ። ብዙ ጊዜም ለብቻው ሆኖ ከእግዚአብሔር እንዲማር ስለ ወደደ በምድረ በዳ ይኖር ነበር ።

* * *

እግዚአብሔርን አመስግኑ ፤ ቸር ነውና ፣
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና ። . . .
እኛን በመዋረዳችን አሰበናልና ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና ።
መዝ. ፻፲፯ (፻፲፰) ፣ ፩ ፣ ፳፱ ።

ሕፃን ቅንና ንጹሕ መሆኑ
በሚያደርገው ሥራ ይታወቃል ።
ምሳሌ ፳ ፣ ፲፩ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ የዮሐንስ አባትና እናት እነማን ነበሩ ?
፪ ፤ ዘካርያስ ዲዳ የሆነ በምን ምክንያት ነው ?
፫ ፤ ዮሐንስ ምን ለማድረግ ተወለደ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፣ አንተ ተስፋዬ ነህ ፣
እግዚአብሔር ሆይ ፣ ከታናሽነቴ ጀምረህ
መታመኛዬ ነህ ፤ . . .
ሁልጊዜም ዝማሬዬ ለአንተ ነው ።
መዝ. ፸ (፸፩) ፣ ፭ ፣ ፮ ።



## ምዕራፍ ፲፯ ።

# የመልአክ ብሥራት ።

ሉቃ. ፩ ፥ ፳፮—፶፮ ፤ ማቴ. ፩ ፥ ፲፰—፳፭ ።

### ፩ ፤ የመልአኩ ገብርኤል መልእክት ።

ሉቃ. ፩ ፥ ፳፮—፴፰ ።

ከኢየሩሳሌም የሦስት ቀን መንገድ ያህል በምትርቅ በናዝሬት ከተማ ዮሴፍ ለሚባል ሰው የታጨች አንዲት ድንግል ትኖር ነበር ፤ ስምዋም ማርያም ነበረ ።

ኤልሳቤጥ በፀነሰች በስድስተኛው ወር መልአኩ ገብርኤል ወደ ማርያም ተልኮ ፥ « ደስ ይበልሽ ፥ ጸጋን የተሞላሽ ሆይ ፥ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው ፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ » አላት ።

ማርያምም ባየችው ጊዜ በንግግሩ በጣም ደነገጠችና ፥ « ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው ? » ብላ አሰበች ።

መልአኩም ፥ «ማርያም ሆይ ፥ አትፍሪ ፤ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋን አግኝተሻልና ። እነሆም ትፀንሻለሽ ፥ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፥ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ ። እርሱ ታላቅ ይሆናል፤ የልዑል ልጅም ይባላል ፤ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሣል ፤ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም » አላት ።

ማርያምም ፥ « ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል ? » አለችው ። መልአኩም መልሶ ፥ « መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል ፥ የልዑል እግዚአብሔርም ኃይል ይጸልልሻል ፤ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል » አላት ።

ማርያምም ፥ ይህን ሁሉ እየሰማች ስትገረም ሳለ መልአኩ ፥ « እነሆ ዘመድሽ ኤልሳቤጥ ፥ እርስዋ ደግሞ በእርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀነሰች ፥ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና » አላት ። ማርያምም ፥ «እነሆኝ የጌታ ባሪያ ፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ » አለች ። መልአኩም ከእርስዋ ሄደ ።

### ፪ ፤ ማርያምና ኤልሳቤጥ ።

ሉቃ. ፩ ፥ ፴፱—፶፮ ።

ማርያምም ከመልአኩ የሰማችውን ሁሉ ስታስብ ወደ ኤልሳቤጥ ለመሄድ ተነሥታ በይሁዳ ወዳለው ተራራማ አገር ተጓዘች ። ወደ ዘካርያስም ቤት በገባች ጊዜ ኤልሳቤጥን ሰላም አለቻት ፤ ኤልሳቤጥም በመንፈስ ቅዱስ በመመላት ነገሩን አስተውላ በታላቅ ድምፅ ፥ « አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ ፥ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው ፤ የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል ?.የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት » አለች ።

ማርያምም ደስታዋን ገልጣ እግዚአብሔርን አመሰገነች ። ብርቱ የሆነ አምላክ ለአብርሃም የሰጠውን ተስፋ አስቦ መድኃኔ ዓለም የሆነ ጌታ ከእርስዋ እንዲወለድ ስለ መረጣት እጅግ ተገረመች። እርስዋ ፥ ምንም ከእስራኤል ንጉሥ ከዳዊት ዘር ብትሆን ወገንዋ ተዋርዶ ነበርና ከዚህ ዓለም ታላላቆችና ባለጠጎች አልነበረችም ። ነገር ግን እግዚአብሔር አምላክ ወደ እርስዋ ተመለከተ ፤ በእርስዋም ታላቅ ሥራ አድርጎአልና እንዲህ ብላ ከልቧ ምስጋናዋን አቀረበች ፡—

« ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች ፥
መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ
ሐሴት ታደርጋለች ፤
የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቶአልና ።
እነሆም ፥ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ
ብፅዕት ይሉኛል ፤
ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ
አድርጎአልና ፤
ስሙም ቅዱስ ነው ።
ምሕረቱም ለሚፈሩት እስከ ትውልድና ትውልድ ይኖራል ።
ለአባቶቻችን እንደ ተናገረ ፥
ለአብርሃምና ለዘሩ ለዘላለም ምሕረቱ
ትዝ እያለው
እስራኤልን ብላቴናውን ረድቶአል ።»

ማርያምና ኤልሳቤጥም እግዚአብሔር ባደረገላቸው ትልቅ ነገር እየተደሰቱ እያመሰገኑም እስከ ሦስት ወር ድረስ አብረው ኖሩ ። ከዚያም በኋላ ማርያም ወደ ናዝሬት ተመለሰች ።

### ፫ ፤ እጮኛዋ ዮሴፍ ።

ማቴ. ፩ ፥ ፲፰—፳፭ ።

እግዚአብሔር የማርያምን መንገድ በማቅናት እስከ ሦስት ወር ድረስ በሰላም ከኤልሳቤጥ ጋር በደስታ እንድትኖር እንዳደረገ እንደዚሁም ወደ ናዝሬት ስትመለስ በቤቱ እንዲቀበላት ለእጮኛዋ ለዮሴፍ በሕልም ነገረው ።



www.ethiopianorthodox.org

ዮሴፍ ጻድቅ ሰው ነበረ ፤ በሁሉም ነገር ለእግዚአብሔር ሊታዘዝ ወደደ ። ስለዚህም እጮኛው ማርያም እንደ ፀነሰች በሰማ ጊዜ በአሳቡ ተጨንቆ ፣ ምን ላድርግ ? በማለት አዘነ ። እንደዚሁም ነፍሱ ሲታወክ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው እንዲህም አለው ፣ « የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ ፣ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ ። ልጅም ትወልዳለች ፤ እርሱም ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ ። »

ዮሴፍም ከእንቅልፉ በነቃ ጊዜ የጌታ መልአክ እንዳዘዘው እጮኛውን ማርያምን ወሰደ ። ከዚያም ቀን ጀምሮ ዮሴፍ ማርያምን ጠበቃት ፣ በሚያስፈልጋትም ነገር ሁሉ ረዳት ።

* * *

ልጅ ትወልዳለች ፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ ።

ማቴ. ፩ ፣ ፳፩ ።

እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች ፣ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል . . . ትርጓሜውም ፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው ።

ማቴ. ፩ ፣ ፳፪ ፣ ፳፫ ፤ ኢሳ. ፯ ፣ ፲፬ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ድንግል ማርያም የት ትኖር ነበር ?
፪ ፤ መልአኩስ ምን አላት ?
፫ ፤ ቃሉን ሁሉ ከሰማች በኋላ ምን አለች ?

ጸሎት ፤ አንተ አምላኬ ነህ አመሰግንሃለሁ ። . . .
መድኃኒትም ሆነኸኛልና አመሰግንሃለሁ ።
መዝ. ፻፲፯ (፻፲፰) ፣ ፳፰ ።





ምዕራፍ ፲፯ ።

## የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ።

ሉቃ. ፪ ፣ ፩—፳፩ ።

፩ ፤ የቄሣር ትእዛዝ ።

ሉቃ. ፪ ፣ ፩ ፣ ፪ ።

በዚያን ዘመን የእስራኤል አገር በነፃነት ሳይተዳደር የሮም መንግሥት ቅኝ አገር ስለ ነበረ ለሮም ንጉሠ ነገሥት መታዘዝ ነበረበት ። የሮም ንጉሠ ነገሥት ሁሉ ቄሣር ተብሎ ይጠራ ነበርና ጌታችን በተወለደ ዘመን አውግስጦስ የሚባል ሰው ቄሣር በመባል ነግሦ ነበር ።

ማርያምና ዮሴፍ በናዝሬት ከተማ ሆነው የሕፃኑን ልደት ሲጠባበቁ ሳለ ከአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ ወጣ ። ይህም ትእዛዝ ሰው ሁሉ እንዲጻፍ ወደ እየራሱ አገር ይሂድ የሚል ነበረ ። ዮሴፍም ከንጉሥ ዳዊት ቤት ስለሆነ ቤተልሔም ከምትባል ከተማ ነበረ ፤ ከናዝሬትም እስከ ቤተልሔም የሦስት ወይም የአራት ቀን መንገድ ይሆናል ።

፪ ፤ የጌታ ልደት ።

ሉቃ. ፪ ፣ ፫—፯ ።

የቄሣር ትእዛዝ የሚያስቸኩል ስለ ነበረ ዮሴፍ ማርያምን ይዞ ወደ ቤተልሔም ተጓዘ ። እንደ እነርሱም ብዙዎች ሰዎች ወደየከተማቸው ገብተው ይጻፉ ስለነበር ማርያምና ዮሴፍ ወደ ቤተልሔም በደረሱ ጊዜ በእንግዶች ማደሪያ ፣ ቦታ አልተገኘላቸውምና በከብት በረት አደሩ ።



www.ethiopianorthodox.org

በዚያም ሳሉ የማርያም የመውለጃ ወራትዋ ደረሰ ፤ የበኵር ልጅዋንም ወለደች ፤ እንደ አገሩም ልማድ ሕፃንዋን በመጠቅለያ ጠቀለለችና አስተኛችው ። በከብት ቤት ስለ ነበረች ፥ ያስተኛችው በግርግም ነበረ ።

፫ ፤ የመልአክ አዋጅ ። ሉቃ. ፪ ፥ ፰—፲፪ ።

በቤተልሔም ከተማ አቅራቢያ በጎቻቸውን በሌሊት የሚጠብቁ እረኞች ነበሩ ። እነሆም የጌታ መልአክ ወደ እነርሱ ቀረበ ፤ የጌታ ክብርም በዙሪያቸው አበራ ፤ ታላቅ ፍርሃትም ፈሩ ።

መልአኩም እንዲህ አላቸው ፥ «እነሆ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ ፤ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና ። ሕፃኑን የምታውቁበት ምልክት ይህ ነው ፤ ተጠቅልሎ በግርግም ተኝቶ ታገኙታላችሁ ። »

፬ ፤ የሰማይ ሠራዊት ምስጋና ።

ሉቃ. ፪ ፥ ፲፫ ፡ ፲፬ ።

መልአኩም ሲናገር ድንገት ብዙ የሰማይ ሠራዊት ከእርሱ ጋር ታዩ ፤ እግዚአብሔርንም ሲያመሰግኑ ፥ «ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ፤ ሰላምም በምድር ፤ ለሰውም በጎ ፈቃድ » አሉ ።

፭ ፤ የእረኞች ምስክርነት ።

ሉቃ. ፪ ፥ ፲፭—፳፩ ።

መላእክትም ከእነርሱ ተለይተው ወደ ሰማይ በወጡ ጊዜ እረኞቹ እርስ በርሳቸው ፥ « እንግዲህ እስከ ቤተልሔም እንሂድ ፤ እግዚአብሔርም የገለጠልንን ይህን የሆነውን ነገር እንይ » ተባባሉ ። ፈጥነውም ሄዱ ፤ በሌሊትም ወደ ከተማ ገብተው የተሰጣቸውን ምልክት በማሰብ በግርግም የተኛውን ሕፃን ፈልገው አገኙት ። አይተውም ስለዚህ ሕፃን የተነገረላቸውን ነገር ገልጠው ተናገሩ ። የሰሙትም ሁሉ እረኞቹ በነገሩአቸው ነገር ተደነቁ ፤ ማርያም ግን ይህን ነገር ሁሉ በልብዋ እያሰበች ትጠብቀው ነበር ። እረኞቹም እንደ ተባለላቸው ስለ ሰሙትና ስላዩት ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እያከበሩ ወደ መንጋቸው ተመለሱ ።

በስምንተኛውም ቀን ሕፃኑን በገረዙት ጊዜ ፥ በማኅፀን ሳይፀነስ በመልአኩ እንደ ተባለ ስሙ ኢየሱስ ተብሎ ተጠራ ።

* * *

የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን የልግስና ስጦታ ዐውቃችኋልና ፤ ሀብታም ሲሆን ፥ እናንተ በእርሱ ድህነት ባለ ጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ድሀ ሆነ ።
፪ ቆሮ. ፰ ፥ ፱ ።

ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው ። ፩ ጢሞ. ፩ ፥ ፲፭ ።



ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ዮሴፍ ወደ ቤተልሔም የሄደው በምን ምክንያት ነበረ ?
፪ ፤ ድንግል ማርያም ሕፃኑን በምን አስተኛችው ?
፫ ፤ መልአኩ ለእረኞች ምን ነገራቸው ?

ጸሎት ፤ ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ፤
ሰላምም በምድር ፤
ለሰውም በጎ ፈቃድ ። ሉቃስ. ፪ ፥ ፲፬ ።



ምዕራፍ ፲፰ ።

## የሰብአ ሰገል ስግደት ።

ማቴ. ፪ ።

፩ ፤ የሰብአ ሰገል ጉዞ ።

ማቴ. ፪ ፡ ፩ ፡ ፪ ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ከሩቅ አገር ሰብአ ሰገል የሚባሉ ጠቢባን ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው ፥ « የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው ? » በማለት ሰዎችን ጠየቁ ። ተጠያቂዎቹ የኢየሩሳሌም ሰዎች ግን በቅርባቸው ከሚገኘው ከቤተልሔም የተወራውን የመላእክትን ብሥራት ሳያውቁ ወይም ሳያምኑበት ስለ ቀሩ ከሩቅ ለመጡ ፈላጊዎች ተገቢ መልስ አጡ ። ሰብአ ሰገልም ፥ «የዚህን የተወለደውን ንጉሥ ኮከብ በምሥራቅ አገራችን አይተን ልን ሰግድለት መጥተናል » አሉ ።

፪ ፤ የንጉሥ ሄሮድስ ተንኰል ።

ማቴ. ፪ ፡ ፫—፰ ፤ ሚክ. ፭ ፡ ፪ ።

በዚያን ዘመን የሮም መንግሥት በእስራኤል ላይ ያነገሠው ሄሮድስ የተባለው ንጉሥ በኢየሩሳሌም ይገኝ ነበር ። የዘር ትውልዱ ግን ከዔሳው ሕዝብ ከኤዶማውያን ነበረ እንጂ የእስራኤል ዘር አልነበረም ። እርሱም በምቀኝነትና በቍጣ የተሞላ እጅግ ጨካኝ ሰው ስለነበረ ፥ «የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው ? » እያሉ ስለሚጠይቁ ስለ ሰብአ ሰገል በሰማ ጊዜ ፥ ምነው ! ከእኔ በቀር እንዴት ሌላ ንጉሥ ይኖራል ? እያለ በማሰብ ደነገጠ ። ነገሩንም ሲያሰላስል ፥ ይህ የተወለደው ንጉሥ «ክርስቶስ» የሚሉት በነቢያት መጻሕፍት ተስፋ የተሰጠበት ይሆን ይሆናል በማለት የቅዱሳት መጻሕፍት ዕውቀት ያላቸውን የእስራኤልን መምህራን ሰብስቦ ፥ «ክርስቶስ ወዴት ይወለዳል ? » ሲል ጠየቀ ።

እነርሱም ፥ ከሰባት መቶ ዓመት በፊት በነቢዩ ሚክያስ የተሰጠውን ቃል ስላወቁ ፥ «ክርስቶስ የሚወለደው በቤተ ልሔም ነው » አሉት ።

ንጉሥ ሄሮድስም ይህን ካረጋገጠ በኋላ ሰብአ ሰገልን በሥውር አስጠርቶ ፥ « ኮከቡን ያያችሁት መቼ ነበረ ? » ብሎ ጠየቃቸው ። ኮከቡ የታየበትንም ጊዜ ከተረዳ በኋላ ፥ «ወደ ቤተልሔም ሂዱ ፤ ስለ ሕፃኑ በጥንቃቄ መርምሩ ፤ ባገኛችሁትም ጊዜ እኔ ደግሞ መጥቼ እንድሰግድለት ንገሩኝ » አላቸው ። ነገር ግን ሊገድለው እንጂ ሊሰግድለት ፈልጎ አልነበረም ።

፫ ፤ የሰብአ ሰገል በረከት ።

ማቴ. ፪ ፡ ፱—፲፩ ።

ሰብአ ሰገልም ወደ ቤተልሔም የሚያስሄደውን መንገድ ይዘው ሲጓዙ እነሆ ፥ በምሥራቅ ያዩት ኮከብ እየመራቸው ሕፃኑ ባለበት ላይ መጥቶ ቆመ ። ኮከቡንም ባዩ ጊዜ ታላቅ ደስታ እጅግ ደስ አላቸው ፤ ወደ ቤትም ገብተው ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩ ፤ ወድቀውም ሰገዱለት ፤ ሣጥኖቻቸውንም ከፍተው እጅ መንሻ ወርቅና ዕጣን ከርቤም አበረከቱት ።

፬ ፤ ከቤተልሔም ወደ ግብፅ ።

ማቴ. ፪ ፡ ፲፪—፲፭ ።

ሰብአ ሰገልም ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይመለሱ በሕልም ስለ ተነገራቸው በሌላ መንገድ ወደ አገራቸው ተመለሱ ። ከሄዱም በኋላ የጌታ መልአክ በሕልም ለዮሴፍ ታየና ፥ «ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልገዋልና ተነሣ ፥ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ ግብፅ ሽሽ » አለው ።

ዮሴፍም ሕፃኑንና እናቱን ይዞ ወደ ደቡብ በሚያስሄደው መንገድ በሌሊት ሸሸ ። ሄሮድስም እስከሚሞት ድረስ በግብፅ ቈዩ ።

፭ ፤ የቤተልሔም ልቅሶ ።

ማቴ. ፪ ፡ ፲፮—፲፰ ።

ንጉሥ ሄሮድስም ፥ ምነው እነዚያ ሰብአ ሰገል ሳይመለሱ ቀሩ በማለት እየተጨነቀ ይጠባበቃቸው ነበር ። በኋላ ግን በሌላ መንገድ እንደ ሄዱ እንደ ተሣለቁበትም አስተዋለ ፤ እጅግ ተቈጥቶም ጭፍራውን ልኮ ከሰብአ ሰገል እንደ ተረዳው ዘመን በቤተልሔምና በአውራጃዋ የነበሩትን ፥ ሁለት ዓመት የሆናቸውን ከዚያም የሚያንሱትን ሕፃናት ሁሉ አስገደለ ። ይህም ሲሆን ልቅሶና ብዙ ዋይታ በቤተልሔም ተሰማ ። ነገር ግን ጨካኙ ንጉሥ ሄሮድስ በብርቱ በሽታ የታመመ ሽማግሌ ሰው ነበረና ብዙ ወራት ሳይቈይ ሞተ ።

፮ ፤ ከግብፅ ወደ ናዝሬት ።

ማቴ. ፪ ፡ ፲፱—፳፫ ።

ዮሴፍም በግብፅ ሲኖር ሳለ የጌታ መልአክ በሕልም ታየውና ፥ «የሕፃኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና ተነሣ ፥ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ እስራኤል አገር ሂድ»





www.ethiopianorthodox.org

አለው ። ዮሴፍም ሕፃኑንና እናቱን ይዞ የጌታ መልአክ እንዳመለከተው ቀድሞ ወደ ነበረበት ወደ ናዝሬት ከተማ ተመለሰ ፤ በዚያም ኖረ ።

*　　*　　*

የምድር ዳርቻዎች ሁሉ ያስቡ ፥ ወደ እግዚአብሔርም ይመለሱ ፤
የአሕዛብ ነገዶች ሁሉ በፊቱ ይሰግዳሉ ።
መዝ. ፳፩ (፳፪) ፥ ፳፯ ።


ወድቀውም ሰገዱለት ፥ ሣጥኖቻቸውንም ከፍተው እጅ መንሻ . . . አቀረቡለት ።
ማቴ. ፪ ፥ ፲፩ ።

*　　*　　*

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ሰብአ ሰገል ለኢየሱስ ምንና ምን ሰጡት ?
፪ ፤ ሄሮድስ በምን ምክንያት የቤተልሔምን ሕፃናት አስገደለ ?
፫ ፤ ከግብፅ በተመለሰ ጊዜ ዮሴፍ ወዴት እንዲሄድ ተነገረው ?

ጸሎት ፤ ጌታ ሆይ . . . . አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና ፥ የጽድቅም ሥራህ ስለ ተገለጠ አሕዛብ ሁሉ ይመጣሉ በፊትህም ይሰግዳሉ ።
ራእይ ፲፭ ፥ ፫ ፥ ፬ ።





ምዕራፍ ፲፱ ።

## ኢየሱስ በልጅነቱ ።

ሉቃ. ፪ ፥ ፴፱—፶፪ ።

፩ ፤ የናዝሬት ኑሮ ።

ሉቃ. ፪ ፥ ፴፱ ፥ ፵ ፤ ማቴ. ፲፫ ፥ ፶፭ ።

ናዝሬት የከበረች ወይም ዝነኛ ከተማ አልነበረችም ፤ ከትልቁ ከተማ ከኢየሩሳሌም ከምትርቀው ከገሊላ አውራጃ ተራ ከተማ ነበረች ። ዮሴፍም የታወቀ ዝና ያለው ሰው ሳይሆን ጠራቢ ሆኖ ዕለት ዕለት በእጁ እየሠራ ቤተሰቡን የሚረዳ ሰው ነበረ ። በዚህም ከተማና ቤተ ሰብ ዘንድ ሕፃኑ ኢየሱስ የተራ ሰውን ደስታና ኀዘን ሁሉ እየተካፈለ ሲያድግ፥ ኃጢአት ከመሥራት በቀር በሁሉ ነገር እንደ እኛ የተፈተነ ነበረ ። ከዓመት ወደ ዓመትም በጥበብ እየተሞላ በመንፈስ የጠነከረ ሆኖ አደገ ።

፪ ፤ አሥራ ሁለት ዓመት ሲሆነው ።

ሉቃ. ፪ ፥ ፵፩—፶፩ ።

በየዓመቱ ዮሴፍና ማርያም ለእስራኤል እንደ ተሰጠ ሕግ የፋሲካ በዓልን ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ይወጡ ነበር ። ኢየሱስም አሥራ ሁለት ዓመት ሲሆ



www.ethiopianorthodox.org

ነው ከእነርሱ ጋር ወጣ ። ለፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም የሚወጡ እስራኤላውያን እጅግ ብዙ ነበሩ ፤ ከየከተማውና ከየመንደሩም እየተሰበሰቡ ሲጓዙ ፤

«ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ
ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ ።
ኢየሩሳሌም ሆይ ፥ እግሮቻችን በአ
ደባባይሽ ቆሙ ።
ኢየሩሳሌምስ እርስ በርስዋ እንደ
ተገጠገጠች ከተማ ተሠርታለች።
የእግዚአብሔርን ስም ያመሰግኑ
ዘንድ ፥
ለእስራኤል ምስክር ሊሆኑ የእግዚ
አብሔር ነገዶች ወደዚያ ይወ
ጣሉ »

የሚለውን መዝሙር ሊዘምሩ ይወድዱ ነበር ። መዝ.፩፻፳፩ (፩፻፳፪) ።

ኢየሱስ በመካከላቸው ሲሄድ ሳለ ፥ ከዳዊት ዘመን ጀምሮ መናገሻ ከተማ የሆነውን ኢየሩሳሌምን በእግሩ ለመርገጥ ፥ በቅርብ ጊዜ ታድሶ በነበረው ቤተ መቅደስ እግዚአብሔርን ለማመስገን ፥ ለጥቂት ቀን ስንኳ በዚያ ከሚገኙት ከእስራኤል መምህራን ለመማር ሲጠባበቅ ፥ « ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ » እያለ በልዩ ደስታ የሄደ አይመስልምን ?

ወደ ኢየሩሳሌምም ደረሱ ፤ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ በጥንት ዘመን ሕዝቡን እስራኤልን ከመቅሠፍት ጠብቆ ከባርነት እንዳዳናቸው በማስታወስ ከታረደው ከፋሲካ በግ ሥጋ በሉ ። የበዓሉም ቀኖች ከተፈጸሙ በኋላ ዮሴፍና ማርያም ወደ ናዝሬት ሊመለሱ ሲነሡ ብላቴናው ኢየሱስ ተለይቶ በኢየሩሳሌም ቀረ። እነርሱም ከመንገደኞች ጋር የነበረ ስለ መሰላቸው ሳያረጋግጡ የአንድ ቀን መንገድ ሄዱ ፤ ከማደሪያ ቦታቸው ሲደርሱ ግን አላገኙትም ፤ ከሚያውቋቸውና ከዘመዶቻቸው ዘንድ ፈልገው ሲያጡትም ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ፤ ከተማ ለከተማም በመዞር እየተጨነቁ ፈለጉት ።

ከሦስት ቀን በኋላም ወደ ቤተ መቅደስ ቢገቡ በመምህራን መካከል ተቀምጦ ሲሰማቸው ፥ ሲጠይቃቸውም አገኙት ። መምህራንና የሚሰሙት ሰዎች ሁሉም ከማስተዋሉና ከመልሱ የተነሣ ይገረሙ ነበር ።

ዮሴፍና ማርያምም ባዩት ጊዜ ተገረሙ ፤ እናቱም ፥ «ልጄ ሆይ ፥ ለምን እንዲህ አደረግህብን ? እነሆ አባትህና እኔ እየተጨነቅን ስንፈልግህ ነበርን» አለችው ። እርሱም ፥ ለአባቱ ለእግዚአብሔር በሚሆነው በቤተ መቅደስ እንደሚያገኙት ካለማስተዋላቸው የተነሣ ተገርሞ ፥ «ስለምን ፈለጋችሁኝ ? በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንዲገባኝ አላወቃችሁምን ? » አላቸው ። እነርሱ ግን ይህን የተናገራቸውን ነገር አላስተዋሉም፤ እናቱም ነገሩን ሁሉ በልብዋ ትጠብቀው ነበር ። እርሱም ከእነርሱ ጋር ወደ ናዝሬት መጣ ፤ ይታዘዝላቸውም ነበር ።

፫ ፤ የናዝሬት ኑሮና ተግባር ።

ሉቃ. ፪ ፡ ፶፪ ፤ ግር. ፮ ፡ ፫ ።

ኢየሱስም በጥበብና በቁመት እያደገ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ሞገስን አገኘ ። በናዝሬትም ዕለት ዕለት የተራ ሰው ኑሮን እየተካፈለ ጠራቢ በተሰኘበት ከዮሴፍ በተማረው ተግባር ቤት ዘመዶቹን እያገለገለ ኖረ ። ለሕዝቡ እስከ ተገለጠበት እስከ ሠላሳኛው ዓመት ድረስ በዕለታዊ ኑሮውና ሥራው እግዚአብሔር አባቱን ደስ አሰኘው ።



በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው ። . . .
ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ ተፈተነ ።
ዕብ. ፪ ፡ ፲፯ ፤ ፬ ፡ ፲፭ ።

ልጆች ሆይ ፥ ይህ ለጌታ ደስ የሚያሰኝ ነውና በሁሉ ለወላጆቻችሁ ታዘዙ ። ቈላ. ፫ ፡ ፳ ።

*   *   *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ኢየሱስ አሥራ ሁለት ዓመት ሲሆነው ወዴት ሄደ ?
፪ ፤ ዮሴፍና እናቱ በምን ቦታ አገኙት ?
፫ ፤ እናቱ ፥ «አባትህና እኔ እየተጨነቅን ስንፈልግህ ነበርን » ባለችው ጊዜ ኢየሱስ ምን መለሰላት ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፥ ብዙ ምርኮ እንዳገኘ በቃልህ ደስ አለኝ።
ዓመፃን ጠላሁ ተጸየፍሁም ፤
ሕግህን ግን ወደድሁ ።
መዝ. ፻፲፰ (፻፲፱) ፡ ፻፷፪ ፡ ፻፷፫ ።



ምዕራፍ ፳ ።

# የዮሐንስ ተግባር ።

ሉቃ. ፫ ፥ ፩—፲፯ ።

፩ ፤ ከምድረ በዳ የተሰማ ድምፅ ።

ሉቃ. ፫ ፥ ፩—፮ ፤ ማቴ ፫ ፥ ፩—፬ ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን ከኃጢአት ለማዳን መጥቶ ገና በግልጽ ሳይታወቅ በናዝሬት ይኖር ነበር ። ሕዝቡ እንዲቀበሉት አልተዘጋጁም ። እርሱ ግን ሠላሳ ዓመት ያህል ሲሆነው ለእስራኤል የሚገለጥበት ጊዜ ሲደርስ ፥ ድንገት በዮርዳኖስ ወንዝ አቅራቢያ ካለው ምድረ በዳ ፥ «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ»* እያለ የሚጮኽ ሰው ድምፅ ተሰማ ፤ ከኢየሩሳሌምና ከየከተማው ከየመንደሩም ሁሉ ብዙ ሕዝብ የዚሁኑ የነቢዩን ቃል ለመስማት ተሰበሰቡ፤ ሁሉም በልባቸው ፥ ይህ ክርስቶስ ይሆንን? ብለው ያስቡ ጀመር ።

እርሱ ግን ክርስቶስ ራሱ ሳይሆን ፥ በፊቱ በመሄድ ለክርስቶስ የተዘጋጁትን ሕዝብ እንዲያሰናዳ ከእግዚአብሔር የተላከው የዘካርያስ ልጅ ዮሐንስ ነበረ ።



ከብዙ ዓመት ጀምሮ ዮሐንስ ከሰዎች ተለይቶ በምድረ በዳ ሲኖር ነበር ፤ ልብሱ የግመል ጠጕር ፥ መብሉም አንበጣና የበረሀ ማር ነበረ ። የእግዚአብሔር ቃል በመጣለት ጊዜ ስብከቱን ጀመረ ። ይህም በመሆኑ ፥ «የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ » እያለ በምድረ በዳ ስለሚጮኽ ሰው ድምፅ ተብሎ ከብዙ ዘመን በፊት የተነገረው የነቢዩ ኢሳይያስ ቃል ተፈጸመ ።

፪ ፤ የዮሐንስ ስብከት ።

ሉቃ. ፫ ፥ ፯—፲፬ ፤ ማቴ. ፫ ፥ ፯—፲ ።

ዮሐንስ የተላከበቱ ከኃጢአት ወደሚያድነው እንዲሄዱ የሕዝብን ልብ ለማዘጋጀት ስለ ነበረ ኃጢአታቸውን በመግለጥና ፥ ኃጢአታቸውም ስለሚያስከትለው ፍርድ እየገለጠ በብርቱ ይወቅሳቸው ነበር ። የፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ወገኖች* ፥ «እኛ የአብርሃም ልጆች ስለ ሆንን እግዚአብሔር አይፈርድብንም» ቢሉ ዮሐንስ ፥ «እረ በዚህ አትኵሩ ፤ እግዚአብሔር ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት ይችላል» ብሎ ንስሐ እንዲገቡና ለንስሐም የሚገባ ፍሬ እንዲያደርጉ መከራቸው ። ችላ እንዳይሉም በምሳሌ ተናገር ፥ «ምሳር በዛፎች ሥር ተቀምጦአል ፥ ንስሐ ካልገባችሁና መልካም ፍሬ ካላፈራችሁ አሁኑኑ ትቈረጣላችሁ » ብሎ አስጠነቀቃቸው ።

ይህንም ከሰሙት ሰዎች ብዙዎች፥ «እንግዲህ ምን እናድርግ ? » ብለው ቢጠይቁት ፥ «ሁለት ልብስ ያለው ለሌለው ያካፍል ፥ ምግብም ያለው እንዲሁ ያድርግ» ይል ነበር።የመንግሥትን ቀረጥ የሚሰበስቡትም ቀራጮች ፥ «መምህር ሆይ፥እኛስ ምን እናድርግ ?» ብለው ቢጠይቁት ፥ «ከታዘዘላችሁ አብልጣችሁ አትውሰዱ » አላቸው ። ወታደሮችም እንዲሁ ቢጠይቁት ፥ «በማንም ላይ ግፍ አትሥሩ፥ ማንንም በሐሰት አትክሰሱ ፥ ደመወዛችሁም ይብቃችሁ » አላቸው ።

፫ ፤ የንስሐ ጥምቀት ።

ሉቃ. ፫ ፥ ፫—፮ ፥ ፲፯ ፤ ማቴ. ፫ ፥ ፮ ፥ ፲፩ ።

ዮሐንስ በብዙ ሌላ ምክር ይመክራቸው ነበር ፤ ሕዝቡም ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ ንስሐ ሲገቡ በዮርዳኖስ ወንዝ ያጠምቃቸው ነበር ። ሲያጠምቃቸውም፥ « እኔ በውኃ አጠመቅኋችሁ ፤ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን እርሱ በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል » እያለ ኃጢአትን የሚያስተሠርየውን የክርስቶስን መምጣት በማመልከት የምሥራችን ሰበከላቸው ።

፬ ፤ ዮሐንስ ለክርስቶስ መሰከረ ።

ሉቃ. ፫ ፥ ፲፭—፲፯ ፤ ማቴ. ፫ ፥ ፲፩ ፥ ፲፪ ።

ዮሐንስም ራሱን ሳያከብር የሚመጣውን ጌታ ክርስቶስን ሁልጊዜ እያሰበ ሕዝቡን ፥ «ከእኔ ይልቅ የሚበረታ ከእኔ በኋላ ይመጣል ፤ ተጐንብሼ የጫማውን ጠፍር መፍታት የማይገባኝ በኋላዬ ይመጣል » ብሎ በሰው ሁሉ ፊት ክርስቶስን ያልቅ ነበር ። ክርስቶስም ፥ በእውነት ንስሐ ገብተው ለሚቀበሉት መድኅን ሲሆን ፥ ለእርሱ ያልሆኑትን ፈጽሞ የሚያውቅ ቅን ፈራጅ ስለሆነ ዮሐንስ ያመኑትን ሰዎች ስንዴ ያላመኑትንም ገለባ አድርጎ ፥ «እርሱ መንሹን በእጁ ይዞ አውድማውን ፈጽሞ ያጠራል ፥ ስንዴውንም በጐተራው ይከታል ፥ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል» አላቸው ።

ዮሐንስ ይህን ሁሉ ሲያደርግ፥ ከመ



www.ethiopianorthodox.org

ወለዱ በፊት በመልአክ እንደ ተነገረለት ሁሉ ግዳጁን እየፈጸመ ብዙዎችን ወደ አምላካቸው በመመለስ የተዘጋጁትን ሕዝብ ለጌታ ያሰናዳ ነበር ።

* * *

ንስሐ ግቡ ፤ ኃጢአትም ዕንቅፋት እንዳይሆንባችሁ
ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ ። ሕዝ. ፲፰ ፥ ፴ ።

አምላክህን ለመገናኘት ተዘጋጅ ። አሞጽ ፬ ፥ ፲፪ ።

* * *


ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ዮሐንስ ምን እያለ መስበክ ጀመረ ?
፪ ፤ ንስሐ በማይገቡ ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ሲናገር በምን ዓይነት ሁለት ምሳሌዎች ገለጠ ?
፫ ፤ ዮሐንስ ፥ « ከእኔ ይልቅ የሚበረታ ከእኔ በኋላ ይመጣል » ሲል የተናገረው ስለ ማን ነው ?

ጸሎት ፤ አምላክ ሆይ ፥ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ ።
ሉቃ. ፲፰ ፥ ፲፫ ።

* « ንስሐ ግቡ » ማለት በልብ መጸጸት ኃጢአታችሁን ትታችሁ ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ ማለት ነው ።

* ፈሪሳውያን ማለት የተለዩ ማለት ነው ። እነርሱም ሰው በዕለታዊ ኑሮው ሕግን መጠበቅ ዋና ነገር ነው ፥ ሲሉ በተለይ ሕግን ተጠንቅቀው ስለ መጠበቅ ያስቡ ነበር ።
ሰዱቃውያን የቤተ መቅደስ ሥርዓትን መፈጸም ዋና ነገር ነው ፥ ይሉ ነበርና ከካህናት የሚበልጡት ሰዱቃውያን ነበሩ ።





ምዕራፍ ፳፩ ።
## ጌታችን ተጠመቀ ።
ማቴ. ፫ ፥ ፲፫—፲፯ ።

፩ ፤ ኢየሱስ ወደ ዮሐንስ መጣ ።
ማቴ. ፫ ፥ ፲፫ ፤ ዮሐ. ፩ ፥ ፴፫ ።

ኢየሱስ በናዝሬት ሲኖር ሳለ መጥምቁ ዮሐንስ ፥ « መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ » እያለ ለእስራኤል ሁሉ እንደሚሰብክ እንደሚያጠምቅም በሰማ ጊዜ ከእርሱ እንዲጠመቅ ለመሄድ ተነሣ ። እርሱ ኃጢአት የሌለበት ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ሲሆን ንስሐ መግባት አያስፈልገውም ነበር ፤ ሁልጊዜ በአባቱ በእግዚአብሔር ፈቃድ ፍጹም ነበርና ። ነገር ግን ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ለማዳን ስለ መጣ ከእነርሱ ጋር አንድ ሆኖ እንደ እነርሱ በዮሐንስ እጅ እንዲጠመቅ የተገባ መሆኑን አሰቦአል ፤ ይህ ደግሞ የአብ ፈቃድ ነበረ ።

ዮሐንስ ከቀን ወደ ቀን ወደ እርሱ የሚመጡትን ሰዎች ተቀብሎ ሲያጠምቅ ሳለ ፥ መቼ አየዋለሁ ? መቼስ ይመጣል ? እያለ የክርስቶስን መምጣት ይጠባበቅ ነበር ። ክርስቶስ ማን እንደ ነበረ ገና አላወቀውም ፤ እግዚአብሔር ግን የሚያውቅበትን ምልክት ሰጥቶ ፥ «መንፈስ ሲወርድበት የምታየው እርሱ ነው» ብሎት ስለ ነበር ይህ ምልክት ሲፈጸም እስኪታየው ድረስ እየተጠባበቀ ሕዝቡን ወደ ንስሐ በመጥራት ይተጋ ነበር ።

፪ ፤ ኢየሱስ ተጠመቀ ።
ማቴ. ፫ ፥ ፲፫—፲፯ ፤ ሉቃ ፫ ፥ ፳፩ ፥ ፳፪ ።

ከዕለታትም አንድ ቀን ተሰብስበውለት የነበሩት ሕዝብ ከተጠመቁ በኋላ ኢየ



www.ethiopianorthodox.org

ሱስ መጣ ፤ እንዲጠመቅም ወደ ዮሐ ንስ ቀረበ ። ዮሐንስ ፥ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ምንም ገና ባያውቅ የሚናዘዘው ኃጢአት የሌለው ቅዱስ ሰው መሆኑን አስተውሎ ተገረመ ፤ እንዳይጠመቅ ሊከ ለክለውም በማሰብ ፥ «እኔ በአንተ ልጠ መቅ ያስፈልገኛል ፤ አንተ ወደ እኔ ትመ ጣለህን ? » አለው ።

ኢየሱስም ፥ «አሁንስ ፍቀድልኝ ፤ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባና ልና » ባለው ጊዜ ፈቀደለት ፤ አጠመቀ ውም ።

ከተጠመቀም በኋላ ኢየሱስ ወዲ ያው ከውኃው ወጣ ፤ ሲጸልይ ሳለም ሰማ ያት ተከፈቱ ፤ መንፈስ ቅዱስም እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ ፤ ከሰማይም ፥ «የምወድህ ልጄ አንተ ነህ ፥ በአንተ ደስ ይለኛል » የሚል ድምፅ መጣ ።

እንደዚሁም ኢየሱስ ራሱን ሳያከ ብር ለአብ ፈቃድ ታዝዞ በዮሐንስ እጅ በተጠመቀ ጊዜ ከተከፈተ ሰማይ በመጣ በአብ ድምፅ ተመሰከረለት ።

፫ ፤ የዮሐንስ ምስክርነት ።

ዮሐ. ፩ ፥ ፴፪ ፤ ፫ ፥ ፴ ፤ ፩ ፥ ፴፩ ።

ዮሐንስ ርግብ እንደሚወርድ መንፈስ ከሰማይ በኢየሱስ ላይ ሲወርድና ሲኖር ባየ ጊዜ የተነገረውን ምልክት በማ ስታወስ ፥ «ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ፤ ይህ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ ነው » እያለ መሰከረለት ። መንገዱን በፊቱ እንዲያሰናዳ ስለ እርሱ የተላከለት እነሆ ሰማያዊው ንጉሥ ራሱ መጥቶ ተገ ለጠ ። እርሱንም ማላቅ የዮሐንስ ደስታ ነበረ ። «እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ» ሲል ለእስራኤል ሁሉ የመዳንን መንገድ እያ ሳየ የሚነድና የሚያበራ መብራት ሆኖላ ቸው በምስክርነቱ ጸና ።

* * *

የምወድህ ልጄ አንተ ነህ ፥ በአንተ ደስ ይለኛል
የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ ። ሉቃ. ፫ ፥ ፳፪ ።

በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው ፤ በልጁ
የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቊጣ በእርሱ ላይ
ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም ። ዮሐ. ፫ ፥ ፴፮ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ስለ ዮሐንስ ስብከት በሰማ ጊዜ ኢየሱስ ምን አደረገ ?
፪ ፤ ዮሐንስ እንዳይጠመቅ ሊከለክለው ባሰበ ጊዜ ኢየሱስ
ምን አለው ?
፫ ፤ ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ ምን ሆነ ?

ጸሎት ፤ አምላኬ ንጉሤ ሆይ ፥ ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ ፤
ስምህንም ለዘላለም ዓለምም እባርካለሁ ።
በየቀኑ ሁሉ እባርክሃለሁ ።
መዝ. ፻፵፬ (፻፵፭) ፥ ፩ ፥ ፪ ።



ምዕራፍ ፳፱ ።
ጌታችን ተፈተነ ።
ማቴ. ፬ ፥ ፩—፲፩ ።



፩ ፤ ከዮርዳኖስ ወደ ምድረ በዳ ።

ማቴ. ፬ ፥ ፩ ፥ ፪ ፤ ሉቃ. ፬ ፥ ፩ ፥ ፪ ፤ ማር. ፩ ፥ ፲፫ ።

ከጥምቀቱ በኋላ ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ ተመልቶበት ከዮርዳኖስ ሲመለስ ከዲያብሎስ እንዲፈተን መንፈስ ወደ ምድረ በዳ አወጣው ። በዮርዳኖስ ዳር ከዮሐንስ ጋር ሲሆን ከተከፈተ ሰማይ የመጣው የአብ ድምፅ ተሰምቶ ፥ «የም ወድህ ልጄ አንተ ነህ » ሲል መጣለት ። አሁን ግን በሚያስፈራ ምድረ በዳ ከአራ ዊት ጋር ሲሆን ዲያብሎስ ቀርቦ ፈተ ነው ። ዲያብሎስም የፈለገው ኢየሱስ ለአባቱ ለእግዚአብሔር ሳይሆን ለእርሱ ለፈታኙ በመታዘዝ እንደ መጀመሪያው ሰው እንደ አዳም እንዲወድቅ ነበረ ። አዳም እየበላ እየጠጣም በተድላ ገነት ሲኖር በአንድ ቀን ፈተና ተሸንፎ ወድቆ ነበር ፤ ኢየሱስ ግን እየተፈተነ ዐርባ ቀንና ዐርባ ሌሊት ሳይበላ በምድረ በዳ ሲሰነብት ለአብ በመታዘዙ ጸና ። ዐርባ ቀንም ከጦመ በኋላ ተራበ ፤ ዲያብሎስም ፈተናውን ይቀጥል ነበር ።

፪ ፤ «ድንጋዩን እንጀራ አድርግ» ።

ማቴ. ፬ ፥ ፫ ፥ ፬ ።

ኢየሱስ ሲራብ ሳለም ፈታኙ ፥ « የእግዚ አብሔር ልጅ ከሆንህ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል » አለው ።

ኢየሱስም ፥ በጥንት ዘመን ለእስራ ኤል ሕዝብ የተነገረውን ቃል አስቦ ፥ «ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ በሕይወት አይ ኖርም ተብሎ ተጽፎአል» ሲል ከእግዚአ ብሔር ቃል በመጥቀስ ፈተናውን ተቋ ቋመ ። ዘዳግ. ፰ ፥ ፫ ።

፫ ፤ « ራስህን ወርውር ። »

ማቴ. ፬ ፥ ፭—፯ ።

ከዚህም በኋላ ዲያብሎስ ወደ ቅድስት ከተማ ወደ ኢየሩሳሌም ወሰደው ፤ በዚ



www.ethiopianorthodox.org

ያም ከቤተ መቅደስ ጫፍ ላይ አቁሞ ፥ «መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል እግርህ ንም በድንጋይ ከቶ እንዳትሰናከል በእጃ ቸው ያነሡሃል ተብሎ ተጽፎአልና የእግ ዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ ወደ ታች ራስ ህን ወርውር » ሲል ፥ እርሱ ራሱ በተ ራው ከእግዚአብሔር ቃል በመጥቀስ ኢየሱስን ሊያታልለው አሰበ ።

ኢየሱስ ግን ባልታዘዘው ነገር እግ ዚአብሔርን ለመፈታተን እንደማይገባ እንደዚሁም ያልታዘዘውን ድንቅ ነገር በማድረግ ሕዝቡን ለማስደነቅ ሳይሆን በትሕትና እንዲያገለግል መጥቶ እንደ ነበረ ዐወቀ ። እንደገናም ከእግዚአብሔር ቃል በመጥቀስ ፥ «ጌታን አምላክህን አት ፈታተነው ተብሎ ደግሞ ተጽፎአል» ብሎ ፈተናውን ተቋቋመ ። ዘዳግ. ፮ ፥ ፲፮ ።

፬ ፤ « ስገድልኝ ። » ማቴ. ፬ ፥ ፰—፲፩ ።

ከዚያም በኋላ ዲያብሎስ እጅግ ረጅም ወደ ሆነው ተራራ ወሰደው ፥ የዓለም ንም መንግሥታት ክብራቸውንም አሳ ይቶ ፥ «ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ » አለው ።

ኢየሱስ ግን ነፍሱን ስለ ኃጢአት በመሠዋት የሰይጣንን ሥልጣን ሽሮ ሰውን ለማዳን መጥቶ ነበረና ወደ ሥቃ ይና ሞት ከሚወስደው ፥ እግዚአብሔር አብ ራሱ ከሚመራበት መንገድ ፈቀቅ አላለም ። ያን ጊዜም ፥ «ሂድ አንተ ሰይ ጣን ፤ ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱ ንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአል » አለው ። ያን ጊዜ ዲያብሎስ ተወው ፤ እነሆም መላእክት ቀርበው ያገለግሉት ነበር ። ዘዳግ. ፮ ፥ ፲፫ ።

* * *

ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ።
ማቴ. ፬ ፥ ፲ ።

ለእግዚአብሔር ተገዙ ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል ፤ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል ። ያዕ. ፬ ፥ ፯ ፥ ፰ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ኢየሱስ በምድረ በዳ እየተፈተነ ስንት ቀን ጾመ ?
፪ ፤ ከዚህም በኋላ ሰይጣን በምን ሦስት ልዩ ፈተና ፈተነው ?
፫ ፤ ኢየሱስ ፈተናውን የተቋቋመበት ምን በማድረግ ነበረ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፥ አንተን እንዳልበድል
ቃልህን በልቤ ሰወርሁ ። . . .
እርዳኝ እድናለሁም ፥
ሁልጊዜም ሥርዓትህን እመረምራለሁ ።
መዝ. ፻፲፰ (፻፲፱) ፥ ፲፩ ፥ ፻፲፯ ።





ምዕራፍ ፳፫ ።

## የሥራው አጀማመር ።

ዮሐ. ፩ ፥ ፳፱—፪ ፥ ፲፩ ።

፩ ፤ የዮሐንስ ምስክርነት ።
ዮሐ. ፩ ፥ ፳፱—፴፬ ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰይጣንን ፈተና ሁሉ ካሸነፈ በኋላ ከምድረ በዳ ተመልሶ ዮሐንስ ወደሚያጠምቅበት ቦታ እንደገና መጣ ። ዮሐንስም ባየው ጊዜ ፥ «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» ብሎ መሰከረለት ።

፪ ፤ እንድርያስና ስምዖን ጴጥሮስ ።
ዮሐ. ፩ ፥ ፴፭—፵፫ ።

በማግሥቱም ደግሞ ዮሐንስ ከሁለት ደቀ መዛሙርቱ ጋር ቆሞ ሳለ ኢየሱ ስን አየ ፤ ትኵር ብሎም በመመልከት ፥ « እነሆ የእግዚአብሔር በግ » አለ ።

ከእርሱ ጋር የነበሩ ሁለት ደቀ መዛ ሙርቱም ይህን በሰሙ ጊዜ ኢየሱስን ተከተሉ ። ኢየሱስም ዘወር ብሎ አይቶ ፥ «ምን ትፈልጋላችሁ ? » አላቸው ። እነር ሱም ፥ «መምህር ሆይ ፥ ወዴት ትኖራ ለህ ? » አሉት ። ኢየሱስም ፥ «መጥታ ችሁ እዩ » አላቸው ። በደስታም ወደ ኢየ ሱስ መጡና በእርሱ ዘንድ ዋሉ ።

ከሁለቱም አንዱ እንድርያስ የሚ ባል ዓሣ አጥማጅ ነበረ ። እርሱም ወዲ ያውኑ ስምዖን የተባለ ወንድሙን ፈለ ገና ፥ «ክርስቶስን አግኝተናል» ብሎ ወደ ኢየሱስ አመጣው ። ኢየሱስም ስምዖንን



www.ethiopianorthodox.org

ተመልክቶ ፥ «አንተ የዮና ልጅ ስምዖን ነህ ፤ ጴጥሮስ ትባላለህ » አለው ። ጴጥሮስ ማለት ድንጋይ ማለት ነው ።

፫ ፤ ፊልጶስና ናትናኤል ።

የሐ. ፩ ፥ ፵፫—፶፩ ፤ ፳፩ ፥ ፪ ።

በማግሥቱም ኢየሱስ ወደ ገሊላ ሊወጣ ወደደ ፤ በዚህን ጊዜ ፊልጶስ የተባለውን ሰው አግኝቶ ፥ « ተከተለኝ » አለው ። ይህም ፊልጶስ እንድርያስና ስምዖን ከተወለዱበት ከተማ ነበረ ፤ ኢየሱስንም ተከተለው ። እርሱም በተራው ናትናኤል የሚባለውን ሰው አግኝቶ ፥ «ሙሴና ነቢያት ስለ እርሱ የጻፉለትን ክርስቶስን አግኝተናል ፤ እርሱ የናዝሬቱ ኢየሱስ የዮሴፍ ልጅ ነው» አለው ። ናትናኤልም ፥ « ከናዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ ይችላል ? » ብሎ ተጠራጠረ ። ፊልጶስም ፥ « መጥተህ እይ » አለው ።

ናትናኤልም ወደ ኢየሱስ መጣ ። ኢየሱስም ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ ፥ «ተንኰል የሌለበት በእውነት የእስራኤል ሰው እነሆ » አለ ። ናትናኤልም ተገርሞ ፥ «ከወዴት ታውቀኛለህ ? » አለው። ኢየሱስም ፥ «ፊልጶስ ሳይጠራህ ፥ ከበለስ በታች ሳለህ አየሁህ » አለው ። ናትናኤልም መልሶ ፥ « መምህር ሆይ ፥ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ፤ አንተ የእስራኤል ንጉሥ ነህ » አለው ። ኢየሱስም፥ « ከበለስ በታች አየሁህ ስላልሁህ አመንህን ? ከዚህ የሚበልጥ ነገር ታያለህ » አለው ። በዚያን ጊዜም ፥ «እውነት እውነት እላችኋለሁ ፥ ሰማይ ሲከፈት የእግዚአብሔርም መላእክት በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወርዱ ታያላችሁ » አላቸው።

፬ ፤ የቃና ዘገሊላ ሠርግ ።

የሐ. ፪ ፥ ፩—፲፩ ።

ጌታችን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ገሊላ ደርሶ ቃና ወደሚባለው ወደ ናትናኤል ከተማ ገባ ። ቃና ከናዝሬት የራቀ አል ነበረምና የኢየሱስ እናት በቃና ወደ ነበረው ሠርግ ተጠርታ ነበር ። ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱም ወደ ሠርጉ ታደሙ ።

ሠርገኞቹም ሲበሉና ሲጠጡ የወይን ጠጅ አለቀ ። የኢየሱስም እናት ፥ «የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም» አለችው። ኢየሱስም ፥ «አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም» አላት ። እናቱም ለአገልጋዮቹ ፥ «የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ » አለቻቸው ።

እንደ አይሁድም ደንብ ይደረግ ለነበረው ለማንጻት ልማድ ብዙ ውኃ ስለሚያሻ ስድስት የድንጋይ ጋኖች በዚያ ተቀምጠው ነበር ። ኢየሱስም ፥ «ጋኖቹን ውኃ ሙሉአቸው » አላቸው ፤ እስከ አፉቸውም ሞሉአቸው ። ኢየሱስም ፥ «አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው ስጡት» አላቸው ። ከአገልጋዮቹም አንዱ ለአሳዳሪው ሰጠ ። አሳዳሪውም ፥ ወደ ወይን ጠጅ የተለወጠውን ውኃ በቀመሰ ጊዜ ሙሽራውን ጠርቶ ፥ «ሰው ሁሉ አስቀድሞ መልካሙን የወይን ጠጅ ያቀርባል፥ ከሰከሩም በኋላ መናኛውን ፤ አንተስ መልካሙን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቈይተሃል » አለው ።

አሳዳሪውም በቀመሰው የወይን ጠጅ ምንም ቢደነቅ ከወዴት እንደ መጣ አላወቀም ። ከወዴት እንደ መጣ ያወቁት



ለኢየሱስ በመታዘዝ ውኃውን የቀዱ አገልጋዮች ናቸው ። በቅርብ ጊዜ ወደ ኢየሱስ የመጡት ደቀ መዛሙርት ፥ ክብሩን የገለጠበትን የመጀመሪያ ምልክት አይተው በእርሱ አመኑ ።

* * *

እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ።

የሐ. ፩ ፥ ፳፱ ።

ኢየሱስ እንዲህ አላቸው ፥ . . . ወደ እኔ የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም ።


የሐ. ፮ ፥ ፴፯ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ እንድርያስ ኢየሱስን ካገኘ በኋላ ምን አደረገ ?
፪ ፤ ኢየሱስ ናትናኤልን ወደ እርሱ ሲመጣ ባየው ጊዜ ምን ብሎ መሰከረለት ?
፫ ፤ ኢየሱስ መጀመሪያ ያደረገው ተአምር ምን ነበረ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፥ አንተ የመድኃኒቴ አምላክ ነህና በእውነትህ ምራኝ ፥ አስተምረኝም ።

መዝ. ፳፬ (፳፭) ፥ ፭ ።



ምዕራፍ ፳፬ ።

# የአንድ ሰንበት ቀን ሥራ ።

ማር. ፩ ፡ ፳፩—፴፱ ።

## ፩ ፤ ጌታችን በገሊላ ስብከቱን ጀመረ ።

ማር. ፩ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ።

ኢየሱስ በገሊላ እየዞረ ፥ « ዘመኑ ተፈጸመ ፤ የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች ፤ ንስሐ ግቡ፤በወንጌልም* እመኑ» እያለ የመዳንን የምሥራች ይሰብክ ጀመር ። ዝናውም በአገሩ ሁሉ ወጣ ።

## ፪ ፤ በቅፍርናሆም ምኵራብ ።

ማር. ፩ ፡ ፳፩—፳፰ ፤ ሉቃ. ፬ ፡ ፴፩—፴፯ ።

ኢየሱስ ቅፍርናሆም ወደሚባል ስምዖንና እንድርያስ ወደሚኖሩበት ከተማ መጣ ፤ በሰንበትም የከተማይቱ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ወደሚሰሙበት ምኵራብ ገብቶ አስተማራቸው ። ትምህርቱንም የሰሙ ሁሉ በጣም ተደነቁ ፤ እንደ እርሱ የእግዚአብሔርን ቃል በሥልጣን የሚያስተምር ከቶ አልሰሙም ነበርና ።

በዚያን ዕለት ወደ ምኵራቡ የገባ ርኵስ መንፈስ ያደረበት ሰው ነበረ። እርሱም ፥ «ተው ፥ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ ፤ ከአንተ ጋር ምን አለኝ? ልታጠፋን መጣህን ? ማን እንደ ሆንህ አውቄሃለሁ፤ አንተ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነህ » ብሎ ጮኸ። ኢየሱስም፥ «ዝም በል፤ከእርሱም ውጣ» ብሎ ጋኔኑን ገሠፀው ። ጋኔኑም ያደረበትን ሰው ጥሎት ሳይጐዳው ከእርሱ ወጣ።

ይህን ሁኔታ ያዩትም ሁሉ በጣም አደነቁ ፤ እርስ በርሳቸውም ፥ «ይህ ቃል ምንድር ነው ? በሥልጣንና በኃይል ርኩሳን መናፍስትን ያዝዛልና እነርሱም ይታዘዙለታል » ብለው ተነጋገሩ ።



## ፫ ፤ በስምዖን ቤት ።

ማር. ፩ ፡ ፳፱—፴፩ ፤ ሉቃ. ፬ ፡ ፴፰ ፡ ፴፱ ።

ኢየሱስም ከምኵራብ በወጣ ጊዜ ወደ ስምዖን ቤት ገባ ። ስምዖንም ሚስት ነበረችው ፤ የሚስቱም እናት በብርቱ ንዳድ ታማ ነበር ። ኢየሱስም ወደ ቤት በገባ ጊዜ ስለ እርስዋ ነግረው ለመኑት። እርሱም በአጠገብዋ ቆሞ እጅዋን ያዘ ፥ ንዳዱንም ገሥፆ አስነሣት ። ወዲያውኑም ንዳዱ ለቀቃት ፥ ያን ጊዜውንም ተነሥታ አገለገለቻቸው ።

## ፬ ፤ በማታ ።

ማር. ፩ ፡ ፴፪—፴፬ ፤ ሉቃ. ፬ ፡ ፵ ፡ ፵፩ ።

የኢየሱስም ዝና በከተማይቱ በጣም ተስፋፋ ። በዚያን ዕለት ፀሐይ ስትጠልቅ በልዩ ልዩ ደዌ የተያዙ በሽተኞችን ሁሉ ወደ እርሱ አመጡአቸው ፤ የከተማይቱ ሰዎችም ሁሉ በቤቱ ደጅ ተሰበሰቡ ። እርሱም በእያንዳንዳቸው ላይ እጁን እየጫነ ፈወሳቸው ፤ አጋንንትንም ከብዙዎች አወጣ ። አጋንንቱም ዐውቀውት ፥ «አንተ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ » እያሉ ይጮኹ ስለ ነበር እንዲናገሩ አልፈቀደላቸውም ። በዚያን ሌሊት በብዙ ሕመምና ኀዘን የተሰበሰቡ ሰዎች በደስታ ወደየቤታቸው ተመለሱ ።

## ፭ ፤ በማለዳ ።

ማር. ፩ ፡ ፴፭—፴፱ ፤ ሉቃ ፬ ፡ ፵፪—፵፬ ።

ሌሊቱ አልፎ ቀኑ ሳይጠባ መለድ ብሎ ኢየሱስ ተነሣና ወደ ምድረ በዳ ለመጸለይ ሄደ ። ስምዖንና ከእርሱ ጋር የነበሩትም ገሥግሠው ተከተሉት ፥ ባገኙትም ጊዜ ፥ «ሁሉ ይፈልጉሃል» አሉት ። እርሱም ፥ «ለሌሎች ከተማዎች ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥራች ልሰብክ ይገባኛል» አላቸው ። በገሊላም ምኵራቦች እየዞረ ይሰብክና አጋንንትን ያወጣ ነበር ።

* * *

በጨለማ የሄደ ሕዝብ ብርሃን አየ ፤ በሞት ጥላ አገርም ለኖሩ ብርሃን ወጣላቸው ።
ኢሳ. ፱ ፡ ፪ ። (ማቴ. ፬ ፡ ፲፬—፲፯ ።)

ኢየሱስ አለ ፥ እናንተ ደካሞች ፥ ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ ።
ማቴ. ፲፩ ፡ ፳፰ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ኢየሱስ እየዞረ ምን ብሎ መስበክ ጀመረ?
፪ ፤ ኢየሱስ ጋኔኑን በገሠጸው ጊዜ ምን ብሎ አዘዘው?
፫ ፤ በስምዖን ጴጥሮስ ቤት ማንን ፈወሰ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፥ ዓይኖቼን ክፈት ፥
ከሕግህም ተአምራትህን አያለሁ ።
መዝ. ፻፲፰ (፻፲፱) ፡ ፲፰ ።

* «ወንጌል» ማለት «የምሥራች» ማለት ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፳፭ ።

# ኢየሱስ ኃጢአትን ያስተሠርያል ።

ማር. ፪ ፥ ፩—፲፪ ፤ ሉቃ. ፯ ፥ ፴፮—፶ ።

### ፩ ፤ የሽባው መዳን ።

ማር. ፪ ፥ ፩—፲፪ ፤ ሉቃ. ፭ ፥ ፲፯—፳፮ ።

ኢየሱስ ወደ ቅፍርናሆም በተመለሰ ጊዜ በቤት እንዳለ ዝናው ተሰማ ። ቤቱ ጠቦ ደጁ እስኪጨናቅም ድረስ ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ ፤ ቃሉንም ያስተምራቸው ነበር ። ከዚያች ከተማ ሰዎች ሌላ ከልዩ ልዩ መንደርና ከተማ እንዲሁም ከኢየሩሳሌም የመጡ ጻፎች የተባሉ የሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን ተቀምጠው ይሰሙት ነበር ።

ቤቱና ደጁም በሰው ብዛት ተጨንቆ ሳለ አራት ሰዎች አንድ ሽባ በአልጋ ላይ ተሸክመው አመጡ ። ወደ ኢየሱስም በደጃፉ በኩል ሊያገቡት ባልቻሉ ጊዜ ወደ ቤቱ ጣራ ወጡና የጣራውን ጡብ አንሥተው ከነአልጋው አውርደው በሕዝብ ሁሉ መካከል በኢየሱስ እግር አጠገብ አኖሩት ።

ኢየሱስም ያደረጉትን ባየ ጊዜ እምነታቸውን አስተዋለ ፤ ሽባውንም ፥ «አይዞህ ፥ ኃጢአትህ ተሠረየችልህ» አለው ።

ጻፎችና ፈሪሳውያንም ይህን በሰሙ ጊዜ ፥ «ይህ የሚሳደብ ማን ነው ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ኃጢአት ሊያስተሠርይ ማን ይችላል ? » ብለው በልባቸው ያስቡ ጀመር ። ኢየሱስም የልባቸውን አሳብ ዐውቆ ፥ « በልባችሁ ይህን ስለ ምን ታስባላችሁ ? ኃጢአትህ ተሠረየችልህ ከማለት ወይስ ፥ ተነሣና ሂድ ከማለት ማናቸው ይቀላል ? ነገር ግን በምድር ላይ ኃጢአት ሊያስተሠርይ ለሰው ልጅ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ ፥ አንተ ተነሣ ፥ አልጋህንም ተሸከመህ ወደ ቤትህ ሂድ እልሃለሁ » አለው ።

በዚያን ጊዜም ሽባ የነበረው ሰው በሰዎች መካከል ተነሣ ፥ ተኝቶበት የነበረውንም አልጋ ተሸከመና እግዚአብሔርን እያመሰገነ ወደ ቤቱ ሄደ ። ይህንም ያዩት ሁሉ ተገረሙ ፤ እግዚአብሔርንም አመስግነው ፥ «ዛሬስ ድንቅ ነገር አየን» እያሉ ፍርሃት ሞላባቸው ።

### ፪ ፤ የአንዲት ሴት እምነት ።

ሉቃ. ፯ ፥ ፴፮—፶ ።

ስምዖን የተባለ አንድ ፈሪሳዊ ኢየሱስ ወደ ቤቱ ገብቶ ምግብ እንዲበላ ለመነው ። ኢየሱስም ወደ ቤቱ ገብቶ በማዕድ ተቀመጠ ።

በዚያችም ከተማ በኃጢአተኝነት የታወቀች ሴት ነበረች ። እርስዋም ኢየሱስ በፈሪሳዊው በስምዖን ቤት እንደ ገባ ባወቀች ጊዜ ሽቱ የሞላበት የአልባስጥሮስ ብልቃጥ አምጥታ በስተኋላውም በእግሩ አጠገብ ቁማ እያለቀሰች በእንባዋ እግሩን ታርስ ፥ በራስ ጠጉርዋም ታብሰው ሽቱም ትቀባው ነበረች ።

ፈሪሳዊውም ፥ ይህ ሰው ነቢይ ቢሆን ይህች የምትዳስሰው ሴት ኃጢአተኛ እንደ ሆነች ባወቀ ነበር ብሎ በልቡ ሲያስብ ሳለ ኢየሱስ ፥ «ስምዖን ሆይ ፥ የምነግርህ ነገር አለኝ» አለው ። እርሱም ፥ «መምህር ሆይ ተናገር » አለው ።

ኢየሱስም ፥ «ለአንድ አበዳሪ ሁለት ተበዳሪዎች ነበሩት ፤ በአንዱ አምስት መቶ ዲናር ነበረበት በሁለተኛውም







www.ethiopianorthodox.org

አምሳ ። የሚከፍሉትም ቢያጡ የሁለቱ ንም ተወላቸው ። እንግዲህ ከእነርሱ አብ ልጦ የሚወደው ማንኛው ነው ?» ብሎ ጠየቀው ። ስምዖንም መልሶ ፤ «ብዙ የተ ወለቱ ፤ አምስት መቶ ዲናር የነበረበቱ ይመስለኛል » አለ ።

ኢየሱስም ፤ «በእውነት ፈረድህ» አለው ፤ ወደ ሴቲቱም ዘወር ብሎ ፤ «ስም ዖን ሆይ ፤ ይህችን ሴት ታያለህን ? እኔ ወደ ቤትህ በገባሁ ጊዜ ውኃ እንኳ ለእ ግሬ አላቀረብህልኝም ፤ እርስዋ ግን በእ ንባዋ እግሬን አራሰችኝ በጠጕርዋም አበ ሰችኝ ። አንተ አልሳምኸኝም ፤ እርስዋ ግን ከገባሁ ጀምራ እግሬን ከመሳም አላ ቋረጠችም ። አንተ ራሴን ዘይት አልቀባ ኸኝም ፤ እርስዋ ግን እግሬን ሽቱ ቀባ ችኝ ። ስለዚህ እልሃለሁ ፤ ብዙ የሆነው ኃጢአትዋ እንደ ተሠረየላት እጅግ በመ ውደድዋ ይታወቃል ፤ ጥቂት ግን የሚሠ ረይለት ጥቂት ይወዳል» አለው ።

በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ሴቲቱን ፤ «ኃጢአትሽ ተሠርዮልሻል » አላት ። ከእ ርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጠው የነበሩት በልባቸው ፤ «ኃጢአትን እንኳ የሚያስተ ሠርይ ይህ ማን ነው ?» ይሉ ጀመር። ኢየ ሱስም ሴቲቱን ፤ «እምነትሽ አድኖሻል በሰላም ሂጂ » አላት ።

* * *

ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን ፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም ። በኃጢአታችን ብን ናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው ። ፩ ዮሐ. ፩ ፣ ፰ ፣ ፱ ።

ልጆች ሆይ ፤ ኃጢአታችሁ ስለ ስሙ ተሠርዮላች ኋል ። ፩ ዮሐ. ፪ ፣ ፲፪ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ አራቱ ሰዎች ሽባውን ወደ ኢየሱስ ያቀረቡት ምን በማ ድረግ ነበረ ?

፪ ፤ ኢየሱስ ሽባውን ባየው ጊዜ ምን አለው ?

፫ ፤ ኢየሱስ ፣ ተነሣ ባለው ጊዜ ሽባው ምን አደረገ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፤ በደልን ይቅር የሚል ፤ . . .


እንደ አንተ ያለ አምላክ ማን ነው ?

አቤቱ ፣ ኃጢአቴ እጅግ ነውና

ስለ ስምህ ይቅር በለኝ ።

ሚክያስ ፯ ፣ ፲፰ ፤ መዝ. ፳፬ (፳፭) ፣ ፲፩ ።





ምዕራፍ ፳፮ ።

## የሐዋርያት መመረጥ ።

ሉቃ. ፭ ፣ ፩—፲፩ ፣ ፳፯—፴፪ ፤ ፯ ፣ ፲፱—፲፯ ።

፩ ፤ አራት ዓሣ አጥማጆች ።

ሉቃ. ፭ ፣ ፩—፲፩ ።

ከዕለታት አንድ ቀን ኢየሱስ ጌንሳሬጥ በሚባል በገሊላ ባሕር አጠገብ ለተሰበ ሰበው ሕዝብ የእግዚአብሔርን ቃል ያስተምር ነበር ። በባሕሩ ዳርም ሁለት ጀልባዎች ነበሩ ፤ አንዱ ጀልባ የስምዖን ጴጥሮስ ሲሆን ሁለተኛው የዘብዴዎስና የልጆቹ ነበረ ፤ ልጆቹም ያዕቆብና ዮሐ ንስ ይባሉ ነበር ። እነዚህም ዓሣ አጥማ ጆች ከጀልባዎቻቸው ወጥተው መረቦቻቸ ውን ያጥቡ ነበር ።

ወደ ኢየሱስ የተሰበሰበው ሕዝብ ከብዛቱ የተነሣ ባጨናቀውና ባጣበበው ጊዜ የስምዖን ወደ ሆነው ጀልባ ገብቶ ፤ «ስምዖን ሆይ ፤ ከምድር ጥቂት ፈቀቅ አድርግልኝ » ብሎ ለመነው ። ስምዖንም ወዲያውኑ ወደ ጀልባው ገብቶ ከምድር ወደ ባሕር ትንሽ እልፍ አደረገው ። ኢየ ሱስም በጀልባው ተቀምጦ በባሕሩ ዳር ለተሰበሰበው ሕዝብ ቃለ እግዚአብሔ ርን አሰማ ።

ነገሩንም ሲጨርስ ስምዖንን ፤ «ወደ ጥልቁ እልፍ በል መረቦቻችሁንም ለማ



www.ethiopianorthodox.org

ጥመድ ጣሉ» አለው። ስምዖንም መልሶ፥ «አቤቱ ፣ ሌሊቱን ሁሉ ስንደክም አድ ረን ምንም አልያዝንም ፤ ነገር ግን በቃ ልህ መረቦቹን እጥላለሁ» አለ ። እንድር ያስ ደግሞ ሲረዳ ወደ ጥልቁ እልፍ አለና መረቦቹን ጣለ ፤ ይህንም ባደረገ ጊዜ እጅግ ብዙ ዓሣ ያዙ ፤ ከዓሣው ብዛትና ክብደት የተነሣም መረቦቻቸው በተቀ ደዱ ጊዜ በሌላ ጀልባ የነበሩት ጓደኞቻ ቸው ያዕቆብና ዮሐንስ እንዲረዱአቸው ጠቀሱአቸው ። እነርሱም መጡ ፤ ሁለ ቱም ጀልባዎች ለመስጠም እስኪደርሱ ድረስ ሞሉአቸው ። ባጠመዱትም የዓሣ ብዛት እጅግ ተደነቁ ።

ስምዖን ጴጥሮስ ግን የኢየሱስን ክብርና ኃይል ባየ ጊዜ በፊቱ ወድቆ ፣ «ጌታ ሆይ ፣ እኔ ኃጢአተኛ ነኝና ከእኔ ተለይ» አለው ። ኢየሱስም ፣ «አትፍራ፣ ከእንግዲህ ወዲህ ሰውን የምታጠምድ ትሆናለህ » አለው ። ጀልባዎቻቸውንም ወደ ምድር ካደረሱ በኋላ እነዚህ አራቱ ሰዎች ፣ ስምዖንና እንድርያስ ያዕቆብና ዮሐንስም ሁሉን ትተው ኢየሱስን ተከ ተሉት ።

፬ ፤ አንድ ቀራጭ ። ሉቃ. ፭ ፣ ፳፯—፴፪ ።

በሌላ ቀን ኢየሱስ በቅፍርናሆም ሳለ ሌዊ የተባለ አንድ ቀራጭ በመቅረጫው ተቀምጦ ተመለከተና ፣ « ተከተለኝ » አለው ። ሌዊም ሁሉን ትቶ ፤ ተነሥቶም ተከተለው ።

የዚያን ዘመን ቀራጮች በሮም መን ግሥት ተቀጥረው ስለ ነበር የተናቁና የተ ጠሉ ነበሩ ። የሕግ መምህራን ግን ቀራ ጮችን ብቻ ሳይሆን ተራ ሕዝብን ጭምር « ሕግን የማያውቁ ናቸው» እያሉ ይንቁ አቸውና ከእነርሱ ይለዩ ነበር ።

ሌዊ በኢየሱስ ስለ ተጠራ ተከታ ዩም ስላደረገው ደስ አለው ፤ ጓደኞቹንና ጐረቤቶቹንም ወደ ቤቱ ጠርቶ ለኢየሱስ ትልቅ ግብዣ አደረገ ። ከኢየሱስና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በማዕድ ተቀምጠው የነ በሩ ቀራጮችና ሌሎች ሰዎች ብዙ ነበሩ፤ በአንድላይም ይበሉና ይጠጡ ነበር ።

ፈሪሳውያንና ጸሐፎቻቸውም ይህን ባዩ ጊዜ ደስ አልተሰኙም ፤ በደቀ መዛ ሙርቱም ላይ ፣ «ስለምን ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር ትበላላችሁ ትጠጡ ማላችሁ ? » ብለው አንጐራጐሩ ። ኢየ ሱስም ሰምቶ ፣ «ባለ መድኃኒት የሚያስ ፈልጋቸው ሕመምተኞች ናቸው እንጂ ባለ ጤናዎች አይደሉም ፤ እኔም ኃጢአ ተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም » አላቸው ።

፫ ፤ አሥራ ሁለቱ ። ሉቃ. ፮ ፣ ፲፪—፲፯ ፤
ማር. ፫ ፣ ፲፫—፲፱ ፤ ማቴ. ፲ ፣ ፪—፬ ።

ኢየሱስም ሊጸልይ ወደ ተራራ ወጣ ፣ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጸ ልይ አደረ ። በነጋም ጊዜ ደቀ መዛሙ ርቱን ጠራ ፤ እነርሱም ቀረቡ ። ከእ ነርሱም መካከል ፣ ከእርሱ ጋር እንዲ ኖሩና ለመስበክ እንዲልካቸው አሥራ ሁለት መረጠ ፤ ለእነዚህም ድውዮችን እንዲፈውሱ አጋንንትንም እንዲያወጡ ሥልጣንን ሰጣቸው ፤ ሐዋርያትም ብሎ ሰየማቸው ። ሐዋርያ ማለትም መልእክ ተኛ ማለት ነው ።

እነዚህም ሐዋርያት የሚቀጥሉት ናቸው ፤ ጴጥሮስ ብሎ የሰየመው ስም ዖን ፣ ወንድሙም እንድርያስ ፣ የዘብዴዎ ስም ልጅ ያዕቆብ ወንድሙም ዮሐንስ ፣ ፊልጶስም በርተሎሜዎስም ፣ ማቴዎስም (እርሱም ሌዊ የተባለው ቀራጭ ነው) ፤



ቶማስም ፣ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብም ፣ ቀናተኛ የሚባለው ስምዖንም ፣ የያዕቆ ብም ወንድም ይሁዳ ፣ አሳልፎ የሰጠ ውም የአስቆሮቱ ይሁዳ ።

* * *

ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ
አልመጣሁም አላቸው ። ሉቃ. ፭ ፣ ፴፪ ።

ወደ መንግሥቱ ወደ ክብሩም ለጠራችሁ ለእግዚ
አብሔር እንደሚገባ ተመላለሱ ። ፩ ተሰ. ፪ ፣ ፲፩ ፣ ፲፪ ።


* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ስምዖን ኢየሱስን ፣ «ከእኔ ተለይ» ባለው ጊዜ ኢየሱስ ምን አለው ?

፪ ፤ ፈሪሳውያን ፣ « ስለምን ከኃጢአተኞች ጋር ትበላላችሁ» ባሉ ጊዜ ኢየሱስ ምን አላቸው ?

፫ ፤ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አራቱ ዓሣ አጥማጆች ነበሩ፤ ስማቸው ማን ማን ነው ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፣ ወደ አንተ ነፍሴን አነሣለሁ ። . . .
አቤቱ ፣ መንገድህን አመልከተኝ ፣
ፍለጋህንም አስተምረኝ ።
መዝ. ፳፬ (፳፭) ፣ ፩ ፣ ፬ ።



ምዕራፍ ፳፯ ።

## የጌታችን ተአምራት ።

ማር. ፭ ፡ ፳፩—፮ ፡ ፮ ።

### ፩ ፤ የኢያኢሮስ ልመና ።

ማር. ፭ ፡ ፳፩—፳፬ ፤ ሉቃ . ፰ ፡ ፵—፵፪ ።

ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የገሊላን ባሕር በጀልባ በመሻገር ጌርጌሴኖን የተባለውን አገር ከጐበኘ በኋላ ወደ ቅፍርናሆም ተመልሶ መጣ ። ከጀልባውም በወጣ ጊዜ ከየስፍራቸው እየተነሡ በባሕር ዳር በመሰብሰብ ይጠባበቁ የነበሩት ሕዝብ በደስታ ተቀበሉት ። ሁሉም ይቀበሉት እንጂ በተለይ አንድ ሰው በችኰላ ቀርቦ በኢየሱስ እግር ላይ ወደቀና፥ «አንዲቱ ልጄ ልትሞት ቀርባለችና እንድትድን መጥተህ እጅህን ጫንባት»በማለት አጥብቆ ለመነው ። እንዲህ ብሎም የለመነው ሰው ኢያኢሮስ የሚባል የምኵራብ አለቃ ነበረ ፤ በጭንቅ ታምማ የነበረች ልጁም የአሥራ ሁለት ዓመት ብላቴና ነበረች ። ኢየሱስም ወዲያውኑ ተነሥቶ ከኢያኢሮስ ጋር ተጓዘ ፤ ብዙ ሕዝብም ተከትሎ ያጨንቀው ነበር ።

### ፪ ፤ አንዲት በሽተኛ ሴት ።

ማር. ፭ ፡ ፳፭—፴፬ ፤ ሉቃ. ፰ ፡ ፵፫—፵፰ ።

በዚያን ጊዜ አንዲት በሽተኛ ሴት የኢየሱስን ወሬ ሰምታ ስለ ነበረች በሕዝብ መካከል መጥታ ከበስተኋላው ቀረበች ። እርስዋም ከአሥራ ሁለት ዓመት ጀምሮ ደም ይፈስሳት ነበርና ንብረትዋን ሁሉ ለባለ መድኃኒቶች በመስጠት ስትከስር ባሰባት እንጂ ምንም አልተጠቀመችም ። አሁን ግን አዲስ ተስፋ አግኝታ ፥ «ልብሱን ብቻ የዳሰስሁ እንደ ሆነ እድናለሁ » አለች ። እንዲህም ብላ በተስፋና በእምነት እየቀረበች በስተኋላው ተጠግታ የልብሱን ጫፍ ዳሰሰች ። ወዲያውኑም ከሥቃይዋ እንደዳነች በሰውነትዋ ዐወቀች ። ደስም ብሎአት በድብቅ እንደ ቀረበች ሳታስታውቅ ወደ ቤትዋ ለመመለስ አሰበች ።

ኢየሱስ ግን በሕዝብ መካከል ዘወር ብሎ ፥ «ልብሴን የዳሰሰ ማን ነው?» ሲል ጠየቀ ። ሁሉም በካዱ ጊዜ ጴጥሮስና ከእርሱ ጋር የነበሩት ፥ «አቤቱ ፥ ሕዝቡ ሲያጨንቁህና ሲያጋፉህ እያየህ ማን ዳሰሰኝ ትላለህን ? » አሉት ። እርሱም ፥ «አንድ ሰው ዳሰሰኝል ፥ ኃይል ከእኔ እንደ ወጣ እኔ ዐውቃለሁ » በማለት የዳሰሰችውን ለማየት ዞሮ ተመለከተ ።

ሴቲቱም እንዳልተሰወረች ባየች ጊዜ እየፈራችና እየተንቀጠቀጠች መጥታ በፊቱ ተደፋች ፤ በምን ምክንያትም እንደ ዳሰሰችው ፈጥናም እንደ ተፈወሰች በሕዝቡ ሁሉ ፊት አወራች ። እርሱም፥ «ልጄ ሆይ ፥ እምነትሽ አድኖሻል ፤ በሰላም ሂጂ ከሥቃይሽም ተፈወሺ » አላት ።

### ፫ ፤ የኢያኢሮስ ልጅ ትንሣኤ ።

ማር. ፭ ፡ ፴፭—፵፫ ፤ ሉቃ. ፰ ፡ ፵፱—፶፮ ።

ኢየሱስ ገና ለሴቲቱ ሲናገር አንድ ሰው ከኢያኢሮስ ቤት መጥቶ ፥ «ልጅህ ሞታለች ፤ ስለምን መምህሩን አሁን ታደክመዋለህ ? » አለው ። ኢየሱስ ግን የሰውየውን ንግግር ሰማና ኢያኢሮስን ፥ «አትፍራ ፥ እመን ብቻ ትድንግለች » ብሎ መንገዱን ቀጠለ ።

ወደ ቤትም በደረሱ ጊዜ ከጴጥሮስና ከያዕቆብ ከዮሐንስም በቀር ማንም ከእርሱ ጋር እንዲገባ አልፈቀደም ። በቤትም ብዙ ሰዎች ተሰብስበው ስለ ልጅቱ ያለቅሱ ዋይ ዋይም ይሉ ነበር ። ኢየሱስም ገብቶ ፥ « ስለምን ትንጫጫላችሁ ታለቅሳላችሁም ? ብላቴናይቱ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም » አላቸው ። እንደ ሞተችም ዐውቀው በጣም ሳቁበት ። እርሱ ግን ሁላቸውን አስወጥቶ የብላቴናይቱን አባትና እናት ከእርሱም ጋር የነበሩትን ሦስቱን ደቀ መዛሙርት ይዞ ወዳለችበት ገባ ። ወደ ብላቴናይቱ አልጋ ሲደርስም እጅዋን ይዞ ፥ «አንቺ ብላቴና ተነሽ እልሻለሁ » አላት ። ወዲያውኑም ነፍስዋ ተመለሰች ፤ ፈጥናም ቆመችና ተመላለሰች ። ወላጆችዋም ሲገረሙ ሳሉ ኢየሱስ ፥ « የምትበላው ስጡአት » ብሎ የሆነውን ለማንም እንዳይነግሩ አጥብቆ አዘዘ ።

### ፬ ፤ የናዝሬት ሰዎች አለማመን ።

ማር. ፮ ፡ ፩—፮ ።

ከዚያም ወጥቶ ወደ አደገባት ከተማ ወደ ናዝሬት ሄደ ፤ በሰንበትም በምኵራብ ገብቶ ያስተምር ነበር ። የሰሙትም ሰዎች፥«ይህ ጠራቢው የማርያም ልጅ የያዕቆብም የዮሳም የይሁዳም የስምዖንም





www.ethiopianorthodox.org

ወንድም አይደለምን? እኅቶቹስ በዚህ በእኛ ዘንድ አይደሉምን ? » ብለው በት ምህርቱ ተገረሙ ። እነርሱም ፤ «እነዚ ህን ነገሮች ከወዴት አገኛቸው ? ለእርሱ የተሰጠው ጥበብ ምንድር ነው ? በእጁም የሚደረጉ እንደ እነዚህ ያሉ ተአምራት ምንድር ናቸው ? » ተባባሉ ።

ከአለማመናቸውም የተነሣ በዚያ ብዙ ተአምራት አላደረገም ። ስለ አለማ መናቸውም ተደነቀ ፤ በሌሎች መንደሮ ችም እያስተማረ ይዞር ነበር ።

* * *

እውነት እውነት እላችኋለሁ ፣ ቃሌን የሚሰማ የላ ከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው ፤ ከሞ ትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይ መጣም ።
ዮሐ. ፭ ፥ ፳፬ ።


ልጅን አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይ ወትን እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው ፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ ።
ዮሐ. ፮ ፥ ፵ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ኢያኢሮስ ኢየሱስን ምን ለመነው ?
፪ ፤ ኢየሱስ የልብሱን ጫፍ ለዳሰሰችው ሴት ምን አላት ?
፫ ፤ ለኢያኢሮስ ፥ «ልጅህ ሞታለች » በተባለ ጊዜ ኢየሱስ ምን አለው ?

ጸሎት ፤ አቤቱ አምላኬ፥ያደረግኸው ተአምራት ብዙ ነው ፤
አሳብህንም ምንም የሚመስለው የለም ፤
ባወራም ብናገርም ከቍጥር ሁሉ በዛ ።
መዝ. ፴፱ (፵) ፥ ፭ ።





ምዕራፍ ፳፫ ።

## ጌታችን የጸሎትን አቅድ አስተማረ ።

ሉቃ. ፲፩ ፥ ፩—፲፫ ።

፩ ፤ ኢየሱስ ጸሎትን ያዘወትር ነበር ።

ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመጣው የላ ከውን የእግዚአብሔር አብን ፈቃድ እን ዲፈጽም ነበርና ብዙ ጊዜ ከሚከብቡት ሰዎች ተለይቶ ወደ ምድረ በዳ ወይም ወደ ተራራ ላይ ይወጣና ወደ አባቱ ይጸልይ እንደ ነበረ እንብበናል ።

፪ ፤ ኢየሱስ ጸሎትን አስተማረ ።
ሉቃ. ፲፩ ፥ ፩—፬ ፤ ማቴ. ፭ ፥ ፭—፲፩ ፤ ፲፰ ፥ ፲፱ ፥ ፳ ።
ከዕለታትም አንድ ቀን ጸሎቱን ሲጨ ርስ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ ፥ « ጌታ ሆይ ፥ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን እንዳስ ተማረ እንድንጸልይ አስተምረን» አለው።

ኢየሱስም ፥ «ስትጸልዩ ፥ በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ ብላችሁ ጸልዩ» ብሎ እግዚአብሔር አብ ራሱ በልጁ የሚ ያምኑትን ሁሉ እንደሚወዳቸው አሳስቦ ወደ ሰማያዊ አባታቸው በመተማመን እየቀረቡ እንዲጸልዩ አስተማራቸው ።

ኢየሱስም ትምህርቱን ቀጥሎ ፥ ከሁሉ አስቀድሞ ሰማያዊ አባታቸው በሁሉ ዘንድ እንዲከበርና ከመንግሥቱም ክፉ እንቅፋትና ዓመፅ ፈጽሞ እንዲወ ገድ ስለሚገባ ፥ «አባታችን ሆይ ፥ ስምህ



www.ethiopianorthodox.org

ይቀደስ ፤ መንግሥትህ ትምጣ ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን ብላችሁ ጸልዩ » አላቸው ።

ከዚህም በኋላ ደግሞ ከአባታቸው የሚያስፈልገውን ነገር እንዲለምኑ ሲያስተምራቸው ፥ « የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ ፤ በደላችንን ይቅር በለን እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል ፤ ወደ ፈተናም አታግባን ከክፉ አድነን እንጂ ብላችሁ ጸልዩ » አላቸው ።

ለእግዚአብሔር አምላካችን ምስጋናን በማቅረብ ታላቅነትንና ክብርን ለእርሱ መስጠት ስለሚገባ ፥ « መንግሥት የአንተ ናትና ኃይልም ምስጋናም ለዘላለሙ ፤ አሜን ብላችሁ ጸልዩ» አላቸው ። አሜን ማለት ይደረግ ማለት ነው ።

ኢየሱስም በሌላ ቀን ደግሞ ጸሎትን ሲያስተምር ደቀ መዛሙርቱን፡ «ሳትለምኑ አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ያውቃልና ፥ በመናገራችን ብዛት ይሰማልናል እንደሚሉ ሰዎች፡ስትጸልዩ አታብዙ በከንቱም አትጩኹ» አላቸው ። ደግሞም ፥ «አንተ ስትጸልይ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ ፤ በስውር የሚያይ አባትህ በግልጥ ይከፍልሃል» ብሎ ለሰው እንዲታዩ እንደሚወዱ ግብዞች እንዳይሆኑ አስጠነቀቃቸው ። ሌላም ጊዜ፡«ከእናንተ ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ » ሲል ለየብቻችን ብቻ ሳይሆን በአንድነት ተሰብስበን በእርሱ ስም ወደ ሰማያዊ አባታችን እንድንጸልይ አስተማረን።

፫ ፤ ኢየሱስ በምሳሌ ጸሎትን አስተማረ ።
ሉቃ. ፲፩ ፥ ፭—፲፫ ፤ ማቴ. ፯ ፥ ፯—፲፩ ።

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ምሳሌ በመስል እግዚአብሔር ጸሎትን እንደሚሰማ አስተማራቸው ። በምሳሌውም አንድ ሰው በእኩለ ሌሊት ለመጣለት እንግዳ የሚያቀርብለት ምግብ ቢያጣ፥ ወደ አንድ ወዳጁ ቤት ሄዶ ፥ «ወዳጄ ሆይ ፥ ሦስት እንጀራ አበድረኝ » ብሎ ለመነው ። ጊዜው የማይመች ስለ ሆነ ወዳጁ ከቤት ውስጥ መልሶ ፥ «አታድከመኝ ፤ አሁን ደጁ ተቈልፎአል ልጆቼም ከእኔ ጋር በአልጋ ላይ አሉ ፤ ተነሥቼ ልሰጥህ አልችልም » አለው ። እንጀራ የፈለገው ሰውዬ ግን እጅግ በመነዝነዝ እየደጋገመ ልመናውን ስላቀረበ ተኝቶ የነበረው ወዳጁ ተነሥቶ እንጀራውን ሰጠው።

ኢየሱስም ፥ «ወዳጅ ስለ ሆነ ተነሥቶ ባይሰጠው እንኳ ስለ ነዘነዘው ተነሥቶ የሚፈልገውን ሁሉ ይሰጠዋል ። እኔም እላችኋለሁ ፥ ለምኑ ይሰጣችሁማል ፤ ፈልጉ ታገኙማላችሁ ፤ መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችሁማል ። የሚለምን ሁሉ ይቀበላልና ፥ የሚፈልግም ያገኛል ፥ መዝጊያውንም ለሚያንኳኳው ይከፈትለታል » አለ ።

ያ ምድራዊ ወዳጅ እንኳ ተነሥቶ ለሚለምነው ወዳጁ እንጀራ ቢሰጥ የማያንቀላፋ የማይተኛም ሰማያዊ አምላካችን እንዴት አብልጦ ለሚለምኑት አይሰጥም ?

ኢየሱስ በወዳጅ ምሳሌ ካስተማረ በኋላ በአባትና በልጅ ምሳሌም አስተማረ ። በዚህም ምሳሌ ፥ «አንድ ልጅ ከአባቱ እንጀራ ቢለምን አባቱ ድንጋይ ይሰጠዋልን ? » ብሎ ጠየቀ ። «ወይስ ልጁ ዓሣ ደግሞ ቢለምነው በዓሣ ፈንታ እባብ ይሰጠዋልን ? ወይስ እንቍላል ቢለምነው ጊንጥ ይሰጠዋል ?» ሲል ጠየቀ ። ይህን ሦስት ጥያቄ ከጠየቀ በኋላ ፥ «እንኪያስ



እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ ፥ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ፥ መልካም ነገርንም አይሰጣቸውም ?» አላቸው ።

* * *

በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ ።
ፊልጵ. ፬ ፥ ፮ ።

የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደ ጻድቃን ጆሮቹም ወደ ጩኸታቸው ናቸው ።
መዝ. ፴፫ (፴፬) ፥ ፲፭ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ጌታችን ወደ ማን እንድንጸልይ አስተማረን ?
፪ ፤ የማንስ ፈቃድ እንዲፈጸም ልንጸልይ አስተማረን ?
፫ ፤ እግዚአብሔር ለሚለምኑት መልካም ነገርን ለመስጠት እንደሚወድ በምን ምሳሌ ተገልጦልናል ?

ጸሎት ፤ አባታችን ሆይ ፥ በሰማይ የምትኖር ፥
ስምህ ይቀደስ ፤
መንግሥትህ ትምጣ ፤
ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነ እንዲሁ በምድር ይሁን ፤
የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ ፤
በደላችንን ይቅር በለን እኛም የበደሉንን
ይቅር እንደምንል ፤
ወደ ፈተናም አታግባን ከክፉ አድነን እንጂ ፤
መንግሥት የአንተ ናትና ኃይልም ምስጋናም
ለዘላለሙ ፤ አሜን ። ማቴ. ፮ ፥ ፱—፲፫ ።

ምዕራፍ ፳፱ ።

# ጌታችን ወደ ኢየሩሳሌም ሲወጣ ።

ማር. ፲ ፡ ፴፪—፵፪ ፤ ሉቃ. ፲፱ ፡ ፩—፲ ።

## ፩ ፤ ኢየሱስ ስለሞቱ ተናገረ ።

ማር. ፲ ፡ ፴፱—፵፭ ።

ኢየሱስ መልካም እያደረገ ፡ ክፉ መን
ፈስ ያደረባቸውን እየፈወሰ ፡ እያስተማ
ረም ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም በመመላ
ለስ ያለውን አገልግሎት ሁሉ ከፈጸመ
በኋላ ሕይወቱን የሚሰጥበት የመሞቻ
ጊዜው እንደ ቀረበ አውቆ ወደ ኢየሩሳ
ሌም ለመሄድ ፊቱን አቀና ። ከእርሱም
ጋር አሥራ ሁለቱ ሐዋርያትና በገንዘባ
ቸው የሚያገለግሉት ሴቶች ነበሩ ።

በመንገድም ሲሄዱ ኢየሱስ አሥራ
ሁለቱን ወደ እርሱ አቅርቦ ፡ ከዚህ በፊት
እንደነገራቸው እንደገና በግልጽ ስለሚ
ደርስበት ሥቃይና ሞት ተናግሮ ፡ «ወደ
ኢየሩሳሌም እንወጣለን ፡ ስለ ሰው ልጅም
በነቢያት የተጻፈው ሁሉ ይፈጸማል ፤
የሞት ፍርድ ይፈርዱበታል ፡ ይዘብቱበ
ትማል ፡ ይተፉበትማል ፡ ይገርፉትማል፡
ይገድሉትማል ፤ በሦስተኛውም ቀን ይነ
ሣል » አላቸው ። እነርሱ ግን ነገሩን አላ
ስተዋሉም ፤ ኢየሱስ በቅርብ ጊዜ ንጉሥ
ሆኖ በክብር እንደሚነግሥ ይመስላቸው
ስለ ነበር የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና
ዮሐንስ ፡ «መምህር ሆይ ፡ በክብርህ ጊዜ
አንዳችን በቀኝ አንዳችንም በግራህ መቀ
መጥን ስጠን » አሉት ። ኢየሱስ ግን ፡
«የምትለምኑትን አታውቁም » ብሎ ወደ
ክብሩ ሳይገባ የሥቃይ ጽዋ መጠጣት
እንደሚገባው አሳሰባቸው ።

የቀሩትም አሥሩ ሐዋርያት በያዕ
ቆብና በዮሐንስ ተቈጡ ። ኢየሱስም ወደ
እርሱ ጠርቶ እንዲህ አላቸው ፡ «በዚህ
ዓለም ሕዝቦች ላይ የሚገዙአቸው ታላ
ላቆች ሆነው በላያቸው እንደሚሠለጥኑ
ታውቃላችሁ ። በእናንተ ግን እንዲህ አይ
ደለም ፤ ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ
ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ
ይሁን ፡ ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን
የሚወድ የእናንተ ባሪያ ይሁን ። እንዲ
ሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም
ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለ
ግሉት አልመጣም » ።

## ፪ ፤ የዘኬዎስ መዳን ። ሉቃ. ፲፱ ፡ ፩—፲ ።

ኢየሱስም ሕይወቱን የሚሰጥበት ጊዜ
እንደ ቀረበ ዐውቆ ሲጓዝ ሁልጊዜ ለራሱ
ሳይራራ ሌሎችን ሊያገለግልና ሊያድን
ይወድ ነበር ።

የሚጓዝበትም መንገድ በዮርዳኖስ
አቅራቢያ በሚገኘው በኢያሪኮ ከተማ
ያልፍ ነበርና ወደ ኢያሪኮ ገባ ። በኢያሪ
ኮም ዘኬዎስ የተባለ የቀራጮች አለቃ
ባለጸጋ የሆነ ሰው ነበረ ፤ በሐሰትም ከሚ
ገባው በላይ ከሰዎች በመውሰዱ በሁሉ
ዘንድ የተጠላ ነበረ ። እርሱም የኢየሱ
ስን ዝና ቀደም ብሎ ተረድቶ ስለ ነበር
በኢያሪኮ በኩል እንደሚያልፍ በሰማ
ጊዜ ሊያየው ወደደ ።

ዘኬዎስ ግን ቁመቱ አጭር ነበረና
በሕዝብ መካከል ሲገባ ኢየሱስን ለማ
የት ባልቻለ ጊዜ ወደ ፊት ሮጠና በአንድ
ሾላ ላይ ወጣ ።

ኢየሱስም ወደዚያ ስፍራ በደረሰ
ጊዜ አሻቅቦ አየና ፡ «ዘኬዎስ ሆይ ፡ ዛሬ
በቤትህ እውል ዘንድ ይገባኛልና ፈጥነህ







www.ethiopianorthodox.org

ውረድ » አለው ። ፈጥኖም ወረደ ፤ በደ ስታም ተቀበለው ። ይህንን ያዩ ሁሉ ግን ፥ «ምነው ከኃጢአተኛ ሰው ጋር ሊውል ገባ » ብለው አንጐራጐሩ ።

ዘኬዎስም ቆሞ ጌታን ፥ « ጌታ ሆይ ፥ ካለኝ ሁሉ እኩሌታውን ለድሆች እሰጣ ለሁ ፤ ማንንም በሐሰት ከስሼ እንደሆንሁ አራት እጥፍ እመልሳለሁ » ብሎ ከፉ መንገዱን እንደሚተው አስታወቀ ። ኢየ ሱስም የዘኬዎስን ንስሐና እምነት ባየ ጊዜ ፥ «ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሆኖለታል ፤ የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና » አለ ።

፫ ፤ የበርጤሜዎስ መፈወስ ።

ማር. ፲ ፥ ፵፮—፶፪ ።

ከኢያሪኮም ሲወጣ የጤሜዎስ ልጅ በር ጤሜዎስ እየለመነ በመንገድ ዳር ተቀ ምጦ ነበር ። እርሱም ዕውር ነበረና ፥ የና ዝሬቱ ኢየሱስ መጣ የሚል ወሬ በሰማ ጊዜ ፥ « የዳዊት ልጅ ኢየሱስ ሆይ ፥ ማረኝ » እያለ ይጮኽ ጀመር ።

ብዙዎችም ሰዎች ፥ « ዝም በል ፥ ለምን ትጮኻለህ » እያሉ ገሠፁት ፤ እርሱ ግን ፥ « የዳዊት ልጅ ሆይ ፥ ማረኝ » እያለ አብዝቶ ጮኸ ።

ኢየሱስም ቆመና ፥ «ጥሩት» አለ ። በዚያን ጊዜ ሰዎቹ በርጤሜዎስን ፥ «አይ ዞህ ተነሣ ፥ ይጠራሃል » ብለው ጠሩት ። እርሱም እየዘለለ ተነሣና ልብሱን ጥሎ ወደ ኢየሱስ መጣ ። ኢየሱስም ፥ «ምን ላደርግልህ ትወዳለህ ? » አለው ። ዕው ሩም ፥ « መምህር ሆይ ፥ አይ ዘንድ » አለው ። ኢየሱስም ፥ «ሂድ ፥ እምነትህ አድኖሃል » አለው ። ወዲያውም አየ ፤ በመንገድም ተከተለው ።

* * *

የሰው ልጅ ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም ።
ማር. ፲ ፥ ፵፭ ።

የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶ አል ።
ሉቃ. ፲፱ ፥ ፲ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ኢየሱስ ስለ ሞቱ ከነገራቸው በኋላ ያዕቆብና ዮሐንስ ምን ልመና በማቅረብ አለማስተዋላቸውን አሳዩ ?
፪ ፤ ኢየሱስ ታላቅ ሊሆኑ ለሚወዱ ምን ምክር ሰጣቸው ?
፫ ፤ ኢየሱስ በኢያሪኮ ሲያልፍ ወደ ማን ቤት ገባ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፥ እንደ ጠፋ በግ ተቅበዘበዝሁ ፤ ትእዛዛትህን አልረሳሁምና ባሪያህን ፈልገው ።
መዝ. ፻፲፰ (፻፲፱) ፥ ፻፸፮ ።





ምዕራፍ ፴ ።

## ሆ ሣ ዕ ና ።

ከማቴ. ፳፩ ፤ ከማር. ፲፩ ፤ ከሉቃ. ፲፱ ።

፩ ፤ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ ።

ማቴ. ፳፩ ፥ ፩—፲፩ ፤ ማር. ፲፩ ፥ ፩—፲ ፤ ሉቃ. ፲፱ ፥ ፳፰—፵፬ ።

ከኢያሪኮ ወደ ኢየሩሳሌም በሚያወጣው መንገድ ላይ ቢታንያና ቤተ ፋጌ የሚ ባሉ መንደሮች ይገኛሉ ። ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን እየቀደመ በዚህ መን ገድ ወጣ ፤ ወደ ቤተ ፋጌም በቀረበ ጊዜ ከእነርሱ ሁለቱን ፥ «በፊታችሁ ወዳለ ችው መንደር ሂዱ ፤ ወደ እርስዋም ገብ ታችሁ ከሰው ማንም ገና ያልተቀመጠ በት ውርንጫ ታገኛላችሁ ፥ ፈትታችሁም አምጡልኝ ። ማንም ሰው ፥ ስለምን ትፈ ቱታላችሁ ብሎ ቢጠይቃችሁ ፥ ለጌታ ያስፈልገዋል በሉት » ብሎ ላካቸው ።

የተላኩትም ሁለት ደቀ መዛሙርት ሄደው ውርንጫውን በመንገድ መተላለ ፊያ በደጅ ውጭ ታስሮ አገኙት ፥ ፈቱ ትም ። በዚያም ከቆሙት አንዳንዶቹ ፥ «የምትፈቱት ምን ልታደርጉ ነው ?» አሉአቸው ። እነርሱም ፥ «ለጌታ ያስፈል ገዋል » ባሉ ጊዜ ተውአቸው ።

ውርንጫውንም ወደ ኢየሱስ አመ ጡት ፥ ልብሳቸውንም በላዩ ጣሉ ፤ እር ሱም በውርንጫው ላይ ተቀምጦ ደብረ ዘይት የሚባለውን ተራራ በማለፍ መን ገዱን ቀጠለ ። ከሕዝቡም እጅግ ብዙዎቹ በሚሄድበት መንገድ ላይ ልብሳቸውን



www.ethiopianorthodox.org

አንጠፉ ፤ ሌሎችም የዛፍ ቅጠሎችንና ቅርንጫፎችን እየቈረጡ በመንገድ ላይ ያነጥፉ ነበር ። የሚቀድሙትም የሚከተሉትም ፥ «ሆሣዕና* ለዳዊት ልጅ ፤ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው ፤ በጌታ ስም የምትመጣ የአባታችን የዳዊት መንግሥት የተባረከች ናት ፤ ሆሣዕና በአርያም » እያሉ ይጮኹ ነበር ።

ይህም ሲሆን በነቢዩ ዘካርያስ የተነገረው ቃል ተፈጸመ ፤ ነቢዩ ፥ «ለጽዮን ልጅ ፥ እነሆ ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ በአህያ ላይና በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል በሉአት » ብሎ ነበርና ። (ዘካ. ፱ ፡ ፱ ።)

ወደ ኢየሩሳሌም ቅይዩ ወደ ደብረ ዘይት ቁልቁለትም በቀረበ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሁላቸው ደስ እያላቸው ተአምራትን ሁሉ ስላዩ በታላቅ ድምፅ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ፤ «በጌታ ስም የሚመጣ ንጉሥ የተባረከ ነው ፤ በሰማይ ሰላም በአርያምም ክብር » አሉ ። በዚያን ጊዜ ከሕዝብ መካከል የሚገኙት ፈሪሳውያን ፥ «መምህር ሆይ ፥ ደቀ መዛሙርትህን ገሥፃቸው» አሉት ። እርሱም ፥ «እነዚህ ዝም ቢሉ ድንጋዮች ይጮኻሉ» አላቸው ።

ሲቀርብም ከተማይቱን አይቶ አለቀሰላት ፥ አለም ፥ «አንቺ ለሰላምሽ የሚሆነውን ዛሬ አውቀሽ ቢሆን ፤ አሁን ግን ከዓይንሽ ተሰውሯል ። ጠላቶችሽም በአንቺ ውስጥ ድንጋይ በድንጋይ ላይ የማይተዉበት ወራት ይመጣብሻል ፤ የመጐብኘትሽን ዘመን አላወቅሽምና ።»

ወደ ኢየሩሳሌምም በገባ ጊዜ መላው ከተማ ፥ « ይህ ማን ነው ? » ብሎ ተናወጠ ። ሕዝቡም ፥ «ይህ ከገሊላ ናዝሬት የመጣ ነቢይ ኢየሱስ ነው » አሉ ።

፪ ፤ ኢየሱስ ቤተ መቅደስን አነጻ ።

ማቴ. ፳፩ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ፤ ሉቃ. ፲፱ ፡ ፵፭ ፡ ፵፮ ።

ኢየሱስም ወደ ቤተ መቅደስ ገባ ፤ በዚያም ለመሥዋዕት የሚሆኑትን በሬዎችንና በጎችን ርግቦችንም የሚሸጡትንና የሚገዙትን አግኝቶ ሁሉን አወጣ ፤ የገንዘብ ለዋጮችንም ገበታዎች ገለበጠ ፤ ዕቃም ተሸክሞ ማንም በመቅደስ እንዲያልፍ አልፈቀደም ፤ አላቸውም ፥ «ቤቴ ለሕዝቦች ሁሉ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፎአል ፥ እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት ። »

፫ ፤ የልጆች ምስጋናና የመሪዎች ቅንዓት።

ማቴ. ፳፩ ፡ ፲፬—፲፯ ፤ ሉቃ. ፲፱ ፡ ፵፯ ፡ ፵፰ ።

በመቅደስም ዕውሮችና አንካሶች ወደ ኢየሱስ ቀረቡና ፈወሳቸው ። ልጆችም ተሰብስበው ፥ « ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ » እያሉ ይጮኹ ነበር ። ነገር ግን የካህናት አለቆችና ጻፎች ኢየሱስ ያደረጋቸውን ድንቆች ባዩ ጊዜ የልጆችንም ምስጋና በሰሙ ጊዜ ተቈጡና ፥ «እነዚህ የሚሉትን አትሰማምን ? » አሉት ። ኢየሱስም ፥ «እሰማለሁ ፤ ከሕፃናትና ከሚጠቡት አፍ ምስጋና ለራስህ አዘጋጀህ የሚለውን ቃል ከቶ አላነበባችሁምን?» አላቸው ።

ኢየሱስ ትቶአቸው ከኢየሩሳሌም ከተማ ወደ ቢታንያ ወጣ ፤ በዚያም አደረ ። በማግሥቱም ወደ ከተማይቱ ገብቶ በመቅደስ ሲያስተምር ሕዝቡ ሁሉ ሊሰሙት ይሰበሰቡ ነበር ። ነገር ግን የካህናት አለቆችና ጻፎች የሕዝቡ ታላላቆችም ቀንተውበት ፥ እንዴት አድርገን ልንገድለው እንችላለን እያሉ ይመካከሩበት ነበር ።



ደቀ መዛሙርቱ ሁላቸው ደስ እያላቸው ተአምራትን ሁሉ ስላዩ በታላቅ ድምፅ እግዚአብሔርን ሊያመሰግኑ ጀምረው ፥ በጌታ ስም የሚመጣ ንጉሥ የተባረከ ነው . . . አሉ ። ሉቃ. ፲፱ ፡ ፴፯ ፡ ፴፰ ።

የእርሱ ወደ ሆነው መጣ ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም ። ለተቀበሉት ሁሉ ግን ፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው ። ዮሐ. ፩ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ።

* * *


ጥያቄ ፤ ፩ ፤ «ውርንጫውን የምትፈቱት ምን ልታደርጉ ነው ? » ላሉ ሰዎች ምን መልስ ተሰጠ ?

፪ ፤ ኢየሱስ በውርንጫው ተቀምጦ ሲሄድ በደስታ የተቀበሉት ሕዝብ ምን አደረጉ ?

፫ ፤ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ የከተማው ሰዎችና አለቆች በመልካም ተቀበሉትን ?

ጸሎት ፤ አቤቱ እባክህ ፥ አሁን አድን ፤
አቤቱ እባክህ ፥ አሁን አቅና ።
አንተ አምላኬ ነህ አመሰግንሃለሁ . . .
መድኃኒትም ሆነኸኛልና አመሰግንሃለሁ ።
መዝ. ፻፲፰ (፻፲፱) ፤ ፳፭ ፡ ፳፰ ።

* በዕብራይስጥ « ሆሣዕና » የሚለው ቃል በአማርኛ « አሁን አድን » ማለት ነውና ከመዝ. ፻፲፰ (፻፲፱) ፥ ፳፭ ፡ ፳፮ የተጠቀሰ ነው ።
ይህም የመዝሙር ክፍል ከብዙ ጊዜ ጀምሮ በዓመት በዓል ጊዜ ይዘመር ስለ ነበር የመልካም አቀባበልና የደስታ መግለጫ ሆኖአል ። መዝሙሩ በትንቢት ስለ ክርስቶስ የሚናገር ነው ።



ምዕራፍ ፴፩ ።

## የጌታችን መያዝ ።

ከማቴ. ፳፮ ፡ ፳፯ ፤ ከሉቃ. ፳፪ ፡ ፳፫ ፤ ከማር. ፲፬ ።

### ፩ ፤ ጌታችን ተሸጠ ።

ማቴ. ፳፮ ፡ ፩—፭ ፡ ፲፬—፲፮ ።

ኢየሱስ የሚሞትበት በፋሲካ በዓል እንደሚሆን ዐውቆ ለደቀ መዛሙርቱ ፤ «ከሁለት ቀን በኋላ ፋሲካ ሲሆን የሰው ልጅ ሊሰቀል አልፎ ይሰጣል » አላቸው። የካህናት አለቆችና የሕዝብ ሽማግሌ ዎች በተንኰል ሊያስይዙትና ሊገድሉት እርስ በርሳቸው ሲመካከሩ ግን ፤ «ሁከት እንዳይነሣ በበዓል አይሁን » አሉ ።

እንደዚሁም ፤ እንዴት አድርገን ልንይዘው እንችላለን ? በሚል አሳብ ላይ ሆነው ሲመካከሩ ፤ ከአሥራ ሁለቱ አንዱ የአስቆሮቱ ይሁዳ ወደ እነርሱ መጣና ፤ « እኔ እርሱን አሳልፌ ብሰጣችሁ ምን ልትሰጡኝ ትወዳላችሁ ? » አላቸው ። ደስ አላቸውም ፤ ሠላሳ ብርም እንዲሰ ጡት ተስፋ አደረጉለት ። ይሁዳም እሺ ብሎ ሕዝቡ በሌለበት ቦታ ኢየሱስን አሳ ልፎ ለመስጠት ምቹ ጊዜ ይፈልግ ነበር።

### ፪ ፤ ጌታችን ከሐዋርያት ጋር ፋሲካን በላ።

ሉቃ. ፳፪ ፡ ፯—፳፫ ፤ ማቴ. ፳፮ ፡ ፳፯—፳፭ ፤ ዮሐ. ፲፫ ፡ ፳፮ ።

በበዓሉ መጀመሪያ ቀንም ኢየሱስ ጴጥ ሮስንና ዮሐንስን ፤ «ወደ ከተማ ሂዱ ፤ ማድጋ ውኃ የተሸከመ ሰው ይገናኛች ኋል ፤ ወደሚገባበትም ቤት ተከተሉት ፤ ለባለቤቱም ፤ መምህሩ ፤ ከደቀ መዛሙ ርቱ ጋር ፋሲካን የምበላበት የእንግዳ ቤት ክፍል ወዴት ነው ? ይልሃል በሉት፤ ያም በደርብ ላይ ያለውን የተነጠፈ ታላቅ አዳራሽ ያሳያችኋል ፤ በዚያም ፋሲካን እንድንበላ አዘጋጁልን » ብሎ ላካቸው ።

ሰዓቱም በደረሰ ጊዜ ከአሥራ ሁለቱ ጋር በማዕድ ተቀምጦ ሳለ ፤ «ከመከራዬ በፊት ከእናንተ ጋር ይህን ፋሲካ ልበላ እጅግ እመኝ ነበር» አላቸው ። እንጀራ ንም አንሥቶ አመስግኖ ፤ ቈርሶም ሰጣቸ ውና ፤ «ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው ፤ እንኩ ብሉ » አለ ። እንዲሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን አንሥቶ እንዲህ አለ ፤ «ሁላችሁ ከርሱ ጠጡ ፤ ስለ ብዙ ዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው ። ነገር ግን አሳ ልፎ የሚሰጠኝ ሰው እጅ እነሆ በማዕድ ከእኔ ጋር ናት ። የሰው ልጅስ እንደ ተወ ሰነው ይሄዳል፤ ነገር ግን አሳልፎ ለሚሰ ጠው ለዚያ ሰው ወዮለት » አለ ። አሳልፎ የሚሰጠው ይሁዳም መልሶ ፤ «መምህር ሆይ ፤ እኔ እሆንን ? » አለ ። «አንተ አልህ ፤ የምታደርገውን ቶሎ ብለህ አድ ርግ » አለው ። ይሁዳም ወዲያው ወደ ውጪ ወጣ ፤ ሌሊትም ነበረ ።

### ፫ ፤ ኢየሱስ በጌቴሴማኒ ተያዘ ።

ማቴ. ፳፮ ፡ ፴—፶፮ ፤ ሉቃ. ፳፪ ፡ ፶፰ ፤ ዮሐ. ፲፰ ፡ ፩ ፡ ፪ ።

የፋሲካን እራት ከበሉና መዝሙርም ከዘመሩ በኋላ ኢየሱስ ከአሥራ አንዱ ጋር ወደ ውጪ ወጣ ፤ ወደ ደብረ ዘይ ትም በሚያመራው መንገድ ሄደ ። ልባ ቸው በኀዘንና በድንጋጤ እንደ ተሞላ ዐውቆ ግና በማዕድ ተቀምጠው ሳሉ ያጽ ናናቸው እንደ ነበር አሁን ደግሞ በመን ገድ ሲሄዱ ሊያዘጋጃቸው በማሰብ ፤ «በዚ ህች ሌሊት ፤ እረኛውን እመታለሁ የመ ንጋውም በጎች ይበተናሉ የሚለው ቃን ቢት ስለሚፈጸም ሁላችሁ ተሰናክላችሁ ትተውኛላችሁ ፤ ከተነሣሁ በኋላ ግን ወደ ገሊላ እቀድማችኋለሁ በዚያም እንገናኛ ለን » ሲል የደስታ ቀጠሮ ሰጣቸው። እነ ርሱ ግን ነገሩን ሳያስተውሉ ቀሩ ።

እንደ ልማዱ በደብረ ዘይት ግርጌ ወዳለው ጌቴሴማኒ ወደሚባለው አትክ ልት ስፍራ ሄደ ። ይሁዳ ደግሞ ስፍራውን ያውቅ ነበረና ጭፍሮችን ሌሎች ሰዎች ንም አስከትሎ በችቦና በፋና ጋሻ ጦርም በመያዝ ወደዚያ መጣ ። ይሁዳም፤ «የም ስመው እርሱ ነው» ብሎ ምልክት ሰጥቶ ነበርና ሊስመው ወደ ኢየሱስ ቀረበ ። ኢየሱስ ግን ፤ « ይሁዳ ሆይ ፤ በመሳም የሰውን ልጅ አሳልፈህ ትሰጣለህን ? » ብሎ ራሱን ሰጠ ። በዚያን ጊዜ ደቀ መዛ ሙርቱ ሁሉ ትተውት ሸሹ ።

### ፬ ፤ የካህናት አለቆች ፍርድ ።

ማር. ፲፬ ፡ ፶፫ ፡ ፷፩—፷፭ ፤ ሉቃ. ፳፪ ፡ ፷፯—፸፫ ፡ ፩ ።

ኢየሱስንም ይዘው ወደ ሊቀ ካህናት ቤት አገቡት ። ሊቀ ካህናቱም ፤ «የቡሩክ ልጅ ክርስቶስ አንተ ነህን ? » አለው ። ኢየሱ ስም ፤ «እኔ ነኝ ፤ የሰው ልጅም በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ » አለ ። ሊቀ ካህናቱም ልብ ሱን ቀደደና ፤ «ስድቡን ሰማችሁ ፤ ምን ይመስላችኋል ? » አለ ። እነርሱም ሁሉ፤ «ሞት ይገባዋል» ብለው ፈረዱበት። በዚ ያን ጊዜም ይዘብቱበትና ይደበድቡት ነበር ፤ ብብዙ ነገርም እየተሳደቡ በእርሱ ላይ ይናገሩ ነበር ። በነጋ ጊዜም የሕዝብ ሽማግሌዎችና የካህናት አለቆች ጸሐፎችም ተሰብስበው ወደ ሸንጎአቸው ወሰዱት ። ሸንጎውም በሞላ ተነሥቶ የሞት ፍርድ ሊሰጥ ሥልጣን ወዳለው ሮማዊ ገዥ ወሰ ደው ። ገዢውም ጲላጦስ ይባል ነበር ።

### ፭ ፤ የጲላጦስ ፍርድ ።

ሉቃ. ፳፫ ፡ ፪—፭ ፡ ፲፫—፳፭ ፤ ማቴ. ፳፯ ፡ ፲፭—፳፯ ።

የካህናት አለቆች ኢየሱስን ወደ ገዢው





www.ethiopianorthodox.org

በወሰዱት ጊዜ ፣ «ይህ ሕዝባችንን ሲያሳምፅ ፣ ለቄሣርም ግብር እንዳ ይሰጥ ሲከለክልና እኔ ራሴ ንጉሥ ነኝ ሲል አገኘነው» ብለው ከሰሱት ። ጲላጦስ ግን ኢየሱስን ከመረመረ በኋላ ፣ «ሕዝቡን ያሳድማል ብላችሁ ይህን ሰው ወደ እኔ አመጣችሁት ፤ እኔም ከምትከሱበት ነገር አንድ በደል ስንኳ አላገኘሁበትም ። ለሞት የሚያደርሰው ምንም አላደረገም ፤ እንግዲያስ ቀጥቼ እፈታዋለሁ» አላቸው ። እነርሱም ፣ « አስወግደው ፤ ስቀለው » እያሉ ጮኹ ።

በዚያም በዓል ሕዝቡ የወደዱትን አንድ እስረኛ ሊፈታላቸው ለገዢው ልማድ ነበረው ። በዚያን ጊዜም ወንበዴና ነፍሰ ገዳይ የነበረ በርባን የተባለ የታወቀ እስረኛ ነበረ ። ጲላጦስም ሕዝቡ ተሰብስበው ሳለ ፣ «በርባንን ወይስ ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን ማንኛውን ልፈታላችሁ ትወዳላችሁ ? » አላቸው ። የካህናት አለቆች ግን በቅንዓታቸው ሕዝቡን አባብለው ነበርና ፣ «በርባንን» አሉ ። ጲላጦስም ፣ « ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን እንግዲህ ምን ላድርገው ? » አላቸው ። ሁሉም ፣ «ይሰቀል» አሉ ። ገዢውም ፣ « ምን ነው ? ያደረገው ክፉ ምን ድር ነው ? » አለ ። እነርሱ ግን ፣ « ይሰቀል » እያሉ ጩኸት አበዙ ።

ጲላጦስም ሁከት እንዳይጀመር ብሎ ስለ ራሱ ፈራና እንደ ፈቃዳቸው ለማድረግ ተስማማ ። ነገር ግን ውኃ አንሥቶ ፣ «እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ ፤ እናንተ ተጠንቀቁ » ሲል በሕዝቡ ፊት እጁን ታጠበ ። በዚያን ጊዜ በርባንን ፈታላቸው ፤ ኢየሱስን ግን ገርፎ ሊሰቀል አሳልፎ ሰጠ ።

*   *   *

እርሱ ኃጢአት አላደረገም ፣ ተንኰልም በአፉ አልተገኘበትም ፤ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም . . . ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ ።
፩ ጴጥ. ፪ ፣ ፳፪ ፣ ፳፫ ።

ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶ አል ።
ሮሜ ፭ ፣ ፮ ።

*   *   *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ይሁዳ ጌታውን በምን ያህል እንዲሸጠው ተስማማ ?
፪ ፤ ኢየሱስ የተያዘው በምን ሥፍራ ነበረ?
፫ ፤ ጲላጦስ ኢየሱስን ከመረመረ በኋላ በሐሰት ለከሰሱት አይሁድ ምን አላቸው?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፣ ጭንቀት ቀርባለችና
የሚረዳኝም የለም . . .
አንተ ግን ፣ አቤቱ ፣ ከእኔ አትራቅ ።
መዝ. ፳፩ (፳፪) ፣ ፲፩ ፣ ፲፱ ።



ምዕራፍ ፴፱ ።

# ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰቀለ ።

ከማቴ. ፳፯ ፤ ከሉቃ. ፳፫ ፤ ከዮሐ. ፲፱ ።

## ፩ ፤ ወታደሮች ዘበቱበት ።

ማቴ. ፳፯ ፣ ፳፯—፴፩ ።

ጲላጦስ ኢየሱስን እንዲሰቀል አሳልፎ በሰጠ ጊዜ ወታደሮች ወደ ገዢው ግቢ ውስጥ ወሰዱት ። ጭፍራውንም ሁሉ ወደ እርሱ አከማችተው ይዘብቱበት ጀመር ። ልብሱንም ገፍፈው ቀይ ልብስ አለበሱት ፤ አክሊልም ከእሾህ ጐንጕነው በራሱ ላይ ደፉበት ፤ በቀኝ እጁም ዘንግ አስያዙት ፤ በፊቱም ተንበርክከው ፣ «የአይሁድ ንጉሥ ሆይ ፣ ሰላም ለአንተ ይሁን» እያሉ ዘበቱበት ተፉበትም ፤ ዘንጉንም ይዘው ራሱን መቱት ። ከዘበቱበትም በኋላ ቀዩን ልብስ ገፈፉት ልብሱን አልብሰው መስቀሉንም አሸክመው ከከተማ ወደ ውጭ ወዳለው ጎልጎታ ወደ ሚባል ስፍራ ሊወስዱት ተነሡ። ጎልጎታ በአማርኛ ሲተረጐም የራስ ቅል ስፍራ ማለት ነው ፤ በዚያም ሞት የተፈረደባቸው ወንጀለኞች ይሰቀሉ ነበር ።

## ፪ ፤ በጎልጎታ ሰቀሉት ።

ሉቃስ ፳፫ ፣ ፳፮—፴፰ ።

ኢየሱስም መስቀሉን ተሸክሞ ወጣ ፤ ሲሄዱም አንድ መንገድ አላፊ ስምዖን የተባለ የቀሬና ሰው አገኙ ፣ የኢየሱስንም መስቀል እንዲሸከም አስገደዱት። ዋይ ዋይ የሚሉ ሴቶችና ከሕዝቡ እጅግ ብዙዎች ተከተሉት።ወታደሮቹም ሁለት ክፉ አድራጊዎችን ደግሞ ከእርሱ ጋር ወሰዱ ።

ወደ ስፍራውም በደረሱ ጊዜ ሰቀሉት ፤ ሁለቱ ወንበዴዎችም አንዱ በቀኝ አንዱም በግራ ከእርሱ ጋር ተሰቀሉ ። ኢየሱስም ፣ « አባት ሆይ ፣ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው » አለ ።

ወታደሮቹም ፣ « ይህ ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ ነው» የሚል የክስ ጽሕፈት ከራሱ በላይ አኖሩ ፤ ልብሱንም ዕጣ ጥለው ተካፈሉ ፤ በዚያም ተቀምጠው ይጠብቁት ነበር ።

ሕዝቡም ቆመው ሲመለከቱ ሳሉ መኳንንቶቹ ፣ « ሌሎችን አዳነ ፤ እርሱ በእግዚአብሔር የተመረጠው ክርስቶስ ከሆነ ራሱን ያድን » እያሉ ያፌዙበት ነበር ።

## ፫ ፤ የወንበዴው ልመና ።

ሉቃስ ፳፫ ፣ ፴፱—፵፫ ።

ከተሰቀሉት ከክፉ አድራጊዎቹም አንዱ ፣ «አንተ ክርስቶስ አይደለህምን ? ራስህንም እኛንም አድን » ብሎ ሰደበው ። ሁለተኛው ግን መልሶ ፣ « አንተ እንደ ዚህ ባለ ፍርድ ሳለህ እግዚአብሔርን ከቶ አትፈራውምን ? እኛ ስላደረግነው የሚገባንን እንቀበላለንና በእኛስ እውነተኛ ፍርድ ነው ፤ ይህ ግን ምንም ክፉት አላ



www.ethiopianorthodox.org

ደረገም » ብሎ ገሠፀው ። ኢየሱስንም ፥ «ጌታ ሆይ ፥ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ » አለው ። ኢየሱስም ፥ «እውነት እልሃለሁ ፥ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆና ለህ » አለው ።

፭ ፤ የኢየሱስ እናት ። ዮሐ. ፲፱ ፡ ፳፭—፳፯ ።

በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱ ፥ የእ ናቱም እኅት ፥ አንዳንዶችም ሌሎቹ ሴቶች ቆመው ነበር።ኢየሱስም እናቱን ፥ ይወደው የነበረውንም ደቀ መዝሙር ዮሐንስን በአጠገቡ ቆመው ባየ ጊዜ እና ቱን ፥ «አንቺ ሴት ፥ እነሆ ልጅሽ» አላት ። ከዚህም በኋላ ደቀ መዝሙሩን ፥ «እናትህ እነኋት » አለው ። ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ደቀ መዝሙሩ ወደ ቤቱ ወሰዳት ።

፮ ፤ ኢየሱስ ነፍሱን ሰጠ ።

ሉቃስ ፳፫ ፡ ፵፬—፵፱ ፤ ማቴ. ፳፯ ፡ ፵፭—፶፬ ፤
ዮሐ. ፲፱ ፡ ፳፰—፴፯ ።

ከስድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ ። በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ ፥ « አም ላኬ አምላኬ ስለምን ተውኸኝ ? » ብሎ ጮኸ ። ከዚያም በኋላ ሁሉ እንደ ተፈ ጸመ ዐውቆ ፥ « ተጠማሁ » አለ ። በዚ ያም ሆምጣጤ የሞላበት ዕቃ ተቀምጦ ነበር ፤ ሆምጣጤውንም በሰፍነግ ሞል ተው ወደ አፉ አቀረቡለት ። ሆምጣ ጤውንም ከተቀበለ በኋላ ኢየሱስ ፥ «ተፈጸመ» አለ።በታላቅ ድምፅም ጮኸ፥ «አባት ሆይ ፥ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰ ጣለሁ » ብሎ ነፍሱን ሰጠ ።

እነሆም ፥ በቤተ መቅደስ በቅድስተ ቅዱሳን ፊት ተንጠልጥሎ የነበረው መጋ ረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ ። ምድርም ተናወጠች ።

በዚያም በአንፃሩ የቆመ የመቶ አለቃ እንደዚህ ጮኾ ነፍሱን እንደ ሰጠ ባየ ጊዜ ፥ « ይህ ሰው በእውነት ጻድቅ ነበረ ፤ የእግዚአብሔርም ልጅ ነበረ » ብሎ እግዚአብሔርን አከበረ ። ተከማች ተውም የነበሩ ሕዝብ ሁሉ የሆነውን ባዩ ጊዜ ደረታቸውን እየደቁ ወደ ከተማ ተመ ለሱ ። የሚያውቁቱ ግን ከገሊላ የተከተ ሉት ሴቶችም ይህን እያዩ በሩቅ ቆመው ነበር ።

በሰንበት ቀን በመስቀል ላይ ሥጋ ቸው እንዳይኖር በማለት አይሁድ ወደ ጲላጦስ ሄደው ጭፍራዎች እንዲያወርዱ አቸው ለመኑት ። ጭፍሮቹም ቀርበው ሁለቱ ወንበዴዎች ወዲያውኑ እንዲሞቱ ጭን ጭናቸውን ሰበሩ ። ወደ ኢየሱስ በመጡ ጊዜ ግን እርሱ ፈጽሞ እንደሞተ አይተው ጭኑን አልሰበሩም ። ነገር ግን አንዱ ጐኑን ወጋው ፤ ወዲያውም ደምና ውኃ ወጣ ።


፯ ፤ በአዲስ መቃብር ተቀበረ ።

ሉቃስ. ፳፫ ፡ ፶—፶፮ ፤ ዮሐ. ፲፱ ፡ ፴፰ ።

በተሰቀለበት አጠገብ የአትክልት ስፍራ ነበረ ፤ በአትክልቱም ውስጥ ማንም ገና ያልተቀበረበት ከዓለት የተወቀረ አንድ አዲስ መቃብር ነበረ ። የዚ ህም መቃብር ባለቤት አርማትያስ ከሚ ባል ከተማ የመጣ የአርማትያሱ ዮሴፍ የሚሉት ጻድቅ ሰው ነበረ ። ዮሴፍም የሸ ንጎ አማካሪ ሲሆን በስውር የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ስለ ነበረ በምክራቸውና በሥ ራቸው አልተባበረም ነበር ።

በዚህም ጊዜ ዮሴፍ ደፍሮ ወደ ጲላ ጦስ ገባና የኢየሱስን ሥጋ ለመነው ። ፈቃድም ተቀብሎ ወደ ጎልጎታ ተመል ሰና ከረዳቶቹ ጋር ሽቱ በመቅባት በነጭ







www.ethiopianorthodox.org

ጨርቅ ከፍኖ የኢየሱስን ሥጋ በአዲሱ መቃብር ውስጥ አኖረ ። ከገሊላም ከኢየሱስ ጋር የመጡት ሴቶች በመቃብሩ ውስጥ ሥጋውን እንዴት እንዳኖሩ አዩ።

*   *   *

ክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቷል ።

፩ ጴጥ. ፫ ፣ ፲፰ ።

መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ ፤ ተቀበረም ።

፩ ቆሮ. ፲፩ ፣ ፫ ።

*   *   *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ኢየሱስ በተሰቀለ ጊዜ ምን ብሎ ጸለየ ?
፪ ፤ ወንበዴው ፤ « በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ » ባለው ጊዜ ኢየሱስ ምን ብሎ መለሰለት ?
፫ ፤ ኢየሱስን በመቃብሩ ያኖረው ሰው ማን ነበረ ?

ጸሎት ፤ ጌታ ሆይ ፤ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ ።

ሉቃ. ፳፫ ፣ ፵፪ ።





ምዕራፍ ፴፫ ።

## ጌታችን ከሙታን ተነሣ ።

ከማቴ. ፳፯ ፣ ፳፰ ፤ ከዮሐ. ፳ ።

፩ ፤ የመቃብሩ ጠባቆች ።

ሉቃስ ፳፫ ፣ ፶፮ ፤ ማቴ ፳፯ ፣ ፷፪—፷፮ ።

ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም ከኢየሱስ ጋር የመጡ ሴቶች መቃብሩን ካዩ በኋላ ወደ ቤታቸው ተመለሱና ወደ መቃብሩ የሚወስዱትን ሽቱና ቅባት አዘጋጁ ። በማግሥቱም ሰንበት ነበረና እንደ ትእዛዙ ዐረፉ ።

የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ግን በዚያ ሰንበት ሳያርፉ ወደ ጲላጦስ ሄደው ፤ «ጌታ ሆይ ፤ ያ አሳች በሕይወቱ ገና ሳለ ፤ ከሦስት ቀን በኋላ እነሣለሁ እንዳለ ትዝ አለን ። እንግዲህ ደቀ መዛሙርቱ መጥተው በሌሊት እንዳይሰርቁት ለሕዝቡም ፤ ከሙታን ተነሣ እንዳይሉ መቃብሩ እስከ ሦስት ቀን ድረስ እንዲጠበቅ እዘዝ » አሉት ።

ጲላጦስም ፤ «ጠባቆች አሉአችሁ ፤ ሄዳችሁ እንዳወቃችሁ አስጠብቁ» አላቸው ። ሄደውም ድንጋዩን አትመው በዘበኞች መቃብሩን አስጠበቁ ።

፪ ፤ ቅዱሳት አንስት ።

ማቴ. ፳፰ ፣ ፩—፲፭ ።

በሰንበትም መጨረሻ በመጀመሪያው ቀን ሲነጋ ይወዱት የነበሩ ቅዱሳት ሴቶች ያዘ



www.ethiopianorthodox.org

ጋጁትን ሽቱ ይዘው ወደ መቃብሩ መጡ። እርስ በርሳቸውም ፥ «ድንጋዩን ከመቃብሩ ደጃፍ ማን ያንከባልልልናል?» ይባባሉ ነበር ፤ ድንጋዩ እጅግ ታላቅ ነበርና ።

እነርሱ ግን ሳይደርሱ በፊት እነሆ የጌታ መልአክ ከሰማይ ወረደ ፥ የምድርም መናወጥ ሆነ ። መልአኩም ድንጋዩን አንከባልሎ በላዩ ላይ ተቀምጦ አገኙት ። መልኩም እንደ መብረቅ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበረ ። ጠባቆቹም ባዩት ጊዜ ከፍርሃት የተነሣ ተናወጡ እንደ ሞቱም ሆኑ ።

ሴቶቹም ሲቀርቡ መልአኩ ፥ «እናንተስ አትፍሩ ፤ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንደምትፈልጉ ዐውቃለሁና እንደ ተናገረ ተነሥቶአል በዚህም የለም ፥ የተኛበትን ሥፍራ ኑና እዩ ፤ ፈጥናችሁም ሂዱና ከሙታን ተነሣ ብላችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ንገሩአቸው» አላቸው ።

እነርሱም በፍርሃትና በታላቅ ደስታ ፈጥነው ሄዱ ፤ ለደቀ መዛሙርቱም ሊያወሩ ሮጡ ። እነሆም ኢየሱስ ተገናኛቸውና ፥ «ደስ ይበላችሁ» አላቸው ። እነርሱም ቀርበው ሰገዱለት ፤ ኢየሱስም ፥ «አትፍሩ ፤ ሂዳችሁ ፥ ወደ ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ንገሩ ፤ በዚያም ያዩኛል » አላቸው ።

ሲሄዱም ሳሉ ከጠባቆች አንዳንዱ ተነሡና ወደ ከተማ መጥተው የሆነውን ሁሉ ለካህናት አለቆች አወሩ ። የካህናት አለቆችም ከሽማግሌዎች ጋር ተሰበሰቡና ተማከሩ ። ከተማከሩም በኋላ ጠባቆቹን ጠሩና ገንዘብ ሰጥተው ፥ « እኛ ተኝተን ሳለን ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት መጥተው ሰረቁት በሉ» አሉአቸው ። ጠባቆቹም ገንዘቡን ተቀብለው እንደ ታዘዙ አደረጉ ።

## ፫ ፤ መግደላዊት ማርያም ።

ዮሐ· ፳ ፥ ፩—፲፰ ።

ከሴቶች አንድዋ መግደላ ከሚባል ከተማ የመጣች መግደላዊት ማርያም የምትባል ነበረች ። ከዚህችም ሴት ሰባት አጋንንት ኢየሱስ ስላወጣላት እጅግ ትወድደው ነበር ። እርስዋም ማልዳ ጓደኞችዋን ቀድማ ድንጋዩን ከመቃብሩ ተፈንቅሎ ባየች ጊዜ እየሮጠች ወደ ጴጥሮስና ዮሐንስ መጥታ ፥ «ጌታን ከመቃብሩ ወስደውታል ፥ ወዴትም እንዳኖሩት አናውቅም» አለቻቸው ። እነርሱም ወደ መቃብሩ ሊሄዱ ተነሡ ።

ሁለቱም እየሮጡ ሲሄዱ ዮሐንስ ቀድሞ ደረሰ ፤ ዝቅም ብሎ ወደ መቃብሩ ውስጥ ሲመለከት የተከፈነበትን ነጭ ጨርቅ ተቀምጦ አየ ፤ ነገር ግን አልገባም ። ጴጥሮስ በመጣ ጊዜ ግን ወደ መቃብሩ ውስጥ ገባና በራሱ የነበረውን ሻሽ ለብቻው ተጠምጥሞ እንደ ነበረ አየ ። በዚያን ጊዜ ዮሐንስ ደግሞ ገባ አየም ፤ ከሙታንም እንደተነሣ አመነ ። ከጴጥሮስም ጋር ወደ ከተማ ተመለሰ ።

ማርያም ግን እያለቀሰች ከመቃብሩ በስተ ውጭ ቆማ ነበር ። ስታለቅስም ፤ ወደ መቃብር ዝቅ ብላ ተመለከተች ፤ ሁለት መላእክትም ነጭ ልብስ ለብሰው የኢየሱስ ሥጋ ተኝቶበት በነበረው ፥ አንዱ በራስጌ ሌላውም በግርጌ ተቀምጠው አየች ።

እነርሱም ፥ «አንቺ ሴት ፥ ስለምን ታለቅሻለሽ ? » አሉአት ። እርስዋም ፥ «ጌታዩን ወስደውታል ፥ ወዴትም እንዳኖሩት አላውቅም » አለቻቸው ።

ይህንም ብላ ወደ ኋላ ዘወር ስትል ኢየሱስን ቆሞ አየችው ፤ ኢየሱስም እንደ ሆነ አላወቀችም ። ኢየሱስም ፥



«አንቺ ሴት ፥ ስለምን ታለቅሻለሽ ማንንስ ትፈልጊያለሽ ? » አላት ። እርስዋም የአትክልት ጠባቂ መስሎአት ፥ « ጌታ ሆይ ፥ አንተም ወስደኸው እንደ ሆንህ ወዴት እንዳኖርኸው ንገረኝ ፥ እኔም እወስደዋለሁ » አለችው ። ኢየሱስም ፥ «ማርያም» አላት ። እርስዋም ዘወር ብላ ፥ «መምህር ሆይ » አለችው ። ኢየሱስም ፥ «ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ ፤ ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሂደሽ ፥ እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁም ዐርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው » አላት ። ሄዳም ጌታን እንዳየችው ይህንም እንዳላት ለደቀ መዛሙርቱ ነገረች ።

* * *

መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ ፥ ተቀበረም ፤ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ ። ፩ቆሮ· ፲፭ ፥ ፫ ፥ ፬ ።

አትፍራ ፤ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ ፥ ሞቼም ነበርሁ እነሆም ፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ ፤ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ ። ራእይ· ፩ ፥ ፲፯ ፥ ፲፰ ።


* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ የኢየሱስ ጠላቶች በምን ምክንያት መቃብሩን አስጠበቁ ?

፪ ፤ ኢየሱስን የሚወዱት ሰዎች ፥ ከሙታን እንደሚነሣ በሰጣቸው ተስፋ አምነው ነበርን ?

፫ ፤ መግደላዊት ማርያም ኢየሱስን ያወቀችው ምን ሲላት ነው ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፥ የሕይወትን መንገድ አሳየኸኝ ፤
ከፊትህ ጋር ደስታን አጠገብኸኝ ፥
በቀኝህም የዘላለም ፍሥሐ አለ ።
መዝ· ፲፮ (፲፭) ፥ ፲፩ ።



## ምዕራፍ ፴፬ ።

# ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ ታየ ።

ከሉቃ. ፳፬ ፤ ከዮሐ. ፳ ፤ ከማቴ. ፳፰ ።

### ፩ ፤ የደቀ መዛሙርቱ ደስታ ።

ሉቃስ ፳፬ ፣ ፴፮—፵፫ ፤ ዮሐ. ፳ ፣ ፲፱ ፣ ፳ ።

በተነሣበት ቀን በመሸ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ አይሁድን ስለ ፈሩ ደጆቹን ዘግተው በአንድ ቤት ተሰብስበው ሳሉ ኢየሱስ መጣ ፤ በመካከላቸውም ቆሞ ፤ «ሰላም ለእናንተ ይሁን» አላቸው ። እነርሱም ደንግጠው ፈሩ ፤ መንፈስንም ያዩ መሰላቸው ። እርሱ ግን ፤ «ስለምን ትደነግጣላችሁ ? ስለምንስ አሳብ በልባችሁ ይነሣል ? እኔ ራሴ እንደሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ ፤ በእኔ እንደምታዩት፣ ለመንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ » አላቸው ። ይህንም ብሎ በእጆቹና በእግሮቹ ያለውን የችንካሩን ምልክት አሳያቸው ። እነርሱም ከደስታ የተነሣ ገና ስላላመኑ ሲደነቁ ሳሉ ፤ «በዚህ አንዳች የሚበላ አላችሁን ? » አላቸው ። እነርሱም ከተጠበሰ ዓሣና ከማር ወለላም ሰጡት ፤ ተቀብሎም በፊታቸው በላ ።

ከበላም በኋላ ከእነርሱ ጋር ሲናገር ከጥንት ጀምሮ በነቢያት መጻሕፍት ስለ ሞቱና ከሙታን ስለ መነሣቱ የተጻፈውን ቃል እንዲያስተውሉ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው ፤ እንዲህም አላቸው ፤ «ከእናንተ ጋር ሳለሁ ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ እንዲፈጸም ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው ። ክርስቶስ መከራ ይቀበላል ፤ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል ፤ በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት በምድር ሕዝቦች ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል ፤ እናንተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ ። » ደቀ መዛሙርቱ ይህን ሲሰሙና ሲያስተውሉ እጅግ ደስ አላቸው ።

### ፪ ፤ የቶማስ መጠራጠር ።

ዮሐ. ፳ ፣ ፳፬—፳፱ ።

ነገር ግን በዚያ ምሽት ቶማስ የተባለው ደቀ መዝሙር ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ከሌሎቹ ጋር አልነበረም ። እነርሱም ፤ «ጌታን አይተነዋል » አሉት ። እርሱ ግን ፤ «የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ ፤ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጎኑ ካላገባሁ አላምንም» አላቸው ።

ከስምንት ቀን በኋላም ደቀ መዛሙርቱ ደግመው በቤት ውስጥ ነበሩ ፤ ቶማስም ከእነርሱ ጋር ነበረ ። ደጆቹ ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጣ ፤ በመካከላቸውም ቆሞ ፤ «ሰላም ለእናንተ ይሁን» አላቸው ። ከዚያም በኋላ ቶማስን፣ «ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው ፤ ያመንህ ሁን እንጂ አትጠራጠር » አለው ። ቶማስም ፤ «ጌታዬ አምላኬም» ብሎ መለሰለት ። ኢየሱስም ፤ «ስላየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው» አለው ።

### ፫ ፤ በገሊላ እንደ ተገናኙት ።

ማቴ. ፳፰ ፣ ፲፮—፳ ።

በተያዘበት ሌሊት እንደ ሰጣቸው ቀጠሮ አሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ ወዳዘዛቸው ተራራ ወደ ገሊላ ሄደው ተገናኙት ። እርሱም ቀርቦ ፤ «በሰማይና በምድር ሥልጣን ሁሉ ተሰጠኝ ። እንግዲህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ፤ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው ፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ » ብሎ ትልቅ አደራ ሰጣቸው ።

* * *

ጌታ በእውነት ተነሥቶአል ። ሉቃ. ፳፬ ፣ ፴፬ ።

ኢየሱስ አለ ፤ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ ። ማቴ. ፳፰ ፣ ፲፰ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን ባዩ ጊዜ ለምን ደነገጡ ?
፪ ፤ ኢየሱስ ፤ እርሱ ራሱ እንደ ሆነ ሊያስረዳቸው ምን ሁለት ነገሮች አደረገ ?
፫ ፤ ኢየሱስ ለቶማስ ከተናገረ በኋላ ቶማስ ምን አለው ?
፬ ፤ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ምን አደራ ሰጣቸው ?

ጸሎት ፤ አምላክ ሆይ ፤ በሰማያት ላይ ከፍ ከፍ በል ፤
ክብርህም በምድር ሁሉ ላይ ይሁን ።
መዝ. ፶፯ (፶፮) ፣ ፲፩ ።





www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፴፭ ።

# ጌታችን ዐረገ ።

ሉቃ. ፳፬ ፡ ፵፱—፶፫ ፤ የሐዋ. ፩ ፡ ፩—፲፩ ።

፩ ፤ ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው ተስፋ ። ዮሐ. ፲፬ ፡ ፲፮—፲፰ ፤ ፲፮ ፡ ፭—፯ ።

በትንሣኤ ዕለት ኢየሱስ ለመግደላዊት ማርያም ፡ « ወደ ወንድሞቼ ሂደሽ ፡ እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁም ዐርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው » እንዳላት ወደ ላከው ወደ አብ የሚሄድበት ጊዜ ቀርቦ ነበር ፤ በዓለም ሊፈጽመው የመጣበትን ሥራ በሞቱ ፈጽሞት ነበርና ።

ወደ አብ ስለ መሄዱ መጀመሪያ በሰሙ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ አዘኑ ። ኢየሱስ ግን ፡ «እኔ አብን እለምናለሁ ፡ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል » ብሎ ተስፋ ሰጣቸው ። ይህም የሚመጣው ሌላ አጽናኝ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው ። ኢየሱስም ፡ «እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል ። እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና ፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ ። ወላጆች እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም ፤ ወደ እናንተ እመጣለሁ» ብሎ መንፈሱ ከእነርሱ ዘንድ እንደሚኖር በውስጣቸውም እንደሚሆን ነገራቸው ።

፪ ፤ ጌታችን ወደ ሰማይ ዐረገ ።

ሉቃ. ፳፬ ፡ ፵፱—፶፫ ፤ የሐዋ. ፩ ፡ ፩—፲፩ ።

ከተነሣበት እስከ ዓርባ ቀን ድረስ ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እየታያቸው ከእነርሱ ጋር ይነጋገር ነበር ። ከእነርሱም ጋር አብሮ ሳለ ፡ «ከእኔ የሰማችሁትን አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠብቁ ፤ በመንፈስ ቅዱስ እስክትጠመቁ ድረስ ከኢየሩሳሌም አትውጡ » ብሎ አዘዛቸው ።


ከሙታን ተነሥቶ ዓርባ ቀን ከሆነ በኋላ ጌታ ሐዋርያትን ይዞ በደብረ ዘይት ወዳለው ቢታንያ ወደሚባለው መንደር አወጣቸው ። በመንገድም ሲሄዱ ሳለ ስለ ተሰጣቸው ሥራ ተናግሮ ፡ «እናንተ በኢየሩሳሌም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁና መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ» አላቸው ።

ይህንም ሲነጋገሩ ወደ ቢታንያ ደርሰው ነበር ። ኢየሱስም ባረካቸው ፤ ሲባርካቸውም ከእነርሱ ተለየ ፡ ከፍ ከፍም እያለ ሲሄድ ደመና ተቀበለችው ፡ ከዓይናቸውም ተሰወረ ።

እርሱም ሲሄድ ወደ ሰማይ ትኵር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በአጠገባቸው ቆመው፡ «የገሊላ ሰዎች ሆይ ፡ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል ? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ፡ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል » አሉአቸው ።

አሥራ አንዱም ሐዋርያት ይህን ከሰሙ በኋላ በብዙ ደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ። ጌታቸው የጠላትን ኃይል ሁሉ ድል ነሥቶ ወደ አብ ወደ ክብሩም ተመልሶ ነበርና ሁለቅ ቅልልቅ









www.ethiopianorthodox.org

ተሰፋዎች ነበሩአቸው ፤ አንዱ ተሰፋ ፥ ከጥቂት ቀን በኋላ መንፈስ ቅዱስ ይመጣላችኋል የሚለው ሲሆን ሁለተኛውም ፣ ጊዜው ሲደርስ ኢየሱስ ራሱ ተመልሶ ይመጣል የተባለው ነበረ ። ደስ እያላቸውም ወደ ከተማ ተመልሰው ዘወትርም እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እየባረኩ በመቅደስ ኖሩ ።

*  *  *

ጌታ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር ከተናገረ በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ ።

ማር. ፲፮ ፣ ፲፱ ።

የገሊላ ሰዎች ሆይ ፣ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችኋል ? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ፣ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል ።

የሐዋ. ፩ ፣ ፲፩ ።

*  *  *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ምን ተስፋ ሰጣቸው ?
፪ ፤ ኢየሱስ ባረገ ጊዜ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች ምን ተስፋ ሰጡቸው ?
፫ ፤ አሥራ አንዱ ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱ በደስታ ነበረ ወይስ በኀዘን ?

ጸሎት ፤ ጌታ ኢየሱስ ሆይ ፣ ና ። ራእይ. ፳፪ ፣ ፳ ።





ምዕራፍ ፶፯ ።

## የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ።

የሐዋ. ፪ ።

### ፩ ፤ ተስፋን መጠባበቅ ።

የሐዋ. ፩ ፣ ፲፪—፲፭ ።

ጌታ ካረገ በኋላ አሥራ አንዱ ሐዋርያት ደብረ ዘይት ከሚባለው ተራራ ወደ ኢየሩሳሌም በተመለሱ ጊዜ ወደሚኖሩበት ሰገነት ወጥተው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ጸለዩ ። መንፈስ ቅዱስም እስከሚወርድላቸው ቀን ድረስ እነርሱ በኢየሱስ ካመኑት ሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው በጸሎት ይተጉ ነበር ። በዚህም ወራት መቶ ሃያ የሚያህሉ አማኞች በኢየሩሳሌም አብረው ሲገናኙና በብዙ ደስታ ያን ሌላ አጽናኝ የተባለውን መንፈስ ቅዱስ ሲጠባበቁ ሳሉ ከአሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር በይሁዳ ምትክ የሚሆን ማትያስ የተባለ ሰው ተመረጠ ።

### ፪ ፤ የጰንጠቆስጤ ቀን ።

የሐዋ. ፪ ፣ ፩—፲፫ ።

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገበት ከአሥር ቀን በኋላ በዓለ ኀምሳ ወይም ጰንጠቆስጤ* የተባለው የአይሁድ የበዓል ቀን ደረሰ ። ለዚህም ዓመት በዓል ከብዙ የውጭ አገሮች እየመጡ ብዙ አይሁድ ወደ ኢየሩሳሌም ይሰበሰቡ ነበር ።



www.ethiopianorthodox.org

ይህም የጰንጠቆስጤ ቀን በደረሰ ጊዜ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ ፤ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሞላው ። እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው ፤ በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው ። በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው ፣ መንፈስም እንዲናገሩ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር ።

ይህም እንደ ዓውሎ ነፋስ ድምፅ በተሰማ ጊዜ በኢየሩሳሌም የሚገኙ ሰዎች ሁሉ የሆነውን ያዩ ዘንድ ተሰበሰቡ ፤ እያንዳንዱም በገዛ ቋንቋቸው ሲናገሩ ይሰማ ስለ ነበር የሚሉትን አጡ ። ተገርመውም እንዲህ አሉ ፤ «እነሆ እነዚህ የሚናገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን ? እኛም እያንዳንዳችን የተወለድንበትን የገዛ ቋንቋችንን እንዴት እንሰማለን ? በመካከላችን ከሰሜንና ከደቡብ ከምሥራቅና ከምዕራብ ካሉት አገሮች የመጣን እንገኛለን ። ቢሆንም የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በየቋንቋችን ሁሉ ሲናገሩ እንሰማቸዋለን» እያሉ ሁሉም ተደነቁና እርስ በርሳቸው ፣ «እንጃ ፣ ይህ ምን ይሆን ? » አሉ ። አንዳንዶች ግን ፣ «ጉሽ የወይን ጠጅ ጠግበዋል » ብለው በደቀ መዛሙርቱ ላይ አፌዙባቸው ።

፫ ፤ የሐዋርያው ጴጥሮስ ስብከት ።

የሐዋ. ፪ ፥ ፲፬—፴፮ ።

በዚህም ጊዜ ጴጥሮስ በኃይልና በድፍረት ተሞልቶ በሐዋርያት መካከል ቆሞ ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲህ ሲል ሕዝቡን ተናገራቸው ። «የእስራኤል ሰዎች ሆይ ፣ ለእናንተ እንደ መሰላችሁ እነዚህ የሰከሩ አይደሉም ፤ ከቀኑ ሦስተኛ ሰዓት ነውና ፤ ነገር ግን ይህ የምታዩትና የምትሰሙት እግዚአብሔር መንፈሱን እንዳወረደ የሚያሳይ ነው ፤ በነቢዩ ኢዩኤል ፣ «ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ» ያለውን የተስፋ ቃል አሁን ፈጽሞአልና ።

« አሁን እናንተ የእስራኤል ሰዎች ሁሉ ቃሌን ስሙ ። የናዝሬቱ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተገለጠ ሰው መሆኑን እግዚአብሔር በእርሱ በኩል በመካከላችሁ ባደረገው በብዙ ተአምራትና ምልክት ራሳችሁ ታውቃላችሁ ። እናንተ ግን በዓመፀኞች እጅ ሰቀላችሁት ገደላችሁትም ፤ በእግዚአብሔር በተወሰነው አሳብ ለዚህ ተሰጥቶ ነበርና። እግዚአብሔር ግን ከሞት አስነሣው ፤ ሕያውም እንደ ሆነ እኛ ያየነው ምስክሮች ነን ። አሁንም እርሱ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሏልና የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ፣ ይህን እናንተ የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው ። እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታና ክርስቶስ እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ ። »

፬ ፤ የሦስት ሺህ ሰዎች መጠመቅ ።

የሐዋ. ፪ ፥ ፴፯—፵፯ ።

ይህንም በሰሙ ጊዜ ልባቸው ተነካ ፤ ከጥቂትም ሳምንታት በፊት ብዙ የኢየሩሳሌም ሰዎች ፣ ይሰቀል ! ይሰቀል ! እያሉ በኢየሱስ ላይ እንደ ጮኹ አስታውሰው ተጸጸቱ ። አሁንም ጴጥሮስንና ሌሎችን ሐዋርያት ፣ «ወንድሞች ሆይ ፣ ምን እናድርግ ? » አሉአቸው ። ጴጥሮስም ፣ «ንስሐ ግቡ ፣ ኃጢአታችሁ እንዲሠረይ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ ። የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ነውና ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና» ብሎ ከኃጢአት እንዲመለሱና በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲድኑ በብዙ ቃል መከራቸው ።

ቃሉንም የተቀበሉ ብዙዎች ነበሩና በዚያን ዕለት ሦስት ሺህ የሚያህሉ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ ። እነርሱም በሐዋርያት ትምህርትና ኅብረት እንጀራንም በመቊረስ በጸሎትም ይተጉ ነበር ።

ከዚያም ቀን ጀምሮ በሐዋርያት እጅ ብዙ ተአምራትና ምልክት ተደረገ። ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ ፣ በደስታና በቅን ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር ፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ ኖሩ ፤ በሕዝቡም ፊት ሞገስ ነበራቸው ። ጌታም የሚድኑትን አዲስ አማኞች ዕለት ዕለት ወደ እነርሱ ይጨምር ነበር ።

* * *

መንፈሴን በውስጣችሁ አኖራለሁ በትእዛዜም እስሄዳችኋለሁ ። ሕዝ. ፴፮ ፥ ፳፯ ።

እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ ፣ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው ? ሉቃ. ፲፩ ፥ ፲፫ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ መንፈስ ቅዱስ በደቀ መዛሙርት በወረደ ጊዜ ምን ድምፅ ተሰማ ፣ ምንስ ታየ ?

፪ ፤ በፊት ይፈሩ የነበሩ ደቀ መዛሙርት በድፍረት ስለ ክርስቶስ እንዲናገሩ ያስቻላቸው የማን ኃይል ነበረ ?

፫ ፤ በዚያ ቀን በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑት ስንት ነበሩ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፣ ቅዱስ መንፈስህ በጽድቅ ምድር ይምራኝ ። መዝ. ፻፵፪ (፻፵፫) ፥ ፲ ።

* «ጰንጠቆስጤ» ማለት «ኀምሳኛ» ማለት ነው ። ይህም የአይሁድ ዓመት በዓል ከመከር መጀመሪያ የታጨደው ነዶ በእግዚአብሔር ፊት ከቀረበበት ኀምሳኛው ቀን ነበረና በዚሁ ኀምሳኛ ቀን ከአዲሱ እህል የተጋገረ እንጀራ በእግዚአብሔር ፊት ይቀርብ ነበር ። ዘሌዋ. ፳፫ ፥ ፲፭—፲፯ ።

## ምዕራፍ ፴፯ ።

# ተአምራት በሐዋርያት ።

የሐዋ. ፫ ፥ ፩ ።

**፩ ፤ አንካሳ ሆኖ የተወለደው ለማኝ ተፈወሰ ።**

የሐዋ. ፫ ፥ ፩—፲ ።

ጴጥሮስና ዮሐንስ በጸሎት ጊዜ በዘጠኝ ሰዓት ወደ ቤተ መቅደስ ወጡ ፤ መልካም በሚሉአት በመቅደስ ደጅ ሲገቡ አንካሳ ሆኖ የተወለደው በዚያ ተቀምጦ የነበረው ሰው ምጽዋት ለመናቸው ። ይህም ሰው ዕድሜው ከአርባ ዓመት በላይ ነበረና ዕለት ዕለት ሰዎች ተሸክመው መልካም በሚሉአት በመቅደስ ደጅ ያስቀምጡት ስለ ነበር በጣም የታወቀ ለማኝ ነበረ ።

ጴጥሮስ ከዮሐንስ ጋር ትኵር ብሎ ወደዚህ ሰውዩ ተመልክቶ ፥ «ወደ እኛ ተመልከት » አለው ። እርሱም አንድ ነገር እንደሚቀበል ተስፋ አድርጎ ወደ እነርሱ ተመለከተ ። ጴጥሮስ ግን፥ «ብርና ወርቅ የለኝም ፤ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ » አለው ። ይህንም ሲል ቀኝ እጁን ይዞ አስነሣው፤ በዚያን ጊዜም እግሩና ቍርጭምጭሚቱ ጸና ፥ ወደ ላይ ዘሎም ቆመ ፥ ይመላለስም ጀመር ፤ እየተመላለሰም እየዘለለም እግዚአብሔርን እያመሰገነ ከጴጥሮስና ከዮሐንስ ጋር ወደ መቅደስ ገባ ፤ የሰሎሞን መመላለሻ በሚባለው የመቅደስ ክፍል ለነበሩት ሕዝብ ሁሉ ታየ ።

ሕዝቡም ባዩት ጊዜ ፥ ይህ ሰው መልካም በሚሉአት በመቅደስ ደጅ ተቀምጦ ዕለት ዕለት ይለምን የነበረው አይደለምን ? እያሉ መደነቅ ሞላባቸው፥ የሆነውንም ለማየት እየሮጡ መጡ ።

**፪ ፤ ጴጥሮስ ለሚያደንቀው ሕዝብ ተናገረ ።**

የሐዋ. ፫ ፥ ፲፩—፳፮ ።

ጴጥሮስም የሕዝቡን አድናቆት ሲመለከት ፥ « እናንተ የእስራኤል ሰዎች ሆይ ፥ በዚህ ስለምን ትደነቃላችሁ ? ወይስ በገዛ ኃይላችን ወይስ እግዚአብሔርን በመፍራታችን ይህ የምታውቁት ሰው እንዲመላለስ እንዳደረግነው ስለ ምን ትኵር ብላችሁ ታዩናላችሁ ? ይህ የሆነው እናንተ በካዳችሁትና በገደላችሁት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በማመን ነው ። እርሱን እግዚአብሔር አከበረው ፥ ከሙታንም አስነሣው ። አሁንም ይህን አንካሳ የነበረውን ሰው ያጸናው የእርሱ ስም ነው ፤ በእርሱም ስም በማመን በሁላችሁ ፊት ፍጹም ጤናማ ሆነ» አላቸው ።

ሕዝቡም ይህን ቃል ሲያዳምጡ ጴጥሮስ ፥ «ወንድሞቼ ሆይ ፥ እናንተ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያደረጋችሁት ሁሉ ባለማወቅ እንደ ነበረ አውቄአለሁ፤ አሁን ግን ኃጢአታችሁ እንዲደመሰስ ንስሐ ግቡ ተመለሱም ። እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስን የሰደደው እያንዳንዳችሁን ከክፋታችሁ እየመለሰ እንዲባርካችሁ ነው» ብሎ መከራቸው ።

**፫ ፤ ጴጥሮስና ዮሐንስ ታሰሩ ።**

የሐዋ. ፬ ፥ ፩—፳ ።

ጴጥሮስ ለሕዝብ ሲናገር የካህናት አለቆችና የመቅደሱ አዛዥ ቀርበው በኢ







www.ethiopianorthodox.org

የሱስ የሙታንን ትንሣኤ ስለ ሰበኩ ተቆ ገሩና ጴጥሮስንና ዮሐንስን ያዙአቸው ፤ ጊዜውም መሽቶ ነበርና በወህኒ አኖሩአ ቸው ። ነገር ግን ቃሉን ከሰሙት ሰዎች ብዙዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ ።

በነጋውም የካህናት አለቆችና የሕ ዝብ ሽማግሌዎች ጴጥሮስንና ዮሐንስን ጠርተው ከመካከላቸው አቆሙና፥ «በምን ኃይል ወይስ በማን ስም እናንተ ይህን አደ ረጋችሁ ? » ብለው ጠየቁአቸው ። የተፈወ ሰውም ሰው ከሐዋርያት ጋር ቆሞ ነበር ።

በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱ ስን ተሞልቶ እንዲህ አላቸው ፥ «እናንተ የሕዝብ አለቆችና ሽማግሌዎች ፥ እኛ ዛሬ ለድውዩ ሰው ስለ ተደረገው መልካም ሥራ ብንመረመር ፥ እናንተ በሰቀላች ሁት እግዚአብሔርም ከሙታን ባስነ ሣው በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይህ ደኅና ሆኖ በፊታችሁ እንደ ቆመ የታወቀ ይሁን ። መዳን በሌላ በማንም የለም ፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰ ዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና » ።

አለቆቹም የተፈወሰውን ሰው ከጴጥ ሮስና ከዮሐንስ ጋር ቆሞ ባዩ ጊዜ የሚመ ልሱትን አጡ ። ጴጥሮስና ዮሐንስም ያል ተማሩ ሰዎች እንደ ሆኑ አስተውለው ስለ ተሰጣቸው ድፍረትና ጥበብ አደነቁ፤ ከኢ የሱስም ጋር እንደ ነበሩ ዐወቁአቸው ። እርስ በርሳቸውም ከተመካከሩ በኋላ ፥ «በኢየሱስ ስም ፈጽማችሁ አትናገሩ አታስተምሩም » ብለው አዘዙአቸው ። ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን ፥ «እግዚአብሔ ርን ከመስማት ይልቅ እናንተን እንድን ሰማ የሚገባ እንደ ሆነ ቍረጡ ፤ እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም » አሉአቸው ።

፬ ፤ ጴጥሮስና ዮሐንስ ተፈቱ ።

የሐዋ. ፬ ፥ ፳፩—፴፩ ።

አለቆቹም ፥ ሰዎች ሁሉ በአንካሳው መፈ ወስ ምክንያት እግዚአብሔርን ያከብሩ እንደ ነበር አስተውለው ጴጥሮስንና ዮሐንስን እንዳይለቁአቸው ፈሩና እንደ ገና ፥ በኢየሱስ ስም አታስተምሩ ብለው ከዛቱባቸው በኋላ ፈቱአቸው ።

እነርሱም በተፈቱ ጊዜ ወደ ወገኖቻ ቸው መጡና የሆነውን ሁሉ ነገሩአቸው ። በኢየሱስ ስም አታስተምሩ እንደ ተባለ በሰሙ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ በአንድ ልብ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ድምፃቸ ውን ከፍ አድርገው እንዲህ ብለው ጸለዩ ፥ «አንተ ሰማይንና ምድርን ሁሉንም የፈ ጠርህ አምላክ ሆይ ፥ በፍጹም ግልጥነት ቃልህን እንዲናገሩ ለባሪያዎችህ ስጣ ቸው።» ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበ ሩበት ስፍራ ተናወጠ ፥ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው ፤ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ከመናገር አላቋረጡም ።

፭ ፤ ሐዋርያት ተገረፉ ።

የሐዋ. ፭ ፥ ፲፯—፵፪ ።

ሊቀ ካህናቱና የሕዝብ ሽማግሌዎች ግን በቅንዓት ተሞልተው ሐዋርያትን አስይዘው ፥ «በዚህ ስም እንዳታስተምሩ አጥብቀን አላዘዝናችሁምን ? እነሆ ኢየ ሩሳሌምን በትምህርታችሁ ሞላችኋት » ብለው ገረፉአቸው ፤ በኢየሱስም ስም እንዳይናገሩ አዘዘው ፈቱአቸው ። እነ ርሱም ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባ ቸው ሆነው ስለ ተቈጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ ፤ ዕለት ዕለትም ስለ ኢየሱስ ፥ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ማስ ተማርንና መስበክን አይተዉም ነበር ።



መዳን በሌላ በማንም የለም ፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና ። የሐዋ. ፬ ፥ ፲፪ ።

ቢነቅፉአችሁና ቢያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ቢናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ ። ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ ፥ ሐሤትም አድርጉ ፤ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢ ያት እንዲሁ አሳድደዋቸዋልና ። ማቴ. ፭ ፥ ፲፩ ፥ ፲፪ ።

* * *


ጥያቄ ፤ ፩ ፤ በአንካሳው ሰው መፈወስ ለሚደነቁ ሕዝብ ጴጥሮስ ምን አላቸው ?

፪ ፤ የካህናት አለቆች ጴጥሮስንና ዮሐንስን በምን ምክንያት አሳሰሩአቸው ?

፫ ፤ « በኢየሱስ ስም አትናገሩ » በተባሉ ጊዜ ሐዋርያት ምን መልስ ሰጡ ?

፬ ፤ ሐዋርያት በተገረፉ ጊዜ ስለምን ደስ አላቸው ?

ጸሎት ፤ ጌታ ሆይ ፥ ባሪያዎችህ በፍጹም ግልጥነት ቃልህን እንዲናገሩ ስጣቸው ። የሐዋ. ፬ ፥ ፳፱ ፥ ፴ ።



ምዕራፍ ፴፰ ።

## የኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ጥምቀት ።

የሐዋ. ፰ ።

### ፩ ፤ ፊልጶስ በሰማርያ ።

የሐዋ. ፮ ፥ ፩ -፮ ፤ ፰ ፥ ፩ ፥ ፬—፰ ።

በኢየሩሳሌም የነበሩ የክርስቶስ እማኞች ከአምስት ሺህ በላይ እየበዙ ሲሄዱ ለድሆች የሚደረገውን እርዳታ በቅንነት እንዲያድሉ ሰባት ሰዎች ተመረጡ ። ከእነዚህም አንዱ ፊልጶስ የሚባል ሰው ነበረ ፤ እርሱም የታመነ ፥ መንፈስ ቅዱስና ጥበብ የሞላበት ነበረ ።

ከዚህም በኋላ አይሁዶች በቤተ ክርስቲያን ላይ ተነሥተው አሳደዱአቸው ። ከሐዋርያትም በቀር ከኢየሩሳሌም ወደ ውጭ እየተበታተኑ ሲሄዱ ፊልጶስ ሰማርያ ወደሚባል ከተማ ገብቶ ለሳምራውያን ስለ ክርስቶስ ሰበከላቸው ። የሰማርያም ሕዝብ የፊልጶስን ቃል በደስታ ተቀበሉ ፤ ብዙዎቻቸውም አምነው ተጠመቁ ።

### ፪ ፤ ፊልጶስና ኢትዮጵያዊው ።

የሐዋ. ፰ ፥ ፳፮—፳፱ ።

ፊልጶስም በዚህ ቅልቅ ተግባር ላይ ሳለ የጌታ መልአክ ፥ «ተነሥተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው መንገድ ሂድ » ብሎ አዘዘው ። ያ መንገድ በምድረ በዳ የሚያሻግረው መንገድ ነበረ ፤ ፊልጶስም ተነሥቶ ሄደ ።

እንደዚሁም ወደ ጋዛ በሚያወርደው መንገድ ብቻውን ሲሄድ እነሆ አንድ ሰረገላ አየ። በሰረገላውም ተቀምጦ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ኢየሩሳሌምን ጐብኝቶ ሲያበቃ ወደ ገዛ አገሩ ይመለስ ነበር ፤ እርሱም ህንደኬ የተባለችው የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥ ሆኖ ገንዘቧን ሁሉ የሚያስተዳድር ባለ ሥልጣን ነበረ ። ወደ ኢየሩሳሌምም የትጓዘው ለእግዚአብሔር ሊሰግድ ነበረና በሰረገላው ተቀምጦ ሲመለስ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር ። መንፈስ ቅዱስም ፊልጶስን ፥ «ወደዚህ ሰረገላ ቅረብና ተገናኘው » አለው ።

### ፫ ፤ የኢትዮጵያዊው ጥያቄ ።

የሐዋ. ፰ ፥ ፴—፴፭ ።

ፊልጶስም ሮጦ የኢትዮጵያ ሰው ሲያነብ ሰማውና ፥ «በእውኑ የምታነበውን ታስተውለዋለህን ? » ብሎ ጠየቀው ። እርሱም ፥ « የሚያስረዳኝ ሳይኖር ለማስተዋል እንዴት ይቻለኛል ? » አለው ። ወጥቶም ከእርሱ ጋር በሰረገላ እንዲቀመጥ ፊልጶስን ለመነው ።

በሰረገላው አብረው ተቀምጠው ሳሉ የኢትዮጵያው ሰው ፥ የማነበው የመጽሐፍ ክፍል ይህ ነው ብሎ በትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ ፶፫ በቍጥር ፯ና ፰ የሚገኘውን ቃል አሳየውና ፥ «እንደ በግ ወደ መታረድ ቱነዳ . . . አፉንም አልከፈተም ። በውርደቱ ፍርዱ ተወገደ ፤ ሕይወቱ ከምድር ተወግዳለች » የሚለውን ትንቢት አንብቦ ፥ «እባክህ ንገረኝ ፥ ነቢዩ ይህን ቃል ስለ ማን ይናገራል ? ስለ ራሱ ነውን ወይስ ስለ ሌላ ? » ብሎ ጠየቀ ።

ፊልጶስም አፉን ከፈተ ፥ ከዚህም የኢሳይያስ ቃል ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ተናግሮ ወንጌልን ሰበከለት ። ሲናገርም እንደ በግ ወደ መታረድ የተነዳው በቅዕግሥትም የሞተው ኢየሱስ እንደ ነበረ አስረድቶ ኢየሱስ የሞተው ስለ ሰው ኃጢአት እንደ ነበረ ከመጽሐፉ ገለጠለት ።

### ፬ ፤ የኢትዮጵያዊው መጠመቅ ።

የሐዋ. ፰ ፥ ፴፮—፵ ።

በመንገድም ሲሄዱ ውኃ ወደሚገኝበት ስፍራ ደረሱ ። የኢትዮጵያውም ሰው ፊልጶስን ፥ «እነሆ ውኃ ፤ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድር ነው ? » አለው ። ፊልጶስም ፥ «በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶአል » አለው ፤ መልሶም ፥ «ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ » አለ ።

ሰረገላውም እንዲቆም ነጂውን አዘዘ ፤ ፊልጶስና ኢትዮጵያዊው ሁለቱም ወደ ውኃው ወረዱ ፤ ፊልጶስም አጠመቀው ። ከውኃውም ከወጡ በኋላ የጌታ መልአክ ፊልጶስን ነጠቀው ፤ ኢትዮጵያዊውም ሰውዬ ሁለተኛ አላየውም ፤ ነገር ግን በክርስቶስ በማመኑ ደስ ብሎት መንገዱን ይሄድ ነበር ።

ፊልጶስም አዛጦን በሚባል ስፍራ ተገኘ ፤ እየዞረም በብዙ ከተማዎች ወንጌልን ይሰብክ ነበር ፤ ቂሣርያም ወደሚባል ከተማ በደረሰ ጊዜ በዚያ ኖረ ።

* * *

ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህ ። ሮሜ ፲ ፥ ፱ ።





www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩ ታል ? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ ? መልካሙን የምሥራች የሚያ ወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ ?

ሮሜ ፲ ፥ ፲፬ ፥ ፲፭ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ፊልጶስ ከጃንደረባው ጋር እንዲገናኝ ማን ላከው ?

፪ ፤ ጃንደረባው በሰረገላ ተቀምጦ ሲጓዝ ምን ያደርግ ነበር ?

፫ ፤ ጃንደረባው ፥ «እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድር ነው ? » ባለ ጊዜ ፊልጶስ ምን መለሰለት ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፥ አንተ የመድኃኒቴ አምላክ ነህና በእውነትህ ምራኝ ፥ አስተምረኝም ።

መዝ. ፳፭ (፳፮) ፥ ፭ ።



ምዕራፍ ፴፱ ።

# የጳውሎስ መጠራት ።

የሐዋ. ፱ ፥ ፩—፴፩ ።

፩ ፤ አሳዳጁ ሳውል ።

የሐዋ. ፳፪ ፥ ፫—፭ ፤ ፳፮ ፥ ፬—፲፩ ፤ ገላ. ፩ ፥ ፲፫ ፥ ፲፬ ፤ ፊልጵ. ፫ ፥ ፭ ፥ ፮ ፤ ፩ ጢሞ. ፩ ፥ ፲፪—፲፭ ።

አይሁዶች በክርስቶስ ተከታዮች ላይ በተነሡ ጊዜ ሳውል የተባለ ጐበዝ ያለ ልክ ይጣላቸውና ያሳድዳቸው ነበር ። እርሱም በክርስቶስ ያመኑትን ወንዶችና ሴቶች እየፈለገ ይይዛቸውና በወህኒ ያሳ ሥራቸው ነበር ፤ ቢገድሉአቸውም ሳውል ደስ ይለው ነበር ።

የሳውል ወላጆች አይሁዶች ሲሆኑ ኪልቅያ በሚባል በውጭ አገር ይኖሩ ነበር ፤ ሳውልም የተወለደው ጠርሴስ በተባለው የኪልቅያ ከተማ ነበረ ። ነገር ግን ገና ወጣት ሲሆን በታወቀው የአ ይሁድ መምህር በገማልያል ትምህርት ቤት እንዲማር ወደ ኢየሩሳሌም መጣ ። በዚያም የአባቶቹን ሕግና ወግ ጠንቅቆ ተማረ ፤ ሕግንም ለመጠበቅ የቀና ፈሪ ሳዊ ሆኖ ከጓደኞቹ ይልቅ በአይሁድ ሥር ዓት ይበልጥ ነበር ። ሳውልም ፥ እንደ ወንጀለኛ ተፈርዶበት የተሰቀለው የናዝ ሬቱ ኢየሱስ አሳች እንጂ ከእግዚአብ ሔር የተላከ አልነበረም ፤ እነዚህም ተከ ታዮቹ ደግሞ ከሃይማኖት የወጡ ከዳተ ኞች ናቸው ብሎ ያስብ ስለ ነበር ቤተ ክር ስቲያንን በማጥፋት እግዚአብሔርን ደስ እንደሚያሰኘው ይመስለው ነበር ።

፪ ፤ ኢየሱስ ለሳውል ተገለጠ ጠራው ።

የሐዋ. ፱ ፥ ፩—፱ ።

ሳውልም የጌታን ደቀ መዛሙርት እን ዲገድላቸው ገና እየዛተ ፥ እስከ ውጭ አገር ከተማ ድረስ ተከትሎ ለማሳደድ ወደ ካህናት አለቃ ሄዶ በደማስቆ ከተማ ለሚኖሩት አይሁድ የሚሰጥ ደብዳቤን ለመነ ። የካህናትም አለቃ የለመነውን ደብዳቤ ሰጥቶ በደማስቆ የሚገኙትን የክርስቶስ ተከታዮች ሁሉ እያሠረ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲያመጣቸው ለሳውል ሥልጣን ሰጠው ።

ሳውልም የሚረዱትን ሰዎች ይዞ ወደ ደማስቆ ለመጓዝ ተነሣ ። መንገዱም ሁለት መቶ ኻያ አምስት ኪሎ ሜትር የሚያህል ርቀት ያለው ስለሆነ ወደ ደማ ስቆ የቀረቡት አያሌ ቀን ከተጓዙ በኋላ ነበረ ።

ወደ ከተማውም ለመግባት ጥቂት ሲቀረው በመንገድ ሳለ እኩል ቀን ሲሆን ድንገት በዙሪያው ከፀሐይ ንጸብራቅ የበ ለጠ ብርሃን ከሰማይ ሲበራና ሲያንጸባ ርቅ አየ ። ከማንጸባረቁም የተነሣ ሳውል በምድር ላይ ወደቀ ፤ ወድቆም ሳለ ፤ «ሳውል ሳውል ፥ ስለምን ታሳድደኛለህ ?» የሚለውን ድምፅ ሰማ ። እርሱም ፥ «ጌታ ሆይ ፥ ማን ነህ ?» አለው ። ጌታም ፥ «አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ» አለው ። ሳውልም እየተንቀጠቀጠና እየተደነቀ ፥ «ጌታ ሆይ ፥ ምን ላደርግ ትወዳለህ ? » አለው ። ጌታም ፥ « ተነሥተህ ወደ ከተማ ግባና ልታደርገው የሚገባህን ይነ ግሩሃል » አለው ።

ከሳውልም ጋር የነበሩ ሰዎች በሆ ነው ነገር ተገረሙ ፥ ፈዘውም ቆሙ ። ሳው



www.ethiopianorthodox.org

ልም ተነሥቶ ለመቆም በቻለ ጊዜ ከዚያ ብርሃን ኃይል የተነሣ ማየት አልሆነለትም ፤ እንደ ዓይነ ስውር ሆኖ ሰው እየመራው ወደ ደማስቆ ገባ ፤ ቅን በሚባለው መንገድ ይሁዳ በሚሉት ሰው ቤት አድሮ ሳያይ ሦስት ቀን ቈየ ፤ በእነዚያም ቀኖች አልበላም አልጠጣምም ።

፫ ፤ ሳውል ተጠመቀ ።

የሐዋ. ፱ ፡ ፲—፲፱ ።

በደማስቆም ሐናንያ የሚሉት አንድ ደቀ መዝሙር ነበረ ። ጌታም በራእይ ፡ «ሐናንያ ሆይ » አለው ። እርሱም ፡ « ጌታ ሆይ እነሆኝ » አለ ። ጌታም ፡ «ተነሥተህ ቅን ወደሚባለው መንገድ ሂድ ፡ በይሁዳ ቤትም ሳውል የሚሉትን አንድ የጠርሴስ ሰው ፈልግ ፡ እርሱ ይጸልያልና ሐናንያ የሚሉትም ሰው ገብቶ ደግሞ እንዲያይ እጁን ሲጭንበት ራእይ አይቶአል» አለው ።

ሐናንያም መልሶ ፡ «ጌታ ሆይ ፡ በኢየሩሳሌም በቅዱሳንህ ላይ ስንት ክፉ እንዳደረገ ስለዚህ ሰው ሰምቼአለሁ ፤ በዚህም በደማስቆ ስምህን የሚጠሩትን ሁሉ ለማሠር ከካህናት አለቃ ሥልጣን አለው» አለ ። ጌታም ፡ «እርሱ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነው ፤ በአሕዛብም በነገሥታትም በእስራኤል ሰዎችም ፊት ስሜን ይሸከማልና ሂድ» አለው ።

ሐናንያም ሄዶ ወደ ቤት ገባ ፤ እጁንም በሳውል ላይ ጭኖበት ፡ «ወንድሜ ሳውል ሆይ ፡ ጌታ ፡ እርሱም በመንገድ የታየህ ኢየሱስ ፡ ደግሞ እንድታይና መንፈስ ቅዱስ እንዲሞላብህ ላከኝ» አለው ። ወዲያውም እንደ ቅርፊት ያለ ከዓይኑ ወደቀ ፡ ያን ጊዜም ደግሞ አየ ፤ ተነሥቶም ተጠመቀ ፤ መብልም በልቶ በረታ።

፬ ፤ ሳውል ስለ ኢየሱስ ሰበከ ።

የሐዋ. ፱ ፡ ፳—፳፪ ።

ሳውልም በደማስቆ ካሉት ደቀ መዛሙርት ጋር ጥቂት ቀን ኖረ ። ወዲያውም ስለ ኢየሱስ ፡ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስም እንደ ሆነ በአይሁድ ምኵራቦች መሰከረ ፤ የሰሙትም ሁሉ ተገረሙና ፡ «ይህ በኢየሩሳሌም ይህን ስም የሚጠሩትን ያጠፋ አይደለምን ?» አሉ። ሳውል ግን እየበረታ ሄደ ፡ በደማስቆ ተቀምጠው ለነበሩት አይሁዶችም ፡ ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ በእውነት ክርስቶስ እንደ ሆነ እያስረዳ መልስ ያሳጣቸው ነበር ።

፭ ፤ አይሁድ አሳደዱት ።


የሐዋ. ፱ ፡ ፳፫—፴ ፤ ገላ. ፩ ፡ ፲፰—፳፬ ።

ብዙ ቀንም ከሆነ በኋላ የደማስቆ አይሁድ ሊገድሉት ፈልገው በሌሊትና በቀን የከተማይቱን በር ያስጠብቁ ነበር ። በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት ሳውልን ወስደው በቅጥር ላይ አሳልፈው በቅርጫት አወረዱት ።

ሳውልም ከደማስቆ አምልጦ ወደ ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ በዚያ ከሚገኙት ደቀ መዛሙርት ጋር ለመተባበር ወደደ ፤ እነርሱ ግን ፡ ይህ ያሳድደን የነበረው ፈሪሳዊ አይደለምን ? ብለው እጅግ ፈሩት ። በዚያን ጊዜ በርናባስ የተባለው የታወቀው ደቀ መዝሙር ሳውልን ይዞ ወደ ሐዋርያት አገባው ፤ ጌታ በመንገድ ከታየው ጀምሮ ስለ ሆነው ሁሉ ተረከላቸው።

ከዚህም በኋላ በጌታ በኢየሱስ ስም ደፍሮ ይናገር ስለ ነበር የዱሮ ጓደኞቹ የነበሩት አይሁድ ሳውልን ሊገድሉት ፈለጉ ። ደቀ መዛሙርቱም ይህን ባወቁ ጊዜ ወደ ጠርሴስ ሰደዱት ። በይሁዳ ሁሉ የነበሩ ደቀ መዛሙርት ፡ ቀድሞ እኛን





ያሳድድ የነበረው እርሱ በፊት ያጠፋው የነበረውን ሃይማኖት አሁን ይሰብካል ተብሎ ሲነገር በሰሙ ጊዜ ስለርሱ እግዚአብሔርን ያከብሩ ነበር ።

እንደዚሁም የቤት ክርስቲያን አሳዳጅ የነበረው ሳውል የተባለው ፈሪሳዊ የክርስቶስ ሐዋርያ እንዲሆን ተጠራ ። ወንጌልን እየሰበከ ወደ ብዙ አገሮች በተጓዘ ጊዜ በአይሁዳዊ ስሙ ሳውል ሳይሆን በሮማዊ ስሙ ጳውሎስ ተብሎ ተጠራ ።

*　　*　　*

በወንጌል አላፍርምና ፤ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው ፥ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና ። ሮሜ ፩ ፥ ፲፮ ።


ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው ፤ አሮጌው ነገር አልፎአል ፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል ። ፪ ቆሮ. ፭ ፥ ፲፯ ።

*　　*　　*

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ሳውል በምን ምክንያት የክርስቶስን ተከታዮች አሳደዳቸው ?
፪ ፤ ኢየሱስ ለሳውል በተገለጠለት ጊዜ ሳውል ወዴት ይሄድ ነበር ?
፫ ፤ ሳውል ከተጠመቀ በኋላ ምን አደረገ ?

ጸሎት ፤ ጌታ ሆይ ፥ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ ? የሐዋ. ፱ ፥ ፯ ።





ምዕራፍ ፴ ።

## ዮሴፍ ተሸጠ ።

ዘፍጥ. ፴፯ ።
( ከም. ፲፫ የሚከተል ነው ። )

፩ ፤ ያዕቆብና ልጆቹ ።

ዘፍጥ. ፴፯ ፥ ፩—፬ ፤ ፩ ዜና. ፭ ፥ ፩ ፥ ፪ ።

ያዕቆብ በኬብሮን ቈላ ድንኳኑን ተክሎ ይኖር ነበር ፤ ልጆቹም የአባታቸውን መንጋ ያሰማሩ ነበር ። በዚህም ጊዜ የራሔል ታላቅ ልጅ ዮሴፍ የአሥራ ሰባት ዓመት ልጅ ነበረና አባቱ ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ ዮሴፍን ወደደ ። ዮሴፍም ከአንዳንዶች ከታላላቅ ወንድሞቹ ጋር በጎቹን ሲጠብቅ ሳለ የክፋታቸውን ወሬ ለአባታቸው ነገረ ።

ከዚህም በፊት የበኵር ልጁ ሮቤል የማይገባ ነገር በማድረግ አባቱን አሳዝኖ ነበርና ያዕቆብ ብኵርናውን ለራሔል ታላቅ ልጅ ለዮሴፍ እንዲሆን በማሰብ በብዙ ኅብር ያጌጠች ቀሚስ አሠራለት ። ወንድሞቹም አባታቸው በተለይ እንደ ወደደው ባዩ ጊዜ ዮሴፍን ጠሉት ፥ ቀኑበትም ፤ በሰላምም ሊያናግሩት አልቻሉም ።

፪ ፤ የዮሴፍ ሕልም ። ዘፍጥ. ፴፯ ፥ ፭—፲፩ ።

ዮሴፍ ሕልምን አለመ ለወንድሞቹ ፥ «በሕልሜ ያየሁትን ልንገራችሁ ፤ እነሆ እኛ በእርሻ መካከል ነዶ ስናስር ሳለን የእኔ ነዶ ቀጥ ብላ ቆመች የእናንተም ነዶዎች በዙሪያ ከብበው ለእኔ ነዶ ሰገዱ » ብሎ ነገራቸው ። ወንድሞቹም ፥ «አንተ በላያችን ትነግሥ ይሆን ? » ብለው ነቀፉት ።



www.ethiopianorthodox.org

ዮሴፍም ደግሞ ሌላ ሕልም አለመ፤ ለአባቱና ለወንድሞቹም እንዲህ ሲል ነገራቸው፤«እነሆ ፀሐይና ጨረቃ አሥራ አንድ ከዋክብትም ሲሰግዱልኝ አየሁ»። አባቱም ፡ «ይህ ያለምኸው ሕልም ምን ድር ነው ? በውኑ እኔና እናትህ ወንድሞችህም መጥተን እንሰግድልህ ይሆን? » ብሎ ገሠፀው ። ወንድሞቹም ቀኑበት ፤ አባቱ ግን ነገሩን በልቡ ጠብቆ ያስብበት ነበር ።

፫ ፤ ዮሴፍ በጉድጓድ ውስጥ ።

ዘፍጥ. ፴፯ ፡ ፲፪—፳፬ ።

ወንድሞቹ የአባታቸውን በጎች ሊያሰማሩ ሴኬም ወደ ተባለው ሥፍራ ሄዱ። እስራኤልም ዮሴፍን ፡ «ወደ ወንድሞችህ ሄደህ ደኅና እንደ ሆኑ እይ ፡ ተመልሰህም ንገረኝ » ብሎ ሰደደው ። ዮሴፍም በሴኬም ባለው ምድረ በዳ አካባቢ ሲፈልጋቸው ሳለ አንድ ሰው አገኘውና ፡ «ወደ ዶታይን እንሂድ ሲሉ ሰምቼአቸዋለሁ» አለው ። ዮሴፍም ወደ ዶታይን ተከታትሎ ሄደ ።

ወንድሞቹም በሩቅ ሳለ አዩት ፤ አንዱም ለአንዱ ፡ «ያ ባለ ሕልም ይኸው መጣ ፤ እንግደለውና ከፉ አውሬ በላው እንላለን ፤ ከሕልሞቹም የሚሆነውን እናያለን » ብለው ተማከሩበት ። ሮቤል ግን ሊያድነውና በደኅና ወደ አባቱ ሊመልሰው ስለ ወደደ ፡ « በአንድ ጉድጓድ ጣሉት እንጂ ደም አታፍስሱ » አላቸው።

ዮሴፍም ደኅንነታቸውን ለመጠየቅ ወደ ወንድሞቹ በደረሰ ጊዜ የለበሳትን በብዙ ኅብር ያጌጠች ቀሚሱን ገፈፉት ፤ ወስደውም ወደ አንድ ጉድጓድ ጣሉት ። እንጀራም ሊበሉ ተቀመጡ ።

፬ ፤ ዮሴፍ ተሸጠ ።     ዘፍጥ. ፴፯ ፡ ፳፭—፴ ።

እንጀራም ሲበሉ ሳለ ከእስማኤላውያን ወገን የነበሩ ነጋዴዎች ግመሎቻቸውን እየነዱ ሲቀርቡ አዩ ። ይሁዳም ወንድሞቹን ፡ « ወንድማችንን ገድለን ደሙን ብንሸሽግ ጥቅማችን ምንድር ነው ? ኑ ለእነዚህ ነጋዴዎች እንሽጠው ፡ እጃችንን ግን በላዩ አንጣል ፡ ወንድማችን ሥጋችንም ነውና» አላቸው ። ወንድሞቹም በዚህ ምክር ተስማሙ ፤ ዮሴፍንም ከጉድጓድ አወጡት ፤ ለነጋዴዎችም በኻያ ብር ሸጡት ። እነርሱም ዮሴፍን ይዘው ወደ ግብፅ በሚያመራው መንገድ ወሰዱት ።

ይህ ሁሉ ሲደረግ ሮቤል ከወንድሞቹ ጋር አልነበረምና ተመልሶ ሲመጣ ወደ ጉድጓዱ ሄዶ ተመለከተ ፤ ዮሴፍም በጉድጓዱ ውስጥ እንደሌለ ባየ ጊዜ ከኀዘኑ የተነሣ ልብሱን ቀደደ ፤ ወደ ወንድሞቹም ተመልሶ ፡ «ብላቴናው የለም ፤ እንግዲህ እኔ ወዴት እሄዳለሁ ?» አለ ።

፭ ፤ የያዕቆብ ኀዘን ።

ዘፍጥ. ፴፯ ፡ ፴፩—፴፮ ።

ከዚህም በኋላ ወንድሞቹ አንድ አውራ ፍየል አረዱ ፡ የዮሴፍንም ቀሚስ በፍየሉ ደም ነከሩት ። ወደ አባታቸውም ተመልሰው ፡ «ይህንን አገኘን ፤ ይህ የልጅህ ልብስ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ እስኪ እየው » አሉት ። እርሱም ፡ «የልጄ ቀሚስ ነው ፤ ክፉ አውሬ በልቶታል ፤ ዮሴፍ በእርግጥ ተቦጫጭቋል» ብሎ ልብሱን ቀደደ ፡ በወገቡም ማቅ ታጥቆ ብዙ ቀን አለቀሰ ። ወንዶች ልጆቹና ሴቶች ልጆቹም ሁሉ ሊያጽናኑት ተነሡ ፤ እርሱ ግን መጽናናትን እምቢ



ብሎ ፡ «ወደ ልጄ ወደ ሙታን ሥፍራ እያዘንሁ እወርዳለሁ» አለ ።

እንዲሁ በታላቅ ኀዘን ስለ እርሱ ሲያለቅስ እነዚያ ነጋዴዎች ግብፅ ደረሱ። በግብፅም ጲጥፋራ ለተባለው ሰው ዮሴፍን ሸጡት ። ጲጥፋራም የግብፅ ንጉሥ የፈርዖን ዘበኞች አለቃ ነበረ ።

* * *


ነፍሴ ሆይ ፡ ለምን ታዝኛለሽ ? ለምንስ ታውኪኛለሽ ?
የፊቴን መድኃኒት አምላኬን አመሰግነው ዘንድ በእግዚአብሔር ታመኚ ።     መዝ. ፵፩ (፵፪) ፡ ፲፩ ።

የጻድቃን መከራቸው ብዙ ነው ፡
እግዚአብሔርም ከሁሉ ያድናቸዋል ።
መዝ. ፴፫ (፴፬) ፡ ፲፱ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ የዮሴፍ ወንድሞች ለምን ጠሉት ?
፪ ፤ ዮሴፍ በሕልሞቹ ምን አየ ?
፫ ፤ ወንድሞቹስ ምን አደረጉት ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ ስለ ስምህ ሕያው አድርገኝ ፤
በጽድቅህም ነፍሴን ከመከራዋ አውጣት ።
መዝ. ፻፵፪ (፻፵፫) ፡ ፲፩ ።



ምዕራፍ ፵፩ ።

## ዮሴፍ ታሰረ ።

ዘፍጥ. ፴፱ ፡ ፵ ።

### ፩ ፤ ዮሴፍ በጲጥፋራ ቤት ።

ዘፍጥ. ፴፱ ፣ ፩—፮ ።

ዮሴፍ በፈርዖን ዘበኞች አለቃ በጲጥፋራ ቤት ባሪያ ሆኖ ይሠራ ጀመር ። እግዚአብሔርም ከዮሴፍ ጋር ነበረ ፤ ሥራውም ሁሉ የተከናወነለት ሰው ሆነ። ጌታውም እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር እንዳለ፥ የሚሠራውንም ሥራ ሁሉ እንደሚያከናውንለት ባየ ጊዜ ታመነበት ፤ ያለውንም ሁሉ በእጁ ሰጥቶ በቤቱ ላይ ሾመው ። ዮሴፍም በጲጥፋራ ቤትና ሀብት ላይ ተሹሞ ሁሉን ሲያስተዳድር ሳለ እግዚአብሔር የግብፃዊውን ቤት ስለ ዮሴፍ ባረከው ፤ በውጭም ሆነ በግቢ ባለው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር በረከት ሆነ ። ጲጥፋራም ይህንን አይቶ ያለውን ሁሉ ለዮሴፍ አስረከበ ፤ ከሚበላው እንጀራ በቀር ምንም የሚያውቀው አልነበረም ።

### ፪ ፤ ዮሴፍ በሐሰት ተከሰሰ ።

ዘፍጥ. ፴፱ ፣ ፯—፳፫ ።

ዮሴፍ መልከ መልካምና ውብ ሰው ነበረ ፤ የጌታው ሚስት በዮሴፍ ላይ ዓይኗን ጣለች፥ «ከእኔም ጋር ተኛ» አለችው። ዮሴፍም ፥ «ጌታዬ በቤቱ ያለውን ምንም ምን የሚያውቀው የለም ፥ ያለውንም ሁሉ ለእኔ አስረክቦኛል ፤ ሚስቱ ስለሆንሽ ከአንቺ በቀር ያልሰጠኝ ነገር የለም። እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ ? በእግዚአብሔርስ ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ ? » ብሎ በቍርጥ እምቢ አላት ። እርስዋ ግን በየዕለቱ እየደጋገመች ታባብለው ነበር ፤ በእምቢተኝነቱም ስለ ጸና በጣም ተናደደች ።

ከዕለታት አንድ ቀን ዮሴፍ ሥራውን ለመሥራት ወደ ቤት በገባ ጊዜ በቤት ማንም አልነበረም ። ሴቲቱም ምቹ ጊዜ እንዳገኘች አስተውላ ፥ «ከእኔ ጋር ተኛ » ብላ የዮሴፍን ልብስ ተጠማጥማ ያዘች ፤ እርሱ ግን ልብሱን በእጅዋ ትቶ ወደ ውጭ ሸሸ ። እርስዋም የዮሴፍን ልብስ አኖረችና ባልዋ በመጣ ጊዜ፥ «ያገባህልን ዕብራዊ ባሪያ ወደ እኔ ገባ ፥ እኔም ድምፄን ከፍ አድርጌ ብጮኽ ልብሱን በእጄ ተወና ወደ ውጭ ሸሸ » ስትል ልብሱን አሳይታ በሐሰት ዮሴፍን ከሰሰችው። ጲጥፋራም እጅግ ተቈጣ ፥ የንጉሥ እስረኞችም ወደሚታሠሩበት ግዞት ቤት አገባው ።

ዮሴፍ ግን ብቻውን አልነበረም ፤ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ሆኖ ምሕረትን አበዛለት ፤ የሚያደርገውን ሥራ ሁሉ ያቀናለት ነበርና በግዞት ቤት አለቃ ፊት ደግሞ ሞገስን ሰጠው ። አለቃውም በግዞት ቤት ካሉት እስረኞች ሁሉ ዮሴፍን ባለ አደራ አደረገው ፤ ዮሴፍም የሚያስፈልገውን ሁሉ ስለሚያደርግ አለቃው ስለ አንድ ነገር ስንኳ አያስብም ነበር ።

### ፫ ፤ የፈርዖን ሹማምንት ሕልም ።

ዘፍጥ. ፵ ።

ከዚህም በኋላ የግብፅ ንጉሥ በሁለት ሹማምንቱ ፥ በጠጅ አሳላፊዎቹ አለቃና በእንጀራ አበዛዎቹ አለቃ ላይ ተቈጣ ፥ አሳሠራቸውም ። እነርሱም በግዞት ቤት አያሌ ቀን ተቀምጠው ሳለ ዮሴፍ ያገለግላቸው ነበር ።

ከዕለታት አንድ ቀን ዮሴፍ ማልዶ ወደ እነርሱ ገባ ፤ አዝነውም አገኛቸውና፥ «ዛሬ ስለምን አዝናችኋል ?» ብሎ ጠየቃቸው ። እነርሱም ፥ «ሕልም አልመን የሚተረጕምልን አጣን» አሉት ። ዮሴፍም ፥ «ሕልምን የሚተረጕም እግዚአብሔር የሰጠው አይደለምን ? እስቲ ንገሩኝ » አላቸው ።

በዚያን ጊዜ የጠጅ አሳላፊዎቹ አለቃ እንዲህ ብሎ ሕልሙን ነገረው ፤ «በሕልሜ ሦስት ሐረግ ያለበት የወይን ዛፍ አየሁ ፤ ዛፊቱም ቅጠልና አበባ አወጣች ፥ ዘለላም አንጠለጠለች ፥ የዘለላዋም ፍሬ በሰለ ፤ ፍሬውንም ወስጄ በፈርዖን ጽዋ ጨመቅሁት ፥ ጽዋውንም ለፈርዖን ሰጠሁት ። » ዮሴፍም ፥ « ሦስት ሐረግ ሦስት ቀን ነው ፤ ከሦስት ቀን በኋላም ፈርዖን ወደ ሥፍራህ ይመልስሃል» ብሎ ከነገረው በኋላ ፥ «ነገር ግን ይህ በጎ ነገር ሲሆንልህ እኔን አስበኝ ፥ የእኔንም ነገር ለፈርዖን ነግረህ ከዚህ አውጣኝ ፤ በግዞት እኖር ዘንድ ምንም አላደረግሁም » ብሎ ለመነው ።

የእንጀራ አበዛዎቹ አለቃም በተራው ሕልሙን ሲተርክ ፥ «በሕልሜ ሦስት መሶብ ነጭ እንጀራ በራሴ ላይ ነበረ ፤ ወፎችም በራሴ ላይ ከላይኛው መሶብ ይበሉ ነበር » አለው ። ዮሴፍም ፥ « ሦስት መሶብ ሦስት ቀን ነው ፤ ከሦስትም ቀን በኋላ ይሰቅልሃል ፥ ወፎችም ሥጋህን ይበሉታል » አለው ።

በሦስተኛው ቀን ፈርዖን የተወለደበት ቀን ስለ ነበረ ግብር ተደረገ ። ፈርዖ





www.ethiopianorthodox.org

ንም የታሠሩትን ሹማምንት አስጠራቸው ፤ የጠጅ አሳላፊዎቹንም አለቃ ወደ ሥፍራው መለሰው ፤ የእንጀራ አበዛዎቹንም አለቃ ሰቀለው። ነገር ግን የጠጅ አሳላፊዎቹ አለቃ ዮሴፍን ረሳው ፤ አላሰበውምም ።

* * *

ከክፉ የጕልማሳነት ምኞት ሽሽ ፤ በንጹሕም ልብ ጌታን ከሚጠሩ ጋር ጽድቅን ፥ እምነትን ፥ ፍቅርን ፥ ሰላምን አጥብቀህ ተከተል ። ፪ ጢሞ. ፪ ፥ ፳፪ ።

ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ ፤ . . . ለጌታ ተገዙ ፤ በተስፋ ደስ ይበላችሁ ፥ በመከራ ታገሡ ፤ በጸሎት ጽኑ ። ሮሜ ፲፪ ፥ ፲፩ ፥ ፲፪ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ የጲጥፋራ ሚስት ኃጢአት እንዲሠራ ባባበለችው ጊዜ ዮሴፍ ምን መለሰላት ?

፪ ፤ ዮሴፍ በጲጥፋራ ቤት ሆነ በግዞት ቤትም ሆነ ትጉህ ሠራተኛ መሆኑ በምን ይታየናል ?

፫ ፤ ዮሴፍ የጠጅ አሳላፊዎቹን አለቃ ምን ብሎ ለመነው ? ልመናውስ ተፈጸመለት ?

ጸሎት ፤ ነፍሴ በውስጤ ባለቀች ጊዜ መንገዴን ዐወቅህ፤...

አቤቱ ፥ ስምህን እመሰግን ዘንድ
ነፍሴን ከወህኒ አውጣት ።
መዝ. ፻፵፩ (፻፵፪) ፥ ፫ ፥ ፯ ።





ምዕራፍ ፴፱ ።

## ዮሴፍ ተሾመ ።

ዘፍጥ. ፵፩ ።

፩ ፤ ፈርዖን ሕልም አለመ ።

ዘፍጥ. ፵፩ ፥ ፩—፰ ።

የፈርዖን የጠጅ አሳላፊዎቹ አለቃ ከግዞት ቤት ከወጣ ከሁለት ዓመት በኋላ ፈርዖን ራሱ ሕልምን አየ ። በሕልሙም በወንዝ ዳር ቆሞ መልካቸው ያማረ ሥጋቸውም የወፈረ ሰባት ላሞች ከወንዙ ሲወጡ ፤ ከእነርሱም በኋላ መልካቸው የከፋ ሥጋቸውም የከሳ ሌሎች ሰባት ላሞች ከወንዙ ወጥተው የወፈሩትን ሰባት ላሞች ሲውጡአቸው አየ ።

ይህንም ሕልም ካየ በኋላ ፈርዖን ነቃ ፤ ደግሞም ተኛ ሁለተኛም ሕልምን አየ ። እነሆም በአንድ አገዳ ላይ መልካም የሆኑ ሰባት እሸቶች ወጡ ፤ ከእነርሱም በኋላ በምሥራቅ ነፋስ የተመቱ ሰባት የጠወለጉ እሸቶች ወጥተው መልካሞቹን እሸቶች ዋጡአቸው ። ፈርዖንም ነቃ ፥ ካየውም ሕልም የተነሣ ነፍሱ ታወከችበት ፤ የሕልም ተርጓሚዎችንና የግብፅን ጠቢባን ሁሉ አስጠርቶ ሕልሙን ነገራቸው ፤ ነገር ግን ሕልሙን የሚተረጕም አልተገኘም ።



www.ethiopianorthodox.org

፭ ፤ ዮሴፍ በቤተ መንግሥት ።

ዘፍጥ. ፵፩ ፣ ፱—፴፯ ።

የዚያን ጊዜ የጠጅ አሳላፊዎቹ አለቃ ፈርዖንን ፣ « ዛሬ እኔ ኃጢአቴን አስ ባለሁ ፤ እኔና የእንጀራ አበዛዎቹ አለቃ በግዞት ሥፍራ በነበርን ጊዜ በአንድ ሌሊት ሕልምን አለምን ። በዚያም አንድ ዕብራዊ ባሪያ ነበረና እርሱ ሕልማችንን ተረጐመልን ፤ እንደ ተረጐመልንም እን ዲሁ ሆነ » አለው ።

ፈርዖንም ልኮ ዮሴፍን አስጠራው ፤ ከግዞት ቤትም አስቸኰሉት ፤ ጠጕሩንም ተላጨ ፣ ልብሱንም ለወጠ ፣ ወደ ፈርዖ ንም ገባ ። ዮሴፍም በፈርዖን ፊት በቆመ ጊዜ የሠላሳ ዓመት ሰው ነበረ ። ፈርዖ ንም ፣ «ሕልምን አየሁ ፣ የሚተረጕመ ውም አልተገኘም ፤ ሕልምን እንደምት ተረጕም ስለ አንተ ሰማሁ» አለው ። ዮሴ ፍም መልሶ ፣ «ይህ በእኔ አይደለም፤ እግ ዚአብሔር ግን ለፈርዖን በደኅንነት ይመ ልስለታል » አለው ።

በዚያን ጊዜም ፈርዖን ለዮሴፍ ሕል ሙን ነገረው፤ ዮሴፍም፣«የፈርዖን ሕልም አንድ ነው ፤ በዚህም ሕልም እግዚአብ ሔር የሚያደርገውን ነገር ለፈርዖን ነግ ሮታል» ብሎ ሰባቱ መልካካሞች ላሞችና እሸቶች ሰባት የጥጋብ ዓመታት ፣ ሰባ ቱም የከሱ ላሞችና የጠወለጉ እሸቶች ሰባት የራብ ዓመታት እንደ ሆኑ ነገረው። ዮሴፍም ፣ « እነሆ በግብፅ እጅግ ጥጋብ የሚሆንባቸው ሰባት ዓመታት ይመጣሉ፤ ከዚያም በኋላ እጅግ ጽኑ ራብ ይሆናል ፤ ሕልሙ ለፈርዖን ደጋግሞ መታየቱ ነገሩ የተቈረጠ ስለሆነ ነው ፣ እግዚአብሔርም ፈጥኖ ያደርገዋል » ብሎ ምድሪቱ በራብ እንዳትጠፋ በሰባቱ የጥጋብ ዓመታት ከሚገኘው ፍሬ ከአምስት እጅ አንደኛ ውን አከማችቶ ስለ ሰባቱ የራብ ዓመታት የሚያኖር አዋቂ ሰው በግብፅ ላይ እንዲ ሾም ለፈርዖን መከረው ።

፮ ፤ ዮሴፍ ተሾመ ።

ዘፍጥ. ፵፩ ፣ ፴፰—፶፪ ።

ዮሴፍም የተናገረው ነገር ለፈርዖንና ለሎሌዎቹ መልካም ሆነ ፤ ፈርዖንም ፣ «በውኑ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበ ትን እንደዚህ ያለ ሰው እናገኛለንን ? » አላቸው ። ፈርዖንም ዮሴፍን ፣ « እንደ አንተ ያለ ብልህ አዋቂም ሰው የለም ፣ እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ገልጦልሃልና። አንተ በቤቴ ላይ ተሾም ፣ ሕዝቤም ሁሉ ለአንተ ይታዘዝ ፤ እኔ በዙፋኔ ብቻ ከአ ንተ እበልጣለሁ » ብሎ ቀለበቱን ከእጁ አውልቆ በዮሴፍ እጅ አደረገው ፤ ነጭ ልብስም አለበሰው ፣ በአንገቱም የወርቅ ዝርግፍን አደረገለት ፤ በሁለተኛይቱ ሰረ ገላም አስቀመጠው ፣ አዋጅ ነጋሪም ፣ «ስገዱ» እያለ በፊቱ እንዲለፍ አደረገ ። ዮሴፍም በግብፅ ሁሉ ላይ ተሾመ ፤ ፈር ዖንም አስናት የምትባለውን ሴት አጋ ባው ።

ዮሴፍም በጥጋብ ዓመታት እጅግ ብዙ የሆነ ስንዴን በየከተማው አከማቸ። በእነዚህም ዓመታት አስናት ለዮሴፍ ሁለት ልጆች ወለደችለት ። ዮሴፍም የበ ኵር ልጁን ስም ምናሴ ብሎ ሰየመው ፣ « እግዚአብሔር መከራዬን ሁሉ የአባቴ ንም ቤት አስረሳኝ » አለ ። ምናሴ ማለ ትም ማስረሻ ማለት ነው ። ሁለተኛ ልጁ ንም ኤፍሬም ብሎ ሲሰይም ፣ «እግዚአ ብሔር በመከራዬ አገር ፍሬአማ አደረ ገኝ » አለ ። ኤፍሬም ማለትም ፍሬአማ ማለት ነው ።



ሰባቱ የጥጋብ ዓመታት አለፉ ፣ ዮሴፍም እንደ ተናገረ የራብ ዓመታት ተጀመሩ ። በየአገሩም ሁሉ ራብ ሆነ ፤ በግብፅ ምድር ግን እህል ነበረ ።

የግብፅም ሰዎች በተራቡ ጊዜ ወደ ፈርዖን ሄደው ፣ « እህል አጣን » አሉ ። ፈርዖንም ፣ «ወደ ዮሴፍ ሂዱ ፣ እርሱ የሚ ነግራችሁንም ሁሉ አድርጉ» አላቸው ። ዮሴፍም እህል ያለበትን ጎተራ ሁሉ ከፍቶ ለግብፅ ሰዎች ይሸጥ ነበር ። ከሌሎ ችም አገሮች ሁሉ የተራቡ ሰዎች ወደ ግብፅ ወደ ዮሴፍ መጥተው እህል ይገዙ ነበር ።

*    *    *

ቁይቼ እግዚአብሔርን ደጅ ጠናሁት ፣
እርሱም ዘንበል አለልኝ ጩኸቴንም ሰማኝ ።
መዝ. ፴፱ (፵) ፣ ፩ ።

በሥራው የቀለጠፈ ሰውን አይተሃልን ?
በነገሥታት ፊት ይቆማል ፤
በተዋረዱም ሰዎች ፊት አይቆምም ።
ምሳሌ ፳፪ ፣ ፳፱ ።

*    *    *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ፈርዖን በሕልም ምን አየ ?
፪ ፤ ፈርዖን ዮሴፍን ፣ «ሕልምን እንደምትተረጕም ስለ አንተ ሰማሁ » ባለው ጊዜ ዮሴፍ ምን ብሎ መለሰለት ?
፫ ፤ ዮሴፍ በግብፅ ላይ የተሾመው ምን ለመሥራት ነበረ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፣ አንተን ታመንሁ ፤ ለዘላለም አልፈር ፤ ...
በአንተ ለሚያምኑ በሰው ልጆች ፊት ያዘጋጀኻት፣
ለሚፈሩህም የሰወርኻት ፣
ቸርነትህ እንደ ምን በዛች ! መዝ. ፴ (፴፩) ፣ ፩ ፣ ፲፱ ።



ምዕራፍ ፵፫ ።

## ዮሴፍና ወንድሞቹ ።

ዘፍጥ. ፵፪ ፥ ፩—፵፭ ፥ ፲፩ ።

### ፩ ፤ የዮሴፍ ወንድሞች ግብፅ ወረዱ ።

ዘፍጥ. ፵፪ ።

በከነዓንም ራብ እጅግ ስለ ጸና ያዕቆብ
ልጆቹን ፥ « በግብፅ እህል እንዳለ ሰም
ቻለሁ ፤ እንዳንሞት ወርዳችሁ ሸም
ቱልን » ብሎ ላካቸው ፤ ብንያምን ግን
አልሰደደውም ።

አሥሩ ታላላቅ ወንድማሞችም ወደ
ግብፅ ደረሱ ፤ ለእህል ሸመታ ከመጡት
ጋር ወደ ገዢው ገብተው በምድር ላይ
በግንባራቸው ሰገዱለት ። ዮሴፍም አወ
ቃቸው ፤ ስለ እነርሱም አይቶት የነበረ
ውን ሕልም አሰበ ፤ እነርሱ ግን አላወቁ
ትም ።

ዮሴፍም የተናደደ መስሎ ፥ « እና
ንተ ከወዴት መጣችሁ ፤ ሰላዮች ናችሁ፥
የአገሩን ዕራቁትነት ልታዩ መጥታች
ኋል » አላቸው ። እነርሱም ፥ «ጌታ ሆይ
አይደለም ፤ እኛ አሥራ ሁለት ወንድማ
ሞች የአንድ ሰው ልጆች ነን ፤ ታናሹም
እነሆ ከአባታችን ጋር በከነዓን ነው፥ አን
ዱም ጠፍቶአል » አሉት ። ዮሴፍም ፥
« ከእናንተ አንዱን ስደዱ ወንድማችሁ
ንም ይዞ ይምጣ ፤ በዚህም ትፈተናላችሁ፤
ታናሽ ወንድማችሁ ካልመጣ በቀር
ከዚህ አትወጡም » ብሎ አሳሠራቸው ።

በሦስተኛውም ቀን ዮሴፍ ፥ «እንደ
ቃሌ ብታደርጉ ትድናላችሁ ፥ እኔ እግዚ
አብሔርን እፈራለሁና ። ከእናንተ አንዱ
በዚህ ይታሠር ፤ እናንተ ግን ሄዳችሁ ለቤ
ታችሁ ራብ እህል ውሰዱ ፥ ታናሽ ወንድ
ማችሁንም ይዛችሁ ተመለሱ » ብሎ ስም
ዖንን ለይቶ አሠረው ። እነርሱም እርስ
በርሳቸው ፥ «በእውነት ወንድማችንን
በድለናል ፥ ጭንቀቱንም ባየን ጊዜ አል
ራራንለትም ፤ ስለዚህ ይህ መከራ መጣ
ብን » ተባባሉ ። ሮቤልም ፥ « ብላቴና
ውን አትበድሉ ብያችሁ አልነበርሁምን?
አሁን ደሙ ይፈላለገናል » አላቸው ።
ዮሴፍም ነገራቸውን እንዳስተዋለ አላወ
ቁም ፤ እርሱም ዘወር ብሎ አለቀሰ ። አቁ
ማዳቸውን ሲሞሉ ብራቸውን በአቁማዳ
ዎቻቸው እንዲመልሱላቸው የመንገድም
ሥንቅ እንዲሰጡአቸው አገልጋዮቹን
አዘዘ ።

ዘጠኙ ወንድማሞችም ወደ አባታ
ቸው በመጡ ጊዜ ፥ «የአገሩ ጌታ በክፉ
ንግግር ተናገረን » ብለው ዮሴፍ ያላቸ
ውን ሁሉ አወሩለት ። ያዕቆብም፥ «ልጅ
አልባ አስቀራችሁኝ ፤ ዮሴፍ የለም ፥ ስም
ዖንም የለም ፥ ብንያምንም ትወስዱብኛ
ላችሁ ፤ ይህ ሁሉ በእኔ ላይ ደረሰ» ብሎ
ብንያምን ለመስደድ እምቢ አለ ።

### ፪ ፤ ሁለተኛ ወደ ግብፅ ወረዱ ።

ዘፍጥ. ፵፫ ፥ ፩—፵፭ ፥ ፲፩ ።

ራብም ጸና ፤ ከግብፅም ያመጡት እህል
እያለቀ በሄደ ጊዜ ያዕቆብ ልጆቹን ፥
« እንደገና ሄዳችሁ እህል ሸምቱልን »
አላቸው ። ይሁዳም ፥ «ያ ሰው ፥ ወንድማ
ችሁ ከእናንተ ጋር ካልሆነ ፊቴን አታ
ዩም ብሎ በብርቱ ቃል አስጠነቀቀን »
አለ ። ያዕቆብም ፥ «ሌላ ወንድም አለን
ብላችሁ ለምን ነገራችሁት ?» አላቸው።
እነርሱም ፥ «ያ ሰው ፥ አባታችሁ ገና በሕ
ይወት ነው ? ወንድምስ አላችሁ ? እያለ
ስለ እኛና ስለ ወገናችን ፈጽሞ ጠየቀን»
አሉት ። ይሁዳም ፥ « በራብ እንዳንሞት
ተነሥተን እንሂድ ፤ እኔ ስለ ብንያም እዋ
ሳለሁ » አለ ። ያዕቆብም ፥ «ለዚያ ሰው
እጅ መንሻ ውሰዱ ፤ ከእህሉ ጋር የተመ
ለሰውንም ብር ይዛችሁ ውረዱ ። ሁሉን
የሚችል አምላክም በዚያ ሰው ፊት ምሕ
ረትን ይስጣችሁ » ብሎ ብንያምን ከእነ
ርሱ ጋር ላከው ። ተነሥተውም ሄዱ ፤
በዮሴፍም ፊት ቆሙ ።

ዮሴፍም ባያቸው ጊዜ የቤቱን
አዛዥ ፥ «እነዚያ ሰዎች ከእኔ ጋር ምሳ
ይበላሉና ወደ ቤቴ አስገባቸው» አለው።
የቤቱም አዛዥ በመልካም ተቀበላ
ቸው ፥ ስምዖንንም አወጣላቸው ። ዮሴፍም
በመጣ ጊዜ እጅ መንሻውን አቅርበው
ሰገዱለት ፤ እርሱም ፥ «የነገራችሁኝ ሽማ
ግሌ አባታችሁ ደኅና ነውን ? » አላቸው።
የእናቱን ልጅ ብንያምንም አይቶ ፥ «ልጄ
ሆይ ፥ እግዚአብሔር ይባርክህ » አለው ፤
ወደ እልፍኙም ለመግባት ቸኩሎ በዚያ
አለቀሰ ። ፊቱንም ታጥቦ ወጣና ፥ «እን
ጀራ አቅርቡ » ብሎ ጋበዛቸው ፤ እነር
ሱም ከእርሱ ጋር ደስ አላቸው ።

ዮሴፍ ግን የወንድሞቹን አሳብ አረ
ጋግጦ ማወቅ ስለሚያስፈልገው የቤ
ቱን አዛዥ ፥ « በአቁማዳዎቻቸው እህል
ስትሞላ ብራቸውንም ጨምረህ ስትመ
ልስ የታናሹ በሆነው አቁማዳ አፍ
ጽዋዬን ደብቅ » አለው ። በማግሥ
ቱም ወንድሞቹ አህዮቻቸውን ይዘው
ከሄዱ በኋላ ዮሴፍ የቤቱን አዛዥ ፥ «ተነ





www.ethiopianorthodox.org

ሥተህ ተከተላቸውና ፥ ጽዋውን ለምን ወሰዳችሁ ? በላቸው » ብሎ ላከው ። እርሱም ደረሰባቸው ፤ ከታላቁም ጀምሮ እስከ ታናሹ አቁማዳዎቻቸውን በረበረ ፤ ጽዋውም በብንያም አቁማዳ ተገኘ። በዚያን ጊዜ ወንድማሞቹ ደንግጠው ልብሳቸውን ቀደዱ ፤ ወደ ዮሴፍም በተመለሱ ጊዜ ይሁዳ ፥ « ለጌታዬ ምን እንመልሳለን ? እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ገልጦብናልና እኛ ለጌታዬ ባሪያዎች ነን » አለው ። ዮሴፍም መልሶ ፥ «ባሪያ የሚሆነኝ ጽዋው የተገኘበት ብቻ ነው ፤ እናንተ ወደ አባታችሁ ሂዱ » አላቸው ።

በዚያን ጊዜ ይሁዳ ቀርቦ ፥ « ሽማግሌ አባቴ በኀዘን እንዳይሞት እኔ በብላቴናው ፈንታ ባሪያ ልሁን ፤ እርሱም ከወንድሞቹ ጋር ይውጣ » ብሎ አጥብቆ ለመነው ። ዮሴፍም የይሁዳን እውነተኛነት የልመናውንም ቅንነት በሰማ ጊዜ ሊታገሥ አልቻለምና ሰዎችን ሁሉ አስወጥቶ ወንድሞቹን ፥ « እኔ ዮሴፍ ነኝ ፤ አባቴ እስከ አሁን በሕይወት ነውን ? » ብሎ አለቀሰ ። እነርሱም ደንግጠው እንደ ፈሩት ባየ ጊዜ ፥ «ወደዚህ ስለ ሸጣችሁኝ አትዘኑ ፤ እግዚአብሔር ከሞት እንዳድናችሁ ላከኝ እንጂ እናንተ ወደዚህ የላካችሁኝ አይደላችሁም» ብሎ አጽናናቸው ፤ እያለቀሰም ሳማቸው ። ከዚያም በኋላ ወንድሞቹ ከእርሱ ጋር ተጫወቱ ።

*   *   *

ክፉን በክፉ ፈንታ ወይም ስድብን በስድብ ፈንታ አትመልሱ በዚህ ፈንታ ባርኩ እንጂ ፥ በረከትን ልትወርሱ ለዚህ ተጠርታችኋልና ።
፩ ጴጥ· ፫ ፡ ፱ ።

እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ፥ ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን ።
ሮሜ ፰ ፡ ፳፰ ።

*   *   *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ የዮሴፍ ወንድሞች ለምን ወደ ግብፅ ወረዱ ?
፪ ፤ ዮሴፍ ፥ ብንያምን ትተው ወደ አባታቸው እንዲመለሱ ለወንድሞቹ ባላቸው ጊዜ ይሁዳ ምን አደረገ ?
፫ ፤ ዮሴፍ ፥ «እኔ ዮሴፍ ነኝ » በማለቱ ወንድሞቹ እንደፈሩ ባየ ጊዜ በምን ቃል አጽናናቸው ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፥ ባሪያዎችህንና ሥራህን እይ ፥
የአምላካችን የእግዚአብሔር ብርሃን በላያችን ይሁን ።
የእጆቻችንንም ሥራ በላያችን አቅና ።
መዝ· ፹፱ (፺) ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ።





## ምዕራፍ ፵፩ ።

## ያዕቆብ ወደ ግብፅ ወረደ ።

ዘፍጥ· ፵፭—፵፯ ።

### ፩ ፤ ዮሴፍ አባቱን አስጠራ ።

ዘፍጥ· ፵፭ ፡ ፱—፳፰ ።

ዮሴፍ ወንድሞቹን ፥ « ፈጥናችሁ ወደ አባቴ ሄዳችሁ ፥ ልጅህ ዮሴፍ ፥ እግዚአብሔር በግብፅ ላይ ጌታ አደረገኝ ፤ ወደ እኔም ና ፥ እኔም እመግብሃለሁ ይላል በሉት » አላቸው ። ፈርዖንም ደስ ተሰኝቶ ዮሴፍን ፥ «ለወንድሞችህ ፥ ለሕፃናቶቻችሁና ለሴቶቻችሁም ሰረገሎችን ውሰዱ ፤ አባታችሁንና ቤተ ሰቦቻችሁንም ሁሉ ይዛችሁ ኑ ፤ የግብፅ በረከት ሁሉ ለእናንተ ነውና በላቸው» አለው ።

አሥራ አንዱ ወንድማሞችም ወደ አባታቸው በመጡ ጊዜ ፥ « ዮሴፍ ገና በሕይወት ነው » ብለው ነገሩን ሁሉ ሲያወሩለት ከድንጋጤ የተነሣ አላመናቸውም ። ነገር ግን ዮሴፍ የላከለትን ሰረገሎች ባየ ጊዜ የያዕቆብ ሕይወቱ ታደሰች፥ አምኖም ፥ «ልጄ ገና በሕይወት ከሆነ ይበቃኛል ፤ ሳልሞት እንዳየው እሄዳለሁ » አለ ።

### ፪ ፤ ያዕቆብ በግብፅ ኖረ ።

ዘፍጥ· ፵፮ ፡ ፩—፵፯ ፡ ፲፪ ፡ ፳፯ ፡ ፳፰ ።

ያዕቆብም ለእርሱ ያለውን ሁሉ ይዞ ተነሣ ። በሌሊትም ራእይ እግዚአብሔር ፥ «የአባቶችህ አምላክ እግዚአብሔር ነኝ ፥ በግብፅ ትልቅ ሕዝብ አደርግሃለሁና ወደ



www.ethiopianorthodox.org

ዚያ ለመውረድ አትፍራ ። እኔ ወደ ግብፅ አብሬህ እወርዳለሁ ፤ ከዚያም ደግሞ አወጣሃለሁ » አለው ።

ያዕቆብም ግብፅ በገባ ጊዜ ይሁዳን አስቀድሞ ወደ ዮሴፍ ላከው ፤ ዮሴፍም ሰረገላውን አዘጋጀ አባቱንም ሊገናኘው ወጣ ። ባየውም ጊዜ በአንገቱ ላይ ወደቀ፣ አቅፎትም ረጅም ጊዜ አለቀሰ ። አባቱም፣ «አንተ ገና በሕይወት ሳለህ ፊትህን አይ ቼሃለሁና አሁን ልሙት» አለው ።

ዮሴፍም ከወንድሞቹ አምስቱን ወስዶ ወደ ፈርዖን አገባቸው ፤ ፈርዖንም ለከብቶቻቸው ምቹ በሆነ ሥፍራ በጌሤም እንዲቀመጡ ፈቀደላቸው ። ዮሴፍም አባ ቱን አስገብቶ በፈርዖን ፊት አቆመው ፤ ያዕቆብም ፈርዖንን ባረከው ። ያዕቆብም በግብፅ አሥራ ሰባት ዓመት ኖረ ፤ ልጆ ቹም እጅግ እየበዙ ሄዱ ።

፫ ፤ ያዕቆብ የዮሴፍን ልጆች ባረካቸው ።

ዘፍጥ. ፵፰ ።

የያዕቆብም የሞቱ ቀን በቀረበ ጊዜ ዮሴፍ ሁለቱን ልጆቹን ፣ ምናሴንና ኤፍሬምን ይዞ ወደ አባቱ አገባቸው ። ያዕቆብም ታምሞ ነበርና ከሽምግልና የተነሣ ለማ የት አልቻለም ነበር ፤ ነገር ግን ፣ ዮሴፍ መጣ በተባለ ጊዜ ተጠናክሮ በአልጋው ላይ ተቀመጠ ። እርሱም ፣ «ሁሉን የሚ ችል አምላክ በከነዓን ተገለጠልኝና ፣ እነሆ ፍሬያማ አደርግሃለሁ ፣ ይህችንም ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ አለኝ ። አሁንም በግ ብፅ የተወለዱልህ ልጆች ፣ ምናሴና ኤፍ ሬም እንደ ሮቤልና እንደ ስምዖን የእኔ ይሁኑ ። እንድባርካቸውም አቅርብልኝ» አለው ።

ዮሴፍም ኤፍሬምን በቀኙ በያዕቆብ ግራ ፣ ምናሴንም በግራው በያዕቆብ ቀኝ አድርጎ አቀረባቸው ። ያዕቆብ ግን እጆ ቹን አስተላልፎ ቀኝ እጁን ዘርግቶ በኤፍ ሬም ራስ ላይ ፣ ግራውንም በምናሴ ራስ ላይ አኖረና ፣ «አባቶቼ አብርሃምና ይስ ሐቅ በፊቱ የሄዱለት ፣ ከታናሽነቴ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የመገበኝ እግዚአብሔር፣ ከክፉ ሁሉ ያዳነኝ መልአክ ፣ እርሱ እነ ዚህን ብላቴኖች ይባርክ » አለ ።

ዮሴፍም አባቱ የቀኝ እጁን በኤፍ ሬም ራስ ላይ እንዳደረገ ባየ ጊዜ ፣ «አባቴ ሆይ ፣ እንዲህ አይደለም ፤ በኵሩ ይህ ነውና » አለው ። አባቱም ፣ «አወ ቅሁ ልጄ ሆይ ፣ አውቅሁ ፤ ምናሴ ደግሞ ታላቅ ይሆናል ፤ ታናሽ ወንድሙ ግን ከእርሱ ይበልጣል » አለው ።

፬ ፤ ያዕቆብ ትንቢት ተናግሮ ልጆቹን ባረከ ።

ዘፍጥ. ፵፱ ፣ ፩—፳፰ ።

ያዕቆብም ልጆቹን ሰብስቦ ፣ «በኋለ ኛው ዘመን የሚያገኛችሁን እነግራች ኋለሁ » ብሎ ስለ እያንዳንዳቸው ተናግሮ እያንዳንዳቸውን እንደ በረከታቸው ባረካ ቸው ። በተለይም አራተኛውን ልጁን ይሁዳንና ብኵርና የተሰጠውን ዮሴፍን በልዩ በረከት ባረካቸው ። ይሁዳንም ፣

«ይሁዳ ፣ ወንድሞችህ አንተን ያመሰ
ግኑሃል ፤ . . .
ይሁዳ የአንበሳ ደቦል ነው ፤ . . .
በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም፣
የገዢም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል ፣
ገዢ የሆነው እስኪመጣ ድረስ ፤
የአሕዛብ መታዘዝም ለእርሱ ይሆናል»

በማለት የምድር ነገዶች ሁሉ የሚባረኩ በት ገዢና መድኅን የሆነው የአብርሃም ዘር ከይሁዳ ቀውልዶ እንደሚወለድ አመለከተ ።



፭ ፤ ያዕቆብና ዮሴፍ ስለ መቃብራቸው አዘዙ ።

ዘፍጥ. ፵፱ ፣ ፳፱—፺ ፣ ፶፯ ።

ያዕቆብ ልጆቹን ፣ «አብርሃም ለመቃ ብር ርስት በገዛው ዋሻ በከነዓን እንጂ በግብፅ አትቅበሩኝ » ብሎ ካዘዛቸው በኋላ ሞተ ። የልቅሶውም ወራት ካለፈ በኋላ ወደ ከነዓን ወሰዱት ፣ አባቶቹ በተ ቀበሩበትም ፣ አብርሃም ለሚስቱ ለሣራ መቃብር በገዛው ዋሻ ቀበሩት ።

ዮሴፍም የመቶ አሥር ዓመት ዕድሜ እስኪሆነው ድረስ ኖረ ። ዮሴፍም ወንድ ሞቹን ፣ «እኔ እሞታለሁ ፤ እግዚአብሔ ርም ይጐበኛችኋል ከግብፅም አውጥቶ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም ወደ ማለላቸው ምድር ያደርሳችኋል ። እግዚ አብሔርም ሲያስባችሁ አጥንቴን ከዚህ እንሥታችሁ ውሰዱ እንጂ ፣ በግብፅ አት ቅበሩኝ » ብሎ አማላቸው ። ከሞተም በኋላ የዮሴፍን ሬሳ በሽቱ አሹት ፤ ከግ ብፅ እስከሚወጡበት ቀን ድረስ በሚጠ በቅበት ሣጥን አኖሩት ።

* * *

እስከ ሽምግልና ድረስ እኔ ነኝ ፣ እስከ ሽበትም ድረስ እሸከማችኋለሁ ።

ኢሳ. ፵፮ ፣ ፬ ።

ለዓለምና ለዘለዓለም ይህ አምላካችን ነው ፤
እርሱም ለዘለዓለም ይመራናል ።

መዝ. ፵፯ (፵፰) ፣ ፲፬ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ያዕቆብ ወደ ግብፅ በወረደ ጊዜ እግዚአብሔር ምን ተስፋ ሰጠው ?

፪ ፤ ያዕቆብና ልጆቹ በግብፅ በምን ክፍለ አገር ተቀመጡ ?

፫ ፤ ዮሴፍ ስለ አጽሙ ምን አዘዘ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፣ ኃጢአትንስ ብትጠባበቅ ፣
አቤቱ ፣ ማን ይቆማል ?
ይቅርታ ከአንተ ዘንድ ነውና ።
አቤቱ ፣ ስለ ስምህ ተስፋ አደረግሁህ ፤
ነፍሴ በሕግህ ታገሠች ።

መዝ. ፻፳፱ (፻፴) ፣ ፫—፭ ።



## ምዕራፍ ፵፰ ።
## የሙሴ ልደትና እድገት ።
ዘጸ. ፩ ፡ ፪ ።

፩ ፤ የእስራኤል ባርነት ። ዘጸአት ፩ ።

ወደ ግብፅ የገቡ የያዕቆብ ልጆችና የልጆቹ ልጆች ሰባ ነበሩ ፤ በግብፅም ሳሉ እጅግ እየበዙ ሄዱ ፡ ትልቅ ሕዝብም ሆኑ ።

ከብዙ ዘመን በኋላ ዮሴፍን ያላወቀ ሌላ ንጉሥ ተነሣ።እርሱም ግብፃውያንን፥ «እነሆ በመካከላችን የሚኖሩ የእስራኤል ሕዝብ ከእኛ ይልቅ በዝተዋልና እንዳይነሡብን ከአገራችንም እንዳይወጡ ኑ እናስጨንቃቸው» ብሎ በብርቱ ሥራ በመከራም ሕይወታቸውን የሚያስመርሩአቸው በግድ የሚያሠሩአቸው ግብር አስገባሪዎችን በእስራኤላውያን ላይ ሾመባቸው ፤ ጽኑ ከተሞችንም እንዲሠሩ በእርሻም እንዲደክሙ አስገደዱአቸው ። ነገር ግን ምንም በብዙ ቢያስጨንቋቸው የእስራኤል ሕዝብ እጅግ እየበዙ ሄዱ ።

ፈርዖንም ሕዝቡ እንዳልደከመ ባየ ጊዜ ፡ «ከእስራኤል ሕዝብ የሚወለደውን ወንድ ልጅ ሁሉ ወደ ወንዝ ጣሉት» ብሎ አወጀ ።



፪ ፤ የሙሴ ልደት ።

ዘጸ. ፪ ፡ ፩—፲ ፤ ዘኍ. ፳፮ ፡ ፶፱ ፤ ዕብራ. ፲፩ ፡ ፳፫ ፤ የሐዋ. ፯ ፡ ፳—፳፪ ።

በዚያ አስቸጋሪና አደገኛ ጊዜ ዮካብድ የምትባል ሴት እንበረም ለተባለው ባልዋ ወንድ ልጅ ወለደች ። ሁለቱም ከሌዊ ወገን ነበሩ ፤ ማርያም የምትባል ሴት ልጅ ፡ አሮንም የሚባል የሦስት ዓመት ወንድ ልጅ ነበራቸው ።

ወላጆቹም የተወለደላቸውን የሕፃኑን መልካምነት ባዩ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ይጠብቀዋል ብለው የንጉሡን ቍጣ ሳይፈሩ እስከ ሦስት ወር ድረስ በቤት ሸሸጉት ። ሕፃኑ እያደገ ሲሄድ ግን ልትሸሽገው እንዳልቻለች ዐውቃ ዮካብድ ፡ በወንዝ ዳር አስቀምጠዋለሁ ብላ ከደንገል የተሠራ ሣጥን ወሰደች ፡ በውኃ እንዳይሰጥምም በዝፍት ለቀለቀችው ፤ ሕፃኑንም አኖረችበት ፡ በወንዝም ዳር ባለው በቄጠማ ውስጥ አስቀመጠችው ። እኅቱም ማርያም በሩቅ ቆማ የሚደረግበትን ለማወቅ ትጉበኘው ነበር ።

እነሆም የፈርዖን ልጅ ደንገጥሮችዋን አስከትላ ልትታጠብ ወደ ወንዝ ወረደች ፤ በወንዙም ዳር ስትሄድ በቄጠማው ውስጥ ሣጥኑን አይታ አስመጣችው ። ሣጥኑንም በከፈተችው ጊዜ ሕፃኑን አየች፤ እርሱም ያለቅስ ነበር ። እርስዋም አዝና ለች ፡ «ይህ ከዕብራውያን ልጆች አንዱ ነው » አለች ።

እኅቱም የሆነውን ባየች ጊዜ ቀርባ፥ «ሕፃኑን እንድታሳድግልሽ ሄጄ ሞግዚት ልጥራልሽ ? » ብላ ጠየቀች ። የፈርዖን ልጅም ፡ « ሂጂ » አለቻት ፤ ሄዳም እናትዋን ጠራች ። ዮካብድም በመጣች ጊዜ የፈርዖን ልጅ ፡ «ይህንን ሕፃን ወስደሽ በሞግዚትነት አሳድጊልኝ ፡ ዋጋሽንም እሰጥሻለሁ » አለቻት ። እናቱም ልጅዋን ይዛ ወደ ቤትዋ በደስታ ስትሄድ ከሞት የጠበቀውን አምላክ እንዴት ታመሰግን ይመስላችኋል !

ሕፃኑም አደገ ፤ ጊዜውም ሲደርስ እናቱ ወደ ፈርዖን ልጅ ቤት አመጣችው፤ ለእርስዋም ልጅ ሆነላት ። ስሙንም ሙሴ ብላ ጠራችው ፤ ትርጉሙም ከውኃ የተገኘ ማለት ነው ።

ሙሴም የፈርዖን የልጅ ልጅ ተብሎ የግብፃችን ትምህርትና ጥበብ ሁሉ እየተማረ አደገ ፤ በቃሉና በሥራውም የበረታ ሆነ ።

፫ ፤ የሙሴ ስደት ።

ዘጸ. ፪ ፡ ፲፩—፲፭ ፤ ዕብራ. ፲፩ ፡ ፳፬—፳፮ ፤ የሐዋ. ፯ ፡ ፳፩ ።

ሙሴም በግብፅ ቤተ መንግሥት ሲኖር ሳለ በጭንቀት የነበሩት ወንድሞቹን ያስብ ነበርና እግዚአብሔር በእርሱ እጅ ከባርነት እንደሚያድናቸው አስተውሎ ሊጐበኛቸው ወጣ ። የሥራቸውንም ክብደት ሲመለከት ሳለ አንድ ግብፃዊ አንዱን ዕብራዊ ሲመታ አየና ግብፃዊውን ገደለ ፤ በአሸዋ ውስጥም ሸሸገው።

በማግሥቱም ሙሴ እንደገና ወጣ ፡ ሁለት ዕብራውያን ሰዎችም ሲጣሉ አየና ሊያስታርቃቸው ወድዶ በዳዩን ፡ «ለምን ባልንጀራህን ትመታዋለህ ? » አለው ። እርሱም ፡ «በእኛ ላይ አንተን አለቃ ወይስ ዳኛ ማን አደረገህ ? ወይስ ግብፃዊውን እንደ ገደልኸው ልትገድለኝ ትፈልጋለህ ? » አለው ።

ሙሴም ያደረገው ነገር እንደ ታወቀ ባስተዋለ ጊዜ ፈራ ፤ ፈርዖንም ሊገድለው እንደሚፈልግ በሰማ ጊዜ በኤርትራ ባሕር ማዶ ወዳለው ምድያም ወደ ተባ



www.ethiopianorthodox.org

ለው አገር ኰብልሎ ሄደ ። በልቡም፥ ወን ድሞቹ እግዚአብሔር በእጁ እንደሚያድ ናቸው አላስተዋሉም ፤ እኔም ልረዳቸው አልቻልሁም ብሎ አዘነ ።

* * *

እግዚአብሔር መልካም ነው ፡ በመከራ ቀንም መሸሸጊያ ነው ፤ በእርሱ የሚታመኑትንም ያውቃል ። ናሆም ፩ ፡ ፯ ።

ሙሴ ካደገ በኋላ . . . ከግብፅ ብዙ ገንዘብ ይልቅ . . . ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ ፤ ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመልክቶአልና ።

ዕብራ. ፲፩ ፡ ፳፬—፳፯ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ሙሴ በተወለደ ጊዜ እስራኤላውያን በምን ሁኔታ ላይ ነበሩ ? ስለ ሕፃናቶቻቸውስ ምን ትእዛዝ ወጥቶ ነበር ?
፪ ፤ የሙሴ እናት ሕፃንዋን ለማዳን ስታስብ ምን አደረገች?
፫ ፤ ሕፃኑንስ ያገኘችና ያሳደገች ማን ናት ?
፬ ፤ ሙሴ ካደገ በኋላ በምን ምክንያት ከግብፅ ሸሸ ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ በመከራ መካከል እንኳ ብሄድ ፥ አንተ ሕያው ታደርገኛለህ ፤ . . .
ቀኝህም ታድነኛለች ። መዝ. ፻፴፰ (፻፴፯) ፡ ፯ ።





ምዕራፍ ፴፮ ።

## የሙሴ መጠራት ።

ዘጸ. ፫ ፡ ፩ ።

### ፩ ፤ ሙሴ በምድያም ።

ዘጸ. ፪ ፡ ፲፭—፳፪ ፤ ፲፰ ፡ ፪—፬ ።

ሙሴ ወደ ምድያም ደርሶ በአንድ ውኃ ጉድጓድ አጠገብ ተቀምጦ ሳለ የአባታቸውን በጎች እንዲያጠጡ ዮቶር ለተባለው ለምድያም ካህን የነበሩት ሰባት ሴቶች ልጆች መጥተው ውኃ ቀድተው የውኃውን ገንዳ ሞሉ ። በዚያን ጊዜ እረኞች መጥተው ገፉአቸው ፤ ሙሴ ግን ተነሥቶ ሴቶቹን ረዳቸው፡ በጎቻቸውንም አጠጣላቸው።ሴቶቹም ወደ አባታቸው በመጡ ጊዜ ነገሩን ሁሉ ነገሩት ። እርሱም ፡ «የረዳችሁን ሰው ጥሩት ፡ እንጀራም ይብላ » አላቸው ። ሙሴም ከዮቶር ጋር ለመቀመጥ ወደደ ፤ በጎቹንም ይጠብቅ ጀመር። ዮቶርም ልጁን ሲፓራን ለሙሴ ሚስት እንድትሆነው ሰጠው ። ሲፓራም ለሙሴ ልጅ ወለደችለት ፤ እርሱም ፡ « በሌላ ምድር እንግዳ ነኝ» ብሎ የልጁን ስም ጌርሳ አለው ። ጌርሳ ማለትም እንግዳ ማለት ነው ። ሙሴም ፡ ሲፓራ የወለደችለትን ሁለተኛውን ልጅ ኤልዓዛር ብሎ ጠራው ። ኤልዓዛር ማለትም እግዚአብሔር ረዳቴ ነው ማለት ነው ። ሙሴም



www.ethiopianorthodox.org

ከዮቶር ጋር ብዙ ዓመት ኖረ ፤ ሊገድለ ውም ይፈልግ የነበረው የግብፅ ንጉሥ ሞተ ።

፪ ፤ ሙሴ ያየው ነበልባል ።

ዘጸ. ፫ ፥ ፩—፮ ።

ሙሴም የአማቱን በጎች ሲጠብቅ ሳለ ኮሬብ ወደ ተባለው ተራራ መጣ ። የእግዚአብሔርም መልአክ በእሳት ነበ ልባል በእሾህ ቊጥቋጦ መካከል ታየው ፤ እነሆም ቊጥቋጦው በእሳት ሲነድ ሳይቃ ጠል አየው ።

ሙሴም የማይቃጠለውን ቊጥቋጦ ባየ ጊዜ ፥ «ልሂድና ይህን ታላቅ ራእይ ልይ» አለ ። እግዚአብሔርም ቊጥ ቋጦውን እንዲመለከት እንደ መጣ ባየ ጊዜ ከቊጥቋጦው ውስጥ ጠርቶ ፥ «ሙሴ ሙሴ ሆይ» አለ ። እርሱም ፥ «እነሆኝ» አለ ። እግዚአብሔርም ፥ «ወደዚህ አት ቅረብ ፤ የቆምህባት ሥፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አው ልቅ » አለው ። ሙሴም ወደ እግዚአብ ሔር እንዳያይ ፈርቶአልና ፊቱን ሸፈነ ።

፫ ፤ እግዚአብሔር ከነበልባል ጠራው ።

ዘጸ. ፫ ፥ ፯—፳፪ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን ፥ « በግብፅ ያለ ውን የሕዝቤን መከራ አየሁ ጩኸታ ቸውንም ሰማሁ ፤ ከግብፃውያንም እጅ እንዳድናቸው ወደ መልካሚቱም ወደ ከነዓን አገር እንዳወጣቸው ወረድሁ ። አሁንም ና ፥ ሕዝቤን ከግብፅ እንድታ ወጣ ወደ ፈርዖን እልክሃለሁ » አለው ። ሙሴም ደንግጦ ፥ «ወደ ፈርዖን የምሄድ እስራኤልንም ከግብፅ የማወጣ እኔ ማን ነኝ ? » አለው ። እግዚአብሔርም ፥ «በእ ውነት እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ ፤ ሕዝቤ ንም ከግብፅ ባወጣህ ጊዜ በዚህ ተራራ ላይ ለእኔ ትገዛላችሁ » አለው ።

ሙሴም ፥ «እኔ ወደ እስራኤላውያን መጥቼ ፥ የአባቶቻችሁ አምላክ ላከኝ ስላቸው እነርሱም ፥ ስሙስ ማን ነው ? ቢሉኝ ምን እላቸዋለሁ ?» አለው ። እግ ዚአብሔርም ፥ «ያለና የሚኖር እኔ ነኝ ፤ ለእስራኤላውያንም እንዲህ ትላለህ ፥ ያለና የሚኖር የተባለው የአብርሃም የይ ስሐቅም የያዕቆብም አምላክ ላከኝ ፤ ከግ ብፅም መከራ ወተትና ማር ወደምታፈ ስስ ወደ ከነዓን አገር አወጣችኋለሁ ብሎ ተገለጠልኝ ብለህ ንገራቸው ። » እግዚ አብሔርም የሚሆነውን ነገር ለሙሴ ገልጦ ፥ «ወደ ፈርዖን ገብታችሁ ፥ ለእግ ዚአብሔር እንድንሠዋ የሦስት ቀን መን ገድ በምድረ በዳ እንሂድ ስትለው እርሱ እንደማይለቃችሁ እኔ አውቃለሁ። እኔም እጄን ዘርግቼ በተአምራቴ ግብፅን እመ ታለሁ ፤ ከዚያም በኋላ ይለቃችኋል » አለው ።

፬ ፤ ለሙሴ የተሰጡ ምልክቶች ።

ዘጸ. ፬ ፥ ፩—፳፫ ።

ሙሴም ገና ስለሚፈራ እግዚአብሔር ፥ « በትርህን ወደ መሬት ጣላት» አለው ። በጣላትም ጊዜ እባብ ሆነች ፥ ሙሴም ሸሻት ። እግዚአብሔርም ፥ «እጅህን ዘር ግተህ ጅራቷዋን ያዝ » አለው ፤ በያዛትም ጊዜ በትር ሆነች ። እግዚአብሔርም ፥ «እጅህን ወደ ብብትህ አግባ » አለው ። አግብቶም ባወጣው ጊዜ እጁ ለምጽ ሆነች ። እርሱም ፥ «እጅህን ወደ ብብትህ መልስ » አለው ፤ መልሶም ባወጣት ጊዜ እንሆ ተመልሳ ገላውን መሰለች ። እግዚ አብሔርም ፥ «ባያምኑብህ እነዚህን ምል ክቶች አሳይ ፤ በሚያዩበት ጊዜ ያምናሉ ። ባያምኑም ከወንዝ ውኃን ወስደህ በመ ሬት ላይ አፍስሰው ደምም ይሆናል» አለው ።

ሙሴ ግን ገና ፈርቶ ስለነበረ ፥ «እኔ አፈ ኰልታፋ ሰው ነኝ » አለ ። እግዚአብሔ ርም ፥ « እኔ ከአፍህ ጋር እሆናለሁ ፥ የም ትናገረውንም አስተምርሃለሁ » አለው ። ሙሴም ፥ «ጌታ ሆይ ፥ በምትልከው ሰው እጅ እንድትልክ እለምንሃለሁ » አለ ። የእግዚአብሔርም ቊጣ በሙሴ ላይ ነደደ ፥ አለውም ፥ «እኔ ወንድምህን አሮንን እን ዲገናኝህ እልክልሃለሁ ፤ እርሱም አፍ ይሆ ንልሃል ። አሁንም ተአምራት የምታደርግ ብትን በትር ይዘህ ሂድ » ብሎ ላከው ።

ሙሴም ወደ አማቱ ተመልሶ ፥ «ተመ ልሼ ወደ ወንድሞቼ ልሂድ » አለው ። ዮቶርም ፥ « በሰላም ሂድ » አለው ። ሙሴም የእግዚአብሔርን በትር ይዞ ሄደ። እግዚአብሔርም ለሙሴ ፥ « ወደ ፈር ዖን ገብተህ ፥ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፤ እስራኤል የበኵር ልጄ ነውና ልቀቀው ፤ አንተ አልለቅም ብትል እነሆ እኔ የበኵር ልጅህን እገድላለሁ በለው » አለው ።

*    *    *


ከእኔ በፊት አምላክ አልነበረም ከእኔም በኋላ አይሆንም ።
እኔ ፥ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ፥ ከእኔ ሌላም የሚያድን
የለም ፤ . . . ከእጄም የሚያመልጥ የለም ፤ እሠራለሁ ፥
የሚከለክልስ ማን ነው ? ኢሳ. ፵፫ ፥ ፲ ፥ ፲፩ ፥ ፲፫ ።

እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ ፤ እኔ አምላክህ ነኝና አት
ደንግጥ ፤ አበረታሃለሁ ፥ እረዳሃማለሁ ፥ በጽድቄም ቀኝ
ደግፌ እይዝሃለሁ ። ኢሳ. ፵፩ ፥ ፲ ።

*    *    *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ሙሴ በምድያም ሳለ ምን ያደርግ ነበር ?
፪ ፤ እግዚአብሔር ለሙሴ የተገለጠው በምን ነበረ ?
፫ ፤ እግዚአብሔር ሙሴን ምን አዘዘው ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፥ ከንፈሮቼን ክፈት ፥
አፌም ምስጋናህን ያወራል ።
መዝ. ፶ (፶፩) ፥ ፲፭ ።



ምዕራፍ ፵፯ ።

## የፈርዖን ደንዳናነት ።

ዘጸ. ፬ ፡ ፳፯—፯ ፡ ፲፫ ።

### ፩ ፤ የእስራኤል ሕዝብ ደስታ ።

ዘጸ. ፬ ፡ ፳፯—፴፩ ።

እግዚአብሔር አሮንን ፡ «ሂደህ ሙሴን ተገናኘው » አለው ፤ ሂዶም በኮሬብ በእግዚአብሔር ተራራ ተገናኘው ፤ ሁለቱም ሂደው የእስራኤልን ሽማግሌ ዎች ሰበሰቡ ፤ አሮንም እግዚአብሔር ለሙሴ የነገረውን ቃል ሁሉ ተናገረ ፡ ተአምራቱንም በሕዝቡ ፊት አደረገ ። ሕዝቡም እግዚአብሔር መከራቸውን ዐውቆ እንደ ጐበኛቸው በሰሙ ጊዜ ደስ አላቸው ፤ አጐነበሱ ሰገዱም ።

### ፪ ፤ የፈርዖን እንቢተኝነት ።

ዘጸ. ፭ ፡ ፩—፲፩ ።

ከዚህም በኋላ ሙሴና አሮን ወደ ፈር ዖን ገቡና ፡ «የእስራኤል አምላክ እግ ዚአብሔር፡በምድረ በዳ በዓል እንዲያደ ርጉልኝ ሕዝቤን ልቀቅ ይላል» አሉት። ፈርዖንም ፡ «ቃሉን እንድሰማ እግዚአብ ሔር ማን ነው ? እግዚአብሔርን አላው ቀውም ፡ እስራኤልንም ደግሞ አልለ ቅም » አለ ።

ሙሴና አሮንም ለመኑት ፡ እርሱ ግን ፡ «ሕዝቡን ለምን ሥራቸውን ታስ ተዋላችሁ ? » ብሎ ሹማምንቶቹን አስ ጠራና ፡ «ሕዝቡ ሰልችተዋልና ከንቱ ቃልን እንዳይሰሙ ሥራቸው ይክበድባ ቸው ፤ ለጡብ ሥራ የሚያስፈልገውን ገለባ ራሳቸው ይሰብስቡ እንጂ ከእንግ ዲህ ወዲህ አትስጡአቸው፤የጡቡ ቍጥር ግን አይቀነስ » አላቸው ። ሹማምንቱም ይህን ሁሉ ለእስራኤላውያን ነገሩአቸው።

### ፫ ፤ የእስራኤል ጭንቀት ።

ዘጸ. ፭ ፡ ፲፪—፳፫ ።

ሕዝቡም በጣም ተጨንቀው በአገሩ ሁሉ እየተበተኑ በገለባ ፈንታ እብቅን ሲሰበስቡ የጡቡን ቍጥር ሊጨርሱ አልተቻላቸውም ። የግብፃውያን ሹማም ንትም ፡ « ቀድሞ ታደርጉ እንደ ነበር ትናንትናና ዛሬ የጡቡን ቍጥር ስለምን አትጨርሱም ? » እያሉ የእስራኤልን አለቆች ገረፉ ።

እነርሱም ወደ ፈርዖን ሄደው አቤ ቱታ አቀረቡ ፤ ፈርዖን ግን ፡ «ሰልችታ ችኋል ፤ ስለዚህም ፡ እንሂድ ለእግዚአብ ሔር እንሠዋ ትላላችሁ » አላቸው ። እነ ርሱም ነገሩ እንደ ከፋባቸው ባዩ ጊዜ ሙሴንና አሮንን ፡ « በፈርዖንና በግብ ፃውያን ፊት ሽታችንን አግምታችሁታ ልና እግዚአብሔር ይፍረድባችሁ» ሲሉ መረር ብለው ተቈጡአቸው ።

ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ ፤ «ጌታ ሆይ ፡ ስለምን ይህን ሕዝብ አስከ ፋህ ? ስለምንስ ላክኸኝ ? » ብሎ ኀዘኑን ሁሉ ገለጠለት ።

### ፬ ፤ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ።

ዘጸ. ፮ ፡ ፩—፱ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን ፡ «አሁን በፈ ርዖን የማደርገውን ታያለህ» ብሎ ለአ ብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም የሰጠ ውን ተስፋ የሚያስብና የሚፈጽም አም ላክ እንደ ሆኑ በማስታወስ እንዲህ ሲል ጽኑ የሆነ የተስፋ ቃል ሰጠው ፡

«እኔ እግዚአብሔር ነኝ ፤
ከግብፃውያንም ባርነት አወጣችኋለሁ፤
ከተገዥነትም አድናችኋለሁ ፤
በተዘረጋ ክንድ በታላቅ ፍርድም እታ
ደጋችኋለሁ ፤
ለእኔም ሕዝብ እንድትሆኑ እቀበላች
ኋለሁ ፡
አምላክም እሆናችኋለሁ ፡ . . .
ለአባቶቻችሁም እንድሰጣት ወደ ማል
ሁባት ምድር አገባችኋለሁ ፤
እርስዋንም ርስት አድርጌ እሰጣች
ኋለሁ ፤
እኔ እግዚአብሔር ነኝ ። »

ሙሴም ይህን የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ለሕዝቡ ተናገረ ፤ እነርሱ ግን ከባድ ከሆነ ከሰውነታቸው ጭንቀት የተነሣ ቃሉን አልሰሙትም ። እግዚአብሔርም ሙሴን ፡ «በግብፅ ድንቄንና ተአምራቴን አበዛለሁ ፤ በፈርዖንም ላይ የማደርገውን ባደረግሁ ጊዜ እርሱ ከአገሩ አስወጥቶ ይሰዳችኋል ፤ ሕዝቤንም ከመካከላቸው ባወጣሁ ጊዜ እኔ እግዚአብሔር እንደሆ ንሁ ግብፃውያን ሁሉ ያውቃሉ» አለው ።

### ፭ ፤ አሮንና የግብፅ ጠንቋዮች ።

ዘጸ. ፯ ፡ ፰—፲፫ ።

ሙሴና አሮንም ወደ ፈርዖን ገቡ ፤ እር ሱም ፡ «ተአምራትን አሳዩኝ» አላቸው፤ አሮንም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አድ ርጎ በትሩን ጣላት ፤ እባብም ሆነች ።

ፈርዖንም የግብፅን ጠንቋዮች አስ ጠራ ፤ እነርሱም እያንዳንዳቸው በትራ





www.ethiopianorthodox.org

ቸውን ጣሉ ፥ እባቦችም ሆኑ ፤ የአሮን በትር ግን በትራቸውን ዋጠች ። ፈርዖን ግን ምንም ይህን ቢያይ ልቡን አጽንቶ እስራኤልን አልለቀቀም ።

*    *    *

ብዙ ጊዜ ተዘልፎ አንገቱን ያደነደነ ድንገት ይሰበራል ፥
ፈውስም የለውም ።
ምሳሌ ፥ ፳፱ ፥ ፩ ።


ትዕቢት ጥፋትን ፥
ኵሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል ።
ምሳሌ ፥ ፲፮ ፥ ፲፰ ።

*    *    *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ሙሴ ወደ ግብፅ ሲመለስ ማን ሊገናኘው መጣ ?
፪ ፤ ሙሴና አሮን ፈርዖንን ፥ «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፤ ሕዝቤን ልቀቅ » ባሉት ጊዜ ፈርዖን ምን መልስ ምንስ ትእዛዝ ሰጠ ?
፫ ፤ ሙሴ አዝኖ በጸለየ ጊዜ እግዚአብሔር ምን አለው ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፥ የድፍረት ኃጢአት እንዳይገዛኝ ባሪያህን ጠብቅ ።
መዝ. ፲፰ (፲፱) ፥ ፲፫ ።





ምዕራፍ ፵፰ ።

## የግብፅ መቅሠፍቶች ።

ዘጸ. ፯ ፥ ፲፬—፲፩ ፥ ፲ ።

፩ ፤ አንደኛ መቅሠፍት ፤

ውኆች ደም ሆኑ ። ዘጸ. ፯ ፥ ፲፬—፳፭ ።
እግዚአብሔርም ለሙሴ ፥ «የፈርዖን ልብ ደንድኖ ፥ ሕዝቡንም ለመልቀቅ እምቢ አለ ። ማልደህ ሂድ ፥ ወደ ውኃ በሚሄድበት ጊዜ ተገናኘው ፤ ደምም እንዲሆኑ በግብፅ ውኆች ሁሉ ላይ እጅህን ዘርጋ » አለው ። ሙሴና አሮንም እንዲሁ አደረጉ ፤ የወንዙም ውኃ ሁሉ ተለውጦ ደም ሆነ ፤ በወንዙም የነበሩ ዓሦች ሞቱ ፤ ወንዙም ገማ ።

የግብፅም ጠንቋዮች በአስማታቸው እንዲሁ አደረጉ ፤ የፈርዖንም ልብ ጸና ፥ ይህንም ደግሞ በልቡ አላኖረውም ። እግዚአብሔርም ውኃውን ከመታ በኋላ ሰባት ቀን ሙሉ ደም ሆኖ ቀረ ። ግብፃውያንም ሁሉ ውኃ ሊጠጡ በወንዙ አጠገብ ቈፈሩ ።

፪ ፤ ሁለተኛ መቅሠፍት ፤ ጓጕንቸሮች ።
ዘጸ. ፰ ፥ ፩—፲፭ ።
እግዚአብሔር ሙሴን ፥ «ወደ ፈርዖን



www.ethiopianorthodox.org

ግብተህ ፡ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፡ ሕዝቤን ልቀቅ ፤ ለመልቀቅ እንቢ ብትል ግን አገርህን ሁሉ በጓጉንቸሮች እመታለሁ ፤ ወንዙም ጓጉንቸሮችን ያፈላል ፤ ወጥተውም ወደ ቤትህ ወደ አልጋህም ፡ በሕዝብህም ላይ ፡ ወደ ምድጆችህም ፡ ወደ ቡሃቃዎችም ይገባሉ በለው» አለው ። አሮንም በትሩን ይዞ በግብፅ ውኆች ላይ እጁን ዘረጋ ፤ ጓጉንቸሮችም ወጡ ፡ አገሩንም ሸፈኑ ። ጠንቋዮቹም በአስማታቸው እንዲሁ አደረጉ ።

ፈርዖንም ሙሴን ጠርቶ ፡ «ጓጉንቸሮቹ እንዲርቁ ጸልዩልኝ ፤ ሕዝቡን እለቅቃለሁ » አለ ። ሙሴም ፡ «ጓጉንቸሮቹ እንዲጠፉ መቼ ልጸልይ ? » አለው ፤ እርሱም ፡ « ነገ » አለው ። ሙሴም ፡ «እግዚአብሔርን የሚመስል እንደሌለ እንድታውቅ እንደ ቃልህ ይሁን » አለው ። በማግሥቱም ፈርዖን ጸጥታ እንደ ሆነ ባየ ጊዜ ልቡን አደነደነ ፡ ሕዝቡንም አልለቀቀም ።

፫ ፤ ሦስተኛ መቅሠፍት ፤ ቅማል ።

ዘጸ. ፰ ፡ ፲፮—፲፱ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን ፡ « ለአሮን ፡ በትርህን ዘርጋ ፡ በግብፅ ሁሉ ቅማል እንዲሆን የምድሩን ትቢያ ምታ በለው» አለው ። በሰውና በእንስሳም ላይ ቅማል ሆነ ። ጠንቋዮቹም በአስማታቸው ምንም ቢሞክሩ ቅማልን ሊያወጡ አልቻሉም፤ ለፈርዖንም ፡ «ይህስ የእግዚአብሔር ጣት ነው » አሉት ። የፈርዖን ልብ ግን ጸና ።

፬ ፤ አራተኛ መቅሠፍት ፤ ዝንቦች ።

ዘጸ. ፰ ፡ ፳—፴፪ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን ፡ « ማልደህ ተነሣ ለፈርዖንም ፡ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፡ ሕዝቤን ባትለቅቅ የዝንብ መንጎች እሰድዳለሁ ፤ ቤቶቻችሁና ምድራችሁ በዝንብ መንጎች ይሞላሉ በለው » አለው ። በማግሥቱም የዝንብ መንጋ በመጣ ጊዜ እግዚአብሔር በሕዝቡና በፈርዖን ሕዝብ መካከል ለየ ፡ በጌሤምና በእስራኤላውያን ቤቶች የዝንብ መንጋ አልደረሰም ።

ፈርዖንም ፡ «በምድረ በዳ እንድትሠዉ እለቅቃችኋለሁ ፤ ነገር ግን ርቃችሁ አትሂዱ ፡ ለእኔም ጸልዩልኝ » አለ። ነገር ግን የዝንብ መንጋ ከጠፋ በኋላ እንደገና ልቡን አደነደነ ።

፭ ፤ አምስተኛ መቅሠፍት ፤ ቸነፈር ።

ዘጸ. ፱ ፡ ፩—፯ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን ፡ « ወደ ፈርዖን ግብተህ ንገረው ፡ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፡ እንዲያገለግለኝ ሕዝቤን ልቀቅ ፤ እንቢ ብትል ግን በከብቶችህ ፡ በፈረሶችም ፡ በአህዮችም ፡ በግመሎችም ፡ በበሬዎችም፡በበጎችም ላይ ብርቱ ቸነፈር ይወርዳል ። ነገ እግዚአብሔር ይህን ያደርጋል » አለው ።

በማግሥቱም የግብፅ ከብት ሞተ ፤ ፈርዖንም ወደ ጌሤም ላከ ፤ እነሆም ከእስራኤል ሕዝብ ከብት አንድ ስንኳ አልሞተም ። የፈርዖን ልብ ግን ደነደነ ።

፮ ፤ ስድስተኛ መቅሠፍት ፤ ቍስል ።

ዘጸ. ፱ ፡ ፰—፲፪ ።

እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን ፡ «በእጃችሁ ከምድጃ አመድ ውሰዱ ፡ ሙሴም በፈርዖን ፊት ወደ ሰማይ ይበትነው ። እርሱም በግብፅ ሁሉ ትቢያ ይሆናል ፡ በሰውና በእንስሳ ላይ ቁንጥር (ሻህኝ) የሚያመጣ ቍስል ይሆናል» አላቸው ። እንዲሁም ሆነ ፤ ጠንቋዮችም ቍስል ስለ ነበረባቸው በሙሴ ፊት መቆም አልቻሉም ፤ ቍስልም በግብፃውያን ሁሉ ላይ ነበረ ። እግዚአብሔርም የፈርዖንን ልብ አጸና ፤ ሕዝቡንም አልለቀቀም ።

፯ ፤ ሰባተኛ መቅሠፍት ፤ በረዶ ።

ዘጸ. ፱ ፡ ፲፫—፴፭ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን ፡ « ማልደህ ተነሣ ፡ ፈርዖንንም በለው ፡ በምድር ሁሉ እንደ እኔ ያለ እንደሌለ እንድታውቅ መቅሠፍቴን ሁሉ እልክብሃለሁ ፤ ኃይሌን እንድገልጥብህ አስነሥቼሃለሁና ። እንዳትለቃቸው ገና በሕዝቤ ላይ ትታበያለህን ? እነሆ ነገ እጅግ ታላቅ በረዶ አዘንብብሃለሁ ፤ አሁን ላክ ፡ በሜዳ ያለህን ሁሉ ወደ ቤት አስገባ » ።

በማግሥቱም ሙሴ በትሩን ወደ ሰማይ ዘረጋ ፤ እግዚአብሔርም ነጐድጓድንና በረዶን እሳትንም ላከ ፤ በሜዳ ያለውን ሁሉ ሰውንና እንስሳን ገደለ ፤ የአገሩንም ዛፍ ሁሉ ሰበረ ። በጌሤም ብቻ በረዶ አልወረደም ። ፈርዖንም ሙሴን ፡ «በዚህ ጊዜ በድልሁ ፤ እግዚአብሔር ጻድቅ ነው ፤ ጸልዩልኝ ፡ እለቅቃችሁማለሁ » አለ ። ሙሴም እጁን ወደ እግዚአብሔር ዘረጋ ፤ በረዶውም ተቋረጠ ። ፈርዖንም ጸጥታ እንደ ሆነ ባየ ጊዜ ኃጢአትን ጨመረ ፡ ልቡንም አደነደነ ።

፰ ፤ ስምንተኛ መቅሠፍት ፤ አንበጣ ።

ዘጸ. ፲ ፡ ፩—፳ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን ፡ « ወደ ፈርዖን ግባ ፡ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፡ በፊቴ ለመዋረድ እስከ መቼ እንቢ ትላለህ ? ሕዝቤን ለመልቀቅ እንቢ ብትል ነገ አንበጣዎችን አመጣለሁ ፤ ከበረዶውም አምልጦ የተረፈላችሁን ይበሉታል ፡ ቤቶቻችሁም በእነርሱ ይሞላሉ በለው » አለው ። ሙሴም ይህን ተናግሮ ከወጣ በኋላ የፈርዖን ባሪያዎች ፡ «ሕዝቡን ልቀቅ ፤ ግብፅ እንደ ጠፋች ገና አታውቅምን ? » አሉት ። ፈርዖንም ሙሴንና አሮንን አስጠርቶ ፡ «ሂዱ ፤ ነገር ግን የሚሄዱ እነማን ናቸው ? » አላቸው ። ሙሴም ፡ «ሁላችን ከልጆቻችንና ከሽማግሌዎቻችን ጋር እንሄዳለን » ብሎ በመለሰ ጊዜ ፈርዖን ፡ «ታላላቅ የሆናችሁትን ወንዶችን እንጂ ልጆቻችሁን አልለቅቅም » አላቸው ። ከፈርዖንም ፊት አባረሩአቸው ።

እግዚአብሔርም የምሥራቁን ነፋስ አመጣ ፤ ማለዳም በሆነ ጊዜ ነፋሱ አንበጣዎችን አመጣ ። የምድሩንም ፊት ፈጽመው ሸፈኑት ፤ አንድም ቡቃያ በግብፅ አልቀረም ። ፈርዖንም ሙሴንና አሮንን በፍጥነት ጠራ ፡ « ኃጢአቴን ይቅር በሉኝ ፡ ይህንም ሞት እንዲያነሣልኝ እግዚአብሔርን ለምኑ » አላቸው።እግዚአብሔርም የሙሴን ጸሎት ሰማ ፤ አንበጣው ሁሉ በነፋስ ተወስዶ በባሕር ጠፋ ። እግዚአብሔርም የፈርዖንን ልብ አጸና ፤ ፈርዖንም ሕዝቡን አልለቀቀም ።

፱ ፤ ዘጠነኛ መቅሠፍት ፤ ጨለማ ።

ዘጸ. ፲ ፡ ፳፩—፲፩ ፡ ፰ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን ፡ «እጅህን ወደ ሰማይ ዘርጋ ፡ ሰው የሚዳስሰው ጽኑ ጨለማ ይሁን » አለው ። እስከ ሦስት ቀንም ድረስ ጽኑ ጨለማ ሆነ ፤ ማንም ሰው ከስፍራው አልተነሣም ። የእስራኤል ሰዎች ግን ብርሃን ነበራቸው ።

ፈርዖንም ሙሴን ጠርቶ ፡ «ሂዱ ፤ ነገር ግን በጎቻችሁንና ከብቶቻችሁን

ቶው » አለው ። ሙሴም ፥ «ከብቶቻችን ከእኛ ጋር ይሄዳሉ ፥ አንድ ሰኰናም አይ ቀርም ፥ ለአምላካችን የምንሠዋው ምን እንደ ሆነ ገና አናውቅም » አለ ። እግዚ አብሔርም የፈርዖንን ልብ አጸና ፥ ሊለቅ ቃቸውም አልወደደም ። ፈርዖንም ፥ «ከእኔ ዘንድ ሂድ ፤ ፊቴን እንዳታይ ተጠ ንቀቅ » አለው ። ሙሴም ፥ «እንደ ተናገ ርህ ይሁን ፤ ፊትህን እንደ ገና አላይም ። በግብፅ ያለ በኵር ልጅ ሁሉ ይሞታል ፤ ከዚያም በኋላ ባሪያዎችህ ሁሉ ፥ ውጡ ውጡ እያሉ ይሰግዱልኛል ፤ በዚያን ጊዜም እወጣለሁ» ብሎ በጽኑ ቍጣ ከፈ ርዖን ፊት ወጣ ።

*  *  *

አቤቱ ፥ . . . የአሕዛብ ንጉሥ ሆይ ፥ በአሕዛብ ጥበበኞች ሁሉ መካከል በመንግሥታቸውም ሁሉ እንደ አንተ ያለ ስለሌለ አንተን መፍራት ይገባልና አንተን የማይ ፈራ ማን ነው ?

ኤር. ፲ ፥ ፮ ፥ ፯ ።

ከእግዚአብሔር ጋር የሚጣሉ ይደቅቃሉ ፤
በሰማይም ያንጐደጕድባቸዋል ፤
እግዚአብሔር እስከ ምድር ዳርቻ ይፈርዳል ።

፩ ሳሙ. ፪ ፥ ፲ ።

*  *  *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ መቅሠፍቶች በግብፅ ላይ የመጡ በምን ምክንያት ነበረ?


፪ ፤ አሥሩ መቅሠፍቶችስ ምንና ምን ዓይነት ነበሩ ?

፫ ፤ ፈርዖን ፥ «ሂዱ ፤ ነገር ግን በጎቻችሁንና ከብቶቻችሁን ተው » ባለው ጊዜ ሙሴ ምን መለሰለት ?

ጸሎት ፤ ማረኝ ፥ አቤቱ ፥ ማረኝ ፥
ነፍሴ አንተን ታምናለችና ፤
ጥፋት እስኪያልፍ ድረስ
በክንፎችህ ጥላ እታመናለሁ ።

መዝ. ፶፯ (፶፮) ፥ ፩ ።





ምዕራፍ ፵፱ ።

## እስራኤል ከግብፅ ወጣ ።

ዘጸ. ፲፪ ።

፩ ፤ የእግዚአብሔር ፋሲካ ።

ዘጸ. ፲፪ ፥ ፩—፲፫ ፥ ፳፩—፳፰ ፤ ፲፩ ፥ ፩—፫ ።

እስራኤል ከባርነት የሚወጣበት ያ የተ ለየ ሌሊት ሳይደርስ እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ አለው ፤ « ይህ ወር የዓ መቱ መጀመሪያ ወር ይሁናችሁ ፤ በዚ ህም ወር በአሥራ አራተኛው ሌሊት እኔ እግዚአብሔር በግብፅ አልፋለሁ፥ ከሰው እስከ እንስሳ ድረስ በኵርን ሁሉ እገድላ ለሁ ፤ በግብፅም አማልክት ሁሉ ላይ እፈ ርድባቸዋለሁ ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ። ከዚያም በኋላ ፈርዖን ይለቅቃችኋል ፤ ሲለቅቃችሁም አባርሮ ይሰድዳችኋል ። ከእናንተ ወንድና ሴት ሁሉ ከግብፃው ያን የብርንና የወርቅን ዕቃ ልብስንም ተለምኑላችሁ ፤ በምትሄዱበት ጊዜ ባዶ እጃችሁን አትሄዱም ፥ በግብፃውያን ፊት ሞገስን እሰጣችኋለሁ ትበዘብዛላችሁም። አሁንም ለእስራኤል ሰዎች የማያደርጉ ትን ሁሉ እንዲህ ብለህ ንገራቸው ፥

በዚህ ወር በአሥረኛው ቀን እያንዳ ንዱ የእስራኤል ሰው ለቤቱ ነውር የሌለበትን ጠቦት ይውሰድ ፤ እስከ አሥራ አራተኛው ቀን ድረስ ይጠ ብቀው ፤ በዚያን ቀንም በምሽት ይረደው ፤ ደሙንም በቤቱ በሁለቱ



www.ethiopianorthodox.org

መቃኖችና በጉበኑ ላይ ይርጩው ፤ በእሳት የተጠበሰውን የጠቦትንም ሥጋ በዚያች ሌሊት ከቂጣና ከመ ራራ ቅጠል ጋር ትበሉታላችሁ ። የምትበሉትም ለመንገድ ተዘጋጅ ታችሁ በትራችሁንም በእጃችሁ ይዛችሁ በፍጥነት ይሁን ፤ እርሱ የእግዚአብሔር ፋሲካ* ነውና ። እኔም እግዚአብሔር በዚያች ሌሊት የግብፅ በኵርን ሁሉ በምገድልበት ጊዜ ደሙ ባላችሁባቸው ቤቶች ምል ክት ይሆንላችኋል ፤ ደሙንም ባየሁ ጊዜ ከእናንተ አልፋለሁ ፤ እኔም ግብፅን በመታሁ ጊዜ መቅሠፍቱ ለጥፋት አይመጣባችሁም ።»

ሙሴም የእስራኤልን ሽማግሌዎች ጠርቶ ፡ «በየቤታችሁ ጠቦት ምረጡ ፡ ወስዳችሁም እረዱት ። ከሂሶጵ ቅጠልም ጭብጥ ውሰዱ ፡ በዕቃ ውስጥ ባለውም ደም ንከሩት ፡ በደሙም ሁለቱን መቃኖ ችና ጉበኑን እርጩ ፤ አንድም ሰው ከቤቱ ደጅ አይውጣ ። እግዚአብሔር ደሙን ባየ ጊዜ በደጁ ላይ ያልፋል ፡ አጥፊውም እንዲመታችሁ ወደ ቤታችሁ እንዲገባ አይተወውም » አላቸው ።

፱ ፤ አሥረኛ መቅሠፍት ፤ የበኵር ሞት ።

ዘጸ. ፲፪ ፡ ፳፱—፴፮ ።

የእስራኤል ሰዎችም እንደ ታዘዘላቸው አደረጉ ፤ እኩለ ሌሊት በሆነ ጊዜ እግ ዚአብሔር ከፈርዖን በኵር ጀምሮ በግ ዞት እስካሉት እስከ እስረኞቹ በኵር ድረስ የግብፃውያንን በኵር ሁሉ ፡ የእን ስሳውንም በኵሮች ሁሉ መታ ። ፈርዖ ንም ግብፃውያንም ሁሉ በሌሊት ተነሡ፤ የሞተ የሌለበት ቤት አልነበረምና ታላቅ ልቅሶ ሆነ ። ፈርዖንም ሙሴንና አሮንን በሌሊት ጠርቶ ፡ «ተነሡ ፡ ከሕዝቤ መካ ከል ውጡ ሂዱም ፤ እኔንም ደግሞ ባር ኩኝ » አለ ። ግብፃውያንም ፈጥነው እን ዲሄዱ እስራኤላውያንን አስቸኰሉአ ቸው ፤ ሁላችን እንሞታለን ይሉ ነበርና ። እስራኤላውያንም ሊጡን ሳይቦካ ተሸ ከሙ ፤ ሙሴም እንዳዘዛቸው ከግብፃው ያን የብርንና የወርቅን ዕቃ ልብስንም ለመኑ ፤ የፈለጉትንም እንዲሰጡአቸው በግብፃውያን ፊት ሞገስ ተሰጣቸው ።

፲ ፤ እስራኤል ከግብፅ ወጣ ።

ዘጸ. ፲፪ ፡ ፴፯—፵፪ ።

የእስራኤልም ሰዎች በግብፅ የተቀመ ጡት ዘመን አራት መቶ ሠላሳ ዓመት ነው ፤ ይህም ዘመን በተፈጸመ ጊዜ በዚያ ቀን የእግዚአብሔር ሠራዊት ሁሉ ከግ ብፅ ወጡ ። እግዚአብሔር ፡ «በግብፅ ትልቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ» ብሎ ለያዕ ቆብ የሰጠውን ተስፋ ፈጽሞ ነበርና ከሕ ፃናቱ ሌላ ስድስት መቶ ሺህ ሰው የሚያ ህል እግረኛ ወጣ ፤ ደግሞም ሌላ ብዙ ድብልቅ ሕዝብ መንጎችና ላሞችም እጅግ ብዙም ከብቶች ከእነርሱ ጋር ወጡ ። ከእነርሱ ጋር ያወጡትን ሊጥ ጋግ ረው ቂጣ እንጎቻ አድርገው በሉት ፤ ግብ ፃውያን ስላስቸኰሉአቸው ስንቅ አላሰና ዱም ነበር ።

፬ ፤ የመታሰቢያ ዓመት በዓል ።

ዘጸ. ፲፪ ፡ ፲፬—፳ ፡ ፵፫—፵፱ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን ፡ « ይህም ቀን መታሰቢያ ይሁናችሁ ፤ ለልጅ ልጃ ችሁ ሥርዓት ሆኖ ለእግዚአብሔር በዓል ታደርጉታላችሁ » አለው ። ሙሴም ሕዝ ቡን ፡ «ከባርነት ቤት ከግብፅ የወጣችሁ በትን ይህን የአቢብ* ወር ቀን አስቡ ፡



እግዚአብሔር ከዚህ ቦታ በብርቱ እጅ አውጥቶአችኋልና በዓመት በዓመት በወራቱ ይህችን ሥርዓት ጠብቋት » አላ ቸው ።

ስለዚህ በየዓመቱ በመጀመሪያው ወር በአሥራ አራተኛው ቀን በምሽት የእስራ ኤል ሰዎች በግ አርደው በየቤተሰባቸው ከቂጣ ጋር ይበሉ ነበር ። ይህን ፋሲካ ሲበሉ ሳሉ በእያንዳንዱ ቤት ልጅ አባ ቱን ፡ «ይህ ምንድር ነው ? » ብሎ ይጠ ይቅ ነበር ፤ አባትዮም መልሶ ፡ « ልጄ ሆይ ፡ በግብፅ አገር በእስራኤል ልጆች ቤቶች ላይ አልፎ ግብፃውያንን በመታ ጊዜ ፡ ቤቶቻችንን ያዳነ የእግዚአብሔር የማለፉ መሥዋዕት ናት » ይል ነበር ። ከአሥራ አምስተኛው ቀን እስከ ሰባት ቀንም ድረስ የቂጣ እንጀራ ይበሉ ነበር። እንደዚሁም እግዚአብሔር ያደረገላቸው ታላቅ ማዳን ከትውልድ ወደ ትውልድ ይታሰብ ነበር እንጂ አልተረሳም ።

* * *

ሙሴ ፡ . . . አጥፊው በኵሮችን ልጆች እንዳይነካ ፋሲካንና ደምን መርጨትን በእምነት አደረገ ።
ዕብ. ፲፩ ፡ ፳፰ ።

ትውልደ ትውልድ ሥራህን ያመሰግናሉ ፡
ኃይልህንም ያወራሉ ። መዝ. ፻፵፭ (፻፵፬) ፡ ፬ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ አሥረኛው መቅሠፍት ምን ነበረ ?
፪ ፤ የእስራኤል በኵሮች እንዳይሞቱ እግዚአብሔር ምን አዘዘ ?
፫ ፤ በእኩለ ሌሊት መቅሠፍት ከደረሰበት በኋላ ፈርዖን ሙሴን ምን አለው ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ ስምህ ለዘላለም ነው ፡
ዝክርህም ለልጅ ልጅ ነው ፤
እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይፈርዳልና ፡
ባሪያዎቹንም ይረዳልና ።
መዝ. ፻፴፭ (፻፴፬) ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ።

* «ፋሲካ» የሚለው የዕብራይስጥ ቃል በአማርኛ ሲተረጐም «ማለፍ» ማለት ነው ። እግዚአብሔር ፡ «ደሙ ባላችሁበት ቤቶች ምልክት ይሆንላችኋል ፤ ደሙንም ባየሁ ጊዜ ከእናንተ አልፋለሁ ፤ . . . መቅሠፍቱ ለጥፋት አይመጣባችሁም » ብሎ ነበርና «የእግዚአብሔር ፋሲካ» ማለት « የእግዚአብ ሔር ማለፍ » ማለት ነው ። ቍጥር ፲፩ ፡ ፲፫ ፡ ፳፯ን ተመልከት ።

* አቢብ ማለት የእስራኤል የመጀመሪያ ወር ነው ፤ እርሱም በፋሲካ ሰሞን የሚውል ወር ነው ።



ምዕራፍ ፴ ።

## እስራኤል የኤርትራ ባሕርን ተሻገረ ።

ዘጸ. ፲፫ ፥ ፲፯—፲፭ ፥ ፳፩ ።

### ፩ ፤ እግዚአብሐር እስራኤልን መራ ።

ዘጸ. ፲፫ ፥ ፲፯— ፲፬ ፥ ፬ ።

ፈርዖን እስራኤልን በለቀቀ ጊዜ እግዚአብሐር መንገድ ሊያሳያቸው በደመና ዓምድ መራቸው ፤ በቀንና በሌሊትም ለመጓዝ እንዲችሉ ሌሊት በሚያበራላቸው በእሳት ዓምድ በፊታቸው ሄደ ፤ የደመና ዓምድ በቀን ፡ የእሳት ዓምድ በሌሊት ከሕዝቡ ፊት ከቶ አልተለየም ። ፍልስጥኤማውያን የተባሉት ሕዝብ እንዳይነሡባቸው እግዚአብሔር ቅርብ በሆነ መንገድ ሳይሆን በዙሪያ መንገድ በኤርትራ ባሕር ባለችው ምድረ በዳ መራቸው ። ወደ ባሕሩም ዳር በደረሱ ጊዜ እንዲሰፍሩበት የመረጠላቸውን ስፍራ ለሙሴ አመለከተው ፤ አለውም ፥ «ፈርዖን ፥ ሕዝቡ በምድረ በዳ ይቅበዘበዛሉ ፥ ምድረ በዳም ዘጋቸው ብሎ ይመጣባችኋል ፤ በፈርዖንና በሠራዊቱም ሁሉ ላይ ክብር አገኛለሁ ፤ ግብፃውያንም እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ » አለው ።

### ፪ ፤ ፈርዖን እስራኤልን ተከተለ ።

ዘጸ. ፲፬ ፥ ፭—፱ ።

እስራኤላውያን ከባርነታቸው እንደወጡ ባስተዋሉ ጊዜ ፈርዖንና ባሪያዎቹ ፥ «እንዳያገለግሉን እስራኤልን የለቀቅነው ምን አድርገናል ? » አሉ ። ፈርዖንም ሰረገላውን አሰናዳ ፥ ሰረገሎቹንና ፈረሰኞቹን ሠራዊቱንም ሁሉ ወስዶ እስራኤልን ለመፈለግ ተነሣ ፤ በባሕሩም አጠገብ ሠፍረው አገኛቸው ።

### ፫ ፤ የእስራኤል ድንጋጤ ።

ዘጸ. ፲፬ ፥ ፲—፲፬ ።

የእስራኤል ሰዎች ግብፃውያን ገሥግሠው እንደ መጡባቸው ባዩ ጊዜ ደነገጡ ፤ ወደ እግዚአብሔርም ጮኹ። ሙሴንም ፥ «በምድረ በዳ ከምንሞት ለግብፃውያን ብንገዛላቸው ይሻል ነበርና ከግብፅ እንድታወጣን ይህ ያደረግህብን ምንድር ነው ? » ብለው አንጐራጐሩበት ። ሙሴም ፥ «አትፍሩ ፥ ዛሬ የምታዩአቸውን ግብፃውያንን ለዘላለም አታዩአቸውምና ቁሙ ፥ ዛሬ ለእናንተ የሚያደርጋችን የእግዚአብሔርንም ማዳን እዩ ። እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል ፥ እናንተም ዝም ትላላችሁ » አላቸው ።

### ፬ ፤ የእግዚአብሐር ማዳን ።

ዘጸ. ፲፬ ፥ ፲፭—፴፩ ።

እግዚአብሐር ሙሴን ፥ « ለምን ትጮኸብኛለህ? እንዲጓዙ ለእስራኤል ልጆች ንገር ። በትርህን አንሣ ፥ እጅህንም በባሕሩ ላይ ዘርጋ ፥ ክፈለውም ፤ ሕዝቡም በባሕሩ ውስጥ በየብስ ያልፋሉ ። እኔም የግብፃውያንን ልብ አጸናለሁ ፤ በኋላቸውም ይገባሉ ፤ በፈርዖንና በሠራዊቱም ላይ ክብር ባገኘሁ ጊዜ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ» አለው።

በእስራኤልም ፊት ይሄድ የነበረው የእግዚአብሔር መልአክ ወደ ኋላቸው ሄደ ፤ የደመናውም ዓምድ ከፊታቸው ተነሥቶ በኋላቸው ቆመ ፤ በግብፃውያን ሠፈርና በእስራኤል ሠፈር መካከልም ገባ ፤ በግብፃውያንም ሠፈር ጨለማ ነበረ ፤ በእስራኤል በኩል ግን ሌሊቱ በራ ፤ ሌሊቱንም ሁሉ እርስ በርሳቸው አልተቃረቡም ።

ሙሴም በባሕሩ ላይ እጁን ዘረጋ ፤ እግዚአብሐርም ሌሊቱን ሁሉ ጽኑ የምሥራቅ ነፋስ አምጥቶ ባሕሩን አስወገደው ፥ ባሕሩንም አደረቀው ፥ ውኃውም ተከፈለ ። እስራኤላውያንም በባሕሩ መካከል በየብስ ገቡ ፤ ውኃውም በቀኛቸውና በግራቸው እንደ ግድግዳ ሆነላቸው። ግብፃውያንም ሁሉ እያሳደዱ በኋላቸው ወደ ባሕር መካከል ገቡ ፤ ንጋትም በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር ሠራዊታቸውን ተመለከተ ፥ አወካቸውም ። የሰረገሎቹንም መንኰራኵር አሰረ ፥ ወደ ጭንቅም አገባቸው ፥ ግብፃውያንም ፥ «እግዚአብሐር ለእስራኤላውያን ይዋጋላቸዋልና ከፊታቸው እንሽሽ » አሉ ።

እግዚአብሐርም ሙሴን ፥ «እጅህን በባሕር ላይ ዘርጋ ፥ ውኃውም በግብፃውያን በሰረገሎቻቸውም በፈረሰኞቻቸውም ላይ ይመለስ » አለው ። ሙሴም እጁን በባሕር ላይ ዘረጋ ፥ ባሕሩም ወደ መፍሰሱ ተመለሰ ፤ ግብፃውያንም ለመሸሽ ሲያስቡ እግዚአብሔር በባሕሩ መካከል ጣላቸው ፤ ከእነርሱም አንድ ስንኳ አልቀረም ። እስራኤልም የግብፃውያንን ሬሳ በባሕር ዳር አዩ ፤ እግዚአብሔር ያደ





www.ethiopianorthodox.org

ረጋትን ታላቂቱን የእጁን ኃይልም አዩ ። ሕዝቡም እግዚአብሔርን ፈሩ ፡ በእግዚአብሔርም በባሪያውም በሙሴ አመኑ ።

፫ ፤ የእስራኤል ምስጋና ።

ዘጸ. ፲፭ ፥ ፩—፳፩ ።

በዚያም ጊዜ ሙሴና የእስራኤል ሰዎች እንዲህ ብለው ለእግዚአብሔር መዝሙርን ዘመሩ ፤

«በክብር ከፍ ከፍ ብሎአልና ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ ፤
ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባሕር ጣለ ።
ጉልበቴም ዝማሬዬም እግዚአብሔር ነው ፤
መድኃኒቴም ሆነልኝ ፤ . . .
በቸርነትህ የተቤዠኻቸውን ሕዝብህን መራህ ፤
በኃይልህ ወደ ቅዱስ ማደሪያህ አገባኻቸው ። . . .
እግዚአብሔር ለዘላለሙ እስከ ፍጻሜ ይነግሣል ። »

የአሮንም እኅት ነቢይቱ ማርያም ከበሮ በእጅዋ ወሰደች ፤ ሴቶችም ሁሉ በከበሮና በዘፈን በኋላዋ ወጡ ። ማርያምም እየ ዘመረች እንዲህ ብላ መለሰችላቸው ፡—

«በክብር ከፍ ከፍ ብሎአልና ለእግዚአብሔር ዘምሩ ፤
ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባሕር ጣለ ። »

* * *

የኤርትራንም ባሕር ገሠጸ እርሱም ደረቀ ፤
በምድረ በዳ እንደሚሄዱ በጥልቅ መራቸው ።
ከሚጠሉአቸውም እጅ አዳናቸው ።

መዝ. ፻፭ (፻፮) ፥ ፱ ፥ ፲ ።

ዕረፉ ፡ እኔም አምላክ እንደ ሆንሁ ዕወቁ ፤
በአሕዛብ ዘንድ ከፍ ከፍ እላለሁ ፤
በምድርም ላይ ከፍ ከፍ እላለሁ ።

መዝ. ፵፭ (፵፮) ፥ ፲ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ እግዚአብሔር ሕዝቡን በምን መራቸው ?
፪ ፤ እስራኤላውያን የግብፅን ጦር ሠራዊት አይተው በፈሩ ጊዜ ሙሴ ምን አላቸው ?
፫ ፤ እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው እንዴት አድርጎ አዳናቸው?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፡ በአማልክት መካከል እንደ አንተ ያለ ማን ነው ?
በምስጋና የተፈራህ ፡ ድንቅንም የምታደርግ ፡ . . .
በቸርነትህ የተቤዠኻቸውን ሕዝብህን መራህ ።

ዘጸ. ፲፭ ፥ ፲፩ ፥ ፲፫ ።





ምዕራፍ ፶፩ ።

## እግዚአብሔር ሕዝቡን እየመገበ መራቸው ።

ዘጸ. ፲፭ ፥ ፳፪—፲፯ ፥ ፯ ።

፩ ፤ ማራና ኤሊም ። ዘጸ. ፲፭ ፥ ፳፪—፳፯ ።

ሙሴም እስራኤልን ከኤርትራ ባሕር አስጓዘ ፤ በምድረ በዳም ሦስት ቀን ሄዱ ፥ ውኃም አላገኙም ። ውኃም ወዳለበት ሥፍራ በደረሱ ጊዜ ውኃው መራራ ነበረና ሊጠጡት አልቻሉም ። ሕዝቡም ፡ «ምን እንጠጣለን ? » ብለው አንጐራጐሩ ፤ የሥፍራውንም ስም ማራ ብለው ጠሩት ። ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ጮኸ ፡ እግዚአብሔርም እንጨትን አሳየው ፤ ሙሴም እንጨቱን በውኃ ላይ በጣለው ጊዜ ውኃው ጣፈጠ ። እግዚአብሔርም ፡ « የአምላክህን የእግዚአብሔርን ቃል አጥብቀህ ብትሰማ በግብፃውያን ላይ ያመጣሁትን በሽታ አላደርስብህም፤ እኔ ፈዋሽህ እግዚአብሔር ነኝና» አለ ።



www.ethiopianorthodox.org

እስራኤልም ተጕዘው ፥ ወደ ኤሊም መጡ ፤ በኤሊምም አሥራ ሁለት የውኃ ምንጮችና ሰባ የዘንባባ ዛፎች ነበሩበት ፤ በዚያም ሠፈሩ ።

## ፱ ፤ በሲን ምድረ በዳ መና ተሰጠ ።

ዘጸ. ፲፮ ።

ከኤሊም በተጓዙ ጊዜ ወደ ሲን ምድረ በዳ መጡ ። በዚያም የሚበሉትን አጥተው ሙሴንና አሮንን ፥ «በራብ ልትገድሉን ወደዚች ምድረ በዳ አውጥታችሁናል ፤ በግብፅ ምነው በሞትን ! » አሉ። እግዚአብሔርም ሙሴን ፥ « እነሆ ከሰማይ እንጀራን አዘንብላችኋለሁ» አለው። ሙሴም ሕዝቡን ፥ «እግዚአብሔር ማጕረምረማችሁን ሰምቶአልና በመሸ ጊዜ ሥጋን ፥ በጥዋትም እንጀራን ይሰጣችኋል ፤ እኛ ምንድር ነን ? ማጕረምረማችሁ በእግዚአብሔር ላይ ነው እንጂ በእኛ አይደለም » አላቸው ። የእግዚአብሔርም ክብር በደመናው ታያቸው ።

በመሸም ጊዜ ድርጭቶች መጥተው ሠፈሩን ከደኑት ። ማለዳም በሠፈሩ ዙሪያ ጠል ነበረ ፤ ጠልም ባለፈ ጊዜ እነሆ በመሬት ላይ እንደ ደቃቅ ውርጭ ሆኖ ቅርፊት የሚመስል ነገር በምድረ በዳ ታየ ። ሕዝቡም ባዩት ጊዜ ፥ «ይህ ምንድር ነው ? » ተባባሉ ። ሙሴም ፥ «ይህ እግዚአብሔር የሰጣችሁ እንጀራ ነውና እግዚአብሔር ያዘዘውን ነገር ስሙ ፤ እያንዳንዱ የሚበላውን ያህል ይልቀም ፤ ማንም ከእርሱ አንዳች ነገር አያስቀር » አላቸው። ነገር ግን ሙሴን አልሰሙትም ፤ አንዳንድ ሰዎችም ከእርሱ ለነገ አስቀሩ ፤ እርሱም ተላ፡ሸተተም ፤ ሙሴም ተቈጣቸው።

በስድስተኛውም ቀን ሙሴ ፥ «እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው ፤ ነገ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ የሰንበት ዕረፍት ነው ፤ በስድስተኛው ቀን ዕለት ዕለት ከምትለቅሙት ይልቅ ሁለት እጥፍ ልቀሙ ፤ ለነገም ይጠበቅ » አላቸው ። ሕዝቡም እንደዚሁ አደረጉ ፤ አልሸተተም ፥ ትልም አልሆነም ። ሙሴም ፥ «ዛሬ የእግዚአብሔር ሰንበት ነው ፤ ዛሬ በሜዳ አታገኙትም » አላቸው ። ነገር ግን ከሕዝቡ አንዳንድ ሰዎች ሊለቅሙ ወጡ ፤ ምንም አላገኙም ። እግዚአብሔርም ሙሴን ፡ «ትእዛዛቴን ለመጠበቅ እስከ መቼ እንቢ ትላላችሁ ? እግዚአብሔር ሰንበትን እንደ ሰጣችሁ እዩ ፤ ስለዚህ በስድስተኛው ቀን የሁለት ቀን እንጀራ ሰጣችሁ » አለ ። ሕዝቡም በሰንበት ቀን ዐረፉ ።

የእስራኤልም ወገን የተሰጣቸውን እንጀራ መና ብለው ጠሩት ፤ መና ማለትም ፥ ይህ ምንድር ነው ? ማለት ነው ። መናውም እንደ ድንብላል ዘር ነጭ ነበረ፤ ጣዕሙም እንደ ማር ቂጣ ነበረ ። የእስራኤል ልጆች ወደሚኖሩባት ወደ ከነዓን እስኪመጡ ድረስ መና በሉ ። እግዚአብሔርም እንዳዘዘ አሮን ለልጅ ልጃቸው የሚጠበቅ በማድጋ ውስጥ አግብቶ አስቀመጠ ።

## ፲ ፤ በራፊዲም ውኃ ተሰጣቸው ።

ዘፀ. ፲፯ ።

እግዚአብሔር እንደ መራቸው ተጕዘው ወደ ራፊዲም ደረሱ ፤ በዚያም ውኃ አጥተው ሙሴን ፥ «የምንጠጣው ውኃ ስጠን ፤ በጥማት ልትገድለን ለምን ከግብፅ አወጣኸን ? » ብለው ተጣሉት ። ሙሴም እግዚአብሔርን ፥ « ሊወግሩኝ ቀርበዋልና በዚህ ሕዝብ ምን ላድርግ?» አለው ። እግዚአብሔርም ፥ «በእጅህ በትርህን ይዘህ በሕዝቡ ፊት እለፍ ። እኔም በዓለት ላይ በፊትህ እቆማለሁ ፤ ዓለቱንም ትመታለህ ፥ ከእርሱም ውኃ ይወጣል » አለው ። ሙሴም ሄዶ ዓለቱን በበትሩ መታ ፤ ሕዝቡም ከዓለቱ ከወጣው ውኃ ጠጣ ። እስራኤልም በዚያን ሥፍራ ፥ « እግዚአብሔር በመካከላችን ነውን ወይስ አይደለም ? » ብለው እግዚአብሔርን ተፈታትነው ስለ ተከራከሩት ሙሴ የሥፍራውን ስም ማሳህ ደግሞም መሪባ ብሎ ጠራው ። ማሳህ ማለት ፈተና ፥ መሪባም ማለት ክርክር ማለት ነው ።

በራፊዲምም ሠፍረው ሳሉ አማሌቃውያን የተባሉት ሕዝብ ከእስራኤል ጋር ተዋጉ ። እግዚአብሔርም ማሸነፍን በሰጣቸው ጊዜ ሙሴ መሠዊያን ሠራ ፥ ስሙንም ያህዌህ ንሲ ብሎ ጠራው ፥ አለም ፥ «እጄን በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ ስለ ጫነ የእግዚአብሔር ሰልፍ በአማሌቅ ላይ ለልጅ ልጅ ይሁን» ። ያህዌህ ንሲ ማለትም እግዚአብሔር ዓላማዬ ማለት ነው ።

* * *

በሙሴና በአሮን እጅ
ሕዝብህን እንደ በጎች መራኻቸው ።
መዝ. ፸፯ (፸፮) ፥ ፳ ።

የሰማይንም እንጀራ አጠገባቸው ።
ዓለቱን ሰነጠቀ ፥ ውኃውም ፈሰሰ ፤
ወንዞች በበረሃ ሄዱ ።
መዝ. ፻፬ (፻፭) ፥ ፵ ፥ ፵፩ ።

* * *

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ ምግብ ባጡ ጊዜ ሕዝቡ ምን ብለው አንጐራጐሩ ?
፪ ፤ እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ መገባቸው ?
፫ ፤ እግዚአብሔር ስለ ሰንበት ቀን ምን አዘዘ ?

ጸሎት ፤ ነፍሴ ሆይ ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ ፥
ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ ፤
ኃጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚል ፥ . . .
በምሕረቱና በቸርነቱ የሚከልልሽ ።
መዝ. ፻፪ (፻፫) ፥ ፪—፬ ።



ምዕራፍ ፶፪ ።

## በሲና ተራራ እግዚአብሔር ሕግን ሰጠ ።

ዘጸ. ፲፱—፳፩ ።

### ፩ ፤ እግዚአብሔር ስለ ኪዳኑ ተናገረ ።

ዘጸ. ፲፱ ፥ ፩—፮ ።

ከግብፅ በወጡ በሦስተኛው ወር በዚያ ቀን እስራኤል ፣ እግዚአብሔር በቍጥቋጦ ለሙሴ ወደ ተገለጠበት ወደ ሲና ምድረ በዳ ደርሰው ሠፈሩ ፤ ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ወደ ሲና ተራራ ወጣ ።

እግዚአብሔርም ጠርቶ ሙሴን እንዲህ አለው ፤ «ለያዕቆብ ቤት ለእስራኤል ልጆች እንዲህ በል ፤ በግብፃውያን ያደረግሁትን ሁሉ አይታችኋል ፤ በንስርም ክንፍ እንደ ተሸከምኋችሁ ወደ እኔም እንዳመጣኋችሁ አይታችኋል ። አሁንም ቃሌን ብትሰሙ ኪዳኔንም ብትጠብቁ ከሕዝቦች ሁሉ የተመረጠ የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ ፤ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ። »

### ፪ ፤ የሕዝቡ ዝግጅት ። ዘጸ. ፲፱ ፥ ፯—፲፭ ።

ሙሴም ከተራራው ወርዶ ለሕዝቡ ሽማግሌዎች ይህን ቃል ሁሉ ነገራቸው ። ሕዝቡም ነገሩን በሰሙ ጊዜ ፣ «እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን» ብለው መለሱ ። እግዚአብሔርም ሙሴን ፣ «ዛሬና ነገ ሕዝቡን ቀድሳቸው ፣ ልብሳቸውንም ይጠቡ ፤ በሦስተኛው ቀን ሕዝቡ ሁሉ ሲያዩ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ይወርዳልና ይዘጋጁ ፤ እንስሳ ሆነ ወይም ሰው እንዳይሞት ተራራውን አይንካ ፣ በተራራውም ዙሪያ ወሰን አድርግላቸው ። ሳያቋርጥ የመለከት ድምፅ ሲነፋ በዚያን ጊዜ ወደ ተራራው ይቅረቡ » አለው ። ሙሴም ሕዝቡን ቀደሰ ፤ ልብሳቸውንም አጠቡ ።

### ፫ ፤ የእግዚአብሔር ክብር ተገለጠ ።

ዘጸ. ፲፱ ፥ ፲፮—፳፭ ።

በሦስተኛው ቀንም በማለዳ ጊዜ ነጐድጓድና መብረቅ ከባድም ደመና እጅግም የበረታ የቀንደ መለከት ድምፅ በተራራው ላይ ሆነ ፤ በሠፈሩም የነበሩት ሕዝብ ሁሉ ተንቀጠቀጡ ። ሙሴም ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ጋር ለማገናኘት ከተራራው ግርጌ እንዲቆሙ ከሠፈር አወጣቸው ።

እግዚአብሔር በእሳት ስለ ወረደ በት የሲና ተራራ ሁሉ ይጤስ ነበር ፤ ተራራውም ሁሉ እጅግ ይናወጥ ነበር ። የቀንደ መለከቱም ድምፅ እጅግ በበረታና በጸና ጊዜ ሙሴ ተናገረ ፤ እግዚአብሔርም በድምፅ መለሰለት ፣ ወደ ተራራውም ራስ ጠራው ፤ ሙሴም ወጣ ።

እግዚአብሔር ሙሴን ፣ «ውረድ ፣ እግዚአብሔርን ለማየት ዳርቻውን እንዳያልፉ ለሕዝቡ አስጠንቅቃቸው» አለው ። ሙሴም ፣ «በተራራው ዙሪያ ወሰን አድርግ ብለህ አስጠንቅቀኸናልና ወደ ተራራው ሊወጡ አይችሉም » አለው ። እግዚአብሔርም ፣ «ሂድ፡ውረድ ፤ አንተ አሮንም ትወጣላችሁ ፤ ሕዝቡ ግን እግዚአብሔር እንዳያጠፋቸው ወደ እግዚአብሔር እንዲወጡ አይተላለፉ » አለው ። ሙሴም ወረደ ፤ ሕዝቡንም አስጠነቀቃቸው ፤ እርሱና አሮንም ወጡ ።

### ፬ ፤ እግዚአብሔር ሕግን ተናግሮ ሰጠ ።

ዘጸ. ፳ ፥ ፩—፳፩ ።

በዚያንም ጊዜ እግዚአብሔር በእሳት ከሚጤሰው ተራራ ተናግሮ እንዲህ አለ ፡—

«ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ ። ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ ።

«በላይ በሰማይ ካለው ፣ በታችም በምድር ካለው ፣ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ ፣ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ ። አትስገድላቸው ፣ አታምልካቸውምም ፤ በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ ፤ ለሚወድዱኝ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና ።

« የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ ፤ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያ





www.ethiopianorthodox.org

ነጻውምና ።

«የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ ። ስድስት ቀን ሥራ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ ፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ሰንበት ነው ፤ አንተ ፥ ወንድ ልጅህም ፡ ሴት ልጅህም፥ ሎሌህም ፥ ገረድህም ፥ ከብትህም ፥ በደጅችህም ውስጥ ያለ እንግዳ በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ ፤ እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን ፥ ባሕርንም ፥ ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ ፥ በሰባተኛው ቀን ዐርፎአልና ፥ ስለዚህ እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ባርኮታል ቀድሶታልም ።

«አባትህንና እናትህን አክብር ፤ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም ።

« አትግደል ።

« አታመንዝር ።

« አትስረቅ ።

« በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር ።

« የባልንጀራህን ቤት አትመኝ ፤ የባልንጀራህን ሚስት ፡ ሎሌውንም ፥ ገረዱንም ፥ በሬውንም ፡ አህያውንም ፡ ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ።»

እግዚአብሔርም ሲናገር ሳለ ሕዝቡ ሁሉ ከነጐድጓዱና ከመብረቁ ከቀንደ መለከቱም ድምፅ የተነሣ ተርበደበዱ ርቀውም ቆሙ ። ሙሴንም ፡ «አንተ ተናገረን እንጂ እንዳንሞት እግዚአብሔር አይናገረን » አሉት ። ሙሴም ፥ « አትፍሩ ፤ እግዚአብሔር ሊፈትናችሁ ፥ ኃጢአትንም እንዳትሠሩ እርሱን መፍራት በልባችሁ እንዲሆን መጥቶአልና» አላቸው ። ሕዝቡም ርቀው ቆሙ ፤ ሙሴም እግዚአብሔር ወዳለበት ወደ ጨለማው ቀረበ ። እግዚአብሔርም ሙሴን ፥ « ለሕዝቡ እንዲህ በል ፤ እኔ ከሰማይ እንደ ተናገርኋችሁ እናንተ አይታችኋል ። በአጠገቤ ምንም አታድርጉ ፤ የብር አማልክት የወርቅም አማልክት ለእናንተ አታድርጉ » አለው ።

፭ ፤ ሕዝቡ ቃል ኪዳን ገቡ ።

ዘጸ. ፳፬ ፥ ፩—፲፩ ።

ከዚህም በኋላ ሙሴ እግዚአብሔር የተናገራቸውን ቃሎች ጻፈ ፤ ለሕዝቡም ባነበባቸው ጊዜ እነርሱ ፥ «እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን እንታዘዛለንም » አሉ ። ሙሴም መሥዋዕትን አድርጎ የመሥዋዕትንም ደም ወስዶ በሕዝቡ ላይ ረጨው ፤ «በዚህ ቃል ሁሉ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ያደረገው የቃል ኪዳኑ ደም እነሆ » አለ ። ሙሴና አሮንም ከእስራኤልም ሽማግሌዎች ሰባ ወጡ ፤ የእስራኤልንም አምላክ አዩ ፤ ከእግሩም በታች እንደ ሰማይ መልክ የሚያበራ ወለል ነበረ ። እነርሱም እግዚአብሔርን አዩ ፤ በሉም ጠጡም ።

* * *

እስራኤል ሆይ ስማ ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው ፤ አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ ። ዘዳግ. ፮ ፥ ፬ ፥ ፭ ።



ዐሠርቱ ቃላትን በቃል አጥና ።

ጥያቄ ፤ ፩ ፤ በሲና ተራራ እግዚአብሔር ክብሩን በምን አሳየ ?
፪ ፤ እግዚአብሔር ከሲና ተራራ ተናግሮ ለሕዝቡ ምን ሰጠ ?
፫ ፤ ከትእዛዛቱ ሁሉ መጀመሪያው ምንድር ነው ?

ጸሎት ፤ አቤቱ ፥ ጐልማሳ መንገዱን በምን ያነጻል ?
ቃልህን በመጠበቅ ነው ።
በፍጹም ልቤ ፈለግሁህ ፥
ከትእዛዝህ አታርቀኝ ። መዝ. ፻፲፰ (፻፲፱) ፥ ፱ ፥ ፲ ።



www.ethiopianorthodox.org